በደቡብ ጦር ግንባር ማርሻል ግራዚያኒ በደረሰው መጽሐፍ የሞቱና የቆሰሉ በደፈናው 2150 ብሎ ጽፈዋል። ጀኔራል ፍሩሺ ግን በዝርዝር በማውጣት ያነሰ ቁጥር ነው የመዘገበው። የሞቱና የቆሰሉ ጣሊያኖች የስም ዝርዝራቸው ሳይቀር በማውጣት የሞቱ 81 የቆሰሉ 81 ብሎ አውጥቷል።

## የኢንዲጀኒ ዝርዝር በማዕርጋቸው እንደሚከተለው አውጥቷል።

| | የሞቱ | የቆሰሉ |
|---|---|---|
| ሹምባሽ | 5 | 7 |
| ቡሉቅባሽ | 19 | 66 |
| ሙንጣዝ | 34 | 111 |
| አስካሪ መደበኛወታደር | 118 | 454 |
| ዛፕቲየ(ፖሊስ) | 21 | 1 |
| ሹሞች (አዛዦች) | 42 | 1 |
| የባንዳ ሹሞች | 10 | 36 |
| ምክትል ሹሞች | 41 | 61 |
| ዱባት (ባንዳ መደበኛ ያልሆኑ | 2 | 32 |
| ያልተመደቡ | 38 | 54 |
| ድምር | 432 | 1055 |
| ጣሊያኖች | 81 | 81 |
| | 513 | 1136 |

### ድምር 1649

በሰሜንና የደቡብ ጦር ግንባር የሞቱና የቆሰሉ 3492 ኢንዲጀኒ 3265 ጣሊያኖች በድምሩ 6757 ነበሩ፡ ይኸውም በማርሻል ግራዚያኒ የተሰጠው ቁጥር ሳይሆን በጀኔራል ፍሩሺ የተሰጠው ቁጥር በመውሰድ ነው።



# ምዕራፍ 13
# የኢጣሊያ ቂም በቀል

40 ዓመት ከዐድዋ ጦርነት በኋላ ጣሊያኖች የሸንፈታቸውን ቂም በቀል የተዋጡት በልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓቶች አፈጻጸም፤ በተለይም የኢትዮጵያ የቀድሞ የጦር አውድማዎች በማከናወን ነው።

ማሪዮ አፔሊዩስ Mario Appellus የተባለው ኢጣሊያዊ በደረሰው መጽሐፍ[1] ‹የኢጣሊያ ቂም በቀል አወጣጥ በሚገባ አብራርቶ ጽፏል።

ኦክቶበር 3 1935 ከጧቱ 11 ሰዓት የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ለብዙ ጊዜ ዝግጅቱን አጠናቀው በመረብ የኢትዮጵያ ወሰን ጥሰው በመግባት ጦርነቱን ጀመሩ። የመጀመሪያ ጥሰው የገቡት ወታደሮች ኤርትራውያንና ባለ ጥቁር ሸሚዝ Camicce Nere የሚባሉ ፍሺስቶች ነበሩ። ኤርትራውያን መዋጋት ስለሚወዱ ጦርነቱን ይፈለጋሉ፤ ጥቁር ሸሚዞች ኢጣሊያን ስለሚወዱ ጦርነቱን ይፈልጋሉ። የመጀመሪያ የተገኙ የትግራይ ነዋሪዎች ሮማዊ ሰላምታ እየሰጡ የኢጣሊያ ወታደሮችን ተቀብሏቸዋል። የትንሽ መንደር ነዋሪዎች ማር፥ ዶሮዎች፥ እንቁላሎችና ወተት ያቀርባሉ፤ ትልቅ መንደሮች ፍየሎችና በሬዎች ያቀርባሉ።

1ኛ በአድዋ ጦርነት ምክትል መቶ አለቃ የነበረው፤ በዓዲግራት ተከበው የነበረው፤የኢጣሊያ ጦር አባል የነበረው፤አሁን ጀነራል የሆነው ሳንቲኒ በሚመራው የኢጣሊያ ጦር ምንም ተኩስ ሳይሰማ አዲግራት በጣሊያኖች እጅ ወደቀች።

2ኛ አምባ አውገር የነበሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች አነስተኛ ተኩስ ከፍተው ወደ ኋላቸው ሸሹ። ጀኔራል ፒርሲዮ–ቢሮሊ ‹Pirzio -Biroli› የአካባቢው የኢጣሊያ ሠራዊት ዋና አዛዥ የነበረው ከፍ በማድረግ መፈክር በማሰማት ኦክቶበር 5 ቀን 1935 ዓ.ም የአንባ አውገር በኢጣሊያ መያዝ በሚከተለው ያከብረዋል።

ጀኔራሉ ‹Saluto Al Re› ለንጉሡ ሠላምታ ሲል፤

ወታደሮቹ ‹Viva Il Re› ንጉሡ ለዘላለም ይኑር ብለው ይመልሳሉ

ጀኔራሉ ‹Saluto al Duce› ለዱቼ ሠላምታ ሲል፤

ወታደሮች ‘A Noi›ለእኛ ይላሉ

3ኛ ዐድዋ በቀኝ በኩል መረብ የተሻገሩ በጀነራል ማራቪኛ የሚመራ የኢጣሊያ ሠራዊት ግን ኦክቶበር 3 መረብ እንደተሻገረ ተኩስ ገጠመው።

1.Mario Appelius : I L Crollo Dell' Impero dei Negus



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከይፋ ሲወርዱ

(fot. Associated Press - Londra)
Hailè Selassiè scende, a Caifa, dall'incrociatore «Enterprise»



እንደተለመደው መንገድ የሚፈትሽ የፊት አጥቂ ፊት አውራሪ ጦር ባንዳ ናቸው። የመቶ አለቃ ሞርጋንቲኒ ደጋፊ ‹Morgantini› የሚመራ ባንዳ ራማ ላይ ተኩስ ተከፈተበት፤ የመቶ አለቃው አፈቱ ላይ በጥይት ተመቶ Viva l'Italia እያለ ሲሞት የመጀመሪያ ኢጣሊያዊ በጦር ሜዳ የሞተ ሆነ። ከባንዳዎች ምን ያህል ሰው እንደሞተና እንደቆሰለ አልተገለጠም። ጣሊያኖች በዐድዋ የነበረው በራስ ሥዩም የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ተቃውሞ ገጠማቸው፤ ታማኝ የኤርትራ ወታደሮችና ባንዳዎች እያስቀደሙ በእግረኛ የኢጣሊያ ነጭ ወታደሮች እየታገዙ ኦክቶበር 4 እና 5 በዳዕሮ ተክሌ እና አካባቢው ውጊያ ሲካሄድ ቆይቶ ኦክቶበር 6 ዐድዋ በጣሊያኖች እጅ ስትወድቅ በ1896 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ለሞቱ ጣሊያኖች በአንድ መቃብር ሐውልት የሚቆመው ቀደም ብሎ የተጻፈው «በዐድዋ የሞቱ በድል አድራጊዎች ተበቅሏል» በሚል የመታሠቢያ ጽሑፍ በማቆም ዐድዋ ለዘለዓለም ኢጣሊያዊት አድርገናታል ብሏል። ኦክቶበር 14 የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ የነበረው ዴ ቦኖ በጦር ሹማምንቶቹ ታጅቦ ዐድዋ ገባ፡ በዐድዋ የሞቱ ጣሊያኖች ፋሺስት ኢጣሊያ ስለተበቀለቻቸው በሠላም መተኛት ይችላሉ በማለት ንግግር አሰምተዋል።

ወደ ትግራይ የገባው የኢጣሊያ ጦር 100.000 ብዛት ነበረው። ኦክቶበር 16 የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ትሆናለህ ብለው ጣሊያኖች ሀገሩን እንዲከዳ ያደረጉት የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ የአፄ ኃይለ ሥላሴ አማች የምሥራቅ ትግራይ ሀገረ ገዥ የነበረው በአንድ ተራ ኢጣሊያዊ ሥር ሆኖ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የዐጋሜ ገዥ አድርጉ ሾሙት።

ኦክቶበር 23 ለወደፊት የዴ ቦኖ ቦታ የሚረከብ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ሹመት ያገኘው ማርሻል ባዶሊዮ ለሥራ ጉብኝት ዐድዋ ድረስ መጥቶ ስለነበረ ጦርነቱ ወደ የተደረገበት ቦታ በመሄድ ድምጹን ከፍ በማድረግ ‹በዐድዋ የሞታችሁ ሁሉ› ብሎ ይጠራል።

የተሰበሰቡ ጀኔራሎች–ወታደሮች በተጠንቀቅ ቆመው በሙታኑ ስም ሆነው «አቤት»Presente ብለው መልስ ይሰጣሉ።

በዐድዋ ጦርነት የተሳተፉ እንደገና ዐድዋ በኢጣሊያ ሥር የተሳተፉ ኤርትራውያን በፈረስ ሆነው የብረት ሰላምታ ያቀርባሉ። በዚሁ ዐይነት የዐድዋ ቲም በቀል አከባበር ተፈጽሟል።

በዐድዋ ጦርነት ጊዜ ጣሊያኖች ወታደሮቹን ሲገድሉ የነበሩ የትግራይ ነዋሪዎች አጆች አሁን የኢጣሊያ ልጆች ወደ ዐድዋ በሚመለሱበት ጊዜ ለኢጣሊያ ባንዲየራ ሮማዊ ሠላምታ በመስጠት ላይ ይገኛሉ።



Fot. Keystone - Londra

Una signora inglese offre fiori ad Hailé Selassié, al suo arrivo a Londra!

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በለንደን ሲደርሱ ከአንድ እንግሊዛዊት ወይዘሮ እንኳን ደህና ገቡ በማለት የአቀፉ አበባ ሲበረከትላቸው



መቀሌን ለመያዝ የተሰጠው ትዕዛዝ ኖቬምበር 2 ነበር፤ ኖቬምበር 3 ከጧቱ 12 ሰዓት ከዕዳጋ ሐሙስ ከሀዲው ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሀገሩን ሥለለቀቀላቸው ወጊያ የሌለው ጉዞ ወደ መቀሌ ይጀምራሉ። የፊት አጥቂ መንገድ ጠራጊዎች ኢንዲጀኖች ‹ኤርትራውያን› ባንዳና መደበኛ ነበሩ። ኖቬምበር 5 ገራዓልታ ላይ ከኢትዮጵያ ትንሽ ተቃውሞ ገጠማቸው ው፤ ሆኖም በቀላሉ እንዲሸሹ አደረጓቸው ኖቬምበር 8 ጣሊያኖች መቀሌ አካባቢ ሲደርሱ አሬዮፕላኖቻቸው መቀሌ ውስጥ የኢትዮጵያ ወታደሮች እንደ ነበሩ ተመልክተው ተመ ለሱ። ግፈኞች ጣሊያኖች መቀሌ ሲገቡ የግማሽ ትግራይ አገሩ የነበረው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የአንድ ምክትል ወረዳ፤ የጄመና ብርጌድ አዛዥ በማድረግ የፊት አጥቂ ለጣሊ ያኖች መንገድ ጠራጊ በማድረግ ኖቬምበር 9 ቀን ምንም ውጊያ ሳይገጥማቸው መቀሌ ገቡ።

መቀሌ 1888 ዓ.ም ‹1896› ጣሊያኖች ከ40 ዓመት በፊት ማለት ጀንዋሪ 6 1896 ዓ.ም ምሽግ ሰርተው ጦር ሰፈር መሥርተው የነበረው የአንድ ሻለቃ ወራቸው በአፄ ሚኒልክ የሚመራው በኢትዮጵያ ጦር ተከቦ እንደነበረ ያስታውሳሉ። በከበባው ጊዜ የተከበቡ ጣሊያኖች እጃቸውን እንዲሰጡ ከኢትዮጵያውን ተጠይቀው ፍቃደኞች ስላል ነበሩ ወደ ምሽጉ ገብው ለመግባት ለሁለት ቀን ኢትዮጵያኖች ሞከረው ስላልተሳካላቸው በእቴጌ ጣይቱ የጦር ታክቲክ በመመራት በሶስተኛ ቀን ጣሊያኖች ውሃ የሚቀዱበትን ቦታ አጥቅቶ ለመያዝ የሞከረው የኢትዮጵያ ጦር ስለተሳካለት፤ ጣሊያኖችን መልሶ በማጥ ቃት፤ምንጩን ለመያዝ ስላልሞከሩ፤ ጣሊያኖች የሚጠጡበት ውሃ አጡ።

አፄ ምኒልክ ጣሊያኖች በውሃ ጥም በከንቱ ሰው እንዳያልቅ እጃቸውን እስኪሚ ሰጡ ድረስ በኃይል የማጥቃት እርምጃ እንዳይደረግ አዘዘ። ጀንዋሪ 10 ጣሊያኖች ከነበራቸው የተጠራቀመ ውሃ ለጋማ ከብቶች እንዳይሰጥ አገዱ። ጀንዋሪ 11 ለመጠጣት ካልሆነ ለሌላ ነገር እንዳ ይጠቀሙ አገዱ፤ በ12 ለእያንዳንዱ ወታደር በቀን አንድ ሊትር ብቻ ውሃ እንዲታደል አደረጉ። በ15 ግማሽ ሊትር ብቻ በቀን እንዲታደል ተደረገ። በ18 ሩብ ሊትር ብቻ በቀን እንዲታደል ተደረገ። በ20 ጣሊያኖች የነበራቸው ውሃ ጥቂትና ጭቃ የተቀላቀለበት ነበር። ቁስለኞቻቸው በውሃ ማጠብ ስላልቻሉ ከውሃ ጥም ሌላ ቁስላቸው በስብሶ ይሞቱ ነበር፤ ያልሞቱም በውሃ ጥም ይሰቃዩ ነበር። ጣሊያኖች በተደጋጋሚ ከጦር ምሽጋቸው መሳሪያ ቸውን እንደያዙ በሰላም እንዲወጡ ከአፄ ምኒልክ የቀረበላቸው ጥሪ ሳይቀበሉ ከቀሩ በኋላ ከበላይ አለቆቻቸው ስምምነት ስለደረሰ ጀንዋሪ 21 ቀን ምሽጋቸውን ለቀው በክብር መውጣታቸው በከፍተኛ ኩራት ያስታውሱታል።

ኤርትራውያን የቅጥር ወታደሮች፤ የኢጣሊያ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች፤ ታዋቂ ሰዎች፤ ባለሥልጣኖች፤ የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች፤ ሌሎችም በበዓሉ ተካፋይ እንዲሆኑ ጥሪ የተደረገላቸው ሰዎች በተገኙበት ግፍ የማይሰማቸው ጣሊያኖች ከሐዲው ደጃዝማች ኃይለ



Negus Hailé Selassié giunge a Southampton il 3 giugno 1936-XIV (Int. Associated Press - London)

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በእንግሊዝ ሀገር አቀባበል ሲደረግላቸው



ሥላሴ ጉግሳ በመቀሌ ከተማ የኢጣሊያ ባንዲራ እንዲተክል አደረጉት፤ ልዩ ልዩ መዝሙሮችና ብሔራዊ መዝሙር እየዘመረ አንድ ኢጣሊያዊ ኰሎኔል ድምጹን ከፍ በማድረግ «ሻለቃ ጋሊያኖ» ብሎ ይጮሃል።

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የተሰበሰቡ ወታደሮች አቤት presente በማለት መልስ ይሰጣሉ።

እንደ ገና ኰሎኔሉ «በ1896 ዓ.ም የሞታችሁ ወታደሮች» በማለት ሲጠራ፤

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች አቤት ‹presente› የሚል መልስ ይሰጣሉ።

በመጨረሻም በተለመደው የኢጣሊያኖች መፈክር፤

ለንጉሡ ሰላምታ Saluto Al Re ብሎ አዛዡ ሲጮህ ወታደሮች Viva Il Re ንጉሡ ለዘለዓለም ይኑር የሚል ጩኸት ከወታደሮቹ መልስ ይሰጣል። Saluto Al Duce ቢ ሰላምታ ለዱቼ የሚል ጩኸት አዛዡ ሲያሰማ ወታደሮች፤ ጀኔራሎች፤ሲቪሎች በአንድ ላይ A Noi ለእኛ በሚል ጩኸት መልስ ይሰጣሉ።

በዚህ ዐይነት የመቀሌ በጣሊያኖች እጅ መውደቅና ከ40 ዓመት በኋላ የቀድሞ የሽንፈታቸውን ቂም በቀል ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል።

# አምባ አላጂ

በጀኔራል ሞንታኛ Montagna የሚመራ የኢጣሊያ ጦር ፌብሯሪ 28 1936 ዓ.ም አምባ አላጂን ጣሊያኖች በተቆጣጠሩ ጊዜ እንደተለመደው መፈክር በማሰማት ነበር ቂም በቀላቸውን ያሰሙት።

ጀኔራሉ «ሻለቃ ቶዜሊ» Maggiore Toselli ብሎ ሲጠራ ወታደሮች በሻለቃ ቶዜሊ ስም አቤት Presente ብሎ ይመልሳሉ።

ቀጥሎም ጀኔራሉ «የክብርና የመስዋእትነት የጦር ጓዶቼ» ብሎ ሲጠራ፡

ወታደሮች በሙታኑ ስም አቤት Presente በማለት መልስ ይሰጣሉ።

የቀድሞ የአምባላጂ ጦርነት የቂም በቀል መታሰቢያ በዚህ ዐይነት ሁኔታ ተከብሯል።

በተምቤን፤በእንደርታ፤ በሽሬ፤ በማይጨው ላይ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ ያደረጓቸው ጦርነቶች ኢጣሊያኖች ድል ሊቀዳጁ የቻሉት 1ኛ ባሰማሩዋቸው ወታደሮች ብዛት 2ኛ በነበራቸው የጦር መሣሪያዎች ብዛትና ጥራት 3ኛ በነበራቸው በአሬዮፕላኖች የበላይነት 4ኛ በአንድ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ብቻ ስለሚመሩ ነበር። ኢትዮጵያውያን ለኢጣሊያ የጦር አሬዮፕላኖች አይበገሩም ነበር፤ ጣሊያኖች ለነበራቸው የጦር መሣሪያ ብልጫም በጀግንነታቸው

ሊደቋቋሙት ይችሉ ነበር፤ ኢትዮጵያውያን ይጉድላቸው የነበረ ማእከላዊ ጠቅላይ አዝና ተመጣጣኝ ያልሆነ የወታደር ብዛት ነበር።

ኢጣሊያ በሰሜን ጦር ግንባር ብቻ 400.000 ወታደር ስታሰልፍ የኢትዮጵያ ወታደር ግን ከዚህ ቁጥር ግማሽ ነበር። የኢጣሊያ ወታደር በአንድ ሰው ሲታዘዙ የኢትዮጵያ ወታደሮች ግን በሰሜን ጦር ግንባር እርስ በርስ የማይገናኙ፤ በአራት ቦታ ተበታትነው ነበር የተዋጉት፤ በደቡብ ጦር ግንባርም በሦስት ቦታዎች ተከፋፍለው ነበር። ስለ ኢትዮጵያውያን ጀግንነት ጠላት ራሱ መስክሮላቸዋል። ኢትዮጵያውያን በዘመናዊ የውትድርና ተደራጅተው የመዋጋት ብቃት የላቸውም የሚለው ኤውሮጳውያን የነበራቸው አመለካከታቸውም ትክክል ሆኖ አልተገኘም። ንጉሡ በተካፈለበት በማይጨው ጦርነት በዘመናዊ ውትድርና የተገነባ የክቡር ዘበኛ ሠራዊት በባህላዊ ከተደራጁ በሌሉች የኢትዮጵያ ወታደሮች ጠላት በመውከረው መሠረት በበለጠ ተዋጋ እንጂ ያነሰ አልነበረም። በጣሊያኖች ግምት ንጉሡ ባገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ድጋፍ ለማግኘት በተወሰነ ቦታ አሸነተኛ ቢሆንም ድል ለመጐናጸፍ ጥር ነበር። ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ :Appelius በደረሰው መጽሐፍ የማይጨው ጦርነት ለሁለት ይከፈላሉ 1ኛ የኢትዮጵያ ክቡር ዘበኛ ጦር በነሮች ጣሊኖች ክፍል መካን በተባለው ቦታ ያደረገው የማጥቃት እርምጃ 2ኛ በጣሊያኖች ላይ የተደረጉ ማጥቃት ውጤት ስላልሰጡ የኢትዮጵያ ክቡር ዘበኛ ጦር የመካን ጥቃቱን በማቆም ኤርትራውያን ሠፍረውበት ወደ ነበረ ወደ ማይጨው ከፍተኛ ጥቃት ሰነዘረ። በተለይ ከሌሎች ክፍሎች ተለይቶ ርቆ ለፍር ይመስል የነበረው 10ኛ የኤርትራ ባታሊዮን ላይ ጥቃቱን አጠናከረ። በዚሁ ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ የተመኘውን አገኘ፡ ኢትዮጵያውያን በወጥመዱ ገቡለት። ድል ያለ መስዋዕትነት አይገኝም በሚለው መፈክር በመከተል የኢጣሊያ ጠቅላይ አዛዥ 10ኛ የኤርትራውያን ባታሊዮን ለአጠቃላይ የኢጣሊያ ድል ሲባል መስዋዕት እንዲሆን ስለወሰነ አንድ ሜትር ወደ ኋላ ሳያፈገፍግ እስከ መጨረሻ እንዲዋጋ ወሰነ። ኤርትራውያን ብቻ ሳይሆኑ ጣሊያኖች የጦር መኰንኖችም መስዋዕት እንዲከፍሉ ስለተወሰነ አብዛኞዎቹ በጦር ሜዳ አለቁ። ከሞቱት መሃል 1ኛ የባታሊዮኑ አዛዥ ኮሎኔል ሩጀሮ Rugero 2ኛ በውጭ ሀገር (ፈረንሳይ) ይኖር የነበረ ወዶ ዘማቹ ሻምበል ታራንቲኖ Tarantino 3ኛ የክፍለ ጦሩ (ዲቪዚዮን) ኢታ ማጆር ሹም ኮሎኔል ሮንዜቲ Ronzetti 4ኛ አብዛኞዎቹ ጣሊያኖች የበታች የጦር መኮንኖች ።5ኛ የተምር 10ኛና 5ኛ የባታሊዮን አዛዥ ኮሎኔል ኮርሲ Corsi የመቁሰል አደጋ ብቻ ደረሰበት።

ከኢትዮጵያ ወገን ከ30.000 የክቡር ዘበኛ ጦር ሌላ በማይጨው የተካፈሉ የሚከተሉት ነበሩ።



1 ሊጋባ ጣሰው 8500 ወታደር
2 ራስ ከበደ 2000.–
3 ራስ ጌታቸው 4000 –
4 ደጃዝማች አደፍርስ 7000 ወታደር
5 ፊታውራሪ ብሩ ምኒልክ 2000 –
6 ፊታውራሪ አሸናፊ 5000 –
7 ፊታውራሪ ነጋሽ 2000 –
8 የፖስታ ሚኒስትር 1500 –
9 ቀኛዝማች በየነ በላይነህ 3000 ፈረሰኞች
10 ቀኛዝማች በለው 900 ወታደሮች
11 ፊታውራሪ አስራት ወ/ገብርኤል 2000 ወታደሮች
12 ሊቀምንኳስ ኃ/ ማርያም 2000 –

ከጣሊያኖች ወገን በአጥቂ የኢትዮጵያ ጦር ላይ ከሩቅ እነጣጥረው የሚተኩሱ መድፎች ስለነበራቸው፤ 10ኛ የኤርትራውያን ባታሉዮን ብቻውን የተገለለ አልነበረም። ስለዚህ በኢትዮጵያ ተዋጊዎች ላይ ከባድ ጉዳት ሊያደርሱባቸው ችለዋል።፤ 5000 የኢትዮጵያውያን አስከሬኖች ተቆጥረዋል፤ በዚህ መሠረት ከቀኑ መጨረሻ የኢትዮጵያ ጦር ጥቃት እያካሄደ መሆኑን እያስመሠለ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ግድ ሆነበት።

የኢጣሊያ የሰለላ አይሮፕላኖች የኢትዮጵያ ጦር ማፈግፈግ በማመልከታቸው በወታደሮች ብዛት ከኢትዮጵያ ጦር አራት ጊዜ የሚበልጠው የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት በሙሉ የመልሶ ማጥቃትና ማሳደድ ጀመረ። የኢጣሊያ ጦር አይሮፕላኖችም ያለማቋረጥ መደብደብ ተጠሉ። ጣሊያኖች የነበራቸው ፍራቻ የኢትዮጵያ ጦር ደሴ ላይ ተሰብስቦ ሌላ የጦርነት ዙር ይገጥመናል የሚል ነበር፤ ይኸውም በጥቂት ቀናት ውስጥ አዲስ አበባ ለመድረስ የነበራቸው ዓላማ በመጠኑም ቢሆን የሚያሰናክል ስለነበረ ዐላማቸው ብርቱ ጥረት አድርገው የኢትዮጵያ ጦር ተበታትኖ እንዲቀር ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ብቃት ያለው መሪ ቢኖረው ጣሊያኖች ከማይጨው ጦርነት በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ ለመግባት ባልቻሉ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ግን መሪ በማጣቱ ብቻ ተበታትኖ ቀረ። ሕይወቱን ለማትረፍ ሸሹቶ ወደ እየትውልድ ሀገሩ በሚያደርገው ጉዞ ብዙዎቹ በኢጣሊያ የጦር አይሮፕላኖች ተረሹ። በኢትዮጵያ ጉሩ የነበረው ስሜት በሚመለከት የንጉሡ ወታደራዊ አማካሪ የነበረው ሩሲያዊ ኮሎኔል ኮኖቶፍ የተባለው በሩሲያ ቋንቋ የጻፈው ማስታወሻ በመጠኑ ገልጾታል። ማስታወሻው የተገኘው ጣሊያኖች አዲስ አበባ ሲገቡ በአንድ ቦታ ተጥሎ ተረስቶ ነበር። ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ በደረሰው መጽሐፉ ከሩሲያዊ

ጽንቁ ወደ ፈረንሳይኛ በአልጋ ቦራኒ ተተርጉሞ የነበረው ወደ ጣሊያንኛ ተተርጉሞ አውጥቶታል። ማስታወሻ የሚያወራው በሦስት ሳምንት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ተዳግሞ ኃይለ ሥላሴ ከማይጨው ጦርነት ሽንፈት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ስላደረገው ሽሽት ነው። በገሉ ንጉሡ በጦርነቱ ወቅት ያሳየው የጀግና ሰው ስሜት ነበር፤ በጦርነቱ ጊዜ በጦር ሜዳ ይገኝ ነበር፤መድፈኛ ክፍል ተገኝቶ ራሱም መድፎቹን ይተኩስ ነበር። የማዘዝ ችሎታ ግን ዜሮ ነበር በማለት ተችቷል። ሠራዊቱም የተዋጋው ያለ እቅድ በዘፈቀደ ነበር ብሏል። የጣሊያኖች ጀግንነትን ያደንቃል፤ የኢትዮጵያ ሹማምንቶችና ንጉሡ ስለጣሊያኖች ጀግንነት የሰጡት አስተያየቶች ይጠቅሳል፤ በሚሸሸው የኢትዮጵያ ጦር ሙሉ ህገ ወጥነትና ብጥብጥ ሰፍኗል። ኮረም አካባቢ ንጉሡ ጦርነት ለመገጠም አስቦ ነበር። ንጉሡ በተሰበሰቡበት በአንድ ዋሻ ውስጥ የጦር ስብሰባ ምክር ቤት በተደረገ በስብሰባው መጨረሻ ንጉሡ የነበሩት ጥይቶች፤ ሽጉጦች ፤ ብርድ ልብሶች ፤መጠጦች፤ የቆርቆር ምግቦች ለወታደሮቹ አደላቸው፤ በጦሩ ላይ ውዥንብሩ ከፍተኛ ነበር። በጦር ሜዳ ውስጥ በየሚደው በየሸን ተረሩ የሚሸሹ ሹማምንቶች፤ወታደሮች በቅሎች፤ አህዮች ብቻ ይታዩ ነበር። ንጉሡ አንድ ሌሊት ያደረበት በማግሥቱ በጣሊያኖች እጅ ይወድቅ ነበር። ኮሎኔሉ ከንጉሡ ጋር ተጠፋፉ፤ማታ ግን ኮረም ላይ ተገናኙ። ራስ ጌታቸው ቆስሉ በመንገድ ተረ፤ ቀኑ ቅዳሜ ነበር ኮረም ላይ የነበረው ብጥብጡ ተባብሶ በቃል ተነገር በማይቻል ሁኔታ ነበር። ጣሊያኖ ች ምናልባት በአሪዮፕላን ሲመለከቱት ቦታ ለመያዝና ውጊያ ለመግጠም ወደኋላ የሚያ ፈገፍግ ሠራዊት ይመስላቸው ይሆናል። ኮረም ላይ ንጉሡ በተዘጋጀለት በአንድ ዋሻ ነበር ያደረው፤ ዋሻው በወታደሮች የተሞላ ነበር።

እያንዳንዱ ወታደር በመጣሪያ እያስፈራራ ያገኘውን ሁሉ ይዘርፍ ነበር። ንጉሡ በወታደሮቹ ከመዘረፍ አላመለጡም። እሁድ ቀኑን ሙሉ ከንጉሡ ጋር ከተጠፋፉ በኋላ ማታ ከአንድ ተራራ በኮረም አጠገብ ተገናኙ። ከሩቅ አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር ኮረም ጣሊያኖች እንደገቡ ይታየን ነበር፤ ብዙ አልነበሩም። ከ2000 አይበልጡም። ንጉሡ እንድን ነገሟቸው ፈልጉ ሹማምንቶቹ ግን ተዋጊ ወታደሮች እንደሌላቸው ነገሩት። ንጉሡም ይኼ የሚታየው ሁሉ ወታደር አይደለም ወይ? ብሉ ይጠይቃል።ሹማምንቶቹም የሚሸሹ ወታደሮች ናቸው ይሉታል፤ ቀጥሎም ንጉሡ አቁሟቸው ብሉ ትእዛዝ ለመስጠት ይሞክራል። «ግርግሩ ሆይ የማይቻል ነው» ብለው መልስ ይሰጣሉ። ንጉሡም ለምን ብሉ ይጠይቃል፤ የንጉሡ ልዩ ጸሐፊ ወ/ጊዮርጊስ ምክንያቱም ውሾች ናቸው፤ በእነሱ ላይ ጥይት መተኮስ በተገባ ነበር በማለት ንዴቱን ለንጉሡ ይገልጽለታል፤ በመጨረሻ ንጉሡ ምግብ ለመብላት ይጠይቃል «ግርግሩ ሆይ አይቻልም» ይሉታል፤ «ትሉ ብለን ካልሸሽን ራያ አዛቦ በጣሊያኖች ጦር መትረየሶች የሚመሩ ከአኛ ከአንድ ኪሉ ሜትር የሚገኙ ይማርኩናል» ብለው ያስረዱታል።



ለንጉሡ በቅሉ ከኮረም የተዘጋጀ ይቀርብለታል። ንጉሡም ወዲያውኑ በቅሉ ጀርባ ወጥቶ «ወደ ቆቦ እንሂድ» ይላል «ግርግሩ ሆይ አይቻልም ከጣሊያኖች ጋር የሚተባበሩ መንገዱ በራያ አዘቦ ተቋርጧል» ሲሉት ንጉሡ «እንግዲያውስ ወደ ላሊበላ እናምራ» ብሉ ትእዛዝ ይሰጣል። እየጋለቡ ቀንና ሌሊት ተጉዘው ላስታ ሲደርሱ ሀገሩና ሕዝቡ ስለጦርነቱ ምንም የማያውቁ ሰላም የሰፈነበት አዩ።

ራስ ሥዩም ከኮረም ከጥቂት የትግራይ ወታደሮች ጋር ወደ ሀገሩ አመራ። ንጉሡ ወደ ትግራይ ተመልሶ የደፈጣ ውጊያ ጦርነት እንዲቀጥል ቢመክረው በ61 ዓመት እድሜ ሽፍታ አልሆንም ብሉ መልስ ሰጠ። ራስ ሥዩም ከሰሜን ትግራይ ወደ ደቡብ፤ተንቤን ከጦሩ እያፈገፈገ ሲመጣ ምንም አይደለም ራስ ካሣ ሲደርስ የተደራጀ ምንም የማይጐድለው ጦር ስላለው ነገሩ ይቀየራል እያለ በተስፋ ይናገር ነበር። ራስ ካሣ ራሱ ተሸንፎ ተንቤንን ለቆ ሲሄድ የሁሉም ተስፋ በዘመናዊ መሣሪያ ተታጥቆና የሰለጠነ ከምርጥ የአውሮፓ ጦር ሠራዊት የማያንስ ያልተነካ ወደ ንጉሡ ጦር ነበር ተስፋቸው፤ በንጉሠ ነገሥቱ ሁሉም እምነት ነበራቸው። አሁን የሚታየው ግን ንጉሡ በመሸሽ ላይ እንደሚገኝ ፤ ብቻው ከሠራዊቱ ተለይቶ፤ጥለውት የሸሹ፤ በየሜካው ለመደበቅ የተገደደ፤ የራሱ ዘጉች ሳይቀር የሚተኩሱበት ሁኔታ ነው። ከሹማምንቶቹ አንዱ ብሪታንያ ምን እያደረገች ይሆን ብሉ ለኮሎኔሉ ሲጠይቀው፤ሌላው ሹም ጃፓንስ ምን እያደረገች ነው ብሉ ይጠይቀዋል። ንጉሡ ነገሥቱ ራሱም ጣሊያኖች አዲስ አበባ ድረስ ለመሄድ ሃሳብ ይኖራቸው ይሆን? ብሉ ከጠየቀ በኋላ መልስ ሳይሰጠው ይኼን ለማድረግ ልናግዳቸው እንችልም ብሉ ራሱ ይመልሳል። ንጉሡ ከኮረም ላሊበላ የደረሰው በሁለት ቀን ጉዞ ነበር። ኃይለ ሥላሴ ወደ ላሊበላ የመጣበት ምክንያት ከጠላት ጦር ለመደበቅ ይሁን ወይንስ ከንጻግት ቄሶች ምክርና ቡራኬ ለመቀበል ይሁን ማንም ሊያውቀው አልቻለም። ንጉሡ በአንድ ቤት ውስጥ ሲገባ ከሁለት ቀን በኋላ ነው የወጣ። ንጉሡ እንደወጣ ኮሎኔሉ በተገኘበት የጦር ስብሰባ ተደርጉ ሁሉም የስብሰባው ተሳታፊዎች ሀገሪቷን ከውድቀትና ሽንፈት ለማዳን እንደማይቻል ተረድተው ነበር። በወቅቱ በስብሰባው ሁሉም የቀድሞ ጠላቶች ወዳጅ ሆነው ነበር፤ ራስ ጌታቸውም በስብሰባ ተገኝቶ ነበር። ንጉሡ በኃዘን ተውጦ ነበር።

የኮሎኔሉ ማስታወሻ የተጻፈበት የጦሩ ቀኑን አይጠቅስም፤የሚጠቅሰው የሳምንቱን ቀናት ብቻ ነው። ከላሊበላ ተነስተው ደሴ አካባቢ ሲደርሱ ንጉሡ ጣሊያኖች ወደ አዲስ አበባ የሚያደርጉትን ጉዞ ለማወቅ ያስባል። አንድ ያጃገማች መሬት ሰጥተን ለምሳሌ አጋዴን ከጣሊያኖች ጋር ዕርቅ ለማድረግ አንችልም ወይ? ብሉ ለንጉሡ ይጠይቃል፤ መልስ አልተሰጠውም። እሁድ ማታ ንጉሡ በምን ቅድመ ሁኔታ ኢጣሊያ ሰላም ለማድረግ ትቀበል ይመስልሃል? በማለት ለኮሎኔሉ ጠየቀ። በግልጽ ለመናገር

ከረቀደልኝ «ግርማዊ» ሆይ አሁን ሙሶሊኒ ባገኘው ወታደራዊ ሚዛን ካልሆነ በስተቀር ሌላ ሰላም አይቀበልም፣ ቢቀበል እንኳ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ተበታትና መንግሥት አልባ ሆና ስለምትገኝ ኢጣሊያ ከየትኛው መንግሥት ልትደራደር ትችላለች» ብሎ መልስ ሰጠው ።ማክሰኞ መቅደላ ስንደርስ ንጉሡ ለ24 ሰዓቶች ቆይታ ለማድረግ ፈልጐ ነበር፣ ሀገረ ገዥው ግን የሀገሩ ሕዝብ በንጉሡ ላይ አደጋ ለመጣል ሃሳብ እንዳለው ለንጉሡ ነገረው።

በችኮላ ብዙ ስንቃችንን ትተን ለቀን መሄድ ተገደናል። በአንድ ትልቅ ሸንተረር እንደደረስን ከሀገሩ ሕዝብ ትልቅ ጥቃት ደረሰብን፣ ብዙ ወታደሮች ሞቱብን፣ ንጉሡም ከአደጋ ሊያመልጥ የቻለው በዕድል ነው። ደሴ በጣሊያኖች እጅ ወደቀች የሚል ዜና ስንሰማ ከእኛ 35 ኪሎ ሜትር ወደ ምትገኝ ወደ ወረኢሉ ለማምራት ሞከርን፣ ሆኖም ወረኢሉም በጣሊያኖች እጅ ወድቃለች የሚል ሌላ ዜና ሰማን። ንጉሡ ጣሊያኖች በአግራቸው ከንፍ አላቸው ልበል የሚል አስተያየት ሰጠ። ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ቀይረን ቀንና ሌሊት በመንዝ ወደ ፊት ለማምራት ወሰን። ንጉሡም ቶሎ ብለን ካልተራመድን ጣሊያኖች ከኛ በፊት አዲስ አበባ ይገባሉ አለ። ብዙ ሕዝብ በሚኖርባቸው መንደሮች ለማለፍ እንቆጠብ ነበር ምክንያቱም ሕዝቡ የመንግሥት ንብረትና የታላላቅ ሰዎችን ቤት ይበርፍ ነበር። ሮቡዕ 21ኛ የሽሽት ቀን የኢጣሊያ ዝቅ ብለው የሚበሩ የጦር አሬዮፕላኖች አይተውን በቦምብ ሊጥሉብን ሊጀምሩ ጥቅጥቅ ባለ ደን በመግባት ሕይወታችንን ለማትረፍ በቅተናል፣ ጣሊያኖች ግን ደኖችን ሳይቀር በአሬዮፕላን ይደበድቡ ነበር።

ሐሙስ ፍቼ ስንደርስ አምስት መኪናዎች ይጠብቁን ነበር። በቅድሚያ ንጉሡ በእጁ ሰላምታ ሰጥቶን በአንደኛው መኪና ውስጥ ገብቶ ወደ አዲስ አበባ ጉዞውን ቀጠለ።

ከደሴ አዲስ አበባ ለመድረስ ጣሊያኖች አስር ቀን ብቻ ነው የፈጀባቸው። ጦርነቱ አብቅቷል፣ ከሁሉ የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ክፍል የሚመከሉ ተካፋይ የሚሆኑበት የሰልፍ ጉዞ ነው። ሰልፉን ከሚመሩ ባለሥልጣኖች መካከል የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ከማርሻል ባዶሊዮ ሌላ የቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ለሶና እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ገዥ ሆኖ የተሾመው የሮማ ከተማ ከንቲባ የነበረው ቦታይ ‹Botal› የተባለው ይገኙባቸው ነበር። ሕዝቡ ጣሊያ ኖች በሚያልፉበት እንቁላሎችን፣ዶሮችን፣ በጉችን፣ ፍየሉችን፣ በሬዎችን ስጦታ እያበረከተ ይቀበላቸው ነበር። በአንዳንድ ቦታ በሽኖ ሕዝቡ በጭፈራ ሲቀበላቸው የኢጣሊያ ወታደሮች ይገረሙ ነበር። ምክንያቱም በዐድዋ ያሸነፉን የማይበገሩ ጀግኖች የሸዋ ቄሮች ነበሩ ፤ የኢጣሊያ ቀንደኛ ጠላቶች ሸዋውያን ናቸው ተብለው ተሰብከው ስለነበረ የኢጣሊያ ወታደሮች የት ነው የሚገኙት እነዚህ ሸዋውያን ጠላቶቻችን እያሉ በአይናቸው ለማየት ጓጉተው ነበር። ከገዥ መደብ ከተባሉ ከሸዋውያን ጥሩ አቀባበል ሲደረ ግላቸው ኃይለ ሥላሴ ሸዋውያንም ጭምር እንደማይወዱት የተገነዘቡ መሰላቸው። አዲስ አበባ ለመድረስ ጓጉተው ጣሊያኖች ሌሊት እንቅልፍ አልነበራቸውም፣



የምግብ ፍላጐትም አልነበራቸውም። የመኪና መንገድ እየሠሩ ኤርትራውያን በአግራቸው ጣሊያኖች በመኪና በ‹1600 መኪና ዎች› እየተጓዙ «አዲስ አበባ የማናት ብሎ ሊጠይቅ አንድ ቡድን ሌላ ቡድን «የኛ ናት» ብሎ መልስ ይሰጣል። እንደገና «አቢሲኒያ የማን ናት»ብሎ ሲጠይቅ የመጀመሪያ ቡድን ሌላ ቡድን ደግሞ «የኛ ናት» የሚል መፈክር እያሰሙ ወደ አዲስ አበባ ይጓዙ ነበር።

ኃይለ ሥላሴ ከ20 ቀናት ሽሽት በኋላ አዲስ አበባ እንደገባ ጣሊያኖች መረጃ ደርሷቸዋል። ያለው ገንዘብና ንብረት በባቡር እየጫነ ወደ ጅቡቲ እየተጓዘ መሆኑን ደርሰውበታል። በአዲስ አበባ የነበረው የእንግሊዝ አምባሳደር ለሁለት ሰዓት ከንጉሡ ጋር ተገናኝቶ ዋና ከተማዋን ወደ ወለጋ አዛውሮ ጦርነቱን እንዲቀጥል የሚል ሃሳብ ለኃይለ ሥላሴ አቅርቦ ነበር። ኃይለ ሥላሴ ግን አወንታዊ ወይም ደግሞ አሉታዊ መልስ ሳይሰጥ የአዲስ አበባ ጅቡቲ ባቡር አስተዳደር ዳሬክተር ሙሴ ጀርባል ‹Gerbal› በአቃቂ ባቡር ጣቢያ ልዩ ባቡር ለንጉሡ እንዲዘጋጅለት አዝዞ ከግቢ የቀረቡለት 4 መኪናዎች ተሳፍሮ ወደ አቃቂ ለመሄድ በባቡር ተሳፈረ። ከምሽቱ 3 ሰዓት ወደ ግቢ መጥቶ የኃይለ ሥላሴን ውሳኔ ይጠባበቅ የነበረው ሕዝብ የእንግሊዝ መረጃ ክፍል ኃይለ ሥላሴ ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከመግባታቸው በፊት ጦርነት ገጥሞ ለመከላከል እንደሚሞክር ለሕዝቡ ንግግር ያሰማ ይሆናል የሚል ግምት ነበረው። ቀጥሎም እስከ መጨረሻ የደፈጣ ውጊያ እንደሚቀጥል ይደረጋል የሚል ግምት ነበረን። የኃይለ ሥላሴ እቅድ ግን ወደ ጅቡቲ ለመሸሽ ብቻ ነበር።

ጣሊያኖች እንደ እስራኤሎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መሬት እንደ ደረሱ ይመስላቸው ነበር።

በአዲስ አበባ ከተማ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ሱቆች፣ መኖሪያ ቤቶች ፣ ኤምባሲዎች ላይ ዝርፊያዎች ይካሄዱ ስለነበረ። የፈረንሳይ አምባሳደር ቢሮ ውስጥ እንዳለ በበራሪ ጥይት እጁ ላይ ቆስሎ ስለነበረ በራዲዮ ስልክ ከጣሊያኖች ግንኙነት አድርጐ ቶሎ ብለው አዲስ አበባ ካልገቡ በከተማዋ የሚገኙ ነጮች በሕይወታቸው የሚያሰጋ አደጋ እንደነበሩ ገልጾላቸው ነበር።ሜይ 4 በእግር የሚጓዙ ከኤርትራውያን ክፍለ ጦሮች 1ኛ ብርጌድ አዲስ አበባ ደረሶ ከእንጦጦ ተራሮች ዙሪያ ተሠማሩ። ሜይ 5 ጠዋት በመኪናዎች የሚጓዙ የኢጣሊያ ወታደሮች ክፍለ ጦሮች አዲስ አበባ ሲደርሱ በማርሻል ባዶሊዮ መሪነት በሰልፍ ከተማ ውስጥ ገቡ። የሰልፉ ተካፋዮች ከማርሻሉ ሌላ 2 የጦር አዛዦች ጀኔራሎች፣8 የዲቪዚዮንና የብርጌድ ጀኔራሎች፣ የቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር፣ የሮማ ከተማ ገዥ ይገኙባቸው ነበር።

የውጭ ሀገር ኤምባሲዎች ከዘራፊዎች ራሳቸውን ለመከላከል ተደራጅተው ነበር። የእንግሊዝ ኤምባሲ በ150 የሕንዳውያን ወታደሮች ይጠበቅ ነበር። በፈረንሳይ ኤምባሲ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የ17 ዜግነት ያላቸው ነጮች ተጠልለው ነበር።በዚሁ ጊዜ

ኤርትራውያን ወታደሮች ባዙር ጣቢያ፣ ጉምሩክ፣ የወታደር መፈሮች፣ ባንክና የከተማ ዋና ዋና መግቢያ በሮች እንዲቆጣጠሩ ሲታዘዙ በማርሻል ባዶሊዮ የሚመሩ በመኪና የሚጓዙ የኢጣሊያ ወታደሮች ሰልፈኞች ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ግቢ አመሩ። ጣሊያኖች በጀርመን፣ በፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ቱርክ ፣ ቤልጂዩም ኤምባሲዎች ደጃፍ ሲያልፉ እንደ ነፃ አውጪዎች በጭብጨባ አቀባበል ተደረገላቸው። በእንግሊዝ ኤምባሲ ደጃፍ ሲያልፉ ግን ጭብጨባ አልነበረም።

በማርሻል ባዶሊዮ የሚመሩ ጣሊያኖች ታላቁ ቤተ መንግሥት ገቡ። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ይሰቀልበት የነበረው የኢጣሊያ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቀለበት። 10.000 የኢጣሊያ ወታደሮች ግቢ ውስጥ ገብተው በአራት ማዕዘን ይቆማሉ፤ ለባንዴራቸው ወታደራዊ ሰላምታ ይሰጣሉ።[1]

ጣሊያኖች የተለመደው መፈክራቸውን ማሰማት ይጀምራሉ።

ማርሻል ባዶሊዮ የሥነ ሥርዓቱ ታላቅነትና ታሪካዊነት ይሰማው ነበር።

ማርሻሉ «ለንጉሡ ሰላምታ» Seluto Al Re ብሉ በከፍተኛ ጩኸት ሲያሰማ

ዙሪያው ያሉ ወታደሮች በአንድ ድምፅ በመጮህ «ንጉሡ ለዘለዓለም ይኑር» Viva Il Re በማለት ይመልሳሉ።

ማርሻሉ «ለዱቼ ሰላምታ» Saluto Al Duce በማለት ጩኸቱን ሲያሰማ

ወታደሮቹ «ለኛ» A Noi ብለው ጩኸት ያሰማሉ

ይህ መፈክር ለሦስት ጊዜ ይደጋገሙታል።

በዚህ ዓይነት አጭር ሥነ ሥርዓት የኢጣሊያ በዐድዋ ጦርነት ሽንፈት በማይጨው ጦርነት ቂም በቀል ድል አድራጊነት ተደምድሟል።

በዋናው ጦር አዛዥ በማርሻል ባዶሊዮ የሚመራ የኢጣሊያ ሠራዊት ከደሴ አዲስ አበባ ሲያመራ ፣ በሌላ ኢጣሊያዊ ሌተና ጀኔራል ስታራቸ የሚመራ የኢጣሊያ ጦር የኢትዮጵያ መሰዮ የአባይ ምንጭ የሆነው የጣና ሐይቅ ሲቆጣጠር ለወታደሮቹ «በዱቼ ስም የጣና ባሕርን ተቆጣጥረናል» የሚል መፈክር አሰምቷል ።[2] በዚሁ ጊዜ በጐርጐራ አድፍጠው የነበሩት የኢትዮጵያ ታጣቂዎች ተታውጊቻውን ለማሰማት ተኩስ ከፈቱባቸው። ጣሊያኖች ተደናግጠው ቢፈልጓቸውም ሊያገኙዋቸው አልቻሉም። ጣሊያኖች በጐርጐራ ተራራ ባንዲራቸውን ተከሉበት።

1. Mario Appelius : Il Crollo dell'Impero dei Negus p.193

2.Luca Dei Sabelli Storia Di Abissinia v 1v p.245



በዚሁ ጊዜ ሌተናል ጀኔራል ስታራቸ ከተሰበሰቡ ወታደሮች «ዛሬ በጦርነት ማእበል የተከበረ ፋሲካ 14ኛ የፋሺስት ዘመን በንጉሡ ስም፣ በዱቼ ስም በጐርጐራ ከፍተኛ ተራራ የኢጣሊያ ባንዴራ ተከያለሁ። የጣና ባሕር ውሃዎችን እንደገና ሊነጥቁን የሚመጣ ማንኛውም ጠላት ለመከላከል በቀይ ደማችን እንደምንደመስሰው ቃል እንገባለን፤ እናንተስ ቃል ትገባላችሁ?» ብሎ በጩኸት ባሰማበት ጊዜ «እንምላለን» የሚል ድምጽ ከወታደሮች ተሰማ።

ወዲያውኑ በአንድ ም/መቶ አለቃ አማካኝነት ከሁሉም ክፍለጦሮች የተውጣጡ ወታደሮች ወደ ጀኔራሉ ፊት ቀረቡ፤ ም/መቶ አለቃውም «በጦር ጓደኞቼ ስም ባንዴራችን የተከልንበት ከፍተኛ የጐርጐራ ተራራ የሙሶሊኒ ተራራ ተብሎ እንዲጠራ አለምናለሁ» ብሎ ሲጠይቅ፣ ጀኔራሉም «እንደጠየቃችሁ ይሆናል» የሚል መልስ ሰጥቷቸዋል። ከማይጨው ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ ጦር በተላን የሚመራ ጠቅላይ አዝ ስላልነበረው፣ የሚያዋጋ የጦር አዛዥ በማጣቱ፣ ተበታትኖ ቀረ ! ለኢጣሊያ ጦር አረዮፕላኖች የእሳት እራት ሆነ። ለዚሁ የዳረጓቸው የኢትዮጵያ መሪዎች በከሐዲነት ያስጠይቃቸዋል። ከማይጨው እስከ አዲስ አበባ የኢጣሊያ ሠራዊት በማርች እየተጓዘ በአንድ ወር አዲስ አበባ ገባ። ጠቅላይ ጦር አዝ ቢኖረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ቢያንስ ለአንድ ዓመት ጣሊያኖች አዲስ አበባ እንዳይገቡ ለማድረግ ይችል ነበር። ጣሊያኖች ራሳቸው ተቃውሞ እንዳያጋጥማቸው ስጋት ነበራቸው፤ በተለይ በጣርማ በር ለመከላከያ አመቺ በመሆኑ አነስተኛ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት ሊገታቸው እንደሚችል ፈርተው ነበር።[1]

## ታላቅዋ ብሪታንያና ኢትዮጵያ

በወቅቱ ታላቅዋ ብሪታንያ ልዕለ ኃያል መንግሥት ነበርች። ብሪታኒያ ጣሊያ ለዓለም ባሕርና ውቅያኖሶች ለሚደረግ ጉዞ ለመቆጣጠር ኃይል ሳይኖራት ዐፀሙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮችዋ ከሀገርዋ 4.000 ኪሎ ሜትር ርቀት ማዝመቷ ዘማች ሠራዊትዋ መንገዱም ቢዘጋበት በእልቂት ከመጋለጥ ሌላ አማራጭ የለውም የሚል አስተያየት ትሰነዝር ነበር።[2] ኢጣሊያ ለጦርነቱ መነሻ እንዲሆናት የወልወል ግጭት ብላ ፈጠረች። ለግጭቱ በመንግሥታቱ ማህበር የተሰየመው አስታራቂ ኮሚቴ ለኢትዮጵያ ጥብቅና የቆመው ፈረንሳዩ ሕግ አዋቂ ወልወል በማን ግዛት እንደምትገኝ በመጀመሪያ ይወሰን ብሎ ባቀረበበት ጊዜ ጣሊያኖች ኮሚቴው ተግባሩን እንዲያከናውን የተፈጠረው መሰናክል ነው ብለው ውድቅ አደረጉት። ወልወል የሚገኘው በ100 ኪሎ ሜትር የሚቆጠር በኢትዮጵያ ውስጥ ነው።

1. Mario Appelius : Il Crollo dell'Impero dei Negus p.193

2. Luca Dei Sabelli Storia Di Abissinia v 1v p.245

ጣሊያኖች የኢትዮጵያን ስም ለማጥፋት ቁም ነገር የሌለው በስድብ ብቻ የተሞላ አንድ ሪፖርት ለዓለም መንግሥታት ማህበር አቀረቡ። ስለጣሊያኑ ሪፖርት ክርክር የአምስት ሀገሮች አጥኚ ኮሚቴ ተቋቁሞ ክርክር በሚደርግበት ጊዜ ያልተጠበቀ የድራማ መልክ የሚያሳይ ነገር ተፈጠረ። ታላቅዋ ብሪታንያ ከዚህ በፊት በመንግሥታቱ ማህበር ዝቅተኛ የመከረል አቋም የነበራት ከሥር መሠረቱ በመቀየር በመንግሥታቱ ማህበር ላይ ከፍተኛ ተካፋይነቷን ለማሳየት የመንግሥታቱ ማህበር ደምቦች በደምብ መከበር እንዳለባቸው ገልፃ ደምቦች በሚጣሱበት ጊዜ የትም ቦታ ድጋፏን ለመስጠት ዝግጁ መሆንዋን ለመጀመሪያ ጊዜ ከማድረጓም በላይ ሆም ፍሊት Home Fleet የተባለው የብሪታንያ ባሕር ኃይል በሚዲትራንያን ባሕር አሰማራች። ይኸውም ሆኖ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሚኒስትር ‹ማፌይMafey› ለሀገሩ መንግሥት ባቀረበው ሪፖርት ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የም ታሳየው የበላይነት የግዛት ማስፋፋት በአካባቢው ለሚገኙ ለእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ጥቅም የማይጐዳ መሆኑን ገልጦ በኢጣሊያ የግዛት ማስፋፋት ብሪታንያ ጥቅም ልታገኝ እንደምትችል የሚል እምነት ሰንዝሮ ነበር። ከዚህ በኋላ ግን የዚህ ዓይነት ፖሊሲ ደጋፊ የነበሩ ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተቀይረው ፀረ–ኢጣሊያ የማስፋፋት ዓላማ ያላቸው ‹ቦል ዊን እና ሳሙኤል ሆር› ተተኩ። ብሪታንያ አቋሟን ለመንግሥታቱ ማህበር በመግለጽ እንደዚሁም እንደ ማስፈራሪያ የባሕር ኃይሏ ‹ሆም ፍሊት› በሚዲትራንያን ባሕር በማሰማራት ብቻ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ ያለው ግጭት እልባት ያገኛል ብላ ግምት ነበራት። ከኢጣሊያ እርቆ መገመት የሚችል መንግሥት ቢኖር የእንግሊዝ ማስጠንቀቂያ በቂ ነበር።

ሆኖም ይህ ሁሉ በአውሮፓ የጦርነት አደጋ ማንዣበብ ስለሚያስከትል በዕብሪት ትክሻቸው ያበጠ ጣሊያኖች ሊገታቸው አልቻለም። በዓለም መንግሥታት ማህበር ያለው ጉዳይ የእንግሊዝ መንግሥት ኃላፊ መልዕክተኛ የነበረው ኤደን ‘Eden› ጁን 24፣ 25 በሮም ጉብኝት አድርጐ ታላቅዋ ብሪታንያ ኢትዮጵያ በዘይላ በኩል የባሕር በር እንድታገኝ ስታደርግ ኢትዮጵያም ለኢጣሊያ ኦጋዴን እንድትሰጥ ነበር። ይህ የባሕር በር ለኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ለማግኘት ብዙ ጥቅም ይሰጣታል በማለት ኢጣሊያ የምድር በረሃዎች ሰብሳቢ አይደለችም በማለት ጣሊያኖች ሳይቀበሉት ቀሩ። የፈረንሳይ መንግሥትም ኢትዮጵያ በዘይላ በኩል የባሕር መውጫ ካገኘች በጅቡቲ በኩል ያለው ንግድ ይወድቃል በማለት ጥርጣሬ አድርባት ነበር። በእንግሊዝ ፓርላማ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባደረገው ንግግር ኢጣሊያ የመስፋፋት መብት እንዳላት ብንቀበልም በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ብዙ ሐሰ ሊደረግ እንደሚቻል ብንቀበልም፣ ይህ ሁሉ ግን በእርቅ የሚፈቱ ናቸው እንጂ ወደ ጦርነቱ አዘቅት የሚወስዱ አይደሉም ብሎ ነበር። የእንግሊዝ አቋም በኢትዮጵያ ጉዳይ በዚሁ አላበቃም። ስለ ኢትዮጵያ በ 1906



እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ኢጣሊያ ባደረጉት ስምምነት መሠረት ማምገግ ለማድረግ ሦስቱ ሀገሮች ኦገስት 16 1935 በፓሪስ ተሰበሰቡ። ፈረንሳይ ለጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት መብት እንዲታወቅላቸው ስምምነት እንዲደረግ የሚል ሐሳብ ብታቀርብም እንግሊዞቹው መልዕክተኛ ኤደን ግን ከፍተኛ ተቃውሞ አሰማ። የኢጣሊያ መልዕክተኛም ባሮኔ አሎይዚ የቀረበለት ሐሳብ ውድቅ አደረገው።

ስለዚህ ስብሰባው ያለምንም ውጤት ተስትና በማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ለክርክር እንዲቀርብ ተደረገ። የመንግሥታቱ ማህበር ጠቅላላ ስብሰባ በእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ንግግር ተጀመረ። ሚኒስትሩ ያለምንም ማወላወል የእንግሊዝ መንግሥት የማህበሩ ውሉችና ደንቦች እንዲከበሩ ድጋፉ ይሰጣል ሆኖም የማህበሩ ውሉች በኢትዮጵያ ጉዳይም በሥራ ላይ መዋል አለባቸው በማለቱ በተለይ ፈረንሳይን የሚነካ ነበር። የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ላቫል‹Laval›ቀደም ብሎ ወደ ሮም ተጉዞ በኢትዮጵያ በጣሊያኖች ጣልቃ ገብነት የግዛት ማስፋፋት ሙሉ መብት ድጋፍ ሰጥቶ ነበር። በሌላ በኩልም 1ኛ የዓለም ጦርነት ፈረንሳይ ከጀርመን የወሰደቻቸው መሬቶች በሚመለከት የእንግሊዝ ድጋፍ ያስፈልጋታል።

በዚህ መሠረት ላቫል ‹Laval› ከእንግሊዝ ወዳጅነት ወይንም ከጣሊያን ወዳጅነት መምረጥ ነበረበት። በሀገሩ ውስጥም የተቃዋሚዎች ከፍተኛ ግፊት ስለነበረበት ላቫል የመንግሥታት ማህበር ውሉች በኢትዮጵያ ጉዳይም በማህበሩ መድረክ እንዲከበሩ መቀበል ግድ ሆነበት። በዚህ በፊት ተቋቁሞ የነበረው የ5 ሀገሮች ኮሚቴ ተብሎ የሚጠራው በጠቅላላው ጉባኤ የቀረበው ሪፖርት ኢትዮጵያ አስተዳደርዋ ለማሻሻል ሁለገብ ድጋፍ ከውጪ መንግሥታት እንደሚያስፈልጋት አምኖ ይህ ድጋፍ ግን ከአንድ መንግሥት ብቻ ‹በኢጣሊያ› መከናወን የለበትም፣ በብዙ መንግሥታት በጋራ መሰጠት አለበት በማለቱ የኢጣሊያ ቁጣ አስከተለ። የኢጣሊያ ቁጣ በይበልጥ የገፈለው የኢትዮጵያ መልእክተኛ ኦክቶበር 5 1935 ኢጣሊያ ወራሪ ተብላ እንድትወገዝ ባቀረበው ሃሳብ መሠረት ጠቅላላ ጉባኤ ሲቀበለው ነው። ጣሊያኖች በእብሪት ተነሳስተው አውሮፓ አንድ ጥንታዊት ፣ የሰለጠነች አውሮፓዊት ሀገር ኢጣሊያን አግልላ ለአንድ ያልሠለጠነች ጥቁር አፍሪካዊት ሀገር የባሪያ አሳዳሪ ሀገር ድጋፏን በመስጠት ለአውሮፓ የውድቀት ምልክት ነው ብለው ቁጣቸውን በመግለጽ ወረራቸውን ገፉበት።

ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከመግባታቸው በፊት ሚይ 2 ማታ ንጉሡ አዲስ አበባን ለቆ በባቡር ወደ ጅቡቲ ተጉዞ፤ በ23.30 ‹ከማታው 5 ሰዓት ተኩል› ድሬዳዋ ገባ። ሚይ 3 ቀን ከቀኑ 14 ሰዓት ‹ከቀኑ 8 ሰዓት› ጅቡቲ ገባ። በማግሥቱ ሚይ 4 17.30 ‹ከቀኑ 11.30› ኢንተርፕራይዝ በተባለው በአንድ የእንግሊዝ የጦር መርከብ ተሳፍሮ ወደ እየሩሳሌም አምርቷል። በጅቡቲ የነበረው ሳልቫቶሬ አፓንተ ‘Salvatore Apante›

የተባለው የአንድ የኢጣሊያ ጋዜጣ ጠኪል የኃይለ ሥላሴ ጉዞ ዝርዝር አውጥቷል[1]፣ ኃይለ ሥላሴ ጅቡቲ ሲደርስ ንብረቱ የኢጣሊያ የሆነው ምግብ ቤት ተሰብስበው ጣሊያኖች Facetta Nera ፋቼታ ኔራ የሚል ዘፈን በሸክላ ተቀርጾ ያሰሙ ነበር። ተጠንቀቁ እኛ ፋሺስቶች ነን እያሉ ጨኸቶቻቸው ያሰሙ ነበር። በእንግሊዝ ጦር መርከብ ከኃይለ ሥላሴ ጋር የተጓዙ 116 ሰዎች ቤተሰብና ባለሥልጣኖች ነበሩ። በፓለስታይን የክብር አቀባበል ተደርጐላቸዋል። ትንሽ ቀን ከሰነበቱ በኋላ ጁን 3 ቀን ኃይለ ሥላ ሴ ታላቅ አቀባበል ተደርጐለት እንግሊዝ ሀገር ገባ። ለኃይለ ሥላሴ የተሰጠው ታላቅ ክብር በግሉ የተሰጠ አልነበረም ፡ ለኢትዮጵያ ነፃነት ክብር የተሰጠ ነበር። ከ5 ዓመት በኋላ ዓለምን በእጇ የጨበጠች መስሏት የነበረ አብሪተኛዋ ፋሺስት ኢጣሊያ 2ኛ የዓለም ጦርነት በእንግሊዝ የጋራ ብልጽግና ሀገሮች ወታደሮች ተሸንፋ ተዋርዳ ከኢትዮጵያ ለቃ ስትወጣ ኃይለ ሥላሴም ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሥልጣን ሲይዝ ከእንግሊዞች የተደረገለት እርዳታ ተገቢ ውለታ የከፈለ አይመስልም፡ ውለታቢስነቱ ኃይለ ሥላሴን ብቻ የሚያስወቅስ አይደለም ኢትዮጵያውያንን በሙሉ የሚያስወቅስ ነው። ከነፃነት መልስ በኋላ ኢትዮጵያ በእንግሊዞች አማካሪዎች እርዳታ በዲሞክራሲ አስተዳደር ብትመሠረት ለእን ግሊዞች ውለታ መመለስ ብቻ ሳይሆን የታየው በደርግ ሥር ነቀል ለውጥ አይከሰትም ነበር። የራሱ የኃይለ ሥላሴ የዘውድ አገዛዝም አይደፈርም ነበር። በ1928 የኢጣሊያ ወረራ ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያ የመጣባት ጠላት ከአቅሟ በላይ ተዘጋጅቶ መሆኑ ባይካድም ኢትዮጵያም ለመከላከል ያደረገችው ጥረት ከአቅሟ በታች ነበር። የኤውሮጳ የውትድርና ጠበብት እንደገመቷት ሆና ያልተገኘችበት ምክንያት በሕዝቧና በወታደሮቿ ድክመት ሳይሆን በነበሩ መሪዎች ችሎታ ማነስ የመሪነት ኃላፊነታቸው በሚገባ ሊወጡ ባለመቻላቸው ነው። ዓላማ ብለው ይዘውት የነበረ በትግራይ ጦርነት በመግጠም ዕድላቸውን አይተው ሲሸነፉ መበታተን ብቻ ነበር የተወሰነ።

# የኢትዮጵያ ጦር መሪ አልነበረውም

የኢትዮጵያ አሰላለፍ ራሱ ለጠላት የሚመች ነበር። እርስ በርስ በመሬት ኩታ ገጠም እንዲሁም በመገናኛ የማይገናኝ ጠቅላይ አዝ የሌለው በመላው ሀገሪቱ በሰሜን ጦር ግንባርም ሆነ በደቡብ ሠራዊቱ ተበታትኖ ሰፍሯል ፤ ሽንፈትና ማፈግፈግ ሲያጋጥምም ተጠባባቂ ጦር አልተዘጋጀም። በመሣሪያ ማነስ የወታደር ብዛት ኃይል ማነስ የባሰ ሁኔታ ነበር። ይህ ሁኔታ ነበር ወደ ሽንፈት የዳረጋቸው፤ ራስ እምሩ ረድዮ መገናኛ አልነበረውም።

1. Fici v3 P.78



የኢትዮጵያ መሪዎች ይለዋወጧቸው የነበሩት ቴሌግራሞች ሁሉ በጣሊያኖች እየተጠለፉ እንደ ማስረጃ ያገለግሉዋቸው ነበር። እነዚህ ቴሌግራሞች በወቅቱ ኢትዮጵያ ጠቅላይ አዝ አልባ ብቻ ሳትሆን መንግሥት አልባ እንደነበረች ያሳያሉ። ፌብሩዋሪ 12 1936 አፄ ኃይለ ሥላሴ ከደሴ ለራስ ካሣ በላከው ቴሌግራም «ጣሊያኖች በ12 ሰዓት ጧት በራስ ሙሉጌታ ላይ ጥቃት ሰንዝረዋል፤ ጣሊያኖች ከምሽጋቸው ወጥተው ስለሚገኙ በስተ ጀርባቸው ምርጥ ጦር ልከህ ጥቃት እንዲፈጸምባቸው ካደረግህ ወደ ራስ ሙሉጌታ የዘመተ ጦራቸው ሊቀንስ ይችላል ወይም መቀሌን መያዝ ያለ ተከላካይ ወታደር ከተገኘች የሚል ነበር።ይህ ቴሌግራም ለራስ ካሣ የደረሰው ፌብሯሪ 15 ከምሽቱ 2:30 ሲሆን በዚሁ ጊዜ ግን ራስ ሙሉጌታ ተሸንፎ የእንደርታ ጦርነት አብቅቶ ነበር።

ፌብሯሪ 19 አፄ ኃይለ ሥላሴ ከደሴ የራስ ሙሉጌታን መሸነፍ ዘግይቶ እንደሰማ ራስ ካሣና ራስ እምሩ ወደ አምባላጂ እንዲሰበሰቡ ትእዛዝ ይሰጣቸዋል። ይህ በተግባር ሊውል የማይችል ትእዛዝ ነው ምክንያቱም ከሽሬና ከተንቤን እስከ አምባ አላጂ ያለው ርቀት ብዙ ከመሆኑም በላይ ጣሊያኖች ከተንቤንና አምባ አላጂ መሀል ያለው መሬት ሁሉ በቁጥጥራቸው አውለውት ስለነበረ ትእዛዙ ተጨባጭ ሁኔታ ያልተገነዘበ ነበር።

ፌብሯሪ 20 ራስ ካሣ ለንጉሡ ቴሌግራም ሲልክ ጣሊዮኖች እርስ በርሳችን እንዳንተጋገዝ አድርገውናል ካለ በኋላ በአጠቃላይ በውኅብር እንደሚገኙ የሚያሳይ የሚተከተው ዕቅድ ለንጉሡ ሃሳብ ያቀርባል።

1ኛ አሬቱ ያለውን ጠላት ማጥቃት ምናልባት ከራስ እምሩ ጋር ለመቀላቀል፣

2ኛ በጀርባዬ ያለውን ጠላት ማጥቃት ከራስ ሙሉጌታ ጋር ለመቀላቀል ፡ መሸነፉን ስለማያውቅ፤

3ኛ የከበብነውን ጠላት እሱም የከበበን እየተዋጋም መጠባበቅ።

አፄ ኃይለ ሥላሴም የጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ ስላልተገነዘበ አዲስ ትእዛዝ ይሰጣል። ራስ እምሩ ወደ መከላከል ያዘንብል፤ ጥቃት ከደረሰበት ይከላከል፡ ሌላው ቢቀር ጊዜ ለመውሰድ። ራስ ካሣ በቂ ኃይል ካለው ይዋጋ፡ ጣሊያኖችን ከያሉበት ከራስ ሙሉጌታ ጋር ተቀላቅሉ ይዋጋ።

በተጨማሪ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፌብሯሪ 20 በላከው ቴሌግራም ከደሴ ተነስቶ ወደ ሰሜን ማይጨው ጉዞውን እንደቀጠለ አስታውቋቸው ነበር።

የራስ ሙሉጌታና የራስ ካሣ ሠራዊት ሳይበታተንና ሳይሸነፍ ከንጉሡ ሠራዊት ጋር ለመቀላቀል ቢችል ኖሮ ጣሊያኖች ከባድ ችግር ይገጥመናል ብለው ነበር። ችሎታ ያለው በጠቅላይ ጦር አዛዥ የሚመሩ ጣሊያኖች ግን የኢትዮጵያ ወታደሮች ሳይሰባሰቡ በተለያዩ ቦታዎች ጦርነት ገጥመው አስቀድመው ባወጡት እቅድ መሠረት አሸንፏቸዋል።

ሌላ ቴሌግራም ራስ ካሣ ለንጉሡ በላከው በጣሊያኖች ተከቦ እንደሚገኝና ያለው ዕድል ወደ ዐድዋ ጥሶ መውጣት ነው ብለዋል። ንጉሡም ፌብሯሪ 25 በሰጡት መልስ ወደ ዐድዋ ጥሶ መሄድ ትክክል መስሎ እንደማይታየው ጠቅሶ በቀድሞ ትእዛዝ መሠረት ወደ አምባ አላጂ እንዲያመራ በድጋሚ ትእዛዝ ሲሰጠው ይኸውም ያለበት 1ኛ አማካሪዎች ስለነበሩት 2ኛ በዚሁ አካባቢ በጠሊያኖች ላይ ጉዳት ለማድረስ ስለማይቻል ነው ብሏል። ይኸ ሁለተኛ ነጥብ ደፈጣ ውጊያ የሚመስል ስለሆነ ጣሊያኖች አስገቷቸው ነበር። ጣሊያኖች ይፈሩት የነበረው ኢትዮጵያውያን በደፈጣ ውጊያ እንዳይጠቀሙ ነበር። የኢትዮጵያ መሪዎች ግን ጣሊያኖች በሚፈሩት ውጊያ እንዳይጠቀሙ ለጣሊያኖች የሚመች የፊት ለፊት ጦርነት ነው የመረጡት። ይኸም ሆኖ ደጀን ጦር ተጠባባቂ ጦር አልነበረም። አስተሳሰባቸው ልክ እንደ ዐድዋ ጦርነት በአፄ ምኒልክ ጊዜ ለመሆን አዝማሚያ ሲኖረው ልዩነቱ ግን በዐድዋ ጊዜ ጦሩ የሚታዘዘው በአንድ ሰው ነበር የሚጓዘውም በአንድ መስመር ነበር።

በ1928 ጦርነት ሠራዊቱ የሚመራው ከበላይ አስተባባሪ ሳይኖረው በብዙ ጦር አበጋዞች ከደቡብ ወደ ትግራይ በብዙ አቅጣጫዎች ይጓዝ ነበር። ይህ የታክቲክ ጉድለት ለመገመት ውትድርና አዋቂ መሆን አያስፈልግም። ፌብሯሪ 27 እና 28 የተንቤን ጦርነት በተጧጧፈበት፤ አምባአላጂም በጣሊያኖች እጅ በገባበት ወቅተ ራስ ካሣ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ በላከው ቴሌግራም አምባአላጂ የሚገኘው የኛ ጦር ጣሊያኖች ከመቀሌ በጦር መኪናዎች ወደ እኛ መጥተው እንዳይወጉት በመድፍ ተኩስ ከፍተው ለማጥቃት እንዳይሞክር በማለት ጥያቄ አቅርቦ ነበር። ቀጥሎም ራስ ካሣ በሉተጀርባ የሚመጣ ሠራዊት ጦር እንደለካና ፊት ለፊት በሚመጣው የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ላይ ለመግጠም እንደተጓዘ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ካስታወቀ በኋላ አፄ ኃይለ ሥላሴም ስሉዋ ወይንም አምባ አላጂ ላይ በጀርባው የሚገኘው ራያ አስተማማኝ ስለማይሆን ተንቤን ላይ እንዲሰለፍ ምክንያቱም በጀርባው የሚገኘው ዋግ አስተማማኝ ነው ብሉ ምክሩን ይለግሳል።

ራስ እምሩ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ በላከው ቴሌግራም አብዛኛው የጉጃም ወታደሮች ከድቷል ፤ በትውልድ ሀገራቸው ካልሆነ ለመዋጋት አይፈልጉም ሕዝቡ ሁሉ ከመጠን በላይ ለሀገረ ገዥው ለደጃዝማች አያሌው አክብሮት የለውም ፤ ይተኩስበታል ብሏል። ራስ እምሩ ለወታደሮቹ ያደረገው ንግግር ግን «እናንተ በምዕራብ ጦር ግንባር የምትገኙ ወታደሮች ካሸነፋችሁ በአሥመራ ፤በምጽዋ፤ በሮማ ባንዲራዎች በጥቁር ቀለም ይውሰበለ ባሉ በእንዳ ጽዮን በአክሱም ቅድስት ሥላሴ የድል ጸሎት እናከብራለን» ብሏል። በማይጨው ማርች 26 የጦር ሜዳ ስብሰባ ተደርጐ አንዳንድ ተካፋዮች የኢትዮጵያ ጦር ወደኋላ ማፈግፈግ እዳለበት ሃሳብ ቢያቀርቡም ግጠላወል ዋና ጠባዩ የሆነ ንጉሡ ግን ጥቂት ከተግደረደረ በኋላ የማጥቃት ደጋፊ የሆኑ አሽሙርተኞች ስለበዙበት ለማጥቃት ወሰነ። በኃይለ



ሥላሴ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ከማይጨው ወደ ደሴ ወይንም ከደሴ ደቡብ ሊያፈገፍግ ብዙ ተጨማሪ ጦር ያገኝ ነበር። ጣሊያኖችም ከባድ ጦርነት ይገጥመናል ብለው ፍርሐት አድሮባቸው ነበር። ይህ ሁኔታ እንዳይደርስ ንጉሡ እንደ ቀድሞ ነገሥታት እንዳይዋጋ ይሸሻል የሚሉ በጣሊያንኛ፤ በትግርኛ፤ በአማርኛ የተፃፉ በራሪ ወረቀቶች ጣሊያኖች ይበትኑ ነበር።

የተሸነፈችው ኢትዮጵያ መሪ አልባ ሆና በደፈጣ ውጊያ ኢጣልያን የሚቋቋሙ ወገኖች አልተሰባሰቡም ነበር

ማርሻል ባዶሊዮ ከማይጨው ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ስለተበታተነ ደሴን ለመያዝ የሚቻለው ሳይሰበሰብ በፍጥነት ገስግሰው ደሴን መያዝ ሲቻል ብቻ ነው ብሉ ወታደሮቹ በፍጥነት ተጉዘው ደሴን እንዲይዙ አደረጋቸው። ከደሴ መያዝ በኋላ የውትድርና ጠበብት ኢትዮጵያ ሊኖራት ስለሚችል እቅድ የተለያዩ አስተያየቶች ይሰነዝሩ ነበር። አንዳንዶቹ ንጉሡ ጠቅላላ ከተት አውጆ ከዋና ከተማዋን ለመከላከል ሐሳብ እንዳለው ብለው ነበር። ሌሎች ደግሞ ኢትዮጵያውያን ከደሴ በስተደቡብ ጣሊያኖችን መመከት የተዘጋጁ ይሆናል የሚል ሐሳብ ነበራቸው። ጣሊያኖች ግን የኢትዮጵያ ጦር አንድ ጊዜ ከተሸነፈ እንደገና የማንሰራራት ጠባይ የለውም፤ ተጠባባቂ ጦርም በደቡብ እንደሌለ ብለው ደምድመዋል። የንጉሡ ከንቱ ተስፋ በመንግሥታቱ ማህበር ብቻ ያተኮረ ነበር። ንጉሡ ነገሥቱ ከማይጨው አዲስ አበባ እንደገባ ከእንግሊዝ አምባሳደር ተገናኝቶ ተነጋግረዋል፤ እስከ መጨረሻም እንደሚከላከል ይገልጽ እንደነበር ጋዜጠኞች ወደ ለንደን ያስተላለፏቸው ከነበሩ ቴሌግራሞች ለመረዳት ይቻላል፤ ሐሳቡን የቀየረው የመጨረሻ ደቂቃ ነበር።

ኃይለ ሥላሴ ጅቡቲ ሲደርስ ብቻ የጠበቀው ተዘታዛ አቀባበል ነበር። ከጦር ሜዳ ሸሽቶ መምጣቱ ያልተደሰቱበት ብዙ መሆናቸውን ለመገመት ወታደሮቹ ለመዋጋት ዝግጁ ሆነው እያሉ ስለነበረ ነው።

ከንጉሡ ጋር የመጡ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች እንደ ሚያወሩት ንጉሡ ከእንግሊዙ አምባሳደር ባርቶን ጋር ከተነጋገረ በኋላ የዘውድ አማካሪዎች ስብሰባ አድርገው እስከ መጨረሻ ለመዋጋት ወስነው ነበር። በኋላ ግን ከሌሎች ሰዎችም ተገናኝቶ ከተነጋገረ በኋላ፤ ከነዚህ ውስጥም የፈረንሳዩ አምባሳደር ቦዳር ጋር ከተነጋገረ በኋላ ንጉሡ ሌላ ውሳኔ ወሰዷል። ንጉሡ ሹማምንቶችን ሰብስቦ በሰሜን የሚደረግ ነገር የለም ወደ ደቡብ መሄድ ያስፈልጋል ብሉ ነገሯቸዋል።

ንጉሡ ቤተሰቡን ጅቡቲ አድርሶ ወደ ጦር ሜዳ እመለሳለሁ ብሉ ይናገር ነበር። ለፈረንሳይ ባለሥልጣኖችም ልጆቹ ለኢጣልያ ቁንስላ እንዳያስረክቧቸው ይማጸን ነበር። ፊታውራሪ ብሩ በሌሎች የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ስም ንጉሡ ወደ ኢትዮጵያ

እንዲመለስ ምክር ለመስጠት ሞክሮ ነበር፤ ኃይለ ሥላሴ ግን እየሳቀ ስለሌላ ጉዳይ እንነጋገር የሚል ብቻ መልስ ሰጧል። ኃይለ ሥላሴ መመሪያ እንዲሰጣቸው ይጠባበቁ የነበሩ ባለሥልጣኖች ኢየሩሳሌም ድረስ ከመጣችሁ እንገናኛለን የሚል መልስ ይሰጣቸው ነበር። ብዙዎች ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በቂ ገንዘብ አልነበራቸውም። ልጆቹና ጥቂት ቅርብ ዘመዶች ብቻ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዙ። ራስ ደስታ ዘይላ ገብቷል ዛሬ ጅቡቲ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቅ ነበር ፤ ነገር ግን ሳይመጣ ቀረ፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ሹማምንቶች ግን ከሀገር አልወጡም። ከኢትዮጵያ መውጣት ያልፈለጉትና ከኢጣሊያ ጋር ውጊያ መቀጠል ከፈለጉ ራስ እምሩ ይገኙበታል።

በሽሬ ጦርነት ከተሸነፈ በኋላ የቀሩት ታማኝ ወታደሮችን ይዞ ራስ እምሩ ወደ ጐሬና ምዕራብ ወለጋ መጥቶ ሰፍሮ ነበር። በጐሬ የነበረው የእንግሊዝ ቆንስል ወደ ኡጋንዳ ጥገኝነት ቢፈቅድለትም ራስ እምሩ ግን አልተቀበለውም ፤ ወደ ጅማና ወደ ሐይቆች በመዝለቅ ከራስ ደስታ ጋር በቅንጅት መዋጋት አቅዶ ነበር። ግራዚያኒ ግን ወደ ሱዳን እንዳይገባ፣ ወደ ጂማ እንዳያመራ ፤ ወደ ለቀምት እንዳይመጣ፤ በራስ እምሩ ላይ ከበባ አደረገበት። ራስ እምሩ ወደ ጂማ እያመራ ነበር። ኖቬምበር 12 1936 በኰ/ማልታ የሚመራው የኢጣሊያ ጦር በጉጀብ ጥቂት የራስ እምሩ ወታደሮችን አግኝቶ ደምስሷቸዋል። ሌላ የኢጣሊያ ጦር በኰሎኔል ፕሪንቺቫለ የሚመራው ዋናው የራስ እምሩ ጦር ከጅማ ደቡብ ምዕራብ አግኝቶ ሙሉ ቀን የቆየ ከባድ ጦርነት ገጥሟል።

ራስ እምሩ ጦሩ ጉዳት ስለደረሰበት ከቦንጋ ወደ ሰሜን ምሥራቅ አፈገፈገ። በዚህ እንዳለ ራስ እምሩ በሦስት አቅጣጫ በሦስት ኰሎኔሎች የሚመሩ የኢጣሊያ ወታደሮች የተከበበ መሆኑን ሲያውቅ በጉጀብ ወንዝ የተሰራው ድልድይ ለማቋረጥ ሲሞክር ጣሊያኖች ውጊያ ስለከፈቱበት እጁን ለመስጠት ግድ ሆነበት። ተይዞ ወደ ቦንጋ፤ ወደአዲስ አበባ፤ ከዚያም ወደ ኢጣሊያ ተወስዶ በእስር ቆይቷል። ችሎታ ያለው ሐቀኛ ጠላታችን ተብሎ በ2ኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ግንባሥት ከእስር ተለቆ በክብር ወደ ሀገሩ ተመልሷል[1]።

በሰላሌ አካባቢ ኦክቶበር 20 1936 ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም ከአንድ የኢጣሊያ ብርጌድ ጋር ጦርነት ገጥሞ ተገድሏል፤ ከሱ ጋርም 1000 አርበኞች ሞተዋል[2]። ደጃዝማች ወንደሰን ካሣ ተከዜ አካባቢ አንድ የኢጣሊያ ባንዳ ዲሴምበር 10 1936 ዓ.ም ከማረከው በኋላ ጣሊያኖች ወዲያውኑ ገደሉት።

1. F.I.o.I v3 p.440

2. F.I.o.I v3 p. 482



ፍቼ አካባቢ ሁለቱ ሌሎች የራስ ካሣ ልጆች አበራና አስፋወሰን የራስ ኃይሉ ባንዳ ተካፋይ በሆኑበት በአምስት አቅጣጫዎች ከከበቡዋቸው በኋላ ዲሴምበር 21 1936 እጃቸውን ሰጥተው ምህረት እንዲደረግላቸው ቢጠይቁም እነስተኛ ተኩስ ተደርጐ ከተማረኩ በኋላ በጥይት ተደብድበው ተገድለው በፍቼ አደባባይ አስከሬናቸውን ሰቅሏቸዋል። በማግሥቱ በግድያው የተካፈሉ 14 ሺህ የኢጣ ሊያ ወታደሮች በፍቼ ከተማ ሰልፍ አሳይተዋል[1]።

የካቲት 12፡ፌብሯሪ 1937 በየዓመቱ የምናከብረው በአዲስ አበባ የተፈፀመው የንጹሃን ደም ጥፍጨፋ ጣሊያኖች እንደሚከተለው ያቀርቡታል። ሽፍቶች በገጠር ሽንፈት ስለደረሰባቸው በአዲስ አበባ ከተማ ተሰግስገው የነበሩ የካቲት 12ቀን ከቀኑ 6 ሰዓት የንጉሡ እንደራሴ ማርሻል ግራዚያኒ ከከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን ለድሆችና ለቤተ ክህነት ሰዎች ስጦታ በሚሰጥበት ጊዜ ወንበዴዎች ፈንጂዎችን በመወርወር የመግደል ሙከራ ፈጽመው ራሱ ሀገረ ገዥውና የንጉሡ እንደራሴ በብዙ ፈንጂዎች ፍንጣሪዎች ቆስለው ስለነበረ፣ ይህ የክህደት ሥራ የከተማዋ የፀጥታ ሁኔታ ሊያናጋ አልቻለም ሁሉም አደገኛ ሊሆኑ የሚችሉ ወንበዴዎች ከመቅጽበት በማያዳግም ሁኔታ ተደምስሷል። ጣሊያኖች የጠረጠሩዋቸው የሚያሰጨንቋቸው የነበሩ የራስ ካሣ ልጆች እና የደጃዝማች ፍቅረ ሥላሴ እጅ እንዳለበት ነበር።

የኢትዮጵያ ሹማምንቶች ለጣሊያኖች እጃቸውን ለመስጠት በዲሴምበር 1936 በአዲስ አበባና በሌሎችም ክፍላተ ሀገሮች ቀጥለው ነበር። ጀንዋሪ 1937 የእጅ መስጠት መሀላ ሥነ ሥርዓት በአዲስ አበባ ተፈጽሞ ነበር።

ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ ማሪዮ አፐሊዩስ ( Mario Appelius) እንደሚከተለው ያቀርባል። የክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ያሉበት 200 የሚደርሱ የቀድሞ ሹማምንቶች በአዲስ አበባ ተሰብስበው ነበር። በስብሰባው ከነበሩ የጐጃሙ ራስ ኃይሉ፣ አቡነ ቄርሎስ፤ ራስ ሃብተ ሚካኤል፤ ደጃዝማች አያሌው ብሩ 11 ፊታውራሪ 20 ቀኛዝማች፤ ብዙ የቤተ ክህነት አለቆችና ሙስሊሞች ይገኙበት ነበር። ከንጉሡ እንደራሴ ጐን ሁሉም የኢጣሊያ ባለሥልጣናት ተገኝተዋል። የዘብ ጠባቂዎች ጉራዴያቸውን እንደመዘዙ ሱማሌዎች ቆመው ነበር። አንድ በአንድ ሁሉም እጁን ለመስጠት የቀረበ የቀድሞ ባለሥልጣን ለማሃላ የተዘጋጀ ቃል እየደገመ ከኢጣሊያ ንጉሥ ሌላ ንጉሥ እንደማያውቅ ይናገር ነበር። የጐሬ ገዥ የነበረ ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ በንጉሡ ነገሥት ምኒልክ፤ በልጅ እያሱ፤ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፤ በንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ያገለገለ ባደረገው ንግግር እስካሁን እጄን ያልሰጠሁ ግዛቴ በኢጣሊያ ወታደሮች ስላልተያዘ ነበር ፤ ከእንግዲ ሕይወቴ እስካለ ድረስ የኢጣሊያ መንግሥት ታማኝ በመሆን አገለግላለሁ።

1.F.I.o.I v3 p.453

እግዚአብሔር በርግ ሥልጣኔ ኢትዮጵያ እንድትስተዳደር ያድርግልን፣ ረጅም ዕድሜ ለኢጣሊያ ንጉሥ፣ ለዱቼ፣ ለንጉሡ እንደራሴ ግራዚያኒ ብሏል። ሌሎችም ንግግር አድርገዋል። በመጨረሻ ማርሻል ግራዚያኒ በአደረገው ንግግር ዛሬ እጃቸውን የሰጡ ማኖቹ ደስታ ይሰማኛል፤ እስከዛሬ ያጠፋችሁ ሁሉ ይቅርታ ተደርጐላችኋል። ብዙ የሃሰት ወሬ ይሰማሉ፤ ለምሳሌ ደጃዝማች ሃብተ ማርያም በመሃከላችሁ ያልተገኙበት ምክንያት ከእኛ ጐን ሆኖ በመጀመሪያ በለቀምት ሽፍቶቹን ለማሳደድ ከተካፈለ በኋላ በራሱ ባንዳዎች በተመላላይ ሥራ ወደ ጅማ ሄዶ ስለነበረ ጤንነቱ ስለተጉሳቆለ ዛሬ በዚሁ ስብሰባ ባይገኝም ከ15–20 ቀን በኋላ በመሃከላችሁ ይገኛል። ሁላችሁም ማወቅ የሚገባችሁ የኢጣሊያ መንግሥት ሃሰት እንደማይናገር ነው። ታላቅ መንግሥት ሃሰት አይናገርም። ስለ ራስ ኃይሉም ሃሰት ይወራል።ስለ ራስ ካሣ እሟሟትም የሃሰት ወሬ ይወራሉ[1]።

ራሥ ኃይሉ ከምዕራብ ከኩሉኔል ቤሊ ጋር ወደ ሬቹ በራስ ካሣ ልጆች ላይ እንዲዘምት የላኩት እኔ ነኝ። ራስ ኃይሉ በመጀመሪያ የራስ ካሣ ልጆችን ደርሶባቸው ተኩስ አልከፈተባቸውም፤ ጠርቶ ልትሞቱ የምትፈልጉ ከሆነ፤ ወንዶች ከሆናችሁ ግጠሙን፤ እጃችሁን ለመስጠት የምትፈልጉ ከሆነ ልንቀበላችሁ ዝግጁ ነን አላቸው። የራስ ካሣ ልጆች ዝም ብለው ሲሄዱ ተኩስ ከፈተባቸው። ራስ ኃይሉ ግዳጁን የፈፀመው የራስ ካሣ ልጆችን በመማረክ ለጣሊያኑ መንግሥት አሥረከባቸው። እሱ ግን በአንድ የኢጣሊያ ጦር መኮንን ሥር ሆኖ የአንድ ባንዳ አዛዥ ብቻ ነበር። ከእናንተ ብዙዎቹ ወግተውናል እጃቸውን ሲሰጡ ግን ይቅርታ አድርገንላቸዋል። አንድ ጊዜ ይቅርታ ተደርጐላቸው እንደገና ሲታወሙን ከተገኙ ግን ይቅርታ አይደረግላቸውም። የዚሁ ጥሩ ምሳሌ የራስ ካሣ ልጆች ናቸው። ወደ እኛ እንዲመጡ ብዙ ጊዜ ጥሪ እንዳደረግንላቸው ታውቃላችሁ ፤ እነሱ ግን ጥሪያችንን አልተቀበሉም። ራስ ኃይሉ፤ ራስ ሥዩም ፤ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ደብዳቤ ጽፈውላቸው፤ ነገር ግን ምንም ውጤት አልተገኘም። በዚህ አጋጣሚ ራስ ኃይሉ ስለፈፀመው ውለታ ላመሰግነው እወዳለሁ።

"ጃዝማች ሃብተ ማርያምም ለኢጣሊያ መንግሥት እጁን እንዲሰጥ ያደረገው ራስ ኃይሉ ነው። ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ሰላም ሰፍኗል። የቀረን ያ የተረገመው ራስ ደስታ ብቻ ነው። ራስ ደስታ ለመንግሥት እጁን ለመስጠት እንደሚፈልግ ገልጾ ነበር፤ እኔ ራሴም ደብዳቤ ጽፌለት ነበር ፤ ደብዳቤውም በእጁ ደርሷል። ለእንደዚህ ያለ ሰው ይቅርታ ማድረግ ይገባልን? የማይቻል ነው። ራስ ደስታ በገዛ እጁ የሞት ፍርድ ፈርዷል። በቅርብ ጊዜ የኢጣሊያ ፍትሐዊ ሕግ በሰይፍ ለዘለዓለም ይቀጣል። ደጃዝማች በየነ መርዕድም አለ። ከሰባት ጦር ጀምር ባላባቶች ፤ ሹማምንቶች ፤ ቤተዘመዶች ጦር መሣሪያን አስቀምጦ ለኢጣሊያ መንግሥት እጁን እንዲሰጥ መክረውታል።

1. F.Lol v3 p.486



እሱ ግን ውጊያ መርጧል። እሱም በቅርብ ጊዜ ይደመሰሳል። እነዚህ ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው በጦርነት የተሰማሩ፤ ከዚህ በኋላ ግን በመላው ኢትዮጵያ ሰላም ይሰፍናል። ኢትዮጵያ ወደፊት በንጉሣችን ሥም በዱቼ ስም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ለንጉሣችን ሰላምታ Saluto Al Re ንጉሡ ለዘለዓለም ይኑር Viva Il Re ሰላምታ ለዱቼ Saluto Al Duceለእኛ A Noi እያሉ 200 የተድሞ ሹማምንቶች በጣሊያንኛ ድምፃቸውን አሰምተዋል።

## የራስ ደስታ ዳምጠው መያዝና አሟሟት

ጦርነቱ አልቆ ጣሊያኖች የፖሊስ አሰሳ ብቻ እንደተጠለ ይናገሩ ነበር። ፀረ ኢጣሊያ የኢትዮጵያውያን አርበኝነት ከማቀጣጠል አልተቆጠቡም ነበር። ከእነሱ ውስጥ ራስ ደስታ፤ ደጃዝማች ገብረ ማርያም፤ ደጃዝማች በየነ ፤ደጃዝማች ሽመልስ ነበሩ። እነሱ ከነበሩበት ከወላሞ ተነስተው ዋና ከተማዋንም ለማጥቃት እቅድ ነበራቸው። ማርሻል ግራዚያኒ ግን ፋታ አልሰጣቸውም። ጣሊያኖች ብዙ ጀኔራሎች ኮሎኔሎች የተካፈሉበት በፌብሯሪ ከፍተኛ ዘመቻ አካሄዱ።

ፌብሯሪ 20 በተደረገው ጦርነት ደጃዝማች ገብረ ማርያም፣ በጃዝማች በየነ መርዕድና ሌሎች የበታች ሹማምንቶች በጦር ሜዳ ሲገደሉ ራስ ደስታ ብቻ ለማምለጥ ችሎ ነበር። ነገር ግን ቱቺ በተባለው ኢጣሊያዊ የጦር መኮንን የሚመራ የትግሬዎች ባንዳ ፌብሯሪ 27 ቀን ደርሶበት ተማርኮ በጥይት ተደብድቦ ተገድሏል። ከራስ ደስታ ሞት በኋላ ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በኢጣሊያ ቁጥጥር ሥር እንደዋለች ይቆጠራል ብለው ጣሊያኖች ይፎክሩ ነበር። ማርዮ ማሣይ ‹Mario Masai› የተባለው ኢጣሊያዊ የCorriere Di Napoli ወኪል የራስ ደስታና ሌሎችም እሟሟት ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ገልጾታል።

ራስ ደስታ ዳምጠው የሞተው እያለቀሰ ነበር። በሶማሌ አነጋገር ራስ ናክ ማለት ራስ ሴት ይሉታል፤ በአማርኛ ወይዘር ደስታ ይሉታል። ጦሩ በገሌ ሲሸነፍ ከንጉሡ ስድብ ሲደርስበት አልቀረም፤ ልጅ ሥዩም የአህቱ ልጅና ባራምባራስ ፈለቀ የራሱ ዋና ፀሐፊ የነበረው እንደመሰከሩበት ማርሻል ግራዚያኒ አርባ ጉጫ ከሸና Vina አካባቢ የሰፈረው የመጨረሻ ጦሩ ጥቃት ፈጽሞበት ሲበታተን አልቀረም። ራስ ናክ የዚምበር መጨረሻ እጁን ለመሥጠት ታስቦ 47 ዓመት በኢትዮጵያ የኖረው ሲዋር ካስታኛ ‘Castagna› ሲላክበት አልቀረም። በኢጣሊያ የጦር መኮንን ቱቺ የሚመራ የደጃዝማች ታከለ መሸሻ ባንዳዎችና በሌላ የኢጣሊያ የጦር መኮንን ፒና የሚመራ ብረት ለበስ የሶማሌ ወታደሮች ተይዞ በማክ ወደ ጦር ፍርድ ቤት ሲቀርብም አልቀረም። «እኔ አልተዋጋሁምን እያለ

ደጋግሞ ይናገር ነበር። እውነቱ ነው እልተዋጋም ተኩስ ሲሰማ የኢጣሊያ ወታደሮች ያልደ ረሱበት ቦታ መሸሽ ነበር ሥራው፤ ወራዳና ጨካኝ ግለሰብ የሲዳሞና የቦረና ጦር በሚያ ዘበትም ጥቂት ሺህ ሽፍቶች መሪ በነበረበትም ጊዜ። ዛሬ የአማራና ለ50 ዓመታት ዋና ከተማዋ የባርያ ንግድ ምንጭ የነበሩ የጉራጌ ዘር ድብልቅ ነው። ተፈሪ ፈረንቱን ስለሚ ያውቅ ከገናሌ ጦርነት ሽንፈት በኋላ ጀግናው ምርጥ ሽፍታው ገብረ ማርያም ከጉኑ እስቀ መጠበት።

ራስ ደስታን የማሳደድ ተግባር አላፊነቱን በቀጥታ ራሱ ማርሻል ግራዚያኒ ወሰደ። በባሌ አግረኛ የጀነራል ጀሎዞ ጦር ሲከታተለው በሰማይ አሬሮፕላን ሲያጠቁት ወደ የተራራውና ማኮው አየሸሸ ከደጀዝማች በየነ ተቀላቀለ። ግራዚያኒ በባሌ በረሃዎች ፋታ አልሰጣቸውም፤ በምሥራቅ የጀ/ናዚ ጦር፤ በሲዳሞ የጀ/ጀሎዞ ጦር ፤ በጉራጌ የጀ/ጋሊና ጦር እንዲሁም በወላሞ፤ በከምባታ፤ በሐደቆች ሌላ ጦር ተሰማርቷል፤ የጦር አሬሮፕ ላኖችም ተካፈለዋል። በዚሁ ጊዜ የንጉሡ እንደራሴ ማርሻል ግራዚያኒ ከሰሜን የሊቢያ ዲቪዚዮን እንደዚሁም የሶማሌ ባታሊዮች ከደቡብ ለጥቃት ያሰማራል፤ በተጨማሪም ከኢሚ ዱባትና ሊቢያውያን ወደ ላይኛው ዋቢ ሲመድብ በየነ መርዕድ በባሌ ለመኖር የማይቻል ስለሆነበት ሽፍቶቹ ባሌን ለቀው ወደ ምዕራብ ጉራጌና ከንባታ ለመሄድ ገድ ሆነባቸው ፤ ሌላ አማራጭ ማምለጫ አልነበራቸውም። ገብረ ማርያም፤ ደስታና በየነ መርዕድ ወደ ዋቢ ምንጭ ሲሸሹ አራት ባታሊዮን ሊቢያውያን ሊይዙዋቸው ተቃረቡ፤ ጦርነት ቅደረገ በውጤቱ ግን ሽፍቶቹ አልተያዙም እስሉ በተባለው ቦታ መንገድ ዘጉተው በወደጃቸው የምከሩ ብረት ለበሰ ጦርና ሱማሌዎች አላገኙዋቸውም፤ ሾልከው አምልጠዋል። የማርሻሌ ግራዚያኒ ትእዛዝ ተጥሎ ፋታ አልሰጣቸውም፤ ሰላም የሰፈነበት ሀገር በራስ ደስታ አለመያዝ መደፍረስ የለበትም ፤ ስንቅ አሬሮፕላኖች ያቀርቡላችኋል የሚል ነበር። ናታስና ቱሼ የተባለው ተቃርበዋል ጋሊና ወደ ጉራጌ ነው፤ ዛምቦን ሆሳዕና ነው፤ ከበባው ተጠናክሯል። ናታለና ቱሼ መሬምቹ ያሉበት መደበቂያ አግኝተው ተኩስ ይከፍታሉ ከውስ ጡ ተቃውሞ ይገጥማቸዋል። ገብረ ማርያም እየተዋጋ ወደቀ ፤ በየነ መርዕድ ተማርኮ ከአጭር የጦር ፍርድ ቤት በኋላ በጥይት ተደብድቦ ተገደለ። ራስ ደስታ እንደልማዱ አሁንም የመጀመሪያው ተኩስ ሲሰማ በትሉውን በኃይል እየጋለበ ይሸሻል ከእሱ ጋርም ፈታውራሪ ካሣ ነበር። ከዝዋይ በስተምዕራብ ወደ አዳሚቱሉ ምናልባት ወደ ጉራጌ ሀ ገር ዘመዶቹ ወደሚገኙበት። ራስ ደስታ ቀንና ሌሊት ይሸሻል፤ ገብረ ማርያም እንደሞተ አያውቅም፤ በተለይ ቡቶቹ የሚመራው ደጃዝማች ተክለ መሸሻ የትግሬዎች ባንዳ እንዲሁም በፒና የሚመራው የሱማሌ ታጣቂዎች እግሩ የረገጠውን እንደሚከታተሉት አያው ቅም። ራስ ደስታ ጉራጌ ሀገር ደርሷል ፤ ያመለጠ መስሎት ነበር። ጧት ፈብሯሪ 25 1937 ባደረበት ቤት ተኩስ ይሰማል። ፊታውራሪ ካሣና የነበሩ ጥቂት ወታደሮች



እንደተከበቡ እወቁ፤ እስከ መጨረሻ ጥይቶቻቸው ተታኩሰው የጀግና አሟሟት ለራስ ደስታ አስተምረው ወደቁ። ራስ ደስታ እጅን ወደ ላይ እውጥቶ ከቤት ይወጣል፤ እጁን ይሰጣል፤ ጣሊያኖች ሕይወቱን የሚያተርፉት መስሎት ተስፋ ያደርጋል። ራስ ደስታ በኤው ሮጳ መዲናዎች ሲጉብኝ የነበረ ልዑል ራስ ደስታ አይደለም፤ ጢማም፤ ቡቲቲ ጨርቅ የለበሰ በድንጋጤና በፍርሃት የእንድ ጥቁር ሰው ፊት ቢጫ ሆኗል።ራስ ደስታ ይቅርታ ይጠይቃል፤ መሬት ወድቀው ሰላምታ ያልሰጡ ይገርፍ የነበረ፤ስለ ኢጣሊያ ፍትህና ሥልጣኔ ለማውራት የሞከረ ሁሉ ያስርና ይገድል የነበረ፤ ሜይ 1936 የኢጣሊያ ጦር መኮንኖች በእጁ የወደቁ አስከሬኖች ይቆራርጥ የነበረ፤ ዛሬ ለእያንዳዱ ኢጣሊያዊ ወታደር እጅ ይነሳል ፍትሐዊ የኢጣሊያ ጦር ፍ/ቤ ት በሜካ ጦር ሜዳ ችሎት የወታደር አሟሟት ክብር ሰጥቶታል[1]።

ጣሊያኖች በራስ ደስታ ላይ ከመጠን ያለፈ ጥላቻ ያደረባቸው ባንዳሩም በራስ እምሩ ላይ አክብሮት መስጠታቸው አሁንም የኢጣሊያኖች ፍትህ እልባንት የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም ሁለቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ነበር ለሀገራቸው የተዋደቁ።

ከሜይ 1936 እስከ ማርች ለ10 ወር ጣሊያኖች 45 የጦር መኮንኖች 207 የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 1200 እንዲጀኒ ወታደሮች ሞተውባቸዋል[2]።

በአጠቃላይ ጦርነቱ በይፋ ከመጀመሩ 3 ወር በፊት በጁላይ 1935 ጦርነቱ ካለቀ 2 ወር በኋላ ድረስ የሞቱ ጣሊያኖች 2911 ሲሆኑ እስከ ጁላይ 31 1939 ድረስ የሞቱ ጣሊያኖች 4915 ደርሰው ነበር ፤ ከኢንዲጀኒ ሌላ።

እላይ ስሙ የተጠቀሰው ካስታኛ ሰለተባለው ኢጣሊያዊ አርናልዶ ቺፖላ ታሪኩ አውጥቷ ል። ካስታኛ በድዋ ጦርነት ከታሰሩ የኢጣሊያ ወታደሮች አንዱ ነበር ፤ የምሕንድስና የበታች መኮንን ነበር። ከአፄ ምኒልክ ጊዜ ጀምሮ መንገዶች፤ ድልድዮች ፤ ቤቶች፤ እየሰራ ከነገሥታትና ከሹሞች ተስማምቶ ይኖር ነበር። አንድ ኢትዮጵያዊት ሴት አግብቶ ብዙ ልጆች ወልዷል። እንደ አሪት ረጅም ጢም የነበረው ካስታኛ በጦርነቱ ወቅት ፈረንጆች ሀገር ለቀው ይወጡ ስለነበረ አጼ ኃይለ ሥላሴ «አንተ ካስታኛ ከኛ ጋር መቀመጥ የምትመኝ ይመስለኛል። የኢጣሊያዊነት ምንም የቀረህ ነገር የለህም» ብሉ ቢጠይቀው «የኢጣሊያዊነት ልብ ነው የቀረኝ» ብሉ መለሰለት።

የኢጣሊያ እምባሳደር ጦርነት ሲጀመር ሀገር ለቆ ሲወጣ ሲኖር ካስታኛ ሊሸኘው በባቡር ጣቢያ ተገኝቶ ነበር። እምባሳደሩ ታዲያ ምን አሰበሃል ብሉ ለካስታኛ ይጠይቀዋል። ከዚህ ሀገር ለቅቄ መውጣቱ የማይቀር ነው፤ ለኔ ቀላል ነገር አይደለም ለመሄድ፤ ስሚስቴ ፤ ለልጆቼ፤ ለቤተሰቤ ማሰብ አለብኝ።

1. F.l.o.i v3 p. 472-74

2. F.l.o.i v3 p. 476 '

ሆኖም አይጠራጠሩ እመጣለሁ። ምንም እንኳ ለ 40 ዓመት በኢትዮጵያ ተቀምጫ ሕይወቴን ለእነዚህ ሰዎች መስዋዕት ባደርግም እኔ ኢጣሊያዊ ነኝ አልረሳውም። እምባሳደሩም ካስታኛ ከኔ ጋር ከዚህ ሀገር ብትወጣ ይሻልሃል ይለዋል። ካስታኛም እንደዚህ ሁኘ? ይለዋል።

እምባሳደሩም አዎ እንደዚህ ሆነህ ይለዋል። አንድ ሻንጣ ሳልይዝ ያለ ገንዘብ ከቤተሰቦቼ ሳልሰናበት በማለት መልስ ይሰጠዋል። እምባሳደሩም ትክክል ይለዋል። ካስታኛም ሲኞር እምባሳደር ይኼ የማይቻል ነው ብሎ መልስ ይሰጠዋል። እምባሳደሩም ካስታኛ ወይንም ዛሬ ከእኔ ጋር ወይንም ምን ጊዜም ከዚህ ሀገር አትለቅም ይለዋል። ካስታኛም ሲኞር እምባሳደር አረጋግጥልሃለሁ ብሎ መልስ ለመስጠት በሚሞክርበት ጊዜ ባቡሩ ሲነሳ ነበር አንባሳደሩ ምልክት በሰጠው መሠረት አንድ የኤምባሲ ሠራተኛ ወደ ባቡሩ ገፍቶ ያስገባዋል! ሌሎችም ጣሊያኖች ከባቡር ውስጥ ሆነው እየሳቁ በጨ ይሰዉታል። ከአንድ ደቂቃ በኋላ ባቡሩ ተነሳ ካስታኛም ከእምባሳደሩ ጉን ተቀመጠ ጅቡቲ እንደደረሱ ቢንቺኖ ካስታኛ ወደ ሞቃዲሾ ሄደ ካስታኛ የማርሻል ግራዚያኒ ዋና ጽ/ቤት ሉግ የማስታወቂያ ክፍል ተመድቦ ይሰራ ነበር። ካስታኛ አንድ ቀን «ክቡር ሆይ ከፈቀዱልኝ እኔ ብቻዬን ራስ ደስታ ወዳለበት ሄጄ እዚህ ላምጣው። ከልጅነቱ ጀምሮ ነው የማውቀው። አባቱ በዐድዋ ጦርነት ጊዜ ሞቷል! የኃይለ ሥላሴ ጭፍራ ምሳሌ እንዲ ከተል ሳይረዳው እችላለሁ» ብሎ ለግራዚያኒ ጥያቄ አቅርቦ ነበር። ነገር ግን ግራዚያኒ ውድ ካስታኛ እርስዎ ከእኛ ጋር ቢቀመጡ የተሻለ ነው ምክንያቱም እርግጠኛ ነኝ 40 ዓመት በኢትዮጵያ ቢቀመጡም ከራስ ደስታ የሚያገኙት አቀባበል ለሕይወትዎ የሚያሰጋ ነው ብሎ መልስ በመስጠት እንዳይሄድ ከለከለው።

ጣሊያኖች አዲስ አበባ ሲገቡ ግራዚያኒ ሱማሊያ ሀገር ሆኖ ያልፈቀደለት ካስታኛ ራስ ደስታ ወደሚገኝበት ጫካ ሄዶ እጁን እንዲሰጥ! መልእክት እንዲያደርስለት ቢልክ ውም ውጤት አላስገኘም።



# ምዕራፍ 14

# ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ አስተዳደርና የአርበኝነት ዘመን የመጀመሪያ ዓመት ታሪክ

ወራሪ የኢጣሊያ ሠራዊት ከኤርትራ ተነስቶ ማይጨው ለመድረስ የ200 ኪሎ ሜትር መንገድ ከ6 ወር በላይ ጊዜ ፈጅቶበታል። እንደዚሁም በደቡብ ጦር ግንባር ከሶማሊያ ተነስቶ ኦጋዴን ለመያዝ፤ ከማይጨው ጦርነት በኋላ ግን አዲስ አበባ ለመድረስ 600 ኪሎ ሜትር አንድ ወር አልፈጀበትም እንደዚሁም በደቡብ ጦር ግንባር ከኦጋዴን ድሬደዋ ለመድረስ አንድ ወር አልፈጀበትም። ሁኔታው የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደተሸነፈና እንደተደመሰሰ ኢትዮጵያም እንዳበቃላት ያስመስል ነበር። ሐቁ ግን ጣሊያኖች በአጭር ጊዜ አዲስ አበባ ሊገቡ የቻሉት ኢትዮጵያ መንግሥት አልባ ሆና በሳተኞቿ ሠራዊቱም ጠቅላይ እዝ ስላልነበረው በዓለም መንግሥታት መድረክ ለፕሮፓጋንዳ ስነ ልቦና እንዲጠቀሙበት ጦርነት ሳይገጥማቸው ተሸለክልከው አዲስ አበባን መቆጣጠር ቻሉ እንጂ በድል አድራጊነት አልገቡም። "ዱቼ" ስለ ሁኔታው ስላልተረዳ አዲስ አበባ ከተያዘች በኋላ ወራሪ የኢጣሊያ ሠራዊት ወደ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገሮች ዘመቻውን ወዲያውኑ እንዲቀጥል ትእዛዝ ያስተላልፍ ነበረ። ሆኖም በስፍራው ያሉት የጦር አለቆች ግን የክረምት ዝናብ ምክንያት በማቅረብ ጨርሶ እንደማይቻል ስለገለጹለት እንደ ነገሩ ሁኔታ አስፈላጊውን ውሳኔ ራሳቸው እንዲወስዱ ለመፍቀድ ተገደደ። በዚሁ መሠረት ወደ ምዕራብና ደቡብ ክፍላተ ሀገሮች ወረራ ለ5 ወር እንዲዘገይ ተደረገ። ስለዚህ የመጀመሪያ አንድ ዓመት የኢጣሊያ አገዛዝ ታሪክ በክረምት 5 ወራትና ከክረምት ፍጻሜ በኋላ ያሉት 7 ወራት ለሁለት ይከፈላል።

ከማይጨው ጦርነት ሽንፈት በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት በደቡብ ጦር ግንባርም ሽንፈት ስለገጠመው ተበታትኖ እየሸሸ ወደ እየቤቱ ይመለስ እንደነበረ የጣሊያኖች ግምት ነበረ። በዚሁ ጊዜም የኢጣሊያ ሠራዊት በተሽከርካሪዎች ይጓዝ ስለነበረ በእግሩ የሚጓዘውን የኢትዮጵያ ወታደር በመቅደም ከተጠበቀው በላይ በፍጥነት አዲስ አበባ ገብቶ ለመላው ዓለም ድል ተቀዳጀሁ ብሎ ቢያበስርም የኢትዮጵያ ሠራዊት ግን ተበታትኖ ተሸነፍኩ ብሎ የኢጣሊያ ድል አምኖ እንዳልተቀበለ ገሐድ እየሆነ ነበር።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በጦር ሜዳ የተሸነፈው መሪ በማጣቱ ነው። አዲስ አበባ በጣሊያኖች እጅ ከወደቀች በኋላም በጣሊያኖች ወራሪዎች ላይ ውጊያውን የቀጠለው በአንድ መሪ ተሰባስቦ ተደራጅቶ አልነበረም፤ በአነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍሎ በተፈጥሮ የወረሰው የሀገር ፍቅር ስሜት ባንዳንድ ቆራጥ የቀድሞ መሪዎቹ ስር ተሰባስቦ ነበረ። ኢትዮጵያውያን በአዲስ መንፈስ ውጊያውን መቀጠል የውጭ መንግሥታት እጅ እንዳለበት የሚል ጥርጣሬ ነበራቸው። ከኢትዮጵያ አጎራባች ቅኝ ግዛት ያላቸው መንግሥታት ኢጣሊያ ደካማ በመሆኑዋ ስለ የኢትዮጵያ ግዛት ለመቆጣጠር ዐቅም የላትም ብሎ በመገመት የኢትዮጵያ መሬት ከኢጣሊያ ጋራ ለመቀራመት ፍላጎት እንደነበራቸው ጣሊያኖች እንደደረሰበት ገልጿል። የኢትዮጵያውያን በጣሊያኖች አገዛዝ ላይ ለውጊያ በማነሳሳት እርዳታ ሰጪ ሆነው በመቅረብ የኢትዮጵያ መሬት ለመከፋፈል ፍላጎት የነበራቸው መንግሥታት እንደነበሩ!

ጣሊያኖችም ደካሞች በመሆናቸው እርዳታ ለመቀበል ይገደዱ እንደነበረ ዘግቧል፡፡ በጣሊያኖች አባባል በዚሁ መንፈስ ነበረ በምዕራብ ኢትዮጵያ በጉሬ ጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት የተቋቋመው፡፡ በጂቡቲ በሶማሊላንድ ፀረ ኢጣሊያ አዝማዝ በኢትዮጵያ ስደተኞች መሐል ቅስቀሳ ይካሄድ ነበረ፡፡ የዚህ ሁሉ ዓላማ ጣሊያኖችን በማዳከም ኢትዮጵያን ለመከፋፈል ነበረ፡፡

ጣሊያኖች ግን የነበራቸው ዓላማ የውጭ መንግሥታት ሰቅድ ውድቅ በማድረግ ብቻቸውን የኢትዮጵያውያንን ተቃውሞ ለማውደም ነበረ፡፡

ጣሊያኖች አራት ቀን አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ሜይ 9 ቀን 1936 ስለ ኢትዮጵያውያን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ባደረጉት ግምገማ የሚከተለው ነበረ፡፡

## በበጌ ምድርና ጉጃም

1. ፊታውራሪ መንገሻ በጋላባት አካባቢ
2. ደጃዝማች ባሄል በባሕር ማና አካባቢ
3. ራስ እምሩ በደብረ ማርቆስ
4. ደጃዝማች አያሌውና አድማሱ ብሩ በጋይንት አካባቢ
5. ደጃዝማች አስፋወሰን ካሣ በበጌምድርና በጉጃም
6. ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ በላሊበላ

### በሸዋ

7. ደጃዝማች አበራ ካሣ በፍቼ
8. ራስ ከበደ በኢፍራታ
9. የሽፍቶች ቡድን በጣርማ በር
10. ፊታውራሪ ፍቅረማርያም በጂሩ
11. ፊታውራሪ አስቸናፊ በሰላሌ
12. ደጃዝማች ባልቻ እና መታፈሪያ በደብረብርሃን መንገድ ግራና ቀኝ

### አዲስ አበባ

በከተማዋ ሰላም ሰፍኗል፤ ራስ ኃይሉ በጉለሌ ይገኛል፡፡ በከተማዋ ዙሪያ ግን ብዙ ሽፍቶች ነበሩ፤ ተለይተው የታወቁ በሰላሌ በእቃቂና ቡልጋ ያሉ ናቸው፡፡ ከእነሱ ውስጥ ባራምባራስ አበበ የፖሊስ አዛዥ የነበረ እና ብላታ ታከለ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሹም የነበረ ይገኙባቸዋል፡፡ በመናገሻም የታጠቁ ቡድኖች ታይቷል፡፡

### ሲዳማ አርሲ ባሌ

13. ራስ ደስታ ዳምጠው ደጃዝማች ገብረማርያም ደጃዝማች መኩንን ወሰኔ በኬንያ በኩል ከእንግሊዞች ጋራ ግንኙነት ያላቸው፡፡
14. ደጃዝማች በየነ መርዕድ ብጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ደጃዝማች ተፈራ

### ሐረር

15. ብዙ ሽፍቶች በጨርጨር ጋራሙለታና ከንዱዶ ሰፍረው ይገኛሉ እጃቸው ለጣሊያኖች ለመስጠት የገለጡ ራስ ኃይሉና ራስ ሥዩም ናቸው፤ ገና እጃቸውን ለመስጠት በማወላወል ላይ የሚገኙ ደጃዝማች አያሌው ብሩና ራስ ከበደ መንገሻ ናቸው፡፡

አዲስ አበባ በኢጣሊያ እጅ እንደወደቀች የኢጣሊያ መንግሥት ጦርነቱ እንዳለቀ ሰላም እንደሰፈነ ግምት አድርጎበት ነበር፡፡ በስፍራው የነበሩ የኢጣሊያ ጦር መሪዎች ግን አዲስ አበባ በመግባታቸው ኢትዮጵያን እንዳልተቆጣጠሩ ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡ የኢጣሊያ ሠራዊት



በእስጊ ሁኔታ እንደሚገኝ ለመንግሥታቸው ለማስረዳት ብዙ መጣር ነበረባቸው፡፡ የተደቀኑባቸው ችግሮች ለመቋቋም ብዙ ትግል ማድረግ እንደሚቀርባቸው ስለተረዱ ከአርበኞች አደጋ ለመከላከል ለአስፈላጊ እርምጃዎች ቢወስዱም ቀላል አልነበረም፡፡ የጣሊያኖች የመጀመሪያ ስጋት ያደፈጡ በየቦታው የነበረ የኢትዮጵያ አርበኞች በአንድ መሪ እንዳይታዘዙ ሲሆን፤ የሁሉም መሪ ይሆናል ብለው የጠረጠሩት ራስ እምሩ ነበረ፡፡

የኢጣሊያ ጦር መሪዎች ከወሰዷቸው እርምጃዎች ዋንኛው ዋና ከተማዋ አዲስ አበባን ከአርበኞች ጥቃት ለመከላከል ነበር፡፡ ለዚሁም በከተማዋ መሃልና በዙሪያዋ ብዙ ወታደሮች ማሰፈር ተገደው ነበር፡፡ ለጣሊያኖች ተደቅኖባቸው የነበረ ሌላ ችግር የመገናኛዎች ደኅንነት መጠበቅ ነበረ፡፡ ስጋት ወድቀው የነበሩ መገናኛዎች ከአዲስ አበባ ጅቡቲ የተዘረጋው ባቡር ሐዲድና ከአዲስ አበባ ደሴ መንገድ ነበረ፡፡ ይህ ሁሉ ለማከናወን ከሞቃዲሽና ከሌሎች ቦታዎች ተጨማሪ ወታደሮች እንዲላኩ አድርገዋል፡፡ ጣሊያኖች የስንቅ ችግር ለመፍታት የተሻለ ሆኖ ያገኙት ከውጭ በሶማሊያና በጅቡቲ ለማስገባት፤ ከሀገር ውስጥ የገበያ አቅርቦት አናሳ ስለነበረ ወደ ገጠር እየሄዱ ከገበሬዎች በመዝረፍ ይጠቀሙ ነበረ፡፡ ሌላ ቅድሚያ የሚሰጠው አስጊ ሁኔታ ብለው የገመቱት በሐረርጌ የሰፈሩ አርበኞች ለመደምሰስ ነበረ፡፡ ይኸንም ለማድረግ የተጠቀሙበት ዘዴ ከጦር ኃይል በተጨማሪ አርበኞችን ለመከፋፈል በመቻላቸው ነው፡፡ ገና በኢጣሊያ ያልተያዙ ክፍለ ሀገሮች፤ በተለይ ጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት የተቋቋመበት በጉሬ አካባቢ ለመዝመት የዓለም ዜና ማሰራጫዎች ኢትዮጵያ በሙሉ በጣሊያኖች እንዳልተያዘች የሚያናፍሱት ዜና ለማስቀረት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነበረ፡፡ የአስተዳደር መዋቅር መዘርጋት የወታደር ቁጥር መቀነስ ቀላል ሥራ አልነበሩም፡፡

የኢትዮጵያ አርበኞች ትግል ለመጀመሪያ ጊዜ ያበሰረው በምሥራቅ ሐረርጌ ከሐረር ጅጅጋ ባለው መንገድ ነው፡፡ ሜይ 14 ቀን 1936 ማለት 9 ቀን አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ አርበኞች ጥቃት ደርሶባቸው 6 ሰዎች ሞተው 2 ቆስለባቸዋል፤ ሁሉም ኢንዲጂኒ ነበሩ፡፡ ከኢትዮጵያ ወገን በውጊያ ከሞቱ ሌላ የተማረኩ 6 ወታደሮች በጣሊያኖች ተረሽነው ተገድለዋል፡፡ የተማረኩ ወታደሮች የተገደሉበት ምክንያት ግራዚያኒ ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር በላከው ቴሌግራም እንደገለጠው የኢትዮጵያ መንግሥት የተደመሰሰ ስለሆነ ማንኛው ወታደር እጁን ለኢጣሊያ ባለሥልጣናት ከሰጠ ምህረት እንደሚደረግለት እጁን የማይሰጥ ግን እንደ ተራ ሽፍታ ዘራፊ ተቆጥሮ እንደሚገደል ለባላባቶችና ለወታደሮች በአዋጅ የተነገራቸው ስለሆነ ወታደሮቹ ሊገደሉ ችሏል ብሏል፡፡

## በሐረርጌ የነበሩ የኢትዮጵያ አርበኞች

1ኛ. በከንዱዶ የነበሩ በፊታውራሪ በሐይደ የሚመሩ ሲሆኑ
2ኛ. በጋራሙለታ የነበሩ በፊታውራሪ ሺመልስ የሚመሩ ናቸው፡፡
3ኛ. በስተምዕራብ በጨርጨር የነበሩ በፊታውራሪ ማሊዮን የሚመሩ ናቸው፡፡ የ3ቱ የኢትዮጵያ አርበኞች ቡድኖች የወታደር ኃይል ብዛት ከ10 እስከ 15.000 መሆናቸውን ተገምቷል፡፡

በኢጣሊያ በኩል ከተሰለፉት፡-

1. የሊቢያ ዲቪዚዮን 1ኛ ሬጂመንት III - V ባታሊዮኖች
   3ኛ ሬጂመንት II - X "
   4ኛ ሬጂመንት VIII - IX "
2. ዓረብ ሶማል ቅይጥ ጦር 1ኛ ሬጂመንት I-III-VI "
   2ኛ ሬጂመንት II-IV-V "

3. ኤርትራውያን XLV ባታሊዮን ነበሩ።

ከአጋዴን ጦር ግዳ ሸሽተው ወደ ሐረርጌ የተሰበሰቡ የኢትዮጵያ ወታደሮች በጣሊያኖች ግምት በድንጋጤና በፍርሐት የሚገኙ መስሏቸው ጦራቸው ወደ ባሌ ያበየን መርዕድ ጦር ወዳለበት ለማዝመት የመጀመሪያ እቅዳቸው ነበረ ። ሆኖም በጨርጨር ጋራሙለታና ኮንዱዶ የሰፈሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ባደረጉዋቸው እንቅስቃሴዎች ራሳቸው ጣሊያኖች ተደናግጠው ወደ ባል ለመዝመት የመጀመሪያ ዕቅዳቸው ተይረው ወደ ባለ ዘመቻ ክረምት ከመግ በኋላ አስተላልፈው ሙሉ ኃይላቸው በሐረርጌ እንዲያውሉ ተገደዱ። ዕቅዳቸው ለማስቀየር ያስገደደዋቸው ሁኔታዎች 1ኛ ግድ 13 ቀን 1936 በሐረርና ጅጅጋ መንገድ በአርበኞች የደረሰባቸው ጥቃት 2ኛ ግድ 14 በቀርሳ በፊታውራሪ መንገሻ የሚመሩ አርበኞች በደረሰባቸው ጥቃት 3ኛ ግድ 28 ከአርበኞች ጋራ የተደረጉ ግጭቶች 4ኛ በሚኤሶና አሰበ ተፈሪ መሐከል ባለው መንገድ በደረሰባቸው የደፈጣ ውጊያ ነበረ። በዚሁ መሠረት መላው ሐረርጌ በአደጋ የወደቀ መሆኑን ሊገነዘቡ ችሏል። ጁን ወር መጨረሻ በሶስት ቦታ የተከፈሉ በጨርጨር ጋራ ሙለታና ኮንዱዶ የተደራጁ የኢትዮጵያ ወታደሮች መኖራቸውን ተገነዘቡ። በዚሁ መሠረት ጣሊያኖች ዓብዱላ ኮንዱዶ የሰፈሩት የኢትዮጵያ አርበኞች ለመደምሰስ በ[illegible]ም ቢርና ኮምቦልቻ መሐከል 4 ባታሊዮኖች አሰፈሩ፣ ጋራሙለታ የሰፈሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ለመደምሰስ በቃር አካባቢ 4 ባታሊዮኖች መድበው አሰፈሩ። እንደዚሁም ጨርጨር የሰፈሩ የኢትዮጵያ ወታደሮችን ለመደምሰስ በቀርሳ 4 ባታሊዮኖች አስግሩ። ተጠባባቂ 2 የሊቢያ ባታሊዮኖችም ተመድበዋል።

## ሀ/ ኮንዱዶ

ጣሊያኖች ሐረርጌን አደጋ ላይ እንድትወድቅ አድርገዋል ከተባሉ በአንዱ ቡድን በኮንዱዶ የሰፈረ የኢትዮጵያ አርበኞች ቡድኑ ላይ በመጀመር የዘመቻ ጥቃታቸውን ጀመሩ። የኮንዱዶ ውጊያ የቆየው ከአንድ ወር በላይ ከጁን 22 እስከ ኦገስት 29, 1936 ዓ.ም. አርበኞቹ ጁን 22-23-24-25 በተደረጉ ውጊያዎች ጉዳት ቢደርስባቸውም ንጉሠ ነገሥቱ ይመለሳሉ የሚል ወሬ ከእንግሊዝ ሶማሊላንድ ሳዛው ከሚኖሩ የኢትዮጵያ ስደተኞች ዜና ያደርሳቸው ስለነበረ እንደገና ሊደራጁና ሊጠናከሩ ችሏል። ሰጋሬ እና ሞሊሰ በተባሉ ቦታዎች አርበኞች እንደገና በተቋቋመዘት ኦገስት 17 ቀን ውጊያዎች ተደርገው እንደገናም ጁላይ 21 ወደ ሰጋሬ ከሚያመሩ አርበኞች ጋራ ጣሊያኖች ውጊያ ስለገጠሙ ጉዳት ስላደረሰባቸው ሰጋሬም በጣሊያኖች እጅ ስለወደቀች በፊታውራሪ በሐይ የሚመሩ አርበኞች ወደ ሰራርታ አፈግፍገው ሲሰፍሩ ብዙዎቹ ለጣሊያኖች እጃቸው ለመስጠት ተገደዱ። በዚሁ በሳረርታ አርበኞች ከመሸጉበት ለማስለቀቅ ከኮምቦልቻ 9ኛ የሊቢያ ባታሊዮን 6ኛ የሶማል ባታሊዮን ከሰጋሬ 3ኛ እና 4ኛ የሶማል ባታሊዮኖች እንደዚሁም ከሰሜን ዱባትና ሌሎች ባንዳዎች በማሰማራት ጁላይ 28 እና 29 የሰራርታ ከበባ ለማጠናቀቅ ጣሊያኖች ዕቅድ አውጥተው ነበረ። በፊታውራሪ በሐይ የሚመሩ የኢትዮጵያ አርበኞች ግን ከጣሊያኖች ወረራ በሌሊት እየተሰገሰ አምልጠው ጋራ ሙለታ ከሚገኙ አርበኞች ሊቀላቀሉ ችሏል።[1]

[1] Governo Generale Stato Maggiore AOI. II Primo Anno dell' Impero VI testo p 64



## ለ. ጋራሙለታና ጨርጨር

ከአጋዴን ጦርነት በኋላ የተመለሰው የኢትዮጵያ ከራስ መኮንን ጊዜ ጀምሮ ወታደራዊ የተፈጥሮ ምሽግ አቀማመጥ ያለው በጋራሙለታ የሰፈሩ በፊታውራሪ ሽመልስ የሚመሩ ቁጥራቸው 4.000 የሚገመት ነበረ። በጨርጨር የሰፈሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች በፊታውራሪ ሚሊዮን የሚመሩ ነበረ። ጋራሙለታን ለመያዝ የተመደበው የኢጣሊያ ጦር 2 ሬጂመንት 4 ባታሊዮን ሊቢያውያን ነበሩ፣ አንድ ሬጂመንት ዓረብ ሶማል ወታደሮችም ተጠባባቂ ረዳት ከጨርጨር የመጣ ዓለመያ ሰፍረው ነበረ። ጁን 29, 1936 ውጊያው ተጀመረ። ጣሊያኖች በአርበኞች መሐከል ክፍፍል እንዲፈጠር ስላደረጉ፣ ፊታውራሪ ሚሊዮን 1000 ወታደር አስከትሉ እጁን ለጣሊያኖች ሲሰጥ ከፊታውራሪ ሺመልስ ጦርም አንዳንዶቹ እጃቸው ሰለሰጡ ቁልቢ ጁላይ 6 በጣሊያኖች ተያዘች፣ ጁላይ 13 ጨለንቆ ተያዘ ጁላይ 21 ደደር በጣሊያኖች እጅ ወደቀ፣ ጁላይ 19 ግራዋ ዋናው የአርበኞች ምሽግ ተያዘ። ፊታውራሪ ሽመልስ ሸሽቶ ወደ ምዕራባዊ ጨርጨር ሄደ። ጣሊያኖች ጋራሙለታ በሙሉ የተቆጣጠሩ መስሏቸው ነበረ፣ ነገር ግን ፊታውራሪ በሐይ 3000 ወታደሮች አሰባስቦ ኦገስት 4 እና 5 በጣሊያ ጥቃት ሲጀምር በክረምት ኃይለኛነት ምክንያት ጣሊያኖች ሊዘምቱበት ስላልቻሉ ክረምት እስከሚያልቅ መጠበቅ ግድ ሆነባቸው። ፊታውራሪ በሐይና ሽመልስ ጣሊያኖች በክረምት መነቃነቅ አቅቷቸው በመቆማቸው በመጠቀም ጦር ሰፈሮችና ባቡር ሐዲዶች ላይ በጣሊያኖች በየጊዜው ጥቃት ከመፈጸማቸው በላይ ንጉሡ ሊመለስ ነው እያሉ ቅስቀሳ ያካሄዱ ነበር። በግራዋ አሰሚያ ኩርፋቸሊ ደሉ የነበሩ የኢጣሊያ ጦር ሰፈሮች ሴፕተምበር 11 ኦክቶበር 1 እና 2 ጥቃት ደርሶባቸዋል፣ ቢጋልዲቱ የነበረ ጦር ሰፈር ሴፕተምበር 6 እና 10 ኦክቶበር 1 እና 2 ጥቃት ደርሶባቸዋል። በኮንቮይ የሚጓዙ የኢጣሊያ መኪናዎች ላይ አርበኞች ተደጋጋሚ ጥቃት አድርሰዋል ከሁሉ ከባድ የነበረው ሴፕተምበር 28 የተደረገው ጥቃት ባስከተለው 9 ሰዓት የቆየው ውጊያ ነበረ። ኦክቶበር መጀመሪያ ግን አርበኞች አቅማቸው እየታደከመ በመሄድ ላይ ይገኝ ነበር።

## ሐ. በጨርጨር

1/ በቁልቢ ኦገስት 14 እና 20 ሴፕተምበር 27 አርበኞች ጥቃት ፈጽመዋል፣ 2/ አሰበ ተፈሪ ሴፕተምበር 26 3/ ጨለንቆ ሴፕተምበር 1-27-28 እና ኦክቶበር 2 4/ ዱር ኦገስት መጨረሻና ኦክቶበር 2 5/ ዋራቢሊ ሴፕተምበር 15 እና 16 6/ ቁኒ ኦገስት 30 7/ የኮንቮይ መኪናዎች ኦገስት መጨረሻ እንደዚሁም ሴፕተምበር 18 እና 20 አርበኞቹ ጥቃት አድርሰዋል። ኦክቶበር ወር የክረምት ዝናብ በመቆሙ ጣሊያኖች ዘመቻቸውን በመጀመሩ የአርበኞች ኃይል እንዲዳከም አድርገዋል።

ከጁላይ እስከ ኦክቶበር በተደረጉ ውጊያዎች በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት

| | ኮንዱዶ | ጋራሙለታ | ጨርጨር | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| የሞቱ ጣሊያኖች | 1 | 1 | 11 | 13 |
| የሞቱ እንዲጀኒ | 62 | 6 | 218 | 286 |
| የቆሰሉ ጣሊያኖች | - | 1 | 16 | 17 |
| የቆሰሉ እንዲጀኒ | 113 | 11 | 316 | 445 |
| | | | ጠቅላላ ድምር | 761 |

ከአርበኞች ወገን በጦር ሜዳ የተገደሉ 1303 ተማርከው የተረሸኑ 39፡፡

## ለ. ሸዋና አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ሠራዊት መሪ በማጣቱ ጣሊያኖች ምንም ተቃውሞ ሳይገጥማቸው ከትግራይ አዲስ አበባ ሊገቡ ችሏል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ጣሊያኖች አዲስ አበባን መቆጣጠራቸው እሜን ብሎ እንዳልተቀበለው ራሳቸው ጣሊያኖች መስክረዋል፡፡ ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ በሰሜን ሸዋ በባቡር ሐዲድ በምዕራብ አዲስ አበባ ወዲያውኑ ጣሊያኖችን ለመፋለም የአርበኞች እንቅስቃሴ የታየው ሁሉ ዓላማው ጣሊያኖችን ከአዲስ አበባ ለማስወጣት ነበረ[1]፡፡

ከአዲስ አበባ ጣሊያኖችን ለማስለቀቅ አዲስ ፍልሚያ የጀመረው በትግራይ ተሸንፎ የተበታተነ የኢትዮጵያ ጦር እንደገና ተደራጅቶ አልነበረም፤ በኃይለሥላሴ ጊዜ ሰጦርነት የከተት ጥሪ በቂ ቅስቀሳ ሳይደረግለት ስለቀረ በጦርነት ያልተሳተፈ አዲስ ኃይል ነበረ፤ የጦር መሪዎቹም ሁሉ አዲሶች ነበሩ፡፡ ኢትዮጵያ የተሸነፈችው በጦር መሣሪያ ብዛትና ዓይነት ማጣት ብቻ አልነበረም፡፡ አብዛኛው ኢትዮጵያ ለሽንፈት የተዳረገችው መሪ በማጣቷ ነው፡፡ ከማይጨው ሽንፈት በኋላ እስከ አዲስ አበባ ደጀን ጦር ባለማደራጀቱ ጣሊያኖች እየዘፈኑ አዲስ አበባ ሊገቡ ችሏል፡፡ የኢትዮጵያ ለጦርነት ማሰለፍ የምትችለውና የሚገባት የወታደር ብዛት ኢጣሊያ ከምታሰልፈው እኩል ወይንም የበለጠ መሆን ሲገባው ኢትዮጵያ ግን በወታደር ቁጥር ብዛትም ከኢጣሊያ ወታደሮች ቁጥር ግማሽ ብቻ ነበረ ያሰለፈችው፡፡ ይህ ሁኔታ ከአመራር ጉድለት ጋራ ተዳምሮ ኢትዮጵያ ለሽንፈት ዳርጓታል፡፡ ባንጻሩ ግን ይህ ሁኔታ ቢሟላ ኖሮ የጦር አሮፕላኖች የታንኮች ግነስ ሊተካው ይችል ነበር፡፡ እርስ በርሳቸው አስተባባሪና ገንዘብ ወዘተ.. ያልነበራቸው አርበኞች ከኃይለሥላሴ ዘመን የበለጠ በሕዝቡ ቅስቀሳ ያደርጉ እንደነበረ በባቡርና በመኪና መገናኛዎች አደጋ እየጣሉ ሰንቅና ትጥቅ ወደ አዲስ አበባ እንዳይገባ ችግር ፈጥረውባቸው እንደነዘረ ጣሊያኖች መስክሮውላቸዋል፡፡

# ሜይና ጁን ወራት 1936

ሀ/ ምዕራብ ጣሊያኖች በጥቂት የወታደር ጥበቃ በሰላም መኖር አልቻሉም የነበሩዋቸው ጦር ሰፈሮች ማጠናከር ወይንም መዝጋት ተገድደው ነበር፤ አንድ የኤርትራውያን ብርጌድ አሰማርተው ነበረ፡፡

ለ/ ባቡር ሐዲድ

ለጥበቃ የተሰማሩ የኢጣሊያ ነጭ ወታደሮች ነበሩ፡፡ ሜይ 16-20-22-23 ጣሊያኖች ከአርበኖች ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል፡፡

ሐ/ ሰሜን ሸዋ

ከምዕራብና ከባቡር ሐዲድ የባሰ ሁኔታ አዲስ አበባ ከተያዘች አንድ ሳምንት ሳይሞላ የአርበኞች እንቅስቃሴ ይታይበት ነበር፡፡ ጣሊያኖች የወታደሮቻቸውና የንብረታቸው ደሕንነት ለመጠበቅ በሕዝቡ ጭፍጨፋ ያካሂዱ ነበር፡፡ በሚያዝያ ወር 1928 (1936) በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራ የኢትዮጵያ ጦር ተበታትኖ ወደ አዲስ አበባ የሚወስደው ገደላ ገደል ለመከላከያ የሚመች

[1] Governo Generale, AOI II ibd VI p 81



መንገድ ለጣሊያኖች የለቀቀላቸው፤ ሕዝቡም በሆታና በእልልታ ተቀበለን እያሉ ሊዝናኑበት የነበረ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ በግንቦት ወር በቂ ትጥቅ ያልነበራቸው አርበኞች በሚመላለሱ ጣሊያኖች ላይ በየቦታው ባቋቋሙት ጦር ሰፈራቸው ሳይቀር ጥቃት ይፈጽሙባቸው ነበር፡፡ ሜይ 11 ቀን ከደሴ ተነስቶ ወደ አዲስ አበባ የሚጓዝ አንድ የጦር አሬፕላን ንብረት የጫነ የመኪና ኮንቮይ ሜይ 13 ቀን ሮቢ ሲደርስ በሰላይ ጦር አረፕላኖች አርበኞች ጥቃት ሊፈጽሙብት ይጠባበቁት እንደነበረ ጣሊያኖች ስለደረሱበት ጉዞውን አቋርጦ ለመከላከያ በተጠንቀቅ እንዲቆም ተገዶ ከአዲስ አበባ በሜይ 19 ኃይለኛ አጃቢ ጦር ሲላክላት ብቻ ጉዞውን ሊቀጥል ችሏል፡፡ ከእሱ በፊት ያለው ሌላ ኮንቮይ ግን ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከባድ ጉዳት ደርሶበት ነበር[1]፡፡

## ኮሮማሽ

ሜይ 22 ቀን ጣሊያኖች በኃይለሥላሴ ዘመን የጦር ሰፈር የነበረ ኮሮማሽ የተባለው ቦታ በሸና አካባቢ ለመያዝ በጀመሩበት ጊዜ ብርቱ ተቃውሞ ከአርበኞች ወገን ገጥሞቸው ነበረ፤ ጣሊያኖች ግን ብዙ ትግል ተቋቁመው ይዞታቸውን ሊያቆዩ ችሏል፡፡

## የመንዲዳ ውጊያ

የኢትዮጵያ አርበኞች የበላይ ጠቅላይ አዛዥ ሳይኖራቸው ሻምበሎቻቸው በሀገር ፍቅር ተነሳስተው አዲስ አበባ በጠላት ከተያዘች ማግሥት ጀምሮ እንቅስቃሴያቸው በጣም አስገራሚ ነበረ፡፡ ሆኖም በመሐላቸው ጀግኖች እንደመኖራቸው መጠን ከሐዲዮች የእንቅስቃሴያቸው መረጃ ለጠላት የሚያስተላልፉ ነበራቸው፡፡ የደሴ አዲስ አበባ መንገድ ፀጥታ ኃላፊ የነበረው ኮሎኔል ትራኪያ ዘደነባ፣ዋዩ፣ ጨርቆስ የሰፈሩ አርበኞች በመንዲዳ የፈረንሳይ ላዛሪስት ሚሲዮንን ለማጥቃት አርበኞች ሃሳብ እንዳላቸው ሜይ 3 ቀን መረጃ ይደርሰዋል፡፡ የአርበኞች ዓላማም የኢጣሊያ ወታደሮችን ለውጊያ በመጋበዝ ጥቃታቸው እስከ ደብረብርሃን ለመዝለቅ እንደነበረ መረጃ ይደርሰዋል፡፡ ኮሎኔሉ አርበኞች ሳይቀድሙት በመቅደም ሜይ 31 ቀን በአንድ ኮሎኔል የሚመሩ ሁለት ባታሊዮን ጦር ወደ መንዲዳ ይልካል፤ ከዚያም አርበኞ ወደ ሰፈሩበት ወደ ዋዩ ሄደው ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ይከፍታሉ፤ጁን 2 ተጨማሪ ሌላ ኮሎኔል አንድ ባታሊዮን በመምራት ተልኮ በመንገድ ትኩስ ስለገጠመው በማግሥቱ ጁን 3 ብቻ ቦታው ሊደርስ ችሉዋል፡፡ ጁን 6 ጣሊያኖች ተልእኮዋቸውን ፈጽመው ወደ ጦር ሰፈራቸው ወደ ደብረብርሃን ሲመለሱ ሚሲዮናውያንም መንዲዳን ለቀው ወደ ደብረብርሃን መጡ፡፡ አርበኞች 1000 እግረኛ 400 ፈረሰኛ ተዋጊ ነበራቸው፡፡ በውጊያው በጣሊያኖች ግምት አርበኞች 100 ወታደር ሞተውባቸዋል፡፡ ከጣሊያኖች ወገን የሞቱ 4 የቆሰሉ 36 ነበሩ ሁሉም ኢንዲጆኒ፡፡

[1] Governo Generale, AOI ibd VI Testo p 90

# የአንኮበር ውጊያ

የመንዲዳ ውጊያ በደብረብርሃን የነበረው የጣሊያኖች ጦር ሰፈር በአርበኞች ጥቃት እንዳይደርስበት አስወግዷል። ለጣሊያኖች የደረሱዋቸው መረጃዎች አርበኞች መንዲዳንና ደብረብርሃንን ከወረሩ በኋላ ወደ አንኮበር በማምራት እዛው የነበረ የኢጣሊያ ጦር አነስተኛ ስለነበረ የጦር ሰፈሩን ለመቆጣጠር እቅድ ነበራቸው። አሁንም ሳይቀደሙ የአንኮበር ጦር ሰፈራቸው ለማጠናከር አንድ ባታሊዮን ላኩ። ከዚህም በተጨማሪ ጁን 7 ሌላ ባታሊዮን በላኩበት ጊዜ 400 የተገመቱ የኢትዮጵያ አርበኞች በየመንገዱ ተኩስ ይከፍቱባቸው ስለነበር፣ በጦር አሬዮፕላን እየተረዱ እየተከላከሉ አንኮበር ሊገቡ ችሏል። አንኮበር በነበረው የኢጣሊያ ጦር ሰፈርም ላይ በተደጋጋሚ ተኩስ ይከፈትበት ነበረ። በውጊያው አርበኞች 200 ሰዎች ሞቶባቸዋል። ከጣሊያኖች ወገን የሞቱ 11 የቆሰሉ 19 ነበሩ ሁሉም ኢንዲጂኒ።

## የሸዋ ወታደራዊ መከላከያ ኃይል

ለአዲስ አበባ የሰንቅ አቅርቦት አሳሳቢነት በመገንዘብ ጣሊያኖች በብዙ የአስተዳደር ክልሎች ይታዘዙ የነበሩ የአዲስ አበባ ዙሪያ ክፍሎች ስፋት ያለው መሬት የሚሸፍን የሸዋ መከላከያ ኃይል በሚል ስያሜ አቋቋሙ።

## በጁላይ ወር

ከጁን 2 ጀምሮ በክረምት ወራት ምክንያት ያልተያዙ መሬቶችን ለመቆጣጠር ማድረግ የነበረባቸው እንቅስቃሴ ስለተቋረጠ፣ ከአርበኞች ጥቃት ለመከላከል ብቻ ተወስነው ነበረ። በዚሁ መሠረት በሽቦ የታጠሩ፣ ሙሉ ትጥቅና ስንቅ ያላቸው የመከላከያ ጦር ሰፈሮች በአዲስ አበባ ዙሪያ ለእያንዳንዱ ጦር ሰፈር አንድ ባታሊዮን በመመደብ ተቋቋሙ። ሆኖም ጁላይ 14 ቀን የሸዋ መከላከያ ልዩ እዝ ፈርሶ የአዲስ አበባ ጸጥታ ለመከላከል በማእከላዊ መንግሥት ስር እንዲሆን እንደገና ተዋቀረ።[1]

## ምዕራብ ሸዋ

በወሊሶ የነበረው የጦር ሰፈር ተጠናከረዋል። ጨሊሞ ሰፍሮ የነበረው የኤርትራ ባታሊዮን ለባንዳዎች ለቆ ወደ አዲስ ዓለም እንዲዛወር በመደረጉ፣ ባንዳዎች ከአምቦ ከመጡ አርበኞች ጥቃት ደርሶባቸው፣ ጦር ሰፈሩ በአርበኞች እጅ ወድቀዋል። ሌሎች ወደ አዲስ ዓለም ለዝውውር ይጓዙ የነበሩ የኢጣሊያ አስካሪ ወታደሮች በመንገድ ተኩስ ተከፍቶባቸዋል።

## ወልመራ

ከወሊታና አዲስ አበባ መሐከል ያለው መንገድ ጣሊያኖች 200 አርበኞች ታይቷል የሚል መረጃ ስለደረሰባቸው፣ ወሊታ ጦር ሰፈር የነበረውና

[1] Governo Generale AOI ibd p 60



ከአዲስ አበባ የተላኩ ወታደሮች ጁላይ 24 በአርበኞች ላይ ተኩስ ከፍተው የተገደሉባቸውና የቆሰሉባቸው 18 ነበሩ ብሏል፣ ከአርበኞች ወገን የደረሰው ጉዳት አልተገለጸም።

## በባቡር ሐዲድ ውጊያዎች

በባቡር ሐዲድ አርበኞች አደጋ እንዳይጥሉ ለመከላከል ጣሊያኖች የታጠቁ ባቡሮች አቋቁመው ነበር። ጣሊያኖች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ቢያደርጉም አርበኞች አዲስ አበባ ለጣሊያኖች ስንቅና ትጥቅ እንዳይደርስ ለማድረግ የሐዲድ ብሎኖችን እያወለቁ ይወስዱ ነበር፣ የስልክ ሽቦችን፣ የውሃ መስመሮችን ያቋርጡ ነበር። ጁላይ 6 አርበኞች ከሞጆ አቃቂ ያሉ ቦታዎች ሁሉ መገናኛዎች እንዲቋረጡ አድርገው በኢጣሊያ ወታደሮች ጦር ሰፈሮች ላይ ጥቃት ፈጸሙ። አድአ ላይ አንድ ባቡር ሐዲድ ወልቆ በመነሳቱ መንገዱን ስቶ ወጣ። በባቡር ውስጥ ከወታደሮች ሌላ ሲቪሎች ሴቶችና ሕፃናት ጣሊያኖች ነበሩ፣ አንድ ጀኔራልም ነበረ። አርበኞቹ ባቡሩን ከበው ተኩስ ከፈቱበት፣ ጣሊያኖች በጀኔራሉ እየተመሩ ተከላከሉ፣ ጣሊያኖች እርዳታ ስለደረሰላቸው ሊከላከሉ ችሏል። የአርበኞቹ ጥቃት ስለተቃለለ ማታ በ2 ሰዓት የተወሰኑ ጣሊያኖች ወደ አዲስ አበባ አመሩ ሌሊት በጭለማ የባቡር ሐዲድ ተከትለው ከሔዱ በኋላ መንገዱ ጠፋባቸው፣ ሊነጋ ዱከም ሲደርሱ በአርበኞች እንደተከበቡ አወቁ፣ ጉድጓድ ውስጥ ገብተው ለመከላከል ሞክረው ከሞት እንደማይተርፉ ስላወቁ አለቃቸው Viva Il Re Viva Il Duce እያሉ እንዲሞቱ ምክር ሰጣቸው። ከመስመር የወጣ ባቡሩን ለማንሳት ሐዲዱን ለመጠገን ከአዲስ አበባ የተላከ ሌላ ባቡር ጣሊያኖች የተገደሉበት ቦታ ዱከም ሲደርስ ባጋጣሚ አንድ ሸሽቶ ያመለጠ ጣሊያን እና አንድ በከባድ የቆሰለ ሌላ ጣሊያን ስላገኘ ከእነሱ ስለ ተገደሉ ሌሎች ጣሊያኖች ሁኔታ ታወቀ። በአድአ የተከበቡ ጣሊያኖች ከሞጆ እርዳታ ስለተላከላቸው ከአደጋ ሊድኑ ችሏል። የሞቱ ጣሊያኖች 4 የጦር መኮንኖች 64 ተራ ወታደሮች የቆሰሉ 3 የጦር መኮንኖች 34 ተራ ወታደሮች ነበሩ። በአድአ ጥቃት የፈጸሙ የኢትዮጵያ አርበኞች ቁጥራቸው 2000 እንደነበሩ ተገምቷል፣ መሪዎቻቸው ማን እንደነበሩ አልተገለጸም።

ቦታውን የሚጠብቁ ከድሬዳዋና ከአዲስ አበባ ተጨማሪ ወታደሮች ተልከዋል። ከድሬዳዋ የተላኩ ጁላይ 8 ከናዝሬት እንዳለፉ ሐዲዱ ተበላሽቶ ስላገኙት ከአርበኞችም ተኩስ ስለተከፈተባቸው ለ3 ሰዓት ከተታኮሱ በኋላ ወደ ናዝሬት መመለስ ግድ ሆኖባቸዋል። በሌላ መጓጓዣ (በመኪና) በማግስቱ ጉዞዋቸውን ቀጥለዋል። ለማግሥቱ ከድሬዳዋ ሌላ ግማሽ ባታሊዮን ጦር ወደ ስፍራው ተላከ።

ከአዲስ አበባ ጁላይ 7 ሁለት ሻለቃ ወታደሮች ተላኩ፣ ነገር ግን መንገዱ ዝግ ሆኖ ስላገኙት አርበኞችም ተኩስ ስለከፈቱባቸው ጉዞዋቸውን መቀጠል ሳይችሉ ቀርተው አቃቂ ሲደርሱ ቆሙ። ከሰዓት በኋላ ከአዲስ አበባ የተነሳ በጀኔራል ጋሊና የሚመራ አልፏቸው በመሄድ ዱከም ሲደርስ የተገደሉ የጣሊያኖች ሬሳ አግኝቶ እንዲቀበሩ አድርጎ ጁላይ 8 ጉዞውን ወደ ሞጆ ከመቀጠሉ በፊት በ10 ኪሎ ሜትር ከመንገድ ግራና ቀኝ የሚገኙ መንደርተኞች ላይ ለጣሊያኖች ግድያ ተባብራችኋል በማለት የበቀል ጭፍጨፋ ፈጽሟል።

ጁላይ 9 ቀን የጦር አሬዮፕላኖች ከድሬዳዋና ከአዲስ አበባ እየተነሱ አርበኞች አሉበት የተባሉ ቦታዎችን በቦምብ ሲደበድቡ ውለዋል። ጁላይ 10

ጄኔራል ጋሊና ከሞጆ እስከ አዳማ ያለው ቦታ ሲያስስ ውለዋል፡፡ ጁላይ 12 የባቡር ሐዲድ ተጠግኖ ሥራውን ቀጥለዋል፡፡ ጁላይ 13 ግራዚያኒ ጄኔራል ጋሊና በሕዝቡ ላይ ጭፍጨፋ በማድረጉ ከፍተኛ አድናቆትና ምስጋና ሲገልጽለት "ክቡር የመንግሥት መሪ እኔ በሰጡሁህ መመሪያ የእሱ ትእዛዝ አክብረህ ምንም ርህራሄ ሳታደርግ ሁሉን በውምብድና የተካፈሉ በማውደምህ አድናቆቴን ያቀርብልሃል፡፡ በዚሁ ተግባር ቀጥል፣ የባቡር ሐድዲ ደህንነት ለማረጋገጥ የሚቻለው በአካባቢው የሚገኙ ሁሉ በማጥፋት ነው" የሚል ቴሌግራም በማስተላለፍ ነው፡፡ ጄኔራል ጋሊና ከአቃቂ አዳማ ያለው መሬት በሙሉ የበላይ ኃላፊ እንዲሆን ተሰጠው፡፡ ጄኔራል ጋሊና የሚያዛቸው 1482 ወታደሮች 492 የጋማ ከብቶች 41 ቀላልና ከባድ መትረየሶች 2 መድፎች ነበሩት፣ ሽፍቶች መሸገውበታል ወደ ተባለው ጁላይ 20 ቀን ከሞጆ ተነስቶ ወደ ደቦ ኪዳዮና ቦካን ተራራ አሰሳ ለማድረግ ሞከረ፤ ሆኖም ተኩስ ስለተከፈተበት በጨበጣ ውጊያ ብቻ በመንገዱ ለማለፍ ችሏል፣ የሸንኮራ ነዋሪዎች ሽፍቶች ተብለው ተጨፈጨፉ፡፡ ሌሊቱ በአካባቢው በአደረበት ጊዜ በሕዝቡ የሚደገፉ በአርበኞች ጥቃት ደረሰበት ጁላይ 21 በየረርና ቡልጋ ብዛት ያላቸው አርበኞች የሰፈሩ መሆናቸው መረጃ ስለደረሰው የተሰጠውም [illegible] የባቡር ሐዲድ ፀጥታ ለማስከበር ብቻ በመሆኑ፣ ወደ የረርና ቡልጋ ለሊት ጊዜ ይተሳሰፍ ብሎ ወደ ሞጆ ተመለሰ፣ የባቡር ሐዲድ በአደጋ ላይ ስለሚገኝ ወደ ሞጆ እንዲመለስ የሚል ትእዛዝም ደረሰው፡፡ እግረ መንገዱ ወደ ሞጆ ሲመለስ ከአርበኞች ጥቃት ይደርስበት ነበር፣ በጦር አሬዮፕላኖች እየተረዳ ብቻ እየተከላከለ ጁላይ 23 ወደ ሞጆ ሊመለስ ችሏል፡፡ የደረሰበት ጉዳት የሞቱ 4 የቆሰሉ 24 ነበሩ፡፡ ጣሊያኖች የባቡር ሐዲድ መስመር የተጠናከረ መከላከያ እንዲኖረው አደረጉ በየ 60 ኪሎ ሜትር አንድ ባታሊዮን ጦር እንዲመደብበት አደረጉ፡፡

## ሸዋ ሰሜን ምሥራቅ

በተደጋጋሚ አዲስ አበባ ከአርበኞች ጥቃት እንደሚደርስባትና እንደምትወረር የሚሉ ወሬዎች ይሰሙ ስለነበረ በኰሎኔል ትራኪያ የሚመሩ ሁለት ባታሊዮኖች ከሰሜን ሸዋ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደረገ፡፡ የዐመፁ መሪ ደጃዝማች አበራ እንደሆነም ተወርቷል፡፡ ዓላማቸውም በመጀመሪያ የኢጣሊያ ጦር ሰፈሮች በቅርብና ሩቅ የሚገኙትን ማጥቃት ቀጥሎም ለጣሊያኖች እንቅስቃሴ የሚያግዳቸው የክረምት ወራት ወቅት በመጠቀም ዋና ከተማዋን መውረር ነበረ፡፡ በክረምት ጭቃ ምክንያት ከደሴ አዲስ አበባ ያለው መንገድ ለጦር ሰፈሮች በቂ ስንቅ ሳይታደላቸው ለትራፊክ ዝግ ሆኖ ነበር፡፡ ጁላይ 4 ወደ ደብረብርሃን ይጓዝ የነበረው አንድ የኢጣሊያ ጦር ወርቄ ሚካኤል በተባለው ቦታ ከአርበኞች ጥቃት ደርሶባቸው ስለተከበቡ ከበባውን ለማስለቀቅ ለእርዳታ ባለተሽከርካሪ ሌላ ባታሊዮን ወደ ስፍራው ሲላክ፣ የተከበበ ጦርም እርዳታ መላኩ ሲያውቅ ራሱ የከበቡትን አርበኞች ለማባረር ችሏል፡፡

ጁላይ 19 በሁሉ ጦር ሰፈሮች ጥቃት ከአርበኞች ይደርሳል ተብሎ እንደተወራ በተግባር ለማዋል ተጀምሮ ነበር፡፡ በደብረብርሃን አካባቢ ጫጫ ወንዝ ላይ አርበኞች ተሰባስበው ስለታዩ የጦር አሬዮፕላኖች ባደረሱባቸው ጉዳት ብቻ ሊበታተኑ ችሏል፡፡ አርበኞች ጁላይ 19 እና 20 በአንኮበር ጦር ሰፈር ጥቃት ለማድረስ ሞከረው የኢጣሊያ ወታደሮች ስለተከላከሉ መልሰዋቸዋል፡፡ ጁላይ 20 ኮርማሽ ላይ የሚገኘው የኢጣሊያ ጦር ሰፈር አርበኞች ወረው ለመያዝ ለ 3 ቀን የቆየው ተኩስ ተካሂዷል፡፡ የኢጣሊያ



ወታደሮች በመከላከል ድነዋል፡፡ አንኮበር የነበረው የኢጣሊያ ጦር ከጦር ሰፈሩ ወጥቶ በአካባቢው የነበረው የአርበኞች ተዋጊዎች ከቦ እልቂት ማድረስ ችሏል፡፡ በሸዋና ኮርማሽ የነበረው የኢጣሊያ ጦር ሰፈር ግን ዕድሉ ብዙ አልቀናውም፣ በ2000 አርበኞች ከባድ ጥቃት ስለደረሰበት ጉዳት ደርሶበት ለማፈግፈግ ተገዶ ነበር፣ በጦር አሬዮፕላኖች እርዳታ ብቻ ለመከላከል ችሏል፡፡ ጁላይ 21 እና 22 5ኛ, 10ኛና 4ኛ ባታሊዮኖች ለእርዳታ ስለተላኩ ብቻ በአካባቢው ሰላም ሊሰፍን ችሏል፡፡ ወደ ስፍረው ተልከው የነበሩ መኪናዎች ግግሾቹ ተበላሽተው ግግሾቹ በጭቃ ተውጠው በመንገድ ቀሩ፣ የአርበኞች ጥቃትም በሸዋ ቀንሶ ወደ አዲስ አበባ ጥቃቱን በማተኮር ቀጠለ፡፡ በአርበኞች የደረሰው ጉዳት በጦር ሜዳ የሞቱ 709 ተማርከው የተገደሉ 110 በኮርማሽ ጦር ሰፈር ለተገደሉ ሙሶሊኒ ኒሻን ሰጥተዋል፡፡ በተገኙ ማስረጃዎች መሠረት በሰሜን ሸዋ የተደረጉ የአርበኞች ጥቃት የጣሊያኖች ኃይል ከአዲስ አበባ ውጭ እንዲሰማሩ በማድረግ አዲስ አበባን ለመውረር የታለመ ነበረ፣ ለዚሁም ብዙ የአርበኞች መሪዎች ከደጃዝማች አበራ ካሣ ስምምነት ፈጥረው እንደነበረ ታውቋል፡፡ በጣሊያኖች በኩል የአርበኞች ተደጋጋሚ ጥቃቶች ከመከላከል በስተቀር በአርበኞች ጥቃት ለመፈጸም ታግደው እንደነበረ አምነዋል፡፡ ሆኖም የተቃጣባቸው ጥቃቶች ሁሉ ለማክሸፍ ችለናል ብሏል፣ አርበኞች እና ደጋፊዎቻቸው ሲደመሰሱ፣ ታማኝ ሆነው ከጣሊያኖች ጉን የተሰለፉም ኒሻን አግኝቷል ብሏል፡፡ የዚህ ዓይነት ውጊዎች እንዳይከሰቱ ግራዚያኒ ከደሴ አዲስ አበባ መንገድ በክረምት ወራት በሙሉ ለትራፊክ ዝግ እንዲሆን ትእዛዝ አስተላልፈዋል፣ የሚንቀሳቀሱ መኪናዎች በአጃቢዎች ብቻ እንዲጓዙ ተደርገዋል፡፡ የመኪና መንገድ በመቋረጡ የጦር አሬዮፕላኖች ስንቅ ያመላልሱ ነበር፡፡

## የአዲስ አበባ የመከላከያ ሁኔታ

ዋናው አዝ የፒያሳ አዝ ይባላል፡፡ የመከላከያ ጣቢያዎችና ምሽጎች ተቋቁሟል፣ የማስጠንቀቂያ ደወሎች ተቋቁሟል፡፡ ከተማዋ ለ3 ተከፍላለች፣ እያንዳንዱ ክፍል ብዙ ንኡስ ክፍል አለው፡፡ ወደ ከተሟ በሚያስገቡ መንገዶች በየ 50-100 ኪሎ ሜትር የወታደር ሰፈር ተቋቁሟል፡፡ በከተማ ዙሪያ የጦር ሰፈሮችና ምሽጎች ተቋቁሟል፡፡ በከተሟ ዋና ክፍሎች የወታደር የመሰብሰብ የመከላከያ ጦር ተሰርቷል፡፡ ተንቀሳቃሽ የወታደር ኃይል በከተሟ በሙሉ ተመድበዋል፡፡ በከተማ ዙሪያ የተሰሩ የወታደር ሰፈሮች ባንድ ቦታ ብቻ መቀመጥ መወሰን የለባቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ገጠር እየሄዱ አሰሳ ማድረግ የመንግሥት ኃይል ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከተማዋ ለምሥራቅ፣ ምዕራብ ደቡብ ተብላ ነበረ የተከፈለችው የፖሊስ ኃይል መደበኛና ልዩ የፖሊስ ኃይል ነበረው፡፡ ልዩ የፖሊስ ኃይል የሚንቀሳቀሰው የማስጠንቀቂያ ደወል ሲሰማ ነበር፡፡ በከተሟ ዙሪያ በየ5-10 ኪሎ ሜትር የፖሊስ ኃይል ተቋቁሟል፡፡ የሙከራ ደወል እየተደወለ ልምምድ በየጊዜው ይደረግ ነበር፡፡ ለአማራ መንግሥት በአባይ በኩል ደጃዝማች አበራን ለማስፈራራት ጭምር ወደ አዲስ አበባ ወታደር ለመላክ ዝግጁ እንዲሆን ትእዛዝ ተሰጥቶታል፡፡ መድፎች በየቦታው በተጠንቀቅ ተተክለዋል፡፡ የአሬዮፕላን ማረፊያ እና ከእንግሊዝ ኤምባሲ በላይ በእንጦጦ መከላከያ ምሽጎች ተሰርቷል፡፡ ወደ አዲስ አበባ የሚያስገቡ መንገዶች ፍተሻ ያለማቋረጥ በፈረሰኞች ጭምር ይካሄድ ነበር፡፡ ከሐረር ታንኮች ወደ አዲስ አበባ እንዲላኩ ተደርገዋል፡፡ እንደዚሁም ተሾረ ዲቪዚዮን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ተደርገዋል፡፡ በኩረምና ደሴ ሙሐል ቀርቶ የነበረ በጄኔራል ተሲቶሬ የሚመራ የባባውዳ ዲቪዚዮን 10.000

የወታደር ብዛት የነበረው ከግንቦት 16 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ድረስ ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ ተደርገዋል። በየጊዜው ለልፍ በማድረግ ሕዝቡ ኢጣሊያ ኃይለኛ የመከላከያ አቅም እንዳላት ለማሳየት ይደረግ ነበር። ጣሊያኖች የነበራቸው ዋና ስጋት አርበኞች በአንድ አዛዥ እንዳይጠቃለሉ ነበረ። በመጀመሪያ የጠረጠሩት ራስ እምሩ ነበሩ፤ አሁን ደግሞ የሚጠረጥሩት ደጃዝማች አበራ ካሣ ነበሩ። በዚሁ የተነሳ በከሐዲው ራስ ኃይሉ ተጠቅመው ደጃዝማች አበራ እንዲገደል አድርገዋል።

## የሙሉ ውጊያ

በእንጦጦ መስመር በሙሉ የሰፈሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ሰኔ 29,1936 ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡና በምትካቸው ባንዳ እንዲሰፍሩበት በማሰብ በቀረበው ሃሳብ ስለተስማሙበት ሐምሌ 10 ወደ አዲስ አበባ ጉዞውን ሲጀምሩ ከጅርባውና ከጉኑ የደጃዝማች አበራ ካሣ ወታደሮች ናቸው የተባሉ ቁጥራቸው 500 (አምስት መቶ) የሚደርስ ወታደሮች በጣሊያኖች ላይ ተኩስ ከፈቱባቸው። ጣሊያኖች ቦታቸውን ይዘው ሙሉ ቀን ተታኩሱ፤ በማግስቱም ሙሉ ቀን ውጊያው ቀጥሎ ዋለ። አርበኞች ጥቃታቸው እየጨመረ ነበር፤ ግታ ግን በሙሉማ ተጠቅመው ኃይለኛ ዝናብም ይጥል ስለነበረ ጣሊያኖች ከከበባው አምልጠው አዲስ አበባ ገቡ፤ ከአዲስ አበባም አንድ ባታሊዮን የኢንጂነር ጦር ለእርዳታ ተልኮላቸው ነበር። በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት የሞተ አንድ የጦር መኮንን 29 ወታደሮች የቆሰሉ 2 የጦር መኮንኖች 44 ወታደሮች የጠፉ 3 ከአርበኞች የሞቱ ከ300 እስከ 400 ተገምቷል።

## የአዲስ አበባ ውጊያ

በተቀነባበረ በብዙ አቅጣጫዎች አዲስ አበባን ወረው ለመያዝ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ይወራ የነበረ ስላልተሳካ አሁን በአሬዮፕላን ግረፊያ ብቻ በደጃዝማች ባልቻ ለመጀመር ተዘጋጅተዋል። ከአሬዮፕላን ጣቢያ የሚጠብቁ የኢጣሊያ ወታደሮች ከቦታው ለቀው ወደ ሌላ እንዲሰግሩ ለማድረግ ለጥቃታቸው እንዲመቻቸው የማስመሰል ጥቃት በባቡር ጣቢያ ለማድረግ ሞክረው እዛው ለጥበቃ የተሰግሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ስለከሸፈ እቅዳቸው ሳይሰራላቸው ቀርቷል።

ለጣሊያኖች በደረሱዋቸው መረጃዎች ደጃዝማች አበራ አዲስ ወታደሮችን በመመልመል ላይ እንደሚገኝ ወደ እንጦጦም እንደ ተጠጋ ያመለክታሉ። ከአዲስ ዓለም ዘስተሰሜን የረር አካባቢ፤ ሶዶ ጉራጌ፤ ቱሪ፤ ዋጫጫ ተራራ፤ አቃቂ፤ ሰንዳፊ ብዙ አርበኞች እንደሚገኙ የሚደርሱ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከተማዋን ለማጥቃት የተዘጋጁ አርበኞች የሚከተሉ ናቸው። በሰሜን አበራና አስፋወሰን ካሣ ወንድማማቾች አፈንጉሥ አረጋዊ መስፍን ስለሺ ወዘተ.. ከምዕራብ አፈ ንጉሥ አጥናፌ ወልደፃድቅና ሌሎችም ከደቡብ ከዝቋላ ቀኛዝማች በቀለ ወልደገብርኤል ከምሥራቅ ከሸንኩራ ደጃዝማች ፍቅረማርያም ብጅሮንድ ለጥይበሉ ወዘተ የአርበኞች የሰው ብዛት ከ8 እስከ 10.000 ሺህ የሚገመቱ ነበሩ። ጋሻና እግራ ቅራኔያቸው ትተው የተስማሙ ይመስላሉ። ደጃዝማች አበራ በአዲስ አበባ ከሚገኙ ከውጭ ሀገሮች ወኪሎች የቀድሞ ኢምባሲዮች ግንኙነት ፈጥር ነበር። የእስጊ ሁኔታ ዜናዎች ይሰራጩ ነበር። የአርበኞች እቅድ በመሪ ደረጃ ይታወቅ ነበር። ደጃዝማች አበራ ከአዲስ አበባ ሰሜን ምዕራብና ሰሜን ምሥራቅ በሁለት አቅጣጫዎች



ጥቃት በመፈጸም ሁለቱ ወረራዎች በታላቁ በተመንገሥት ይገናኙ ነበር፤ ጥቂቶቹም በእንጦጦ ከኢጣሊያ ወታደሮች ውጊያ እያደረጉ ይቆዩ ነበር። አፈንጉሥ አጥናፌና ደጃዝማች ባልቻ ከወጫጫ ተራራና ከቱሪ የአሬዮፕላን ጣቢያ ወረው እንዲይዙ ተመድበው ነበር። ደጃዝማች ፍቅረማርያም ለዚሁ ተግባር ከምሥራቅና ከደቡብ ምሥራቅ ለእርዳታ ይሰግራ ነበር። ለሐምሌ 20 እንዲሆን ተወስኖ የነበረ ወረራ እርጥ ትብብር ባለማድረጋቸው ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ ተደርጎ የክረምት ወቅት እስከሚብስ ጣሊያኖች መንቀሳቀስ በማይችሉበት ጊዜ፤ አሬዮፕላን ጣቢያ አገልግሎት በማይሰጥበት ጊዜ ይጠባበቁ ነበር። ሐምሌ 16 ግራዚያኒ በጀነራል ተሲቶሬ የሚመሩ አራት የኤርትራ ባታሊዮኖች በከተማዋ ዙሪያ ከሙሉ ትጥቃቸው እንዲሰግሩና ለሐምሌ 20 ዝግጁ ሆነው እንዲቀመጡ ለጀነራል ተሲቶሬ ትእዛዝ ይሰጠዋል። በዚሁ ሐምሌ 20 የኤርትራ ባታሊዮኖች በሰልፍ ሆነው በግራዚያኒ ተጐብኝቷል። የኤርትራ ባታሊዮኖች VII, VIII, XVI, XX የተባሉ አራት ነበሩ። የአዲስ አበባ መከላከያ ዝግጅት በግራዚያኒ አገላለጥ።

አዲስ አበባ መከላከያ ለሁለት ባለ አንድ ብሪጌድ ወይንም ለአራት ባለ አንድ ሬጂመንት የተከፈለ ነው። የአዲስ አበባ ዙሪያ በ9 ጦር ሰፈር ጣቢያዎች የታጠረ ነው። ለእያንዳንዱ ጣቢያ አንድ ባታሊዮን ጦር ተመድቦዋል፤ በሽቦ ያልታጠረ አቃው በሙሉ ስላልደረሰ ነው። በተጨማሪ 4 ተንቀሳቃሽ ጣቢያዎች አሉ።

### የአዲስ አበባ (ፒያግ) ጦር አዛዥ ስለ መከላከያ የሰጠው መግለጫ

1. አዲስ አበባን ለመከላከል አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም ሀ/ የዙሪያ ስፋት (ርዝመት) ብዙ በመሆኑ (39 ኪሎ ሜትር) ለ/ ቦታው ጫካ በመሆኑ
2. አርበኞች ወደ ከተማ ሰርጎ እንዳይገቡ በተለይ በሌሊት ለመከላከል አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም ከአንድ ወታደር ጣሊያን ወደ ሌላው ያለው ርቀት ከ3 እስከ 4 ኪሎ ሜትር ነው። ስለዚህ ከመንገድ ውጭ የሚገባና የሚወጣ ሰው ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ነው።
3. አርበኞች ሳይታዩ ተደብቀው ከመንገድ ውጭ ወደ ከተማዋ መግባት ይችላሉ።
4. የመከላከያ ጣቢያዎች ባሉበት ወደ ከተማ መግባት ከሞከሩ በመከላከያ ሠራዊት ተኩስ ያልቃሉ።

በሸዋና በባቡር ሐዲድ ያለው ሁኔታ ግራዚያኒ ሐምሌ 22 ቀን በሚከተለው ቴሌግራም አብራርቶ ገልጾታል። ባለፉት ጥቂት ቀናት የአርበኞች (ሽፍቶች) እንቅስቃሴ ከባቡር ሐዲድ ወደ ደብረሲና ደብረብርሃን ሸዋ አዲስ አበባ መንገድ መስመር ተዛውረዋል። እንደዚሁም በአዲስ ዓለም ወሊታ መስመር እስጊ እንቅስቃሴ ታይቷል። ይህ ሁሉ ፕላን ከሐበሻ ሐንጕል የመነጨ አይመስልም። እቅዱ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉት የመከላከያ ጣቢያዎች ለማውደምና ከተማዋን ለመቆጣጠር ነው።

ከዚህ ቀጥሎ የዕለቱ ሁኔታ እገልጻለሁ፦

1ኛ. መሐል አዲስ አበባ (ፒያግ) ምንም ነገር የለም።
2ኛ. ምዕራባዊ አዲስ አበባ በደረሱን መረጃዎች አፈ ንጉሥ አጥናፌ አዲስ ዓለምን ለማጥቃት ተነቃንቀዋል። ለማንኛውም አስፈላጊ ጥንቃቄ አድርገናል።
3ኛ. ሰሜን ምሥራቅ ክፍል የኮርማሽ ጦር ሰፈር ትናንት ቀን 6 ጊዜ ከአርበኞች ጥቃት ደርሶበት 6ቱን ጊዜ ተከላከሉ መልሰዋል። የወታደሮች

እርዳታ ተልኮለታል ከ X ባታሊዮን፡፡ ወደ ምኒልክ ግቢ ገብተው የነበሩ ሽፍቶች (አርበኞች) እንዲባረሩ ተደርጎ ነበር፣ ተመልሰው ግን ቦታውን ተቆጣጥረውታል፡፡ ስንቅ የሚነ ኮንቮይ ወደ ደብረብርሃን ያመራ የነበረ ዛሬ ተኩስ ተከፍቶበታል ቁጥራቸው 1000 ከሚደርሱ አርበኞች አጃቢዎች በሚገባ ተከላከለዋል፣ ሆኖም አሁንም በውጥረት ይገኛል፡፡ ከሸዋ የወታደር ኃይል እርዳታ ተልኮለታል፣ ሌላ የኤርትራ ባታሊዮን ባሬ ሌሊት በስፍራው ይደርሳል፡፡

4ኛ. ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ ጀነራል ጋሊና ከሸንኩራ ወደ ሞጆ በሚያመራበት ጊዜ ከአርበኞችና ከነዋሪዎች ገበሬዎች ተኩስ እየተከፈተበት ነበር፡፡ በተደረጉ ተኩሶች 5 አስካሪ ሞቷል 18 ቆስሏል፡፡ በየቦታው በገበሬዎች ላይ አስፈላጊው ቅጣት ተፈጽመዋል፡፡

5ኛ. ባቡር ሐዲድ አገልግሎት የታጠቁ ፋርጎኖች በመቋቋማቸው ስራው ቀጥሏል፣ በጂቡቲ 12 ሺህ ቶን ተከማችቷል፡፡

6ኛ. የጦር አሬዮፕላኖች የአየር ንብረትና የነዳጅ እጥረት ቢያጋጥማቸውም በምግብ ከመጣልና ስንቅ ከማቀበል አላቋረጡም፡፡

መረጃዎች እንደሚደርሱን ከሆነ በጁላይ መጨረሻ ሳምንት አርበኞች በአዲስ አበባ ወረራ ይፈጽማሉ፡፡

ራስ ኃይሉ ከደጃዝማች አበራ ካሣ ትናንት አንድ ደብዳቤ እንደደረሰው ደጃዝማች አበራ የአርበኞች እንቅስቃሴ መሪ መሆኑን አስተባብሎ በቅርብ ቀን ውስጥ እጁን ለጣሊያኖች እንደሚሰጥ ገልጧል፡፡ ትክክለኛ ሁኔታ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፣ ጊዜውን ጠብቀን ለማንኛውም ተዘጋጅተን እንገኛለን፡፡

ከተማዋን ከጠላት ለመከላከል ከተመደቡ 9 በዙሪያዋ የተቋቋሙ የወታደር ሰፈሮች ሌላ ተንቀሳቃሽ የፖሊስ ኃይል አደጋ ሲደርስ ደወል የሚያሰሙ ይኖራሉ፡፡ 50 አባላት ያላቸው በመኪና ሆነው ሌሊት በዋና ዋና መንገዶች ጥቃት ለደረሰበት ክፍል እርዳታ የሚሰጡ ይኖራሉ፡፡ የከተማ ዘበኞች የመሥሪያ ቤቶች ድርጅቶች ድንገት ጥቃት ቢደርሳቸው ራሳቸው መከላከል እንዲችሉ፡፡ ጁላይ 27 በቁጥር 217 (Allegati) በተደረገው ሪፖርት ሪጅም የወታደሮች አሰፋፈርና ዝርዝር ወጥቷል ወረራ በተፈጸመባቸው ቀናት ጁላይ 28-29-30 በተግባር በውጊያ ተካፋይ የነበሩ የኤርትራ ባታሊዮኖች VII VIII-XVI እና እንጦጦ ሰፍረው የነበሩ ባንዳዎች ብቻ ነበሩ፡፡

## ጁላይ 28 - 29- 30 ቀናት በአዲስ አበባ ከተማ

ከብዙ ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው የአርበኞች አዲስ አበባን የመውረር ዘመቻ ጁላይ 28 ቀን ጧት ተጀመረ፡፡ ከበላይ በሰቀ መንገድና ጉጃም መስመር ጉለሌ መንገድ መሐል የአርበኞች ሰርጎ ገቦች ይታያሉ፡፡ በዚሁ ጊዜ አስቀድሞ ተዘጋጅቶ በተጠንቀቅ የነበረ ወታደር ቢንቀሳቀስም ግንባር ተደም ሆኖ በተግባር በውጊያ ተዋናይ የነበረ ግን በጀነራል ተሲቶሬ (General Tessitore) የሚመራው VII እና VIII የኤርትራ ባታሊዮኖች እንደዚሁም በእንጦጦ የሰፈረው በኩሎኔል ዲ ማርቲኖ (Di Martino) የሚመራ ባንዳ ጦር ብቻ ነበረ፡፡ VII ተቃውሞ ሳያጋጥመው ሲጓዝ VIII ግን ከአርበኞች ተኩስ ተከፈተበት፣ ሆኖም ብዙ ሳይቆዩ መሸሽ ጀመሩ፡፡ በሚሸሹበት ጊዜ ከእንጦጦ ከባንዳዎችና ከጣሊያኖች መድፈኛ ክፍል አርበኞች እልቂት ደረሰባቸው፡፡ በግምት እንደሚታየው የአርበኞች ቁጥር 4000 ነበረ፡፡ በዚሁ ዓይነት በምዕራብ ሰርገው ገብተው የነበሩ አርበኞች አበቃ፡፡ XVI ባታሊዮን ኢንዲጂኒ በራስ መኩንን ቤት እንዲሰፍር ተደርጎ የነበረ ከእነሱ ውስጥ ወደ ሾላ ለአሰሳ ፈረሰኞች



የተላኩ 300 የሚገመቱ አርበኞች አጋጥሟቸው ምንም ተኩስ ሳይከፍቱ ወደ ራስ ጌታቸው ቤት በጫካ ሲጓዙ በአኪፒንቲ (Occhipinti) ከሚመራ ባንዳ ተጋጩ፡፡ በማግሥቱ ጁላይ 29 በደቡብ ምሥራቅ በራስ ጌታቸው ቤት አካባቢ ብዛት የነበራቸው አርበኞች ሰፍረውበት የነበረ ለመቋቋም VII እና VIII ባታሊዮን ኢንዲጂኒ ተሰማራ፡፡ በጫካ በተጠንቀቅ ሆነው ከነበሩ አርበኞች ሙሉ ቀን ውጊያ ሲካሄድ ዋለ፡፡ አርበኞች በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመሩ ነበሩ፣ የኤርትራ VII እና VIII ባታሊዮኖች ከሩቅ በመድፍ እርዳታ የሚያደርጉላቸው ጣሊያኖች ነበሩዋቸው፡፡

በወሊሶና በሞጆ የሚገኙ የኢጣሊያ ጦሮች አስፈላጊ ከሆነ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ተነግሮዋቸው ነበር፡፡ ጀነራል ጋሊና የኤርትራውያን የሚያዝዝ ከሞጆ ወደ አቃቂ እንዲጠጋ ተደረገ፡፡ ጁላይ 29 ከሰዓት የአርበኞች ኃይል ሳላልተዳከመ በሰሜን በጀነራል ተሲቶሬ የሚመሩ የኢንዲጂኒ የኤርትራ ወታደሮች በደቡብ በጀነራል ጋሊና (General Gallina) የሚመሩ የኢንዲጂኒ የኤርትራ ወታደሮች በአርበኞች ላይ ተባብረው ጥቃት እንዲፈጽሙ ተደረጉ፡፡ ጁላይ 30 ጧት አርበኞችን በወጥመድ አስገብተው ለመፍጀት ነበር፡፡ አርበኞች ግን የጣሊያኖች ዓላማ ስለተረዱ ሌሊት ቦታውን ለቆ ሄዱ፣ ስለዚህ የኢጣሊያ ጦር ከቀኑ 5 ሰዓት ከበባው ፈጽመው በቀበና ወንዝ ሲገናኙ ማንም ጠላት አላገኙም፡፡ በእነዚሁ ቀናት ሁሉ የጦር አሬዮፕላኖች ተካፋይነ ታቸው የጐላ ነበረ፡፡

በጣሊያኖች የተገደሉ 3 ጣሊያኖች 16 አስካሪ የቆሰሉ 3 የጦር መኩንኖች 2 ተራ ወታደሮች 62 አስካሪ ነበሩ፡፡ የአዲስ አበባ ወረራ በዚሁ ዓይነት ከሸፈ፡፡ በዚሁ ጊዜ ነበረ አቡነ ጴጥሮስ ከወራሪዎች አርበኞች ተቀላቅለው የተያዙና ከሌሎች አርበኞች አንድ ላይ የጦር ፍ/ቤት ቀርቧል ተብሎ በመርካቶ ገበያ ላይ የተረሸኑ፡፡

ስለ አቡነ ጴጥሮስ መረሸን ግራዚያኒ ጁላይ 29 ለቅኝ ግዛት ሚኒስትር በላከ ቴሌግራም ከቀኑ 11 ሰዓት ተኩል መረሸናቸውና ሕዝቡ በጭብጨባ ፍርዱን እንደተቀበለው ገልጾዋል፡፡ በዚሁ ቀን Allegati 224 በላከው ሌላ ቴሌግራም አቡነ ጴጥሮስ በራስ ኃይሉ ተይዘው ወዲያውኑ ለመንግሥት አስረከቧቸው ከደጃዝማች አበራና አስፋወሰን ተባባሪ መሆናቸውን ተከሰው አምነው ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት መረሸናቸውን ገልጧል፡፡ በAllegati ቁ 225 ባስተላለፈው ሌላ ቴሌግራም ከ4ቱ የኢትዮጵያ አቡኖች አንዱ የነበረው የአቡነ ጴጥሮስ መረሸሐ በሕዝቡ ድንጋጤ አሳድረዋል፤ ይኸም በማድረግ ያለው የኢጣሊያ ቆራጥ የፖለቲካ አመራር ነው ብሏል፡፡ ግራዚያኒ ጁላይ 31 ባስተላለፈው ሌላ ቴሌግራም በጁን 2 እስከ ጁላይ 31 በሸዋ የሞቱና የቆሰሉ የጦር መኩንኖች 12 የቆሰሉ 9 የጠፉ አንድ፣ የኢጣሊያ ተራ ወታደር የሞቱ 71 (ሰባ አንድ) የቆሰሉ 70 የጠፉ 9፡፡ ኢንዲጂኒ የሞቱ 104 የቆሰሉ 277 የጠፉ 1፡፡

## የኦገስትና የሴፕተምበር ወር ውጊያዎች

ለራስ ኃይሉ በወሊሶ መንገድ አሰሳና በአጥፊዎች ላይ አስፈላጊ ቅጣት ለመስጠት መምሪያ ተሰጥቶታል፡፡ ኦገስት 2 VI ባታሊዮን ኢንዲጂኒ ከከተማዋ በስተሰሜን ለአሰሳ በተሰማራበት ጊዜ ከአንድ አነስተኛ የአርበኞች ቡድን ተጋጭቶ ሁለት ሰዓት የቆየ ውጊያ በኋላ አርበኞች 24 ተገደሉባቸው ሸሽቷል፡፡ በዚሁ ጊዜ በአካባቢ መንደሮች ቤቶቹን በማቃጠል ቅጣት ፈጽሟል፡፡

ሕዝቡን ለማስፈራራት በከተማዋ የወታደራዊ ሰልፍ በየቀኑ ቀጥሏል፡፡ በከተማዋ ዙሪያ ያሉት የጦር ሰፈሮች ተጠናክረዋል፡፡ ይኸም ሆኖ በከተማዋ

ዙሪያ የአርበኞች ቡድኖች ሲዘዋወሩ ይታዩ ነበረ፡፡ በከተማዋ ደቡብ ምሥራቅ ደጃዝማች ባልቻ ሕዝቡን ይቀሰቅስ ነበረ፡፡ በአቃቂም በብጆርገድ ፍቅረሥላሴ የሚመሩ አርበኞች ይታዩ ነበር፡፡ ከመስቀል በዓል በፊት ጠቅላላ ጥቃት ይፈጸማል የሚል ፍራቻ በተግባር አልታየም፡፡

## በቁሪና በመጫጫ ተራራዎች አሰሳና ውጊያ

ኦገስት 26 ቀን VIII ባታሊዮን ኢንጂጀኒ ለአሰሳ ወደ ቁሪ ተራራ በተሰማሩበት ጊዜ 1000 የሚደርሱ የደጃዝማች ባልቻ ወታደሮች በተኩስ ስለተቀበሏቸው ውጊያ ተካሄደ፡፡ 1 የኢጣሊያ ጦር መኰንን ሲሞት 15 ኢንጂጀኒ ተገድለዋል፡፡ 40 ኢንጂጀኒም ስለቆሰሉባቸው ሸሽተው ወደ ጦር ሰፈራቸው ወደ ድር አሬዮፕላን ማረፊያ ለመመለስ ተገደዋል፡፡ እስከ ጦር ሰፈራቸው እያሳደዷቸው ይመጣሉ ብለው ፈርተው ነበር፡፡ ግራዚያኒ በማዘዙት ጀኔራል ጋሊና እንዲሁም ጀኔራል ተሲቶሬ ሰፈሩን በመድፍ ከደበደቡ በኋላ አሰሳ እንዲያካሂዱ አድርገዋል፡፡ ሴፕቴምበር 1 ቀን ወደ ቁሪ ተራራ የጣሊያ ወታደሮች ለአሰሳ ሲሄዱ አነስተኛ ተኩስ ብቻ ነው ያጋጠማቸው፣ 2 ኢንጂጀኒ ብቻ የቆሰሉ ነበሩ፡፡

## ምዕራብ አዲስ አበባ

ምንም እንቅስቃሴ ባያሳዩም ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ በአፈ ንጉሥ አጥናፌና በደጃዝማች ባልቻ የሚመሩ አርበኞች ሰፍረውበት ነበር፡፡ ጣሊያኖች በኦገስት ወር በኮሎኔል በሊ (Colonel Belly) አማካኝነት በአርበኞች ላይ አሰሳና ሕዝቡን በመስበክ ሥራ ያካሄዱ ስለነበረ ወደ ጣሊያኖች የሚገቡ ሽማግሌዎች ነበሩ፣ ሕዝቡም የኢጣሊያ ባንዲራ ይጠይቅ ነበር፡፡ በተለይ ብዛት ያለው ባንዳ በራስ ኃይሉ ተቋቁሞ በዚሁ መስመር ተሰማርቶ ነበር፡፡ ጣሊያኖች እምቦ ድረስ ቁጥጥራቸውን ለማስፋፋት ቢያስቡም የደጃዝማች ባልቻ አርበኞች ያሰጉዋቸው ስለነበረ በኦገስት ወር ወደፊት ለመሄድ አልደፈሩም ነበር፡፡ ሴፕቴምበር 13 በግራዝማች ኃይለሥላሴ ተክሉ ባንዳዎች አማካኝነት በ200 የራስ ኃይሉ ባንዳዎች እየተረዱ ወደ ፊት በመግፋት በመጫጫ ተራራ የደጃዝማች ባልቻ አርበኞችን ማጥቃት አካሄዱ፡፡ ደጃዝማች ባልቻም ከጥቂት ተከታዮቹ ጋራ ሸሽቶ አመለጠ፡፡ ከአሰሳ መልስ ባንዳዎች በሜታ አቦ ሕዝብ ላይ ከአርበኞች ጋራ ስለተባበረ የበቀል እርምጃ ወስደውባቸዋል፡፡ ሴፕቴምበር 15 ኮሎኔል በሊ ከራስ ኃይሉ ባንዳዎች ጋራ በመሆን ወደ አዲስ ዓለም ዘልቆ በመሄድ ሕዝቡን ይሰብክ ነበረ፡፡ ሴፕቴምበር 17 አፈ ንጉሥ አጥናፌ እጁን ለጣሊያኖች ሰጠ፡፡ ወደፊት ጉዞውን በመቀጠል የኮሎኔል በሊ ጦር ኦክቶበር 5 ከፍ ያለ አቀባበል ተደርጎለት እምቦ ገባ፡፡

## ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ ክፍል

ኦገስት 1 ቀን በአርባ የነበረው የኢጣሊያ ጦር ሰፈር ጥቃት ይደርስበታል፡፡ ኦገስት 5 ከአዋሽ ወደ አንኮበር የሰፈረው የኢጣሊያ ወታደር ስንቅ ለማመላለስ ጭነቱ በግመሎች ሆኖ አጃቢ ወታደሮች ለመመደብ ታስቦ ነበር፡፡ ነገር ግን እቅዱ ብዙ ችግር ስላጋጠመው፣ የጦሩ አባላትም ከቦታው



ስንቅ ለማግኘት እቅድ ስላወጣ፣ ለወታደሮች የሚሰጠው ስንቅም በመቀነሱ ችግሩ ሊፈታ ችሏል፡፡

በባቡር ሐዲድ አነስተኛ ግጭቶች በየጊዜው ያጋጥሙ ነበር፣ በተለይ በመልካ ጂሎ ብዙ አርበኞች ነበሩ፡፡ ከአዋሽ እስከ አቃቂ ያለው መስመር ጥቃት ይደርስበታል የሚሉ መረጃዎች ይደርሱ ነበር፡፡

ጀኔራል ተሲቶሬ ከአዋሽ አንኮበር በግመሎች የሚጓጓዝ ስንቅ ለማጀብ የተሰጠው መመሪያ አቋርጦ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ትእዛዝ ሲሰጠው እግረ መንገዱ በባቡር ሐዲድ አካባቢ በሚገኘው ሕዝብ ላይ ሥነ ሥርዓት ለማስከበር ቅጣት እየሰጠ እንዲመጣ በተጨማሪም በቦታው ስንቅ ማግኘት ይቻል እንደሆነ ጥናት እንዲያደርግ መመሪያ ስለተሰጠው፣ በዚሁ መሠረት ኦገስት 15 ከመልካ ድሉ ተነስቶ 16 መታሐራ ገባ፡፡ ከአርበኞች ጋራ ተኩስ ያጋጥመው ነበረ፣ ከሁሉ የሚጠቀስ ኦገስት 20 በፋንቲ የተደረገው ግጭት ነው፡፡

## ሰሜን ምሥራቅ ሸዋ

አዲስ አበባ ላይ የተደረገው ወረራ ከከሸፈ በኋላ በደጃዝማች አበራ ባደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመሩ አርበኞች በሰላሌ፣ ሞዬ፣ መንዲዳና ቅርማሽ ጊዳዎች ሰፍረው ይገኙ ነበር፡፡ ሌሎችም አነስተኛ ቡድኖች ተጉለት፣ መንዝ፣ አንኮበርና ደብረሲና ሰፍረው ነበር፡፡ በተለይ ሸኖና ቅርማሽ አካባቢ የነበሩ አስጊ ነበሩ፡፡ እነዚህ ቡድኖችን ለመደምሰስ አስፈላጊ ነበረ፣ ሁልጊዜ በአየር ኃይል እየተረዱ ወታደሮች ሊያጠፏቸው ሞክረዋል፡ ያደረጉት በአርበኞች ላይ ዘመቻዎች የሚጠቀሱት በመርቆሬዮስ ኦገስት 24፣ እንጎለላ ኦገስት 25፣ በሙሽ ሸለቆ ሴፕቴምበር 5፣ ደብረሲና ሴፕቴምበር 5 እና 6 ናቸው፡፡

## የአርበኞች እቅድ

የአርበኞች ዓላማ አዲስ አበባን ለመያዝ ነው፡፡ በክረምት ወራት መያዝ ካልቻሉ ለዘለዓለም የጣሊያኖች ባሪያ ሆነው እንደሚቀሩ እቅድ ነበራቸው፡፡[1]

ታክቲካቸው ግልጽ ነው፣ ወደ አዲስ አበባ የሚያመሩ የመገናኛ መንገዶች በማቋረጥ ከተማዋን ማገለል፡፡ በከተማ ዙሪያ የተሰሩ የጦር ሰፈሮችን ማውደም፡፡ ከተማዋን ወረው ነዋሪ ሕዝብ በጣሊያኖች ላይ እንዲነሳና ተባባሪያቸው ሆኖ እንዲያምፅ ማድረግ ነበረ፡፡ የዚሁ ዓይነት የጦር ስልት ግን ኢትዮጵያውያን ራሳቸው ሊያቅዱት የሚችሉ አይመስልም ነበረ፣ ከፍተኛ አንጎል ያላቸው የጦርነት ልምድ ያላቸው ሊዘጋጅ የሚችል እቅድ ነው፡፡ እቅዳቸው ግን በኢጣሊያ ወታደራዊ ችሎታ ከሽፎባቸዋል፣ ጣሊያኖች የአርበኞች ዓላማ በየቀኑ መረጃ ማግኘት በመቻላቸው የበላይነት አግኝቷል፡፡

## ሐ. ምዕራባዊ ሶማሊያ

### ግንቦት (ሜይ) በነገሌ የኢትዮጵያ አርበኞች ድል፡፡

ጣሊያኖች በዋናው ጦርነት ከከፍተኛ የጦር መኰንኖች ማንም የሞተ ወይንም የቆሰለ አልነበረም፡፡ አዲስ አበባ ከተያዘች 2 ሳምንት በኋላ ግን ሜይ

[1] Governo Generale AOI ibd Testo VI p 138

19, 1936 ከነገሌ የኢጣሊያ ጦር አዣዥ የነበረው ጀነራል በርጎንዞሊ (General Bergonzoli) አርበኞችን ለማዳን ባደረገው አሰሳ ባስከተለው ጦርነት ራሱ ጀነራሉ ተገድለዋል፡፡ ጀነራሉ በአርበኞች ላይ በነበረው ንቀት በእብሪት ተነሳስቶ፣ ጦርነት እንዳይከፍት ከአለቃው ከግራዚያኒ የተሰጠውን ትእዛዝ በመጣስ፣ 9ኛ የዓረብ ሶማል ባታሊዮን ወታደሮችን በመምራት የደጃዝማች ገብረማርያም የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሰፈረበት ዘልቆ ሊገባ ከፊት ለፊትና ከጐን ሳያስበው ተኩስ ተከፍቶበት ከባድ ውጊያ ከተደረገ በኋላ ጀነራሉ ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ትእዛዝ ቢሰጥም ባሰጊ ሁኔታ ይገኝ ነበር፡፡ የኢጣሊያ ጦር ከባሰ እስከፊ ሁኔታ ሊድን የቻለው ከቦምብ ጣይ አሬዮፕላኖች ባገኘው እርዳታና በተጓከሰት ብረት ለበስ ጦር ከዋናው ጦር ሰፈሩ ከነገሌ እንዲገናኝ በመደረጉ ነው፡፡ በተደረገው ውጊያ 3 የኢጣሊያ ጦር መኰንኖች ተገድሏል፡፡ (አንድ ሻምበል 2 የመቶ አለቆች) 4 የረሰብት ያልታወቀ /አንድ ሻምበል 2 የመቶ አለቆች አንድ ም/የመቶ አለቃ) 2 የቆሰሉ ከእነሱ አንዱ ራሱ ጀነራሉ ነበረ፡፡ ጀነራሉ አስጊ ሁኔታ ስለነበረ ወደ ነገሌ ሆስፒታል ተወስዶ ተኝቷል፣ በቦታው ሌላ ጀነራል ተተክቷል፡፡ ኢንዲጂኒ የሞቱና የደረሰበት ያልታወቀ 121 የቆሰሉ 55 ነበሩ፡፡

## ሰኔ /ጁን/ 1. መጋ በጣሊያኖች እጅ መውደቅ

ጁን 25 ጣሊያኖች በብዙ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ባንዳዎች እየተረዱ ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋራ ከፍተኛ መከላከያ ከገጠማቸው በኋላ መጋን ተቆጣጥረዋል በውጊያው ጣሊያኖች 2 ኢንዲጂኒ 4 ሞቷል፡፡ የቆሰሉ 5 የጦር መኰንኖች፣ 13 የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች፣ 10 ኢንዲጂኒ ነበሩ፡፡

## 2. ጣሊያኖች ሞያሌን ተቆጣጠሩ

ሞያሌ ሰፍረው የነበሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች 200 ብቻ ነበሩ፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጣሊያኖች መቋቋም ስለማይችሉ ነጭ ሰንደቅዓላማ በከተማዋ ተክለው የጣሊያኖች መምጣት ይጠባበቁ ነበር፣ ይሁን እንጂ ጣሊያኖች ወደ ከተማዋ ሲገቡ ተኩስ ተከፍቶባቸዋል፡፡ ጁን 30 ሞያሌ በጣሊያኖች እጅ በወደቀች ዕለት በተደረገው ውጊያ 2 ሲሞቱ 6 ቆስሏል፡፡ ሁሉም ኢንዲጂኒ -Allegato ቁ 143፣ ውጊያው የቆየው ለአንድ ሰዓት ነው፡፡

## 3. የጃባሲረ ውጊያ

ጁን 16 ጃባሲረን ለመያዝ አስቀድመው የተላኩ ባንዳዎች ነበረ፣ ሆኖም ድንገተኛ አደጋ ለማድረስ ሲሞክሩ ኃይለኛ መከላከል ከአርበኞች ስለገጠማቸው ባንዳዎች ሸሽተው ወደ መጡበት እንዲመለሱ ተደርገዋል፡፡ ጣሊያኖች ለባንዳዎች እርዳታ ቢመጡም አርበኞቹ ከዘው ሊደመስሷቸው ሞክረው ነበር፣ ሆኖም ብዙ መትረየስ የነበራቸው ሌሎች ጣሊያኖች ስለመጡላቸው ከከበባ ቢድኑም፣ አሁንም አርበኞች አዲስ የመጣባቸው ጦርም ከበው ለመደምሰስ ሞክረው ነበረ፣ ጣሊያኖች መልሰው ማጥቃት ቢሞክሩም የአርበኞቹ ግፊት ለማቆም አቅቷቸው ነበር፡፡ በኋላ ግን ጣሊያኖች ከባድ መድፎችን እስመጥተው ስለተጠቀሙ ለተከበቡ ጣሊያኖች መውጫ ስለከፈተላቸው ጣሊያኖች ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ችሏል፣ ከአዲስ ያዞታቸው ጣሊያኖች አዲስ መልሶ ማጥቃት አካሄደው አርበኞችን ሊያባርሩ ችሏል፡፡





ሲልቪያ ፓንክኸርስት ለኢትዮጵያ ነፃነት ተሟጋች በቢሮዋቸው ውስጥ እንዳሉ።

በተደረገው ውጊያ አንድ የኢጣሊያ የመቶ አለቃ ሉፖ (Lupo) ዘጁን 16 የተገደለ ጁን 17 አስከሬኑ ተገኝቷል፡፡ 24 ዓረብ ሶማል አስካሪና ዱባት ተገድለዋል፤ 33 ቆስሏል፤ 10 ጠፍቷል፡፡ ውጊያ የቆየው ለ 8 ሰዓት ነበረ፡፡ Allegati ቁ 227, 258, 259፡፡ ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋራ ከዱተኞች ኤርትራውያን ተቀላቅለውባቸው ነበረ፡፡ Allegati 258

## የሴፕተምበር ወር ሁኔታዎች

በጥቢ ሸበሌ (ጀስትሮ) ጣሊያኖች ብዙ ተቃዋሚ አላጋጠማቸውም፡፡ በፖለቲካ ቅስቀሳ በኩል ቆንስል ሆኖ እርሲ በነበረው ሻለቃ አጎስቲኖ /Mqggiore Agostino/ ተጠቅሟል፡፡ እንደዚሁም በውትድርና ባንዳ ጋናለ ዶሪያ 2 ባንዳ ባለ 3 ባንዳ ጀስትሮ ብለው አቋቁመው በሰየሟቸው ባንዳዎች ተጠቅሟል፡፡ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ የነበሩዋት ቆንስላዎች በምን ዓይነት ሰዎች ይመሩ እንደነበሩና ምን ዓይነት ስራ ያከናውኑ እንደነበሩ ለመረዳት እንችላለን፡፡ በሴፕተምበር ወር ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ አርበኞች አዲስ አበባ ትወረራለች የሚል ወሬ ይናፈስ ስለነበረ ግራዚያኒ ሴፕተምበር 1 ቀን 1936 ለጀነራል ሳንቲኒ Santini የሶማሊያ ክልላዊ መንግሥት አስተዳደርና ለጀነራል ጀሎዞ Geloso የጋላና ሲዳማ መንግሥት አስተዳዳሪ ስለዚሁ ጉዳይ Allgati ቁ 291 ቴሌግራም ሰልኮ ገልባጭም ለአማራ ክልላዊ መንግሥት አስተዳዳሪ ጀነራል ፒርዚዮ ቢሮሊ Pirzio - Biroli ለሐረር ክልላዊ መንግሥት አዛዥ ጀነራል ናዚ General Nasi እንደዚሁም ለኤርትራ ክልላዊ መንግሥት አስተዳዳሪ ጉዞኒ Guzzoni አስተላልፎ ነበር፡፡ ባስተላለፈው በዚሁ ቴሌግራም በባሌና በሲዳሞ የሚገኙ ፀየነ መርዕድ ገብረማርያም ለጣሊያኖች እጃቸውን ለመስጠት እንደሌላቸውና በአዲስ አበባ ላይ በሚደረገው ወረራ እንደሚካፈሉ ተደጋጋሚ ወሬ ስለሚሰማ ይኸንን አውቀው በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ነው፡፡ ንጉሡም በቅርብ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ መሆኑን፤ ብዛት ያለው ጦር ራስ እምሩ በወለጋ ሰፍሮ እንደሚገኝ፤ ራስ ጊታቸውና ደጃዝማች መኩንን ከካይሮ ወደ ጎሬ እያመሩ መሆናቸውን ስለሚወራ በሸዋ ያሉት የቀድሞ መንግሥት ሹማምንቶች እንደ አበራ ካሣ የመሳሰሉ እጃቸውን ለጣሊያኖች ለመስጠት ሃሳብ የነበራቸው በሚነፍሱ ወሬዎች ተወናብደው እጃቸውን ከመስጠት እንዲቆጠቡ እንዳደረጋቸው ይገልጻል፡፡ ስለዚህ 1ኛ ሶማሊያ የሚገኘው አየር ኃይል ወደ አዲስ አበባ የሚወስዱ መንገዶች እንዲቆጣጠር 2ኛ ጀነራል ጀሎዞ ከአርበኞች ጋራ ግንኙነቱ እንዳያቋርጥ፤ ምናልባት ወደ ሰሜን የሚያመሩ ከሆነ በስተጀርባቸው እንዲወጋቸው፡፡ 3ኛ ጀነራል ናዚ ከአርሲ ከሶማሊያ ወደ ባሌ ወታደራዊ ዘመቻ እንደሚካሄድ ቀደም ብሎ በታቀደው መሠረት ዝግጅቱን እንዲያፋጥን የአማራ ክልላዊ መንግሥትም ለወደፊት ወደ ምዕራብ ወደ ወለጋ የሚደረገው ዘመቻ ተካፋይ እንደሚሆን በማለት ለሁሉም መመሪያ አስተላልፈዋል፡፡

## መ. የአማራ ክልላዊ መንግሥት

ጣሊያኖች ሲገቡ በላስታ ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ የሰፈረበት በስተቀር ተቃውሞ አላጋጠመንም ብሏል፡፡ ሌላ ቦታ አርበኞች አሉበት እየተባለ ሲወራለት የነበረ ወረኢሉ ነበረ፡፡ እንደተባለውም ኦገስት 20 አርበኞቹ በጣሊያኖች ላይ ጥቃት ለመፈጸም ሞክረው በቦታው የሰፈረው የኢጣሊያ ጦር ሰፈር ተባርረው 81 ሞቶባቸዋል፤ ከነመግሪያቸው የተማረኩ አርበኞች



ተረሸነዋል፡፡ በአማራ ክልላዊ መንግሥት ጣሊያኖች በየቦታው ባንዳዎች አሰልጥነው አሰማርተዋል፡፡ ስለ ወረኢሉ ውጊያ ግራዚያኒ ዝርዝር ሁኔታ ባስተላለፈው ቴሌግራም ከጣሊያን ወገን 1 አስካሪ ሲሞት 11 ቆስሏል ከእነሱም 3 በከባድ የቆሰሉ ነበረ፡፡ በውጊያው ከጣሊያኖች ጎን ተካፋይ ከነበሩ የአካባቢ ነዋሪዎች 6 ተገድለዋል፡፡ 18 ቆስሏል፡፡ ከአርበኞቹ 81 በጦር ሜዳ ሲገደሉ የተማረኩ 8 አርበኞች 4 በወረኢሉ 4 በደሴ በስቅላት ተገድለዋል ብሏል Allegato ቁ 269

## ላስታና ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ

በአማራ ክልላዊ መንግሥት ፀረ ኢጣሊያ አዝዝ እንቅስቃሴ የተካሄደበት በላስታ ነበረ፡፡ በደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ አማካኝነት ከጁን ወር ጀምሮ ደጃዝማች ወንድወሰን በይፋ ለጣሊያኖች እጁ እንደሰጠ ነበረ የሚታወቀው Allegato 104. ይሁን እንጂ በተግባር ሕዝቡ ፀረ ጣሊያኖች ለዓመፅ ለማነሳሳት ቅስቀሳ ያደርግ ነበረ፤ ወደ ጣሊያኖች እንዲቀርብ የተደረገለት ጥሪም በሽታ ምክንያት እየፈጠረ አልቀረበም፡፡ ጣሊያኖችም የበሽታም ሰባብ በማድረግ በዘዴ በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ በማሰብ አንድ ሐኪም ከሰቆጣ ወደ ሙኙ እንዲላክለት ሲፈቅዱ ደብዳቤም እንዲላክለት ይወስናሉ፡፡ ከሚላከው ሐኪም ብዛት ያላቸው ከነ ሙሉ ትጥቃቸው የኤርትራ አስካሪና የላስታ ባንዳ አብረው ይሄዳሉ Allegato 235 ደጃዝማች ወንድወሰን ግን ከላሊበላ ለቆ ሄዶ ነበረ፡፡ በኦክቶበር ወር ብቻ ጣሊያኖች በደጃዝማች ወንድወሰን ላይ መውሰድ ስላለበት እርምጃ 9 ጊዜ ደብዳቤዎች እርስ በርሳቸው ተለዋውጠዋል (12-7-18-21-24-29-30) በላስታ ባንዳና በነዋሪ ሕዝብ መሐል ግጭት ስለተፈጠረ ሻለቃ ካፋሮ (Maggiore Cafuro) የኤርትራ 24ኛ ባታሊዮን በሙሉ ይዞ ከሰቆጣ ወደ ላሊበላ እንዲሄድ ትእዛዝ ይሰጠዋል፡፡ ኦገስት 24 ከሰቆጣ ተነስቶ ሻለቃ ካፋሮ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ወደ ላሊበላ በመሄድ ፋንታ ኦገስት 27 ሌላ የደጃዝማች ወንድወሰን ተባባሪ ኃይሉ ከበደ ከቦ ለመያዝ ሞከሮ ነበረ፡፡ በኋላ ግን ኦገስት 29 ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ከበባውን አምልጦ ሸሽቶ ስለጠፋ ሻለቃ ካፋሮ ጉዞውን ወደ ላሊበላ ቀጥለዋል፡፡ ሰፕተምበር 7 ቀን የኢጣሊያ ጦር ሰፈር በላሊበላ የ24ኛ ባታሊዮን ኢንዲጂኒ 450 ወታደሮች በድንገት በአርበኞች ይከበባል፡፡ በሻላቃ ካፋሮ የሚመሩ የ24ኛ ባታሊዮን ኢንዲጂኒ ኤርትራውያን ላይም ከአርበኞች ጥቃት ይፈጸምባቸዋል፡፡ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሁለቱ ቡድኖች በራድዮ ግንኙነት የነበራቸው የጦር አሪዮፕላኖች ለንቅ ትጥቅ በመላክ በቦምብም አርበኞችን በመደብደብ እርዳታ ጠይቀው ነበር፡፡ ደጃዝማች ወልደሥላሴ የተባለው የኢጣሊያ ባንዳ መሪ ሰፕተምበር 8 ሻለቃ ኡጎሊኒ (Maggiore Ugolini) ባዘዘው መሠረት 300 ባንዳዎች በመምራት ከሰቆጣ ወደ ቢልባላ ጊዮርጊስ ያመራል፡፡ ከአሥመራና ከመቀሌ የሚነሱ የጦር አሪዮፕላኖች ሰፕተምበር 8 ስንቅና ትጥቅ በማቀበልና የቦምብ ድብደባ ሲያደርጉ ውለዋል፡፡ ከሰዓት በኋላ አርበኞቹ ኃይለኛ በቢልባላ ጊዮርጊስ በተከበበ የኢጣሊያ ባታሊዮን ላይ ጥቃት ፈጽመው ውጤት አላገኙም፡፡ ከአርበኞቹ ጋራ የኤርትራ አስካሪ ከዳተኞች ይገኙባቸው ነበር፡፡ ኦክቶበር 9 አርበኞች እንደገና በቢልበላ ጊዮርጊስ ላይ ጥቃት ፈጽሟል፤ ይህ ጥቃት ግን ለመሸሽ እንዲመቻቸው ያደረጉት ይመስል ነበር፡፡ አርበኞች በአሪዮርላን ጉዳት ስለደረሰባቸው ተበታተኑ ደጃዝማች ወንድወሰንም አምልጦ ከደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ለመገናኘት ወደ ተከዜ ሄዷል፡፡ ሻለቃ ኡጎሊኒ ከደብረታቦር፤ ደጃዝማች ወልደሥላሴና ሌሎች ባንዳዎች በተጨማሪም 25ኛው የኢጣሊያ ኢንዲጂኒ ባታሊዮን እንደዚሁም በመኪና የሚጓዙ ባለጥቁር ሸሚዝ (ፋሺስት) የኢጣሊያ ወታደሮች ከሞራ

ፀለምቲ ደጃዝማች ወንድወሰንን ለመያዝ ተሰማርቷል በተለይ በአርበኞች ላይና ደጋፊ በተባለው ሕዝብ ላይ በአሬዮፕላን የሚደርሰው ጉዳት አስከፊ ነበረ። የደጃዝማች ወንድወሰን ሁኔታ ያባበሰው የነበረ ነዋሪዎች የአሬዮፕላን ድብደባ በመፍራት በመንደራቸው ለማስጠጋት አይፈልጉም ነበረ። በሰፕተምበር ወር መጨረሻ ደጃዝማች ወደ ግሊያኖች ለመምጣት እንዲፈቀድለትና ይቅርታ እንዲደረግለት በማለት ደብዳቤ ለሻለቃ ኡጎሊኒ ይጽፋል። ወዲያውኑ ወደ ደብረ ታቦር በመምጣት እጅ እንዲሰጥና ምህረት ተደርጎለት ወደ አዲስ አበባ የሚላክ መሆኑን የሚል መልስ ይላክለታል። ደጃዝማች ግን አልቀረበም፣ ምክንያቱም በወቅቱ ንጉሡ በእንግሊዞች እየተረዳ ወደ ኢትዮጵያ ሊመለስ ነው የሚል ዜና ይናፈስ ነበር። በሰፕተምበር ወርም ስለ ደጃዝማች ወንድወሰን ጉዳይ ግሊያኖች እርስ በርሳቸው 17 ቴሌግራሞች ተለዋውጧል።

## የግራዚያኒ ደብዳቤ ለደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ

እንደምን አለህ፣ እኛ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነን ታመህ ወደ አዲስ አበባ ስትመጣ እንደቀረህ ሰምተናል በቶሎ ድነህ እንደምትመጣ ተስፋ እናደርጋለን። ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ የጠራንህ ልንተዋወቅህ ፈልገን ነው፣ እንደዚሁም ያንተ እዚህ መምጣት ወንድሞችህ አበራና አስፋወሰን ለመንግሥት እጃቸው እንዲሰጡ ለማደፋፈር ይረዳ ይሆናል ብለን በማሰብ ነበረ። እኛ አንተ እንድትረዳልን የምንፈልገው የሚነፍሱ ወሬዎች ሐሰት መሆናቸውና እግዚአብሔር ከፈቀደው ማንም ሊለውጠው እንደማይችል ነው። ለሌሎች እጃቸውን ለሚሰጡ ሁሉ እንደምናደርገው ጥሩ አቀባበል አዘጋጅተንልህ ነበር። ራስ ሥዩም ከእኛ ደብዳቤ ጋራ አንድ ደብዳቤ ጽፎልሃል። ስለ እኛ በጎ አስተሳሰብ ዋስትና ሊሰጥህ ይችላል። ስለዚህ ምንም መፍራት የለብህም። ያንተ ወዳጅነት ወደ አዲስ አበባ መምጣት በሽታ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በእኛ አለመተማመን እንዳለህ ጥርጣሬ አድሮብናል። ወንድሞችህ መንግሥትን እጅ ለመንሳት ወደ አዲስ አበባ እንደሚመጡ ነግረውናል። አንተም ብትገኝ የቤተሰቦችህ ታማኝነት ተረጋግጦ ለሁላችሁ የሚጠቅም ነበር።

አዲስ አበባ ሰፕተምበር 2 ቀን 1936 ዓ.ም. Allegato 292

ሰፕተምበር 8 ቀን በቢልባላ ጊዮርጊስ በተደረው ውጊያ 3 ግሊያኖች ቆስሏል፣ ኤርትራውያን የሞቱ 2 የቆሰሉ 11። ከአርበኞች ጋራ የተሰለፉ የድሮ አስካሪ ኤርትራውያን ከዳተኞች ነበሩባቸው። Allegato N 306 ሰፕተምበር 9 ቀን በቢልባላ ጊዮርጊስ በተደረገው ውጊያ የሞቱ 2 የቆሰሉ ከኤርትራውያን የሞቱ 10 የቆሰሉ 16። በላሊበላ የተደረገው ውጊያ ኤርትራውያን የሞቱ 5 የቆሰሉ 2። የላስታ ባንዳ 2 ሲሞቱ 8 ቆስሏል። ጠቅላላ ድምር 46 Allegato ቁ 307 ሻለቃ ካፋሮ ሰፕተምበር 11 ቀን በቢልባላ ጊዮርጊስ መንደር አካባቢ የነበሩ መንደሮች በሙሉ አቃጥሏል፣ የተማረኩ አርበኞችም በጥይት ተደብድበው ተገድለዋል። Allegato ቁ 312።

ከሰፕተምበር 14 ቀን ጀምሮ በሸፈቱ መንደሮች ላይና በአርበኞች ላይ የበቀል እርምጃዎች የሚወሰዱ መሆናቸውን በአሬዮፕላን የተበተኑ በራሪ ወረቀቶች አማካኝነት ጭምር ተገልጸዋል። Allegato ቁ 315። ደጃዝማች ወንድወሰን ሰፕተምበር 30 ቀን ለሻለቃ ኡጎሊኒ በላከው ደብዳቤ እጁን ለመስጠት እንደሚፈለግና ይቅርታ እንዲደረግለት ጠይቋል። የአማራ ክልላዊ መንግሥት አዣዥ በሰጠው መልስ፣ ይቅርታ እንድንሰጥህ ከፈለግህ። 1ኛ ወዲያውኑ እጅህ እንድትሰጥ 2ኛ አስካሪ ከዳተኞች እንድታስረክብ 3ኛ በላስታ የሚገኙ መሣሪያዎች እንዲያስታውቅ የሚጠይቁ ቅድመ ሁኔታዎች በማቅረብ ነው። ግራዚያኒ ግን ከአማራ ክልላዊ መንግሥት ኃላፊ ለተላከለት ቴሌግራም



ደጃዝማች እንዲያሟላ የተሰጡት ቅድመ ሁኔታዎች ውድቅ በማድረግ ከደጃዝማች ወንድወሰን የሚጠየቀው ቅድመ ሁኔታ ቶሎ ብሎ እጁን እንዲሰጥና ወደ አዲስ አበባ በአሬዮፕላን እንዲመጣ ፈቃደኛ እንዲሆን ብቻ ነው በማለት አሻሽሎለታል።

በሁሉ አካባቢ የሚደረጉ ውጊያዎች በሙሉ ለመጥቀስ አስቸጋሪ ነው። በሰሜን ምሥራቅ ሸዋ ጁላይ 20, 21, 22, 23 በኮሎኔል ትራኪያ የሚመሩ ግሊያኖች በአርበኞችና በሕዝቡ የፈጸሙት ጭፍጨፋ የሚጠቀስ ነው። በተባሉት ቀናት ውጊያዎች ከተካሄዱ በኋላ ጁላይ 24 እና 25 ውጊያዎች ጋብ ሲሉ ግሊያኖች ሰላማዊ ሰዎችን መቅጣት ይጀምራሉ፣ 50 የተማረኩ አርበኞችም ተረሸነዋል፣ ቤቶች ተቃጥለዋል፣ 1000 ከብቶች ተዘርፈው ለነበራቸው የስንቅ እጥረት ተጠቅመውባቸዋል፣ 100(አንድ መቶ) አሰሳ ሲያደርጉ የያገኙዋቸው ሰላማዊ ሰዎች ሰላይ፣ ከዳተኛ ፣ መሣሪያ ይዘዋል በሚል ሰበብ ተረሸነዋል በውጊያ የተገደሉ አርበኞችም 709 ነበሩ ብሏል። ከግሊያኖች 2 ም/መቶ አለቆች ተገድሏል፣ አንድ ሻምበል፣ አንድ ም/የመቶ አለቃ፣ 3 ባለ ጥቁር ሸሚዝ ወታደሮች 2 ሹፌሮች ግሊያኖች። ከኢንዲጂኒ ኤርትራውያን የሞቱና የቆሰሉ 63 ነበሩ። Allegato N 214 ጀነራል ትራኪያ ሪፖርት እንዳደረገው። በሰሜን ምሥራቅ ሸዋ በኮሎኔል ጂኖ ፑቺ ዳ ፊሊካያ Colonel Gino Pucci Da Filicaya የአንድ ባታሊዮን አዛዥ የሚመሩ ግሊያኖች ባደረጉት አሰሳ በአንድ መንደር ቁጥራቸው ያልተገለጠ ሰዎች ተረሸነዋል ብሏል፣ በሌላ መንደርም ቤቶችን ለማቃጠልና የተያዙ መንደርተኞች ለመግደል አንድ ሰዓት ጊዜ ፈጀብን ይላል፤ የተቃጠሉ ቤቶች ቁጥጥርና የተረሸኑ የሰው ብዛት አልተገለጠም። ዘሌላ መንደርም ሩፋ በሚባለው ወንዝ አካባቢ ብዙ ቤቶች ተቃጥሏል፣ 50 ሰዎች ተገድሏል፣ ብዙ ከብቶች ተዘርፈዋል። በአሰሳ ዘመቻ ወደ ጦር ሰፈራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ከነበሩዋቸው መኪናዎች 37 በየመንገዱ ለመተው ተገደዋል። እግረመንገዳቸው፣ በግሊያኖች ላይ ተኩስ ከፍተው ነበረ ተብለው የተጠረጠሩ የመንደሮች ቤቶች ሁሉ አቃጥለዋል፣ 1000 ከብቶች፣ በሬዎች፣ በጎች፣ ፈረሶች፣ በቅሎች ተዘርፈዋል። Allegato ቁ 216

ይህ ሁሉ ለወደፊቱም በኢትዮጵያውያን ላይ ተሸንፈው እስከ ወጡ ድረስ የሚፈጽሙት ወንጀል ትክክለኛ የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው። የኖም በወንጀላቸው አልተጠየቁም፣ እንደ በጎ አድራጊዎች ተቆጥረው ነው ከሀገራችን የወጡ ግሊያኖች በክረምት ወራት ጭቃ ምክንያት እንዲሁም አርበኞች በሚያደርሱባቸው የማያቋርጥ ጥቃት በሰሜን ሸዋ ለወታደሮቻቸው ስንቅ ለማቀበል ችግር ስለነበራቸው ከሕዝበ እየዘረፉ ለምግባቸው ይጠቀሙበት ነበር። ለወታደሮቻቸው የሚሰጣቸው ምግብም ለመቀነስ ተገደደው ነበር። የምግብ ቅነሳ በሚያደርጉበት ጊዜ ግን ለግሊያኖችና ለኤርትራውያን እኩል አልነበረም። የራሲዮናቸውም እንደሚከተለው ነበረ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | ፎርኖ ዱቄት ተጨማሪ | ለግሊያኖች 400 ግራም | ለኤርትራውያን 300 ግራም |
| 2 | ፎርኖ ዱቄት | 100 ግራም ፓስታ ካልተሰጣቸው | X |
| 3 | ሩዝ በፓስታ ፋንታ | 150 ግራም | X |
| 4 | ዕንጨት | 1500 | 1000 |
| 5 | ስኳር | 25 | 40 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | ሻይ | X | 15 |
| 7 | ቡና ጨው | 20 | X |
| 8 | ጨው | | 15 |

አስካሪ እንጀራ ስለሚመርጡ በቀን 1000 ራሲዮን ፎርኖ ዱቄት መቀጠብ ተችሏል። ነሐሴ 26 1946 በደጃዝማች ባልቻ የሚመሩ አርበኞች ከወሚጫ ተራራ ወደ አዲስ አበባ የድር አሬዮፕላን ማረፊያ ሲያመሩ ስለታዩ፣ ከጣሊያኖች ጋራ ውጊያ ፈተረው፣ ከጣሊያኖች ወገን 15 አስካሪ ሲሞቱ 40 ቆስሏል።

# ከክረምት ወራት በኋላ የኢጣሊያ 2ኛ ዙር ዘመቻ ያልተያዙ የምዕራብና የደቡብ ክፍላተሀገሮች ለመቆጣጠር

በዋናው ጦርነት ጊዜ እንደተከሰተው አሁንም አርበኞች የሰው ብዛት አልነበራቸውም።በጣሊያኖች ግምት ወደ ምዕራብና ደቡብ ክፍለተሀገሮች ዘመቻ ለማድረግ በሚዘጋጁበት ጊዜ ቁጥራቸው ከ30.000 አይበልጡም ነበር። የኢጣሊያ ሠራዊት ግን 339.000 የወታደር ብዛት ነበረ። ከእነሱ ውስጥም 249.000[1] ኢንዲጂኒ 90.000 ጣሊያኖች ነበሩ።




## በየወሩ የተከናወኑ ውጊያዎች

### ኦክቶበር ሰሜን ምሥራቅ ሸዋ

ዋናው ዓላማ የመኪና መንገዱ ለ[illegible]ጠበቅ ነበረ።የባቡር ሐዲድን ከአርበኞች ጥቃት ለመከላከል በ3 ጄነራሎች የሚመሩ ጄነራል ማሪዮቲ ጋሊና ተሲቶሬ (Mariotti, Gallina Tessitore) ወታደሮች ተሰማርተው ነበረ። በደቦኮዲዮ 3ቱ ጄነራሎች በ3 አቅጣጫ ባደረጉት ዘመቻ ኦክቶበር 26 ታዋቂ የአርበኞች መሪ የነበረው ደጃዝማች ፍቅረማርያም ተከበው ሊገደሉ ችሏል።

በምዕራብ በኰሎኔል በሊ የሚመራው ጦር ኦክቶበር 4 ቀን አምቦ ገብተዋል፣ ኦክቶበር 16 በኰሎኔል በይትርኪ የሚመራ ቡድን በአሬዮፕላን የለቀምት አሬዮፕላን ማረፊያ በናያ አርፈዋል፣ ባንዳ ለማቋቋም ሙከራ አድርገዋል። 1ኛ ብረጌድ ኦክቶበር 12 ከአዲስ አበባ ተነስቶ ኦክቶበር 24 ለቀምት ገብቷል።

[1] Governo Generale A.O.I ibd testo VII p 14



ሐረር የጋራሙለታ ጨርጨር ከአርበኞች ለማጽዳት ተሞክረዋል ወደ ባሌና አርሲ ለመዝመትም ዝግጅት ተጠናቅቀዋል።
ሲዳማ ኦክቶበር 2 የአየር ድብደባ በጀባሲረ ተፈጽመዋል።
አማራ ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣን ለመያዝ ከደብረታቦር ከደሴ ከላሊበላ በ3 አቅጣጫ ወደ ተከዘ ዘምተው ከዘው እንዲያዙ ተዘጋጅቷል።

## ኖቬምበር ወር

በሸዋና በቡር ሐዲድ ብዙ አነስተኛ ግጭቶች ከአርበኞች ጋራ ይከሰቱ ነበር።
በምዕራብ ኖቬምበር 5 በኰሎኔል ፕሪንቺቫለ (Colonel Princivalle) የሚመራ ጦር በአንድ እስላም ባለበት እየተመራ ከአዲስ አበባ ወደ ጂማ ለመሄድ ተነስቷል፣ ሌላ ጦር በጄኔራል ተሲቶሬ የሚመራ ወደ ለቀምት ለመሄድ ኖቬምበር 6 ከአዲስ አበባ ተነስቷል ኖቬምበር 11 በኰሎኔል ማልታ የሚመራ ጦር ከአዲስ አበባ ወደ ለቀምት ጊምቢ ተነስቷል። ሌላ ቡድን የጆቴ ልጆች ወንድማማቾች እየተረዳ በአሬዮፕላን ወደ ሰዩ ተጉዘዋል። ሌላ ጦር በሚላኖ የሚመራ ኖቬምበር 16 ከአዲስ አበባ ተነስቶ (X ብርጌድ) ወደ ለቀምት አምርቷል ራስ እምሩን ለመያዝ ኖቬምበር 24 በኰሎኔል ሚላኖ የሚመራ ጦር ከለቀምት በወለጋ ባንዳ እየተረዳ ወደ ጂማ አምርቷል።
የሐይቆች ቀጠና በጄኔራል ጄሎዞ የሚመራ የኢጣሊያ ሠራዊት ወደ ሰሜን ለመግፋት ያደረገው እንቅስቃሴ በራስ ደስታ ኃይሎች ስለታገደ፣ ሲርዳታ በሻሲቃ ቱቺ (Tucci) የሚመራ ጣሊያኖች የትግሬዎች ባንዳ ያላቸው ራስ ደስታ በሰፈጀርባው ሰመውጋት ግራዚያኒ አሰማሩ።
ሐረር የሶሊያ ዲቪዚዮን ጨርጨርን ከአርበኞች ለማጽዳት ቀጥሎ የፈታውራሪ በለዩ ኃይሎች፤ ለመከበብ ሞከሮ እንዲበታተኑ አድርገዋል።
አማራ በደጃዝማች ወንድወሰን ላይ ከዘባው እየተጠናከረ ነበረ፣ ከደሴ ወደ ዶባ ሰመገለቅ ዓላማ የነበረው ከኰሎኔል ቶሴቲ የሚመራው የኢጣሊያ ጦር ከአርበኞች ከባድ ውጊያ ሰላጋጠመው ወደ መጣበት እንዲመለስ ተገዷል።

## ዲሴምበር ወር

ሸዋ ጣሊያኖች ፊቼን ተቆጣጥረዋል ዓላማው የራስ ካሣ ልጆች አበራና አስፋወሰንን ለመያዝ ነበረ። በአምስት አቅጣጫ በጄነራሎችና በኰሎኔሎች የሚመሩ የኢጣሊያ ወታደሮች በትራኪያ ጋሬሊ ናታሌ ኮስታ Tracchia Garelli Belly Natale - Costa የሚባሉ ዲሴምበር 21 ከበው ከማረኳቸው በኋላ ከዳተኞች ሽፍቶች ተብለው በጥይት ተገድለዋል።
ምዕራብ ሸዋና ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ። በጄነራል ማሪዮቲ የሚመራ የኢጣሊያ ጦር ተልእኮ ሊቾን ለመያዝ ነበረ።
የራስ እምሩ መያዝ። በ 3 ጄነራሎችና ኰሎኔሎች የሚመሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ማልታ፣ተሲቶሬ፣ ፕሪንቺቫለ የተባሉ ዲሴምበር 11 ደጃዝማች ታዬ ጉሉላቴ ተያዘ፣ ዲሴምበር 12 ቢተወደድ ወልደጻዲቅ ተያዘ ዲሴምበር 15 ራስ እምሩ ተያዙ። ዲሴምበር በአሬዮፕላን የተላኩ 100 ሰው ብዛት ያላቸው ወታደሮች ጋምቤላን ተቆጣጠሩ። ከአማራ የተላኩ ሌሎች ወታደሮች ዲሴምበር 24 ቤን ሻንጉልን ተቆጣጠሩ።
ሐይቆች ዲሴምበር 1 ቀን ይርጋለም ተያዘች
ሐረር ወደ አርሲ ለመዝመት ተጀምረዋል።

አማራ ሌሎች ተጨማሪ ወታደሮች በማሰማራት በተከዜ የነበረ ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ ዲሰምበር 10 ተይዞ ተረሽነዋል፡፡

## ጃንዋሪ ወር

ሸዋ ሰላሌን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ተሞክሯል፡፡ ምሥራቅ ሰሜን ሸዋ በአርበኞች የታመሱ ስለነበረ ጣሊያኖች ብዙ ወታደሮች አሰማርተው ከመንዲዳ በስተሰሜን እምበርተራ በተባለው ቦታ ሰፍረው ከነበሩ በአበበ አረጋይ ከሚመሩ አርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሟል፡፡ ሸዋ ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ በአርበኞች አስሳ ቀጥሏል፡፡
ምዕራብ የከፍለ ሀገሩ አውራጃዎች የመቆጣጠር ተሞክሯል፡፡
ቤንሻንጉል ዲሰምበር 31 አሶሳ ተያዘች፡፡
ሐይቆች ራስ ደስታ እጅን ለጣሊያኖች እንዲሰጥ የተደረገው ሙከራ ስለከሸፈ ከጋላና ሲዳማ ክልላዊ መንግሥት ሁለት ጀነራሎች ከአርሲ የተውጣጡ ባንዳዎች ከአዲስ አበባ የተላኩ የትግራይ ባንዳዎች የተከፈለበት ራስ ደስታን ለመያዝ በግራዚያኒ ራሱ የሚመራ ዘመቻ ተካሄደ ራስ ደስታ ደጃዝማች ገብረማሪያምና በየነ መርዕድ ሁለት ጊዜ ከተከበቡ በኋላ ሁለት ጊዜ ለማምለጥ ችሏል፡፡
ሐረር የሊቢያ ዲቪዚዮን አዋሽ፣ ሚኤሶ፣ አዳማ በሰፈሩ አርበኞች አሰሳ አካሄዷል፡፡ XL የአማራ XX የኤርትራ XXX VIII የዓረብ ሶማል ባታሊዮኖች ወሩ በሙሉ ምዕራባዊ አርሲ ለመቆጣጠር ተሰማርቷል፡፡
አማራ በሽፍትነት የተሰማሩ ለመደምሰስ ተባባሪ ሕዝቡን ለመቅጣት የጣሊያኖች አሰሳ ቀጥሏል፡፡ ከሁሉ የሚጠቀሱ በባሊል ደስታና በመብነህ ተሰማ የሚመሩ አርበኞች ላይ በእም ሐጀር ጉንደር መንገድ የተደረጉ ውጊያዎች ናቸው፡፡

## ፌብሩዋሪ ወር

<u>በአሰልቱ ሸዋ አጠገብ</u> ፌብሩዋሪ 15 በግርማ ስንቡ ከሚመሩ አርበኞች ጋራ ጣሊያኖች ውጊያ አካሄዷል፡፡ በመገር ከታዋቂው በአርበኞች መሪ ኃይለማርያም ማሞ የሚመሩ አርበኞች ጋራ ፌብሩዋሪ 10, 15 እና 18 ጣሊያኖች ውጊያ አካሄዷል፣ ከነበረው ቦታ ለቆ ወደ ሙሉ እንዲሄድ አድርገውታል፡፡ በተጉለት በጀነራል ትራኪያ የሚመሩ የኢጣሊያ ጦር አርበኞች ጋራ በጣርማበርና እምባ በተርጌ ላይ፣ ፌብሩዋሪ 24 ውጊያ አድርገው አርበኞች ወደ ዘንደጉርና ሰላ ድንጋይ አፈግፍገዋል፡፡
<u>ባቡር ሐዲድ</u> በአርበኞች ላይ አሰሳ አላቋረጠም፡፡
<u>አዲስ አበባ</u> በግራዚያኒ ላይ ፌብሩዋሪ 19 (የካቲት 12) ከውጭ በመጡ ሰዎች አማካኝነት ነው የተባለለት የመግደል ሙከራ ተፈጽመዋል፡፡ ሁኔታው የኢጣሊያ ርእዮተ ዓለምና ጽንሰ ሐሳብ ባላባቶችና የቀድሞ ሹማምንቶች እንዲቀበሉ አስተማማኝ የመሳብና የማዋሐድ ይደረግ የነበረ መልካም ሥራ ለአንድ አፍታ እንዲስተጓጉል አድርገዋል፡፡
<u>ምዕራብ ጋላና ሲዳማ</u>፡፡ ከቦታው የተውጣጡ ባንዳዎች ተቋቁመዋል፣ ከአረበኞች ጋራ ውጊያ አካሂዷል፡፡
<u>ሐይቆችና ጉራጌ</u>፡፡ ጣሊያኖች ከብዙ የአርበኞች ቡድኖች ጋራ ውጊያ ገጥሟል፡፡ ፊታውራሪ ሺመልስ በዎባኒ ተራራ ሰፍሮ ስለነበረ ፌብሩዋሪ 1 ከሻሸመኔ ጦር



ተልኮበት ከባድ ውጊያ ተደርገዋል፡፡ ከብዙ ትግልና ከትትል በኋላ ፊታውራሪ ሺመልስ ደጃዝማች ገብረማርያምና ራስ ደስታ (ፌብሩዋሪ 24) ተገድለዋል፡፡
<u>ሐረር</u> ብዙ አነስተኛ ግጭቶች ከአርበኞች ቡድኖች ጋራ
<u>አማራ</u> በእም ሐጀር ጉንደር መንገድ አሰሳ ቀጥሏል፡፡

## <u>የማርች ወር</u>

<u>ሸዋ</u>፡፡ ጀነራል ትራኪያ ማርች 1 ጉር ሥላሴ 10 ሰላ ድንጋይ ተቆጣጥረዋል በመገር 21 ከኃይለማርያም ማሞ ጋራ ውጊያ ተካሄዷል፡፡ በአንኮበር አሰሳ ተካሄዷል፡፡ 28 በአደባይ በአበበ አረጋይ ከሚመሩ አርበኞች ጋራ ውጊያ ተካሄዷል፡፡
<u>ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድና ጉራጌ</u>፡፡ ከባቡር ሐዲድ ዝዋይ ወልቂጤ ወዙተ ኤርትራውያንና ዓረብ ሶማል ባሉበት ሰፈ አሰሳና ትጥቅ ማስፈታት አካሄዷል፡፡
<u>ጋላ ሲዳማ</u>፡፡ ሰፊ አሰሳ ተካሄዷል፡፡ ማርች 19 አርበኞችን አባርረው ጣሊያኖች ማጂን ተቆጣጠሩ፡፡ ማርች 31 ቀን ከአርበኞች ጋራ ውጊያ አካሄዶ ኩሉን ተቆጣጠረ፡፡
<u>ሐረር</u> ታማና በተባለው ቦታ ማርች 2 ጣሊያኖች ከአርበኞች ጋራ ውጊያ አካሄዷል፡፡ ከዚሁ ውጊያ በኋላ ብዙ አርበኞች ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ ተሰዷል፣ ብዙ እጃቸው ሰጥቷል፡፡
<u>አማራ</u> አንቶ በተባለው ቦታ ጣሊያኖች በአርበኞች ላይ አሰሳ ተካሄዷል፡፡
<u>ኤርትራ</u> ወሰሬ ዘባር በተባሉ ቦታዎች (ትግራይ) ጣሊያኖች በአርበኞች ላይ አሰሳ አካሄዷል፡፡

## <u>አፕሪል ወር</u>

<u>ሸዋ</u>፡፡ በአባዳይ የነበሩ አርበኞች በጣሊያኖች አፕሪል 4 ጥቃት ተሰንዝሮባቸው ከ5 እስከ 11 ጣሊያኖች አሰሳ ሲያካሄዱ ሰንበቱ፣ በአንኮበር አንደዚሁ፣ 19 እና 20 ወደ ፍቼ በሚመለሱበት ግን ከአርበኞች ተኩስ ስለተከፈተባቸው የአንኮበር አካባቢ ነዋሪዎች መግረያን ለማስረከብ ስላልፈለጉ ቅጣት ደርሶባቸዋል፡፡
<u>የጋላና ሲዳማ</u>፡፡ ከልል በኩሉ ኮንታ ጋርዱላ አሰሳው ቀጥሏል፡፡
<u>ሐረር</u> 1000 የፊታውራሪ በሐዴ አርበኞች ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ አምርቷል፣ ተሰደዋል፡፡ XXX VIII ባታሊዮን ይከታተሏቸው ስለነበር ዘሁድን ተከተፍለዋል፡፡ ፊታውራሪ በኮንዱዶ ይገኝ የነበረ ሶማሊላንድ እንዳይገባ ለመከልከል አንድ ባታሊዮን ተልኮለታል፡፡ በጋራሙለታ የቀሩት አርበኞችን ለማደን አንድ ባታሊዮን ተመድበዋል፡፡ XXX VIII ዓረብ ሶማል ባታሊዮን አርበኞችን ይከታተል የነበረ ከከባድ ውጊያ በኋላ አርበኞች እንዲበታተኑ አድርገዋቸዋል፡፡ ብዙ አርበኞች በሐዴ ያለበት ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ ለመግባት ችሏል፡፡
<u>አማራ</u> ሰፊ አሰሳ በአርማጭሆ አካባቢ ተደርገዋል፡፡

# የ 7 ወሮች ከክረምት በኋላ ክንውኖች በዝርዝር

በእጥሩ በየወሩ የተገለጹ ክንውኖች በቀጠና በመከፋፈል በዝርዝር ይቀርባሉ ቀጠናዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ሀ/ ሸዋ ለ/ ባሕር ሐዲድ ሐ/ አማራ መ/ምዕራብ ሰ/ሐይቆች ረ/ ጨርጨርና አርሲ ሠ/ባሌ ቀ/ ሰላሌ

## ሀ. ሸዋ

ሸዋ ዋና ፀረ ኢጣሊያ ትግል አንዣዥ ማእከል ሆኖ ነበር፣ በተደጋጋሚ ጣሊያኖች አርበኞችን ለመደምሰስ ቢሞክሩም አልቻሉም፡፡ የአርበኞች ቁጥር በጣሊያኖች ግምት ከ9 እስከ 10,000 የሚደርስ ነበረ፣ በዙድን የተከፈሉ ነበረ፡፡

1ኛ. በራስ ካሣ ልጆች የሚመሩ በሰላሌ
2ኛ. ከአዲስ አበባ አዲስ ዓለም መንገድ በፊታውራሪ ዘውዴ አስፋው የሚመራ፡፡
3ኛ. በደብረብርሃን አካባቢ በአበበ አረጋይ የሚመራ፣ የዚሁ ክፍል እስከ ደብረሲና ይደርስ ነበረ
4ኛ. ከደሴ አዲስ አበባ መንገድ እስከ ባሁር ሐዲድ በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመሩ ነበረ፡፡

የኢጣሊያ አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበር፡፡
1ኛ. የዋናው ከተማ ጥበቃ ቡድን
2ኛ. ምሥራቅ ሰሜን ደሴ አዲስ አበባ መንገድ ጥበቃ ቡድን በጀነራል ማሪዮቲ (Mariotti) የሚመራ
3ኛ. ከአዲስ አበባ አዲስ ዓለም መንገድ በኮሎኔል በሊ የሚመራ የባቡር ሐዲድ ጥበቃ የተመደበ

ከሸዋ ሮቢ እስከ አዲስ አበባ ፋታ ሳይሰጡ ከጣሊያኖች ጋራ ሲዋጉ የነበሩ አርበኞች በአበበ አረጋይ የሚመሩ ነበሩ፡፡ በዚሁ መስመር የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ኃላፊ ጀነራል ትራኪያ ነበረ፡፡ ጀነራሉ አርበኞቹን መቋቋም ስላቃተው ከደሴ ክፍ ጦሩ ተመርቶ ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ ሌላ ጀነራል Mariotti ስለነበረ እግረ መንገዱን አርበኞቹን ለማውደም ድጋፍ የሚሰጡ የመንደሮች ቤቶች ለማቃጠል እንዲተባበረው September 14 ለግራዚያኒ ልመና ያቀርባል፡፡ [1] ሰፕተምበር 17 ግራዚያኒ ጀነራል ትራኪያ (Tracchia) በሰየቀው መሰረት ጀነራል ማሪዮቲ (Mariotti) እንዲተባበር ያዝዛቸዋል፡፡[2] ሁለቱ ጀነራሎች የኢንዲጂኒ ጦር (የኤርትራውያን) አዛዦች ናቸው፣ ጀነራል ትራኪያ የ II የኤርትራ ብሬጌድ አዛዥ ሲሆን ጀነራል ማሪዮቲ የIX ብሬጌድ የኤርትራ ኢንዲጂኒ አዛዥ ነበረ፡፡

ጀነራል ማሪዮቲ ለእርዳታ እንዲቆይ የተፈቀደለት ለ10 ቀን ብቻ ነበረ፡፡ ወደ ደብረሲና የሚወስደው መንገድ በአርበኞች ተደጋጋሚ ጥቃት ተቋርጦ ደብረሲና

---
[1] Governo Generale A.O.I Allegati N 8 V II
[2] Governo Generale A.O.I Allegati N 12-19-117



የጣሊያኖች ሰፈር ተከቦ ያለ ግንኙነት ይገኝ ነበረ፡፡ የጀነራል ማሪዮቲ ተልእኮና በቦታው የሰፈሩ አርበኞች ለመደምሰስ ነበረ፡፡

አርበኞች በተጉለት፣ አራምባ፣ ዋዩ፣ ቆላ፣ ሸና ሰፈረዋል፡፡ ተጉለት የሰፈረው የአርበኞች ቡድን 1000 የሰው ብዛት የነበረው ሰፕተምበር 25 የደብረ ሲና የኢጣሊያ ጦር ሰፈር ያጠቃል፡፡ ከደሴ የሚመጣ የጀነራል ማሪዮቲ ጦር ሰፕተምበር 26 ከደብረሲና 8 ኪሎ ሜትር ብቻ ርቆ ይገኝ ነበረ፡፡ በ27 ቀ ጀነራል ማሪዮቲ ጦር ከአርበኞች ተኩስ ይከፈትበታል፡፡ በዚሁ ጊዜ ጀነራሉ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ምንም እንኳን አርበኞች የጣሊያኖች እስካሪ ብዛት አይተው የሸሸ ቢሆኑም 3 ባታሊዮኖች ኤርትራውያን ተከታትለው አርበኞችን ብቻ ሳይሆን ያገኙት ሰው ሁሉ ለመጨረስ ለቀቁዋቸው 45 አርበኞች ተገደሉ፣ በደብረሲና አካባቢ 100 ቤቶች ተቃጥለዋል፣ የአካባቢ መንደሮች በሙሉ እንደወደሙ ይቆጠራል፣ በደብረሲና የሰፈሩ የኢጣሊ ወታደሮችም ከጦር ሰፈራቸው መጥተው ቤቶችን ለማቃጠል ተካፍለው ነበሩ፣ የቀንድ ከብቶች ተዘርፈዋል፣ በእኛ የደረሰ ጉዳት ወደፊት ይገለጻል፣ የጦር አሮፕላኖች በምብ የሚጥሉበት ቦታ ምልክት ሰጥቻለሁ፣ የአካባቢው መንደሮች ሹም ከጣሊያኖች ጋራ ሆኖ ቤቶችን ለማቃጠል ተካፍለዋል፣ ሁለት ቀን ሰረፍት አድርገን ቤቶችን ሙሉ በሙሉ ለማቃጠል ይቀጥላል ብሏል፡፡ ጀነራሉ ከደሴ ሰፕተምበር 12 ተነስቶ 4 ባታሊዮን ኤርትራውያን (ወይንም ኢንዲጂኒ) በመምራት ኦክቶበር 16 አዲስ አበባ እስገባበት ጊዜ ድረስ ስላደረጋቸው ውጊያዎች ረጅም ሪፖርት አቅርበዋል፡፡

1. የደብረሲና ውጊያ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ነበረ፡፡ ከኢጣሊያ ወገን የደረሰው ጉዳት የሞቱ ኢንዲጂኒ 4 የቆሰሉ 9 የጠፉ 1 ነበሩ፡፡
2. ሰፕተምበር 29 አርበኞችን ፍለጋ በደብረሲና አካባቢ ሰሜን ምሥራቅ በተደረገው አሰሳ፣ አብዛኛው በአካባቢው የነበሩ ቤቶች ተቃጥሏል፣ 150 አርበኞች ተገድለዋል፡፡ ብሏል፡፡ ከኢጣሊያ ወገን አንድ መቶ አለቃና አንድ ም/መቶ አለቃ ቆስሏል፣ ከኢንዲጂኒ 12 ተገድለዋል 33 ቆስሏል፡፡
3. ኦክቶበር 4 በደብረሲና አካባቢ ጉድኝምባ ማክፋድ በተባሉ ቦታዎች ብሬጌዱ አሰሳ አድርጎ ሰፈፉ ሰላም የሰፈነበት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ብሬጌዱ ኦክቶበር 6 ከደብረ ሲና ተነስቶ ኦክቶበር 7 ደብረብርሃን ይገባል፡፡
4. ኦክቶበር 9 በጫጫ አካባቢ ተኩስ ተከፍቶበት ከአርበኞች ጋራ ባደረገው ውጊያ የተገኙ ቤቶች (ቱኩል) በሙሉ ተቃጥለዋል፣ 20 አርበኞች (ሽፍቶች) ተገድለዋል፣ ከጣሊያኖች ወገን ምንም ጉዳት አልደረሰም ብሏል፡፡
5. ኦክቶበር 10 በዋዩ በተደረገው ውጊያ 188 አርበኞች (ሽፍቶች) ተገድለዋል፡፡ ብዙ ቆስሏል፡፡ ከጣሊያኖች ወገን አንድ የመቶ አለቃ ቆስሏል፣ ከኢንዲጂኒ 2 ተገድለዋል፡፡ 7 ቆስሏል፡፡ 250 ቤቶች (ቱኩል) ተቃጥለዋል፣ 400 የቀንድ ከብቶች፣250 በጎች 30 ፈረሶች ተዘርፈዋል፡፡
6. ኦክቶበር 11 በደነባ በተደረገው ውጊያ 50 አርበኞች ተገድለዋል፡፡ ከጣሊያኖች ወገን አንድ መቶ አለቃ ቆስሏል፣ ከኢንዲጂኒ አንድ ቢሞት 7 ቆስሏል፡፡ በድምሩ 453 አርበኞች ተገድለዋል፣ ከጣሊያኖች 4 የጦር መኮንኖች ሲቆስሉ ከኢንዲጂኒ 19 ተገድለዋል 66 ቆስሏል፡፡

እስካሁን ጣሊያኖች ለአገዛዛችን ያስጉናል ብለው በወጥመዳቸው አስገብተው የገደሏቸው ወይንም በወጥመዳቸው በማስገባት ላይ የሚገኙ የራስ ካሣ ልጆችና እነ ራስ እምሩ ራስ ደስታ ወዘተ ነበሩ፡፡ እነሱን ከጠፉን ኢትዮጵያን በሰላም እንገዛለን የሚል ተስፋ ነበራቸው፡፡ አሁን ግን ከዚህ በፊት ያልታወቁ የአርበኞች መሪዎች ብቅ ማለት ጀመሩ፣ ከእነሱ አንዱም አበበ አረጋይ ነው፡፡ በአምስቱ ዓመት የኢጣሊያ ትግል አገዛዝ አበበ አረጋይን ለማጥፋት ሳይሞክሩ ቀርተው ሳይሆን ስላቃታቸው በድል አድራጊነት ሊወጣ

ችሏል፡፡ ከደሴ አዲስ አበባ ያለው መንገድ የጦር ኃላፊ ጀነራል ትራኪያ (Tracchia) ስለ አበባ አረጋይ ጽፈዋል[1]፡፡ የጀነራል ትራኪያ 2ኛ ብርጌድ ኢንዲጂኒ 6 ኤርትራውያን ኢንዲጂኒ ባታሊዮኖች ያቀፈ ወንፊራ ብርጌድ ነው፣ 2,17,18, 4,9 እና 21 ባታሊዮኖች// እሱ የሚያደርገው የማጽዳት ዘመቻ ከአዲስ አበባ ወደ ደብረሲና በመጓዝ ነው፡፡ ጫጫ ከመድረሱ በፊት ኦክቶበር 9,1936 ከአርበኞች ከፍተኛ ተኩስ ተከፍቶበት ሆኖም አርበኞቹ በታቸው ለቀው ስለሄዱ መንገዱን ሊቀጥል ችሏል፡፡ ኦክቶበር 10 ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ተካሄዶ 190 አርበኞች ተገድለዋል ብሏል፣ ለማግስቱም ደነባ ላይ ኦክቶበር 11 ሌላ ውጊያ ተካሄዷል፣ የደረሰው ጉዳት አልተገለጠም፡፡ ከደሴ አዲስ አበባ መንገድ የሚሰሩ የኢጣሊያ ሲቪል ሰራተኞች ደኅንነት ለመጠበቅ የጀነራል ትራኪያ 2ኛ ኢንዲጂኒ ብርጌድ በቂ ሆኖ ስላልተገኘ፣ የጀነራል ማሪዮቲ 9ኛ ኢንዲጂኒ ብርጌድ እርዳታ በቂ ስላልሆነ በጀነራል ተሲቶሬ (Tessitore) የሚመራ 7ኛ ኢንዲጂኒ ብርጌድ ኦክቶበር 11 ጠዶ በታው ተልኮ ነበር፣ ነገር ግን ደጃዝማች ፍቅረማርያም አዲስ አበባን ለማጥቃት አቅዷል የሚል ወሬ ስለተሰማ ጀነራል ተሲቶሬ ከሰንዳፋ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ትዕዛዝ ተሰጠው፡፡ ጀኔራል ማሪዮቲም ወደ አዲስ አበባ ቶሎ እንዲመጣ የተደረገው በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ 2ኛ ብርጌድ መንዲዳ ማዚያ በማድረግ ወደ እንኮበር፣ ሞበኪ የአይራራ ሸለቆ፣ ሰምበላት፣ አሰላቱ፣ የነገ ሸለቆ በመሄድ በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ መቀጣጫ ፈጽሟል፣ የመንደርተኞች ባንደዎችም ተካፋይ ነበሩ፡፡ ለጣሊያኖች ብዙ ያስቆጣቸው ከደሴ ወደ አዲስ አበባ ይጓዝ የነበረው በጀነራል ፓዎሊኒ (Paolini) የሚመራ በአንድ የኢጣሊያ ነጭ ዲቪዚዮን ኦክቶበር 18 ቀን ሸዋ አካባቢ አርበኞች ያደረሱት ጥቃት ነው፡፡ በውጊያው አንድ የጦር መኮንን ቆስሏል፣ ተራ የኢጣሊያ ወታደሮች 3 ሞቷል፣ የቆሰሉ 8 ከእነሱ ውስጥም 4ቱ በከባድ ነበሩ፡፡ አንድ ኢጣሊያዊ ወዛደር መንገድ የሚሰራ በድንጋጤ ሞቷል፣ አንድ አሽከሩም ሞቷል፣ አንድ ሲቪል ሾፌር ቆስሏል፡፡ ከአርበኞች 200 ተገድለዋል፣ ከ100 ቤቶች (ቱኩል) በላይ እንዲቃጠሉ ተደርገዋል፣ ኤርትራውያን ወታደሮች ባስቸኳይ ሌሊት ተጉዘው ወደ ሰፈረው እንዲደርሱ ግራዚያኒ ትእዛዝ አስተላልፈዋል፡፡[2] በገጠር የሚሰማራ የኢጣሊያ ጦር ስሚያስፈልገው ሰንቅ ሁሉ ከሚያርፍበት ቦታ ይጠቀም ነበረ፡፡ [3] ከውትድርና ተግባር ሌላ በሕዝቡ ላይ የግሳብ ትሰቀሳ ይደረግ ነበር፣ በታቃራኒዎች ላይ ከባድ ቅጣት ይፈጸም ነበር፡፡ ከጣሊያኖች ጋራ ለሚስማሙ ርሕራሔ የተሞላበት አያያዝ የደረግላቸው ነበር፣ ከእነዚህ ውስጥም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ከጣሊያኖች ጎን ተሰልፈው በታማኝነት ተዋግቷል፡፡[4]፡፡ በሸዋ የነበረው ሁኔታ በአጠቃላይ ሲታይ ከደሴ አዲስ አበባ ያለው መንገድ አርበኞችን ለማራቅ የተደረገ ቢሆንም አርበኞች ግን አልጠፉም ነበረ፡፡

## ለ. ባቡር ሐዲድ

ምዕራባዊ ክፍል ከአዋሽ እስከ አዲስ አበባ ያለው መስመር በሚመለከት ነው፡፡ በዚሁ አካባቢ በየረር ደቦኮዲዮ በካን እንዲሁም በዙቋላ ጋለታ ሲረዱ የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ አርበኞች በአየለ አባ ግርሳ የሚመሩ

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegati 25-29-45 V II
[2] Governo Generale A.O.I ibd Allegati N119 V II
[3] Governo Generale A.O.I ibd Testo p 74 V II
[4] Governo Generale A.O.I ibd Testo p 74 V II



ናቸው፡፡ ሌላ የአርበኞች መሪ ከደጃዝማች አበራ ካሣ ጎን ሆኖ የሚንቀሳቀስ በባቡር መስመር የኢጣሊያ ጦር ሰፈሮችና በዋናው ማእከላዊ ባቡር ሐዲድ አዲስ አበባ ጥቃት የሚፈጽም ደጃዝማች ፍቅረማርያም ነበረ፡፡ ያለማቋረጥ ጥቃቶች ይፈጸሙ የነበሩ የሚቀጠሉ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ኦክቶበር 2 በዱከም ሚና 3 ኪሎሜትር ከዱከም በአንድ ባቡር ላይ የተደረገው ጥቃት ነው፡፡
2. ኦክቶበር 10 ከአቃቂና ዱከም መሐል
3. ኦክቶበር 10 አዳማ አዳስ እና ሞጆ ተብለው በሚጠሩ የኢጣሊያ ባንዳዎች ላይ በዙቋላ ለመፈተሽ ሄደው የነበሩ ከአንድ ሺህ አርበኞች ተኩስ ስለተከፈተባቸው ሸሽተው ወደ ሰፈራቸው ስለተመለሱ ግጭቱ ተወግዷል፡፡
4. በዱከም ወንዝ አጠገብ በዱከምና መልካ ጂሉ ኦክቶበር 12 ቀን በአርበኞች የተሰነዘረው የኢጣሊያ ሚኒስትሮች የሚጓዙባቸው በ2 የታጠቁ ባቡሮች ነበረ፡፡ ሆኖም በባቡሮች የነበሩ አጃቢዮች ጥር ቦታዎች በመያዝ ተከላከለው አርበኞች ወደ የረር ተራራ እንዲሸሹ አድርገዋቸዋል፣ በባቡሩም ያለ ችግር ጉዞውን ቀጥሏል፡፡ ከሰዓት በኋላ ለመቀጣጫ በሕዝቡ ላይ በተደረገው ጭፍጨፋ የ2ኛ ባቡር አጃቢዮች ተካፋይ ነበሩ፡፡ አርበኞች ፊት ለፊት ፍልሚያ ስላልፈለጉ ሸሽተው አምልጠዋል፣ 200 ሰዎች ሞተባቸዋል፡፡ ከኢጣሊያ ወገን 5 የሞቱ ጣሊያኖች 20 የቆሰሉ ነበሩ፣ ከኢንዲጂኒ 1 ሞቷል 3 ቆስሏል፡፡ ለማግስቱ ኦክቶበር 13 በጀነራል ሚስኪ (Mischi) 650 ጣሊያኖች 4 መድፎች ያላቸው በሕዝቡ ላይ ቅጣቱ ቀጥሰዋል፡፡ በዙቋላ አካባቢ 800 የንጉሡ የጋማ ከብቶች ይገኛሉ ስለተባለ ለጣሊያኖች ያደረ ቀኛዝማች ቃደስ ለማረጋገጥ ወደ ስፍራው ይላካል፡፡ ቀኛዝማች ከብቶቹ ዝብረዎች ተከፋፈሉባቸው መኖራቸው ካረጋገጠ በኋላ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ዝብረዎች ከብቶቹን ካልመለሱ ቅጣት እንደሚፈጸምባቸው ብሉ አስጠንቀቃቸው፡፡ ለፍተሻ ወደ ዝቋላ ተልከው ከነበሩ ባንዳዎች 2 ሲሞቱባቸው 8 ቆስሏል አንድ ም/መቶ አለቃና የአዳማ ባንዳዎች አዛዥ ቆስሏል፣ በዝቋላ አጠገብ የሚገኙ 500 ቤቶች /ቱኩል/ በጦር አሬሮፕላኖች እንዲደበደቡ አንድ ሻላቃ ሃሳብ አቅርቦ ለማግስቱ ኦክቶበር 11 ተደብድበዋል፡፡ ጀነራል ሚስኪ ኦክቶበር 13 ሕዝቡንና አርበኞቹን ለመቅጣት በተሰማራበት ጊዜ 2 የኢጣሊያ ወታደሮች ተገድለው የተቆራረጡ አግኝቷል፡፡
5. አርበኞች ከማጥቃት አላቋረጡም፡፡ ከአዳማ ሞጆ መሐል ያለው መንገድ አርበኞቹ ባደረጉት አደጋ ባቡሩ ከሐዲድ ስለወጣ ጀነራል ኦክቶበር ሚስኪ ሌላ ጥቁር ሸሚዞችና (Camicie Nere) እና የሞጆ ባንዳዎች ወደ ስፍራው አሰማርቷል፡፡ መሣሪያ የያዙ ተይዘዋል፣ የተረጋገጡ 50 አርበኞች ተገድለዋል፣ ከአርበኞች 100 ሰዎች ሞቷል፡፡ ከጣሊያኖች ወገን የሞቱ 7 ጣሊያኖችና አንድ ባንዳ ከቆሰሉ 19,14 ጣሊያኖቹ ነበሩ፡፡ አሁን አርበኞች ስለራቁ አካባቢው ሰላም ነው፤
6. ይህ ተደጋጋሚ በባቡሮች የደረሰው ጥቃት የኢጣሊያ ክብር የሚቀንስ ሆኖ ስለታየው ማርሻል ግራዚያኒ አርበኞችን ማጥፋት አስፈላጊ በመሆኑ ጀነራል ጋሊና ኦክቶበር 16 ወደ ቦታው እንዲላክ ሲያደርገው ከራሱ ወታደሮች ጭምር ይዞ ወደ ባቡር ሐዲድ እንዲሰማራ ሲያደርገው የሰጠው መመሪያ የወጫጫ መናገሻ፣ ሱልልታ፣ የረር ተራራዎች በወታደር እንዲያዙ በተለይ በየረር ተራራ በማተኮር፡፡ የጀነራል ማሪዮቲ ወታደሮችም በባቡር ለመጀመሪያ ጊዜ ከሄደ በኋላ በየረር ተራራ እንዲሰማራ ትእዛዝ ተሰጠው፡፡ ግራዚያኒ በጀነራል ጋሊና የሰጠው መመሪያ በየረር ደቦኮዲዮ፣ ዝቋላ የሚገኘው አርበኞችን ለመደምሰስ ለማውደም ጥበቅ የሆነ በሕዝቡ

መቀጣጫ እንዲፈጸም ጀነራል ጋሊና የግራዚያኒ ትእዛዝ ለመፈጸም ተዘጋጅቷል፤ ስለሆም በደቦኮዲዮ በነበረ በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመሩ አርበኞች ላይ ዘመቻ ለመጀመር ይወስናል።

## የደጃዝማች ፍቅረማርያም መገደል

ኦክቶበር 22 ግራዚያኒ የሚከተለው መመሪያ ለጀነራል ጋሊና ሰጥዋል።

1ኛ. ለዘመቻው ያወጣኸው ፕላን አንብቤዋለሁ፤ ይሁን እንጂ አልተስማማሁበትም

2ኛ. ምዕራባዊ ባቡር ሐዲድ የተሰጠዎት ኃላፊነት ቋሚ መሆኑን መውሰድ አለበዎት፤ ኃላፊነትዎም ብቻዎ መውጣት አለበዎት፤ ከሌሎም ለብዙ ንኡስ ክፍል መከፋፈል የለበትም፤ በአንድ አዛዥ ብቻ ሲመራ ሥራው የተቃና ይሆናል።

3ኛ. በስርዎ ሥር የሚሆኑ 1ኛ ተቨረ ዲቪዮን 2ኛ. የማሪዮቲ ብሪጌድ ባለ 4 ባታሊዮኖች ኢንዲጂኒ 3 የታጠቁ ባቡሮች። ዲቪዚዮን ተቨረ ከሁን በፊት እንደነበረው በቋሚ ቦታ መሰፈር አለበት። የማሪዮቲ ባታሊዮኖች በአዛዦቻቸው እየተመሩ ተንቀሳቃሽ ኃይል በመሆን ፋት በታዎች ለመቆጣጠር ሆኖ ዓላማውም የአርበኞች ቡድኖች ለማውደምና ባቡር ሐዲድ መስመር የሚገኙ መንደሮች ለማጥፋት ነው።

4ኛ. በዚሁ ባቡር ሐዲድ በቺረናይካ እንደተከሰተው ተመሳሳይ ነው፤ በጦር አዛዦች እሻቸው የሰጡና ሽፍቶች እየተባሉ ለሁለት ክፍሉ የማየት አዝማሚያ እየታየ ነው። ይህ በቺረናይካ ለጣሊያኖቹ መጥፎ ውጤት የሰጠ እንቅስቃሴያችን ያሰናከለ ነው። ይህ አስተሳሰብ መወገድ አለበት፤ ሁሉም ምንም ልዩነት ሳይደረግ እንደ ሽፍቶች መቆጠር አለባቸው ምክንያቱም እሻቸው የለጡ አመቺ ሁኔታ እየጠበቁ እንደገና ሽፍቶች ይሆናሉ።

5ኛ. አርበኞች (ሽፍቶች) የተከማቹባቸው ቦታዎች የረር፤ ዙቋላና ደቦኮዲዮ ተራራዎች ናቸው። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ሕዝቦች እየተረዱ ነው ወደ ባቡር ሐዲድ እየመጡ መስመሩን እንዲቋረጥ እያደረጉ አሻጥር የሚሰሩብን። ስለዚህ በእነዚህ የሽፍቶች ማእከሎች በሚገባ ሰርጎ መግባት ያስፈልጋል፤ ወንበዴዎችና ኗሪ ሰዎችን ያለ ምንም ርሕራሔና ምሕረት ማውደም ያስፈልጋል።

6ኛ በእነዚህ ቦታዎች የጦር አሬዮፕላኖች፤ የማውደም ሥራ ፈጽሟል፤ ነገር ግን ሥራቸው የወታደሮች የማውደም ሥራ ካልተጨመሩበት የተሟላ ሊሆን አይችልም።

7ኛ. በአሁኑ ወቅት ከቡርነትዎ የማሪዮቲ ብሪጌድ ኢንዲጂኒ ማማሾቹ በጦር ሰፈር እያስተመሯቸው ይታያል። ይህ አሰራር መታረም ያለበት ነው፤ ሁሉም የኢንዲጂኒ ወታደሮች ተንቀሳቃሽ መሆን አለባቸው፤ ወደ ዓማፂያን ሰፈሮች ሰርጎ መግባት አለባቸው እነሱ ብቻ ሳይሆን በጀነራል ሚስኪ የሚመሩ የተቨረ (Tevere) ዲቪዚዮን ወታደሮችም ከጦር ሰፈሮች ውጭ መሰማራት ይችላሉ። ይህ ካልሆነም ለጀነራል ሚስኪ ሌሎች ወታደሮች ሊመደቡለት ይቻላል፤ በዚሁ ዓይነት ከጀነራል ማሪዮቲ ጋራ ሆኖ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል።



8ኛ. ክቡርነትዎ እንደሚያውቁት በአንድ ቦታ ብቻ ትኩረት ከሰጠን ሽፍቶቹ በሌላ አካባቢ ጥቃት ሊፈጽሙ ስለሚችሉ መዘንጋት የለብንም። ስለዚህ ሁሉ አየር ኃይል ተገቢ ወሳኝ ትብብር ሊያደርግ ይችላል።

9ኛ. እላይ በገለጹኩት መሠረት የበላይ ኃላፊነት በእኔ ሆኖ የእርስዎ ልምድ ያለው የቆ የቅኝ ገዥዎች ችሎታ ታክሎበት ግሪጋጋሚ በሰሚወሰዱት ውሳኔዎች እንዲያስታውቁኝ እጠይቀዎታለሁ። የዚሁ ኮፒ ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትርና ለመንግሥት መሪ ለዱቼ መላኬን ልከያለሁ[1] በትእዛዙ መሠረት ጀነራል ጋሊና ለባቡር ሐዲድ ከሁሉ እስጊ የነበረው የደጃዝማች ፍቅረማርያም አርበኞች የሰፈሩበት በደቦኮዲዮ ለመጀመር ወሰነ።

ኦክቶበር 25 ዘመቻው ተጀመረ። ጀነራል ማሪዮቲ ከመሰንቆ ⌐2ኛና
21ኛ 2 ባታሊዮኖችን በመምራት ሻለቃ ላኖቲ ⌐2 ባታሊዮኖች የ9ኛ ብሪጌድ
17ኛና18ኛ ከእላበ ወደ ደቦኮዲዮ አመሩ። ሁለቱ ቡድኖች እንደመገናኛቸው መንደሮቹን እያቃጠሉ ግታው ደቦኮዲዮ ሲደርሱ ደጃዝማች ፍቅረማርያም ወደ በሜን ወደ በካን የተዛወረ መሆኑን ሰላወቁ ተድሞ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ደጃዝማች ወደአለበት ወደ በካን ለማገሥቱ አመሩ። እስከ እጅሬ ድረስ ሀገሩ በረሃማ ስለሆነ ወንበዴዎቹን ያስተናግዱ መንደርተኞች፤ እያወደሙ ብቻ ማሪዮቲ ከመሰንጪቲ ሻለቃ ላኖቲ Lanuti ከእላበ፤ ሁሉም የ9ኛ ብሪጌድ ባታሊዮኖች ኦክቶበር 26 ማታ ወደ በካን አመሩ። ከእጅሬ እንዳለፉ ከአርበኞች ተኩስ ተከፈተባቸው። ከባድ ውጊያ በጨበጣ ሳይቀር ተደረገ። ደጃዝማች ፍቅረማርያም በዚሁ ውጊያ ተገድለዋል፤ ከእሱ ሌላ ነጋ ድራስ በገብ፤ ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ፤ ግራዝማች ማተቡ፤ አቶ መኩንን እንደዚሁም ደባ የተባለው ነጋዴ ለደጃዝማች ፍቅረማርያም የባቡር ሐዲድ ቡሉኖች መፍቻ ያቀበል ነበረ የተባለው በዚሁ ውጊያ ተገድለዋል። ከአርበኞች የተገደሉ 600 ነበሩ። ከቆሰሉ ባሻ እምሩና ሌሎች ነበሩ፤ በሕዝቡ ላይ የደረሰ ጉዳት በጣም ብዙ ነው። ብዙ ሰዎች ቤታቸውን ትተው በየእቅጣጫው ተበታትነዋል[2] ከጣሊያኖች ወገን ሁለት ጦር መኩንኖች ሲሞቱ 3 ቆስሏል፤ 10 ኢንዲጂኒ አርትራውያን ሞቷል 43 ቆስሏል፤ ጣሊያኖች ተደብቷል። የበካን ውጊያ እንዳበቃ የማሪዮቲ ብሪጌድ ወደ ባልቴ በማምራት በደጃዝማች ባልቻ የሚመሩ አርበኞች እንዲደመስሱ ግራዚያኒ ትእዛዝ ይሰጣል። የኢጣሊያ 9ኛ ኢንዲጂኒ ጦር ወደ ባልቴ በሚገዙበት ጊዜ አርበኞች አላገጠሟቸውም ሆኖም አገሪ መንገዳቸው የባልቺ መሪናዮስ ሽንኩራ መንደሮች ቤቶች እንዲቃጠሉ አድርገዋል።[3] ማርሻል ግራዚያኒ የማሪዮቲ ብሪጌድ ወደ ባልቺ እንዲያመራ ትእዛዝ ሲሰጠው ደጃዝማች ባልቻ ይገኛል ስለተባለ እሱ እንኳን ቢሸሽ ቤቱና ያካባቢ መንደሮች እንዲወድሙ ብሏል።[3] ለዝቋላ አቡን ለአንድ አርበኛ እንኳን መጠለያ ከሰጠ ያለ ምሀረት ቤተክርስቲያኖችን ገዳምን እና መነኩሴዎችን በሙሉ እንደማወድማቸው በእኔ ስም ንገራቸው ብሏል።

በበካን ውጊያ ጣሊያኖች ደጃዝማች ፍቅረማርያምን በመግደላቸው ድል ተቀዳጅተናል ብለው እርስ በርሳቸው ይመሰጋገኑ ነበር፤ በመጀመሪያ 300 አርበኞች ገድለናል ብለው መግለጫ ካወጡ በኋላ ቆይተው ግን የተገደሉ አርበኞች 600 ነበሩ ብሏል። ሆኖም አርበኞች አልቃቸው ኦክቶበር 26 ቢገደልባቸውም 3 ቀን ባልሞላ ጊዜ ኦክቶበር 29 ቀን በጨፈናርሚ 6 ኪሎ ሜትር ከጨፈዶንሳ ተሰባሰበው መታየታቸው ታክቲካዊ ማረጋገጥ እንጂ

---

[1] Governo Generale A.O.I Allegato N 136 V II
[2] Governo Generale A.O.I Testo p 234 V II
[3] Governo Generale A.O.I Testo N 96 V II
[3] Governo Generale A.O.I Allegato N 179 V II

ሽንፈት እንዳልገጠማቸው ያሳያል፤ ገድለናል ያሉዋቸው 600 አርበኞችም ተዋጊዎች ሳይሆኑ ሴቶችና ሕፃናት የአካባቢ መንደሮች መሆናቸውን ያስረዳል። ጄኔራል ጋሊና ቦታ የተየሩ አርበኞች እየመሰላሉ፣ አሁንም የዐኛ ኢንዲጂኒ ብሪጌድ አንድ ቦታሊዮን ይሰጠኝ ብሎ አስፈትዖ ከአካባቢው የተውጣጡ ባንዳዎችም በመጠቀም በባልቺና በየረር ለ2ኛ ዙር ውጊያ ይዘጋጃል። በዚሁ መሠረት በ4 ጄኔራሎች የሚመሩ ወታደሮች መደበኛና ባንዳ ወደ የረር ተራራ ኦክቶበር 30 ይሰማራሉ።

1. ጄኔራል ቶሲተረ ከአዲስ አበባና ከለንዳፋ
2. ጄኔራል ቲራባሲ (Tirabassi) ከራዲዮ ማዚያ
3. ጄኔራል ማሪዮቲ ከባልቺ
4. ጄኔራል ጋሊና ዋና አዛዡ ራሱ ከአዳስ (አድአ)

የዚሁ ዘመቻ ዓላማ ተዋጊውን ጠላት ለማግኘት ሳይሆን በሕዝቡ ላይ ሽብር ለመፍጠር የኢጣሊያ ኃያለኛነት ትልቅነት ለማሳየት፣ እልገዛም ብሎ አርበኞችን የሚረዳ ሕዝብን ለማጥፋት፣ በግልጽ ባወጡት ሰትራቴጂ ሕዝቡን በመግደል ቤቶቻቸውን ለማቃጠል ንብረታቸውን ለመዝረፍ ነበረ። የአየር ኃይልም ተካፋይ ነበረ። ጄኔራል ማሪዮቲ ብቻ ያከናወነው ተግባር ማሊያኖች በትልቅ ኩራትና ጀግንነት ሲገልጹ ኦክቶበር 30 ጨፈዶጋላ እንደደረሰ 2 መንደሮች አቃጥለዋል ብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሽፍቶችን ረሽነዋል፣ 150 ከብቶችን ዘርፈዋል ብሏል። [1] ጄኔራል ጋሊና ራሱ ስለፈፀመው ጀብዱ ለግራዚያኒ ሲያስታውቅ በጨፈዶንሳ፣ ጨፈገርማ፣ እፋ፣ እፍቱ፣ ለሳሊ ዘመንደሮች ሰሬው ጭፍጨፋ ማካሄዱን፣ ብዛት ያለቸው የቀንድ ከብቶችን ዘርፎ ለባንዳዎች ማከፋፈሉን ከጥቂት አርበኞች ጋራ ግጭት ማድረጉንና 5 መግደሉን ጽፈዋል።[2] ማሊያኖች ጭማሪያ ከታጠቁ አርበኞች ጋራ ጦርነት ገጥመው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ገድለናል ሲሉ ከእነሱ ወገን እስር የማይሞሉ ሞተብናል ሲሉ የማያሳምን ነው ማሊያኖች ይገድሉ የነበሩ መሣሪያ የሌላቸው ሰላማዊ ሰዎች ሴቶችና ሕፃናት ነበሩ። ግራዚያኒ የአርበኞች መናኸሪያ ብሎ ትኩረት የሰጠበት ቦታ ዝቋላ ነበር። ግራዚያኒ ወደ ዝቋላ ሕዝቡን እንዲጨፈጭፍና ያሰማራቸው ወታደሮች ወትሮው እንደሚያደርገው ኢንዲጂኒ ኤርትራውያን አልነበሩም፣ ደፋሮች ተብለው ቅጽል የተሰጣቸው በእሊቶቸው በጀኔራልና ቆንስል ተብሎ የሚጠራ ጄኔራል ሚስኪ (Gen. Mischi) የሚመሩ ባለ ጥቁር ሸሚዞች የኢጣሊያ ፋሽዝም ልዩ ወታደሮች የተሾረ ዲቪዚዮን አባሎች ነበሩ። ጀራል ሚስኪ ለቅርብ አለቃው ለጄኔራል ጋሊና ያቀረበው ሪፖርት[3] ከሞጆ ኖቨምበር 14 1936 ስላደረገው ዘመቻ ባለ ጥቁር ሸሚዝ ፋሽስቶች ብቻቸው አልዘመቱም አዲስ ሞጆ አዳማ የሚባል ስም የነበራቸው ባንዳዎች አብረው ዘመተዋል።

1. ኖቨመበር 9 በአንድ ኢጣሊያዊ የሚመሩ ባንዳዎች ወደ ወምበርና ኩተማ የሚባሉ መንደሮች ልኮ አሰሳ ባደረጉበት ጊዜ ከሕዝቡ ተቃውሞ አላጋጠማቸውም አርበኞች አላገኙም ተዶቶች በውስጣቸው ተገኝቷል የተባሉ የ3 ያልተያዙ አርበኞች የአንድ ቄስ ቤት እንዲቃጠሉ ተደርገዋል። ኖቨምበር 10 ደፋሮች ባንዳዎች ጂዳ ወደ ተባለው መንደር ሄደው እንዲፈትሹ አደረገ ሕዝቡ የተለመደ የእርሻ ስራው ሲያካሂድ አገኙት የጦር አሪዮፕላኖች ግን እኩለቀኑን በቦምብ ይደበድቡ ነበር ሕዝቡ ከኢጣሊያ ወታደሮች ከጦር አሪዮፕላኖች የበቀል እርምጃ ሳይወሰድባቸው ለመኖር ከፈለጉ ማድረግ

(1) Governo Generale A.O.I Allegato N 205 V II
(2) Governo Generale A.O.I Allegato N 213 V II
(3) Governo Generale A.O.I Allegato N 329 V II



የሚገባቸው ነገራቸው፤ አንድ ጨዋ የታጠቀ ሰው ስለተገኘ በባላባቱም አደገኛ ሰው መሆኑን ስለነገራቸው ተረሸነ። ባንዳዎቹ ፍተሻ እንዲያደርጉ ታዝዘው መሣሪያ የተገኘባቸው ቤቶች ተቃጥለዋል። ሌሊት ኖቨምበር 12 ባንዳዎች ለፍተሻ ተልከው ቼካላ እና ባሬሳ ቦታ ወንድማማቾች የተባሉ እንዲይዙ ታዘው አንዱ ብቻ ተገኘ፣ ሕዝቡ በሰጠው ጥቆማ ተገደለ። ዞሬ ኢጣሊያ ትስቶሳ ያደርጋል የተባለ መምሬ ግዋ በሌሊት ተይዞ ታሰረ፣ በተደረገው ተኩስ ሁለት አርበኞች ተገደሉ ሌሎች ቆስለው ሸሽተው አመለጡ፤ መንደሩ አርበኞች የተገኙበት እንዲቃጠል ተደረገ። በነጋታው ቀን መምሬ ግዋ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በጥይት ተገደሉ። ለኢጣሊያ ታማኝ የነበሩ ሁለት ባላባቶች ለሁለት መንደሮች ተሾሙ። ሲሬዎ ጢቾ ማሊያኖች ገሊታ የተባለው ቦታ አርበኞች አሉበት ስለተባለ፣ 600 የነበሩ አርበኞች ኖቨምበር 19 ቀን ባንዳ አዳማን ልከው እንዲዋጉ አድርገው 100 አርበኞች ሲገደሉ ከባንዳዎች 20 ተገድለው 30 ቆስሏል። የደፋሮች "Arditi" ፋሽስቶች ዘመቻ አንድ ሰው ሳይዋጉባቸውና ሳይቆስልባቸው በወኪሎቻቸው በባንዳዎች ተዋጋን ብለው ወደ ሰፈራቸው ተመልሰዋል።

ሲሬዎ ጢቾ። ማሊያኖች በሲሬዎና ጢቾ አርበኞች የተሰበሰቡበት ነው ውጊያ ይገጥመናል በሚል ጥርጣሬ ነበረ የተጓዘ፣ አርበኞች ግን ደፋሮችና የአዳማ ባንዳዎች ሲመጡባቸው ትንሽ ተኩሰ ከፍተው ለተቁላቸው እንደዚሁም የ9ኛ ኢንዲጂኒ ሲመጡባቸው ያለ ውጊያ ለቀቁላቸው ሲሬዎን ሕዝቡም ተከትሎዋቸው ሸሽቶ ለቀዋል።

በበቀለ እና አባመርሳ የሚመሩ አርበኞች በበኩላቸው፣ ማሊያኖች ጢቾን በያዙበት ቀን ዲሰምበር 3 በአሩሲ በነበረው የማሊያኖች ጊዜያዊ ጦር ሰፈር ጥቃት ፈጽሞባቸው ሸሽተው ወደ አዳማ እንዲገቡ አድርገዋቸዋል። አሪዮፕላኖች ግን ባገኙት ድል እንዳይኩሩ በቦምብ ደብድበዋቸዋል። ከዚህ በኋላ ማሊያኖች በባቡር ሐዲድ መስመር ሰላምና መረጋጋት የተፈጠረ መስሏቸው ነበር።

## ሐ. አማራ

ጉጃም። አንድ ቡድን የኢጣሊያ ደጋፊ 2 ቡድኖች ተቃዋሚ ኩተቃዋሚ ዘለቀና በበላይ ይግዙ ናቸው።
በላስታ ቢሆምድር በደጃዝማች ወንድወሰን የሚመሩ ናቸው።
በደባርቅ ወረኢሉ በአበበ አረጋይ የሚመሩ አርበኞች ነበሩበት።

## የደጃዝማች ወንድወሰን ካሣ መያዝና መገደል።

ደጃዝማች ወንድወሰን በማሊያኖች ለመያዝና ለመገደል የበቃው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለማሊያኖች እጄን አሰጣለሁ ብሎ በማስማቱና ንግግር በማድረጉ ነው። ማሊያኖች ደጃዝማች እጄን እሰጣለሁ ማለቱ ሐሰት መሆኑን ተረድተናል ሆኖም እንቅስቃሴውን ለመከታተል እንዲመቸን ከበን ለመያዝ እንዲመቸን ንግግርችን እናካሄድ ነበር ብሏል። ማሊያኖች በ3 አቅጣጫዎች ከበባ አድርገውበታል፣ 1ኛ ከደሴ 2ኛ ከሰቆጣ 3 ከደብረታቦር፣ እያንዳንቸው ከ1000 በላይ የሰው ኃይል ነበራቸው። የአማራ ክልላዊ መንግሥት መሪና የክልሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የሚል ሹመት የነበረው ጀኔራል ፒርዚዮ ቢሮሊ ደጃዝማች ወንድወሰን በልዩ ልዩ በደ

በጣሊያኖች ወጥመድ የገባ መሆኑንና ለማምለጥ የማይችል መሆኑን በዓወቀ ጀግንነቱንና የጦር ታክቲኩን ለማሳየት በጣሊያኖች ጦር መኩንኖች የሚመሩ ታጣቂዎች ለመግራት ወደ ደብረታቦር መጣ። በ3 አቅጣጫዎች የዘመቱ ደጃዝማች ወንድወሰንን ለመያዝ የተሰማሩ ታጣቂዎች ከበባቸውን አጠናክተው ተገኝተዋል። ይሁን እንጅ ከበባውን ለማጠናከር አስተማማኝ ለማድረግ ጣሊያኖች 2 አዲስ ተጨማሪ ተዋጊዎች አስገርቷል። ከወልዲያና ከላሊበላ የመጡ ባንዳዎች የደጃዝማች ቅርብ ተባባሪዎች ለመያዝ ችሏል። የ5ኛ ዲቪዚዮን ባለጥቁር ሸሚዝ ፋሽሲቶችና የኤርትራ ራያ ጋላ ሌሎች የባንዳ ቡድኖችም በዘመቻው ተካፋይ ሆነው ነበር የደሴው በአመዴ ዓሊ የሚመሩ ባንዳዎችም ተካፋይ እንዲሆኑ ታዞ ነበር።

በዚሁ ጊዜ ግራዚያኒ ደጃዝማች ወንድወሰን እንደሚያዝ ሙሉ በሙሉ ርግጠኛ ስለነበረ ኖቬምበር 9 ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ባስተላለፈው ቴሌግራም ጀነራል ፒርዚዮ ቢሮሊ ዋና ጊዜያዊ ሰፈሩ ወደ ደብረታቦር ያዛወረ መሆኑን ከገለጸ በኋላ በዚሁ ቀን ደጃዝማቹ እንደተያዘ ሕግ ፊት ሳይቀርብ እንዲገደል የነገረው መሆኑን ገልጸዋል። ኖቬምበር 10 ከደሴ ተነስቶ የዘመቱ በሻምበል ፋሬሎ (Farello) የሚመሩ የወሎ ባንዳዎች በ1ኛ ተራ ቁጥር አሳይ የተጠቀሱ በተከዜ ወንዝ በአንድ ዋሻ ይገኝ የነበረ ደጃዝማች ወንድወሰንን በቁጥጥራቸው ሊያውሉ ችሏል፣ ወዲያውኑ ተረሽነዋል። የዘመቻው አዛዥ ጀነራል ፒርዚዮ ቢሮሊ በየቀኑ የሚያስተላልፋቸው ከነበሩ ቴሌግራሞች የኖቬምበር 13[1] ቴሌግራም ግራዝማች አበጥ ደጃዝማች ወንድወሰን ቀኛዝማች ሹመት ሰጥቶ የንጥዓና መከት ገዢ አድርጎት የነበረ በጣሊያኖች ቁጥጥር ስር እንደዋለ አንድ የኢጣሊያኖች መረጃ አቀባይ ከሰፍራው ወደ ላሊበላ የመጣ ደጃዝማች አሬዮፕላኖች በጣሉት ቦምብ ታፋው ቆስሎ በዓይኑ እንዳየው መመስከሩ [2] ታጣቂዎች ከዳተኞች እንደተረሸኑ በደረሳቸው እነሱም የተድጥ አስካሪ መሬዝጊ ወልዴ የ19ኛው ባታሊዮን ዓዲ ተክሌ ወረዳ እንዲሁም የ17ኛ ባታሊዮን ባልደረባ የነበረው የተድጥ አስካሪ የጓዲ ኳላ ወረዳ አባል የነበሩ ናቸው። ይህ ጣሊያኖች ከእነሱ የከዱ እየለቀሙ በጭካኔ የመግደል ሁኔታ በታማኞች ኤርትራውያን መሐል እንዴት ጥቂት እንክርዳዶች ተገኙ ብለው ንዴታቸውን በጊዜው ያሳዩት የነበረ ነው።

ከደሴ ጀነራል ሪካርዲ (General Riccardi) ዲሴምበር 11 ቀን 1936 ወደ አዲስ አበባ ባስተላለፈው ቴሌግራም በሻምበል ፋሬሎ (Farello) የሚመሩ የወሎ ባንዶች ዲሴምበር 10 ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከተከዜ በአንድ ዋሻ አንድ ቀን የፈጀ ከባድ ከበባ በኋላ ደጃዝማች ወንድወሰንን የያዙ መሆናቸውን ገልጿል። ጀነራሉ በዚሁ ቀን በሌላ ቴሌግራም ደጃዝማቹ የተገደለ መሆኑን አለመሆኑን አላውቅም ካልተገደለ በትእዛዙ መሠረት እንዲገደል ለሻምበል ፋሬሎ እነግረዋለሁ ብሏል። እንደገና በዚሁ ቀን ዲሴምበር 11 ቀን በላከው ሌላ ቴሌግራም ደጃዝማች ወንድወሰን ዲሴምበር 10 ከምሽቱ 3 ሰዓት ተኩል የተገደለ መሆኑን ገልጿል።

ጀነራል ፒርዚዮ ቢሮሊ በበኩሉ ወደ አዲስ አበባ በዚሁ ቀን ዲሴምበር 11 ቀን በላከው ቴሌግራም በደጃዝማች ወንድወሰን እንደተደረገ ሁሉ በደጃዝማች ከበደ እና በአቡነ ይስሐቅም እንዲፈጸም አስፈላጊውን ትእዛዝ አስተላልፌያለሁ ብሏል። እንደዚሁም በተድጥዎቹ የኢጣሊያ አስካሪ ከዳተኞች ርሕራሔ እንዳይደረግ ትእዛዝ ሰጥቻለሁ ብሏል። በዚሁ ቀን በጀነራል ፒርዚዮ

[1] Governo Generale A.O.I Allegato N 315 V II
[2] Governo Generale A.O.I Allegato N 639 V II



ቢሮሊ ስለ ደጃዝማች ወንድወሰን መገደል ባጠባው መግለጫ ለተካፈሉ ሁሉ ምስጋናውን አቅርቧል።

1. ለፋሽስቶች መጀመር ለላለበት ለ1ኛና 5ኛ ባለጥቁር ሸሚዞች
2. ለባለ ጥቁር ሸሚዞች አንደኛ ግሩፕ የኤርትራ
3. ለኢንዲጂኒ 10ኛ 24ኛ እና 25ኛ ባታሊዮኖች
4. ለአየር ኃይል
5. ለላስታ ቤጌምድር ወሎ በለሳ ሰሜን ሕዝብ
6. ለኤርትራ ዘገሬ ገዥ ያለማማ ራያ ጋላ ባንዳ በመፍቀዱ.

## የዶባ ውጊያዎች፣ አበበ አረጋይ

ባንዳንድ የዘሃች ሹሞች አማካኝነት እንደ አበበ አረጋይ የመሳሰሉት የራስ ካሣ ልጆች የፈጠሩት ስሬ የሽፍትነት እንቅስቃሴ በዶባ እንዳለ ብለው ጣሊያኖች ስለተገነዘቡ፣ ሽፍቶችን ለመደምሰስ ከደሴ በአምባሰል ባንዳ እየተረዳ በኮ/ቶስቲ (Tosti) የሚመራ 6ኛ ኢንዲጂኒ ብርጌድ ኖቬምበር 16 ሽፍታው ይልካሉ። ሆኖም በአበበ አረጋይ የሚመሩ አርበኞች በቀላሉ የሚበገሩ ሆነው አልተገኙም። የጣሊያኖች ዶባ ዋና ጦር ሰፈር አድርገው አካባቢውን ሁሉ ለመቆጣጠር የነበራቸው ዓላማ በአርበኞች ብርቱ ተቃውሞ ሊሳካላቸው አልቻለም፣ በዶባ ጦር ሰፈር ትወለና እንዲቀመጡ ተደረጉ።

በሌላ የአማራ አካባቢም ደጃዝማች ወንድወሰን ዚገዎልምዎ በዘመቻ በባዚል ደሰታ የሚመሩ፣ ከእም ሐጀር ጎንደር የሚወስደው መንገድ በውብነህ ተሰማ የሚመሩ አርበኞች ስለነበሩ፣ ጣሊያኖች አርበኞችን ማጥፋት ስላልቻሉ የአርበኞች ደጋፊ የተባሉ ነዋሪዎች ፌብርዋሪ 1937 ጭፍጨፋ ያካሄዱ ነበር። የአርበኞች ዋና ምሽግ የነበረው ዘአርማጭሆም ተመሣሣይ ጭፍጨፋ ያካሄዱ ነበር።

ወደ ዶባ ስለ ዘመቱው በኮሎኔል ቶስቲ የሚመራ ስለ ኢንዲጂኒ 6ኛ ብርጌድ ጦር ኖቬምበር 26 የደሴ ወታደራዊ አዛዥ ጀነራል ሪካርዲ እንዳወጣው ቀኛዝማች አበበ አረጋይ 6 መትረየስ አንድ መድፍ 2000 ተዋጊዎች እንዳሉት ገልጿል፣ ውጊያው ተካሂዶ ከጣሊያን ወገን አንድ አስካሪ ሲሞት፣ አንድ የጦር መኮንንና 6 አስካሪ ቆስሏል፣ ከአርበኞች ወገን 100 ሰዎች ተገድለዋል፣ የአካባቢው ሕዝብ አርበኞችን ይረዳል ስለተባለ፣ አካባቢው በጦር አሬዮፕላኖች እንዲደበደብ ብሏል። ከዚህም ሌላ ኮሎኔል ቶስቲ አርበኞችን ለመቋቋም ኃይል ስለሚያንሰው፣ በደሴም በቂ ወታደር ስለሌለ፣ ከአዲስ አበባ 40 የጦር መኮንኖች፣ 43 የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 1832 ኢንዲጂኒ ወታደሮች 928 የጋማ ከብቶች ወደ ዶባ እንዲላኩ የሚል ሃሳብ አቅርቦ ነበር። ግራዚያኒ ግን ለወደፊት በሰፍራው ሰፊ ዘመቻ ለማድረግ እቅድ ስላለው ለጊዜው ወታደሮች መላክ አስፈላጊ አይደለም ብሎ ሃሳቡ ውድቅ አደረገው[1]። የጦር አሬዮፕላኖች በአርበኞች ላይ ባደረጉት ድብደባ፣ ከአርበኞች ተተኩሶባቸው በተደጋጋሚ ተመትቷል ብሏል።

## ጎንደር

የአማራ ክልላዊ መንግሥት መሪ ጀነዋሪ 27, 1937 ለአዲስ አበባ በላከው ሪፖርት[2] የውቤ ተሰማ ሚስት ተይዛ እንደታሰረች፣ በመረባት አካባቢ

[1] Governo Generale A.O.I Allegato N 468 VII
[2] Governo Generale A.O.I Allegato N 1021 V II

መንደሮቹን ማቃጠል ዘመቻ ቀጥለዋል ብሏል፡፡ የተቃጠሉ ቤቶች የጦር መሣሪያ ነበራቸው ብሏል፡፡ ሕዝቡ ውብነህ እጁን ለጣሊያኖች እንዳይሰጥ እየገፋፋው ይገኛል፡፡ 57 ሰዎች በጥርጣሬ ተገድለዋል፡፡ የአማራ ቁስቋም ሕዝብ ብዙ በሉግ ሐጀር ጉንደር የደረሱ ግጭቶች ተጠያቂ ሆኖ ስለተገኘ ተደምስሰዋል፤ የምሽግ ቦታዎች ተገኝቷል፤ የአንድ ኢጣሊያዊ የተገደለ መታወቂያ ወረቀት ተገኝቷል፡፡ ሕዝቡ መኖሪያውን እየለቀቀ ወደ ምዕራብ እየተሰደደ ነው፡፡ በአቸፈር ባቢል ደሴት ለመያዝ ሙከራ ተደርገዋል፡፡ ተራራ ዮሐንስ የተባለው መንደር ከባቢል ደሴት ተባባሪ በመሆኑ እንዲወድም ተደርገዋል፡፡

በአርማጭሆ በአንድ ባታሊዮን ኢንዲጂኒና በባንዳ አማካኝነት አካባቢውን ለመቆጣጠር በተደረገው አሰሳ አንዳንድ ቦታ ሕዝቡ ወታደሮችን በደስታ ተቀብሉዋቸዋል፤ መሣሪያም አስረክበዋል፡፡ በማይተባበሩ መንደሮች ያስርጎራሉ የማቃጠል ስራ ተከሄዷል፡፡ 2 ጭቃ ሹሞች 3 ወንበዴዎች (አርበኞች) ተገድለዋል ብሏል፡፡[1]

## መ. ምዕራብ ክፍለተ ሀገሮች

የምዕራብ ክፍላተ ሀገሮች ለመቆጣጠር ጣሊያኖች የተጠቀሙበት በሚሲዮናዊ አባ ቦሬሉ አማካኝነት ነው፤ ይኸውም ግራዚያኒ በጥቅምት 28, 1936 ለአባ ቦሬሉ (Padre Borello) በጻፈለት ደብዳቤ በግልጽ ያስረዳል[2]፡፡ በጥቅምት 29 የኮሎኔል በሊና የራስ ኃይሉ ባንዳዎች አምቦን በቋሚነት ይይዛሉ፡፡ ኮሎኔል በሊና ራስ ኃይሉ ጦርና ከደጃዝማች ሃብተማርያም ጋራ እና ከአባ ቦሬሉ ግንኙነት በመፍጠር ሕዝቡን ወደ ጣሊያኖች ለመሳብ የፖለቲካ ስራ ያካሂዳሉ፡፡ የኢጣሊያ ወታደሮች ወደ ለቀምት በሚዘምቱበት ጊዜ አባ ቦሬሉ የኢጣሊያ የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊ በመሆን ያገለግላል፤ ባላባቶች የቀድሞ ሹሞችን ያስተባብራል፤ ቋሚ መኖሪያው ለቀምት ያደርጋል፡፡

1. በአሮፕላን የራዲዮ መገናኛ ማሽን እና ሠራተኛው ይላክል
2. በአሮፕላን ለአባ ቦሬሉና ለደጃዝማች ሃብተማርያም የሚያገለግሉ የጦር መሣሪያዎች በተለይ ለአባ ቦሬሉ የሚያገለግሉ ባንዳዎች ለማቋቋም አስልጣኞች የጦር መኮንኖች ይላካሉ፡፡
3. የማሪያ ተሬዛ ብር ለአባ ቦሬሉና ለደጃዝማች ሃብተማርያም በአሮፕላን ይላካሉ፤ ሌላም ማንኛውም አስፈላጊ ሁሉ ይላካሉ፡፡

አባ ቦሬሉና ደጃዝማች ሃብተማርያም የሚያከናውኑት ተግባር በእምቦ ቱወስና አይቀርም በሁሉ አቅጣጫ መሆን አለበት፤በተለይ ከጐሐንስና ከሆሣዕና ወንድማማቾች ግንኙነት መፍጠር ያስፈልጋል፤ በኃይልም ቢሆን ከነሱ ያለውን መንግሥት እንዲቋቋሙ፤ ግራዚያኒም ደብዳቤ አጽፍላችዋለሁ ብሏል፡፡ ወለጋና ምዕራብ ኢትዮጵያ ያለ ደም መፋሰስ በጣሊያኖች እጅ እንዲገቡ ወሳኝ ሚና የተጫወተው ኢጣሊያዊ ሚሲዮናዊ አባ ቦሬሉ (Padre Borello) የተባለው ነው፡፡ በአባ ቦሬሉ አማካኝነት ሜይ 5/ሚያዝያ 27 አዲስ አበባ በጣሊያኖች እጅ እንደወደቀች በጁን ወር 26 ሰኔ 19, 1928 በጦር አሮፕላኖቻቸው አማካኝነት በቂ ጥናትና ዝግጅት ሳያደርጉ ጣሊያኖች በከፍተኛ ባለሥልጣኖቻቸው አማካኝነት በለቀምት አሮፕላን ማቢያ ለማረፍ ያደረጉት ሙከራ በጥቂት ለሀገር ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን ጀግንነት ከሽፎባቸው በለቀምት አሮፕላን

[1] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 260 V II
[2] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 21 V II



ማቢያ ያረፉ ጣሊያኖች በሙሉ ተገድለዋል፡፡ ኦክቶበር ወር በአባ ቦሬሉ አማካኝነት አስተማማኝ ሁኔታ በለተፈጠረላቸው ጣሊያኖች እንደገና በተሳካ ሁኔታ በለቀምት አሮፕላን ማቢያ ለማረፍ ችለው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም በራሳቸው ሙሉ እምነት አልነበራቸውም፡፡ 1/ንጌሌ የነበረው ራስ እምሩ ወደ ለቀምት እየገሰገሰ ነው የሚል ወሬ ይሰማ ነበር፡፡ 2/ በመጀመሪያ የጣሊያኖች ወደ ለቀምት በሬራ ጣሊያኖችን ፈጅቷል ተብለው የሚጠረጠሩ የቀድሞ በወለጋ የጦር መኮንኖች ማስጠለያ የሰጠው ያሉባቸው 300 የኢትዮጵያ የጦር መኮንኖች በለቀምት አካባቢ አሉ የሚል ወሬ ይሰማ ስለነበረ አሁንም ጣሊያኖች ፍራት ነበራቸው፡፡ 3/ ደጃዝማች አበራ ካሣ ከሰላሌ ከራስ እምሩ ጋራ ለመገናኘት ወደ ለቀምት አምርቷል የሚል ወሬም ይሰማ ነበር 4/ ፊታውራሪ ሃብቴ እና ገብረወልድ የተባሉ እያንዳንዳቸው 30,000 ጦር በመምራት ጣሊያኖችን ለመዋጋት ከጎሬ ወደ ለቀምት እየገሰገሱ ናቸው የሚል ዜናም ከጂቡቲ ተሰራጭቶ ነበር፡፡ 5/ ከንጉሡ የተላኩ በሕዝቡ ላይ ቅስቀሳ እያካሄደ ነው የሚል ወሬም ተሰምቶ ነበር፡፡

## New times and Ethiopia News

ኦገስት 22 ቀን 1936 በእርእሰት የተጠቀሰው ጋዜጣ ስለ ምዕራባዊ ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ የሚገልጽ ጽሑፍ አውጥቷል[1]፡፡ ሻምበል ብሮፊል የተባለው እንግሊዛዊ በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ቀይ መስቀል ኃላፊ የነበረ ነው፡፡ Capitain Brophil ሻምበል ብሮፊል ምዕራባዊ ኢትዮጵያ ጉብኝቶ ከልሉ ዘዓለም መንግሥታት ሞግዚትነት እንዲስተዳደር የሚል አስተያየት ነበረው፡፡ ምዕራባዊ የኢትዮጵያ መንግሥት መኖር በእንግሊዝ ፓርላማና የጋዜጦቹ ክርክር ያስነሳው ጉዳይ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ስታንሌይ ጀቮንስ Prof. Stanley Jevons ኢትዮጵያን የሚደግፍ ማሕበር የክብር ፕሬዚዳንት የሆነ ከሻምበል ብሮፊል አንድ ደብዳቤ ይደርሰዋል፡፡ ስለ ምዕራብ ኢትዮጵያ በትክክል መናገር ይቻላል፤ ምክንያቱም በኢጣሊያ ሠራዊት ገና አልተያዘም፤ ስለ ሌሎች ክፍላተሀገሮች የሚደርሱን ዜናዎች የተምታቱ ናቸው፡፡ የምዕራባዊ ኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ የሆነችው ጎሬ ናት፡፡ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ በጎሬ ጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ተቋቁሞ ይገኛል፡፡ መንግሥቱ የሚመራው በራስ እምሩና በደጃዝማች መስፍን እየተረዳ በቢትወደድ ወልደጻድቅ ነው፡፡ ቢተወደድ ወልደጻድቅንና ራስ እምሩን አነጋግሬያቸዋለሁ፤ ሁሉም የነገሩኝ ከአማራም ሆነ ከጋላ የተውጣጣ ሠራዊት ለመመልመል ተስፋ አላቸው፤ ነገር ግን የጦር መሣሪያ የላቸውም፡፡ በየአጋጣሚ ይቀርብልኝ የነበረ ጥያቄ የመንግሥታቱ ማሕበር እርዳታ ሊያደርግላቸው ይችል እንደሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም የዚሁ ዓይነት ተስፋ ካለ ኢትዮጵያ በማኅበሩ ሞግዚትነት ስር እንድትሆን ብለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የጊዜያዊ መንግሥት አባላት ከንጉሠ ነገሥቱ ያለ ማቋረጥ በራዲዮ ግንኙነት አላቸው፡፡ ሌሎች የጊዜያዊ መንግሥት አባላት 1/ ነጋድራስ ወልደሰማያት 2/ ነጋድረስ ብረሃን ሥላሴ 3/ ፊታውራሪ በፈቃዱ 4/ ልጅ ይልማ ድሬሳ 5/ ፊታውራሪ ዮሐንስ ጆቴ 6/ የደጃዝማች ሃብተማርያም ወኪል ናቸው፡፡ ምዕራብ ኢትዮጵያ ምን ያህል ጊዜ በሰላም እንደምትኖር አይታወቅም የዝናም ወቅት (የክረምት) እንዳለቀ፤ ጣሊያኖች ወደፊት ገፍተው ምዕራብ ኢትዮጵያን ከያዙ እንደ ሌሎች ክፍላተ ሀገሮች ምዕራብ ኢትዮጵያም ወደ ሥርዓት

[1] Governo Generale A.O.I. ibd Allegato N 57 VII

እልበኘነትና ሲታይ እንዳትወድቅ ያሰፈራል፡፡ በሀገር ውስጥም ሆነ (በእንግሊዝ ሀገር) በመንግሥቱ ማኅበር ውስጥ ምዕራብ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ሰር እንዳትወድቅና በከንቱ የንፁሐን ደም ማፍሰስ እንዳይደርስ ግፊት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልተደረገ የሚመጣው ውጤት በጣሊያኖች በሚጣል ቦምብና በጋዝ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የንፁሐን ሕዝብ ሞትና የዚሁ ለም መሬት መውደም ይሆናል፡፡ የመንግሥቱ ማኅበርም ምዕራብ ኢትዮጵያ በራሱ ሞግዚትነት ሰር እንዲስተዳደር ባለማድረጉ በኃላፊነት ያስጠይቀዋል፡፡ የኢጣሊያ ወደፊት መግፋት እንዲቆም አድርጉ! የመንግሥታቱ ማሕበርም ቶሎ ብሎ እንዲንቀሳቀስ አድርጉ፡፡ የአማራና የጋላ ሕዝብ በእንግሊዝ ሕዝብ ያላቸው እምነት ስሜት የሚቀሰቀስ ነው፣ እርዳታ ሳይደረግላቸው ከቀረ ከፍተኛ ወንጀል ይሆናል ጠዙት ብሏል፡፡

## ምዕራብ ኢትዮጵያ (ወለጋ) ያለ ደም መፋሰስ በኢጣሊያ እጅ መውደቅ

እላይ የተጠቀሰው ደብዳቤ ጣሊያኖች እላትመው ሲያወጡ የሰጡት ትችትና ማስተባበያ የለም፡፡

ሰፕተምበር 7, 1936 አባ ቦሬሉ ለግራዚያኒ ያቀረበው ቁ 9 ሪፖርት በቁ 7 Allegati ታትሞ ወጥቷል፡፡ ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከተቆጣጠሩ ጀምሮ በየጊዜው ለግራዚያኒ ደብዳቤ ሪፖርት ይጽፍ ነበር፣ በአማካኝ በወር 2 ጊዜ፡፡ በዚሁ ሪፖርት አባ ቦሬሉ ስለ ምዕራብ ኢትዮጵያ በተለይም ስለ ለቀምት የነበረው ሁኔታ ለግራዚያኒ በሰፊው አስረድቷል፡፡ የጻፋቸው ሪፖርቶች ሁሉ ለማወቅ ቢቻል ዘሚሲዮናዊው በሰተፈጸመው የስለላ ስራ የበለጠ ግንዛቤ እናገኝ ነበር፡፡ ስለ ደጃዝማች ሃብተማርያም ለጣሊያኖች ታማኝነት አስረድቶ ግራዚያኒ ደብዳቤ እንዲጽፍለት ተማጽኖዋል፣ እንዲሁም ለ2ኛ ጊዜ ጣሊያኖች በለቀምት አሬዮፕላን ማቢያ ቦታ ስለሚያርፉበት ሁኔታ ኮሎኔል በይስትሮኪ Baistrocchi በአየር እየጣለለት ይሰጡት ስለነበሩ መመሪያዎችና ግንኙነቶች ጽፏል፡፡

ሰፕተምበር 27 ግራዚያኒ አባ ቦሬሉ ባሳሰበው መሠረት ለዳጃዝማች ሃብተማርያም ለፊታውራሪ ሞሳ ጂጂዮ ለሌሎችም ባላባቶች ስለ ኢጣሊያ መንግሥት ታላቅነት በማውራት ደብዳቤ ጽፈዋል፣ ሰፕተምበር 30 (መስከረም 20, 1929 ዓ.ም.) ደጃዝማች ሃብተማርያም መልስ ሰጥቷል፡፡ ኮሎኔል ባይስትሮኪ ሰፕተምበር 29 የለቀምት አሬዮፕላን ማረፊያ ደኅንነት ካረጋገጠ በኋላ ከአባ ቦሬሉ ከተሰማ በኋላ ኦክቶበር 2 ከግራዚያኒ አስፈቅዶ በለቀምት አሬዮፕላን ማረፊያ ቦታ በደኅና ማረፍ ችሏል፡፡

ኦክቶበር 2 ግራዚያኒ በለቀምት የኢጣሊያ አሬዮፕላን ያረፈ መሆኑን ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ለሶና (Lessona) በላከው ቴሌግራም ከአባ ቦሬሉ የተላከለት ሪፖርት በማስተላለፍ ነው፡፡ አባ ቦሬሉ በዚሁ ሪፖርቱ ካወሳቸው ብዙ ጉዳዮች ስለ ቀኛዝማች በለው የአፄ ኃይለሥላሴ ልዩ ባለሟል ከኢየሩሳሌም ተልኮ ለቀምት መሰንበቱ ገለጸዋል፡፡ ኦክቶበር 14 ቀን 1936 14 የጦር አሬዮፕላኖች ከፍተኛ የአየር ኃይል ባለሥልጣኖች ያሉበት ለቀምት አሬዮፕላን ማረፊያ አርፈው ውለው ማታ ሁሉ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል፡፡ ይህ ዕለት ለቀምት በኢጣሊያ ቁጥጥር ስር መሆኑዋን ቢቆጥሩትም በየብስ የሚጓዝ የኢጣሊያ ሠራዊት ለቀምት እስኪደርስ በዜና ማሰራጫዎች ለመግለጽ ተቆጥበዋል፡፡ ጣሊያኖች የመጀመሪያ ሥራቸው በለቀምት ባንዳዎች ማቋቋም ነበር፡፡



## ለቀምትን ለመያዝ የኢጣሊያ የአየር ወረራ ከሸፈ

ጣሊያኖች አዲስ አበባ እንደተቆጣጠሩ መሶሊኒ ምዕራብና ደቡብ ከፍላተ ሀገሮች ሳይውል ሳያድር ኢጣሊያ እንድትቆጣጠራቸው ፍላጎት ነበረው፡፡ ግራዚያኒ ግን ይህ በየብስ የማይሞከር መሆኑን ስለተረዳ፣ የአለቃውን ፍላጎት ለማሟላት ሌላ ዕቅድ ይፈጥራል፡፡ በአባ ቦሬሉ አማካኝነት በለቀምት ደጃዝማች ሃብተማርያም የኢጣሊያ ደጋፊ መሆኑን ማረጋገጫ በማግኘቱ፤ ቅኝ ግዛቶች ለመያዝ የሚደረጉ ጦርነቶች ድፍረት ከ ታከለበት ሁሉ ነገር የሚቻል ነው በሚል አስተሳሰብ፣ በአየር ወረራ ተደርጎ፣ ከደጃዝማች ኃብተማርያም በማስማማት፣ የመጀመሪያ የኢጣሊያ ያጦር አሬዮፕላኖች ለቀምት እንዲያርፉ የባንዳ ተዋጊዎች በማቋቋም፣ ከደጃዝማች ሃብተማርያም ታማኞች ጎን ተሰልፈው ሀገሩን እንዲቆጣጠሩ ከተደረገ በኋላ መደበኛ የኢጣሊያ ጦር በአየር ወደ ለቀምት ማጓጓዝ ነበር፡፡ ለዚሁ ተግባር የተመረጡ የመጀመሪያዎቹ የኢጣሊያ የጦር መኮንኖች የሚከተሉት ነበሩ፡፡ 1. የአየር ኃይል ጀነራል ማልዮኮ (Magliocco) 2 ሎካቴሊ (Locatelli) 3. ኮሎኔል ካልደሪኒ (Calderinil) የኢጣሊያ ሠራዊት የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ የነበረ በአዲስ አበባ የኢጣሊያ ኢምባሲ ወታደራዊ አታሼ የነበረ 4 የኮንሶላታ ሚሲዮናዊ አባ ቦሬሉ ለብዙ ዓመታት በለቀምት ኗሪ 5 መሐንዲስ ፕራሶ (Prasso) 6 ከኢትዮጵያ ወገን የኢጣሊያ ተባባሪና ደጋፊ ልጅ ደረጀ የቢትወደድ መኮንን ደምሰው የአርጆ ሀገረ ገዥ ልጅ፡፡

በወለጋ የጦር ት/ቤት የተመረቁ 150 ኢትዮጵያውያን ጦር መኮንኖች በስፍራው የሚንቀሳቀሱ በደጃዝማች ነሲቡ ልጅ የሚመሩ መኖራቸውን ስለሰማ ግራዚያኒ የኢጣሊያ ጦር አሬዮፕላኖች በለቀምት ከሚያርፉ በአርጆ እንድያርፉ ፈልጎ ነበር፡፡ አባ ቦሬሉ ግን ከሌሎችም የዘመቻ አባላት ድጋፍ በማግኘቱ በለቀምት እንዲያርፉ መረጠ፡፡ ጁን 25 አቡነ ሳንታ (Monsignor Santa) በለቀምት ተተክሉ የሚውለበለብ የኢጣሊያ ባንዲራን ከግራዚያኒ መኖሪያ ቤት ተገኝቶ ባርኮታል፡፡ ጁን 26 አሬዮፕላኑ በ8 ሰዓት ለቀምት ዐረፈ፡፡ ደጃዝማች ሃብተማርያም በአየር በተወረወረ መልእክት እማካኝነት ስለተነገረው ሰውና ለጭነት የጋማ ከብቶች ወደ አሬዮፕላን ማቢያ ልኮ ነበር፡፡ ጣሊያኖች በአሬዮፕላን ማቢያ ለማደር ወሰኑ፣ ከግራዚያኒ ጋራ በራዲዮ ግንኙነት አድርገው እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት ድረስ ደኅና መሆናቸውን ይገልጹ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ግንኙነታቸው ተቋረጠ፣ ምን እንደደረሰባቸው አልታወቀም፡፡ ጁን 26 ሁኔታውን ለማጣራት ከአዲስ አበባ ወደ ለቀምት ተልኮ 3ቱ አሬዮፕለኖች የተቃጠሉ መሆናቸውን አይቶ ተመለሰ፣ ከዘመቻው አባላት ከሞት የተረፈ አባ ቦሬሉ ብቻ ነበረ፡፡ አንድ የአሬዮፕላን ሠራተኛ ቆስሎ ከሞት አምልጦ በፊታውራሪ ሞሳ ቤት ተደብቆ የነበረ አርበኞች ተኩስ ከፍተው ገደሉት፡፡ ደጃዝማች ሃብተማርያም ግን ጣሊያኖች በለቀምት ከተማ በቀል ይወስዳሉ በሚል ፍራቻ ከለቀምት ሸሽቶ ወጥቶ ነበር፡፡ የነገሩ ማብራሪያ የተገኘው አባ ቦሬሉ ጁን 30 በጻፈው ሪፖርት ነው፡፡

3 ወር በኋላ 27 ሰፕተምበር ኮሎኔል ባይስትሮኪ በለቀምት ለማይ በረራ ያደርጋል፡፡ ኦክቶበር 2 በአሬዮፕላን ማቢያ ወርዶ ከአባ ቦሬሉና ደጃዝማች ሃብተማርያም ጋራ ይገናኛል፡፡ ኦክቶበር 8 በአባ ቦሬሉ ፊትና ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በለቀምት ግቢ የኢጣሊያ ሰንደቅዓላማ ይሰቅላል፡፡ ኦክቶበር 11, ሁለት አሬዮፕላኖች አርፈው የራዲዮ ተክኒሺያኖች በለቀምት እንዲቀመጡ ይመደባሉ፡፡ ከዚሁ ቀን ጀምሮ በየቀኑ የኢጣሊያ ጦር አሬዮፕላኖች ወደ ለቀምት ይመላለሳሉ፡፡ ኦክቶበር 14 ጣሊያኖች ለቀምት

በቁጥጥራቸው መሆኗን ለማለት እንዲችሉና የመጀመሪያ ዓላማቸው ባንዳዎች ማጽዳት እዲችሉ 13 የኢጣሊያ የጦር መኰንኖች 23 ተራ ወታደሮች ለቀምት ያሳርፉሉ። ኦክቶበር 24 ከአዲስ አበባ ወደ ለቀምት ይገሰግስ የነበረው አገሬኛ የኢጣሊያ ጦር 1ኛ 6ኛ 8ኛ የኤርትራውያን ኢንፋንጀሪ ባታሊዮኖች እንደዚሁም 3ኛ መድፈኛ ኢንፋንጀሪ በኩሉኔል ማልታ እየተመሩ ለቀምት ገቡ። በዚሁ ቀን አንድ የኢጣሊያ ጦር አሬሮፕላን ወደ ስዮ በመብረር ለጆቴ ልጆች ወንድማማቾች ከአማራ የባርነት አገዛዝ ኢጣሊያ ነፃ እንድታወጣቸው የሚል መልእክት ወትንዋል።[1] ከዚህ በኋላ ጣሊያኖች ጊዜያዊ አስተዳደራቸው በባላባቶች መስርተው ለእያንዳንዱ ባላባት 200 ብር ደጃዝማች ሃብተማርያም 1500 ብር (ማሪያ ተሬዛ) ደመወዝ ፈተዱላቸው። ለቀምትን ለመያዝ ተመድቦ የነበረው የራስ ኃይሉ ባንዳና የኩሉኔል ቤሊ (Belly) ጦር ነበረ፣ ደጃዝማች ሃብተማርያም ግን የጣሊያኖች ባንዳ ታማኝ ቢሆንም ደጃዝማች ሃብተማርያም አማራ ነኝ እንዳታመጡብን በማለት ስለተቃወመ በኩሉኔል ማልታ የሚመሩ ኢንፋንጀሪ ኤርትራውያን ወታደሮች ለዚሁ ተግባር ተተኩ። የኩሉኔል ማልታ ጦር ወደ ለቀምት እየገሰገሰ መሆኑን ደጃዝማች አበራ ካሣና ወንድሞቹ አምቦን ለመያዝ ሃሳብ እንዳላቸው የሚል ዜና ለጣሊያኖች መረጃ ስለደረሳቸው ግራዚያኒ አምቦን የተቆጣጠሩ የኢትዮጵያ አርበኞች በአስቸኳይ የኩሉኔል ጦርን እንዳይወጉ ወደ ለቀምት ጉዞውን እንዲያፋጥን የሚል ትእዛዝ ስለሰጠው በ2 ቀን የመጨረሻዎቹ 100 ኪሎ ሜትር እንዲሸፍን ተገዶ ነበር። ለዚሁ ጀብድም ከመሶሊኒ የደስታ ቴሌግራም ተልኮለታል።

ግራዚያኒ ኦክቶበር 28 ኬንምቤላ ከአንድ የውጭ ሀገር ዜጋ የተላከ ቴሌግራም በደረሰው መሠረት የጆቴ ልጆች ወንድማማቾች በዩብዶ ስፍረው ከራስ እምሩ የሚሰነዘረውን ጥቃት ለመቋቋም ዝግጁ ናቸው። እንደዚሁም በኒምቢ የሚገኙ የደጃዝማች ሃብተማርያም ወታደሮች ለዚሁ ዓላማ ተዘጋጅተው ይገኛሉ ካለ በኋላ እናንተ ጣሊያኖች በምትሰጧቸው መመሪያ መሠረት የጋራ ጠላታችን ለማውደም ዝግጁ ነን ብሏል።

## የግራዚያኒ ጥላቻ በአማራ ሕዝብ ላይ

ለቀምት በጣሊያኖች እጅ ከወደቀች በኋላ ግራዚያኒ ኖቬምበር 3 በአርጆና በወርባ የሚገኙ አማራ የራስ እምሩ ደጋፊ መሆናቸውን የሚል መረጃ ይደርሰዋል። ቀደም ብሎም ኩሉኔል ማልታ ኦክቶበር 28-31 የራስ እምሩ ደጋፊ የተባሉ ቡድኖች ለመደምሰስ 8ኛ 2 የኢንፋንጀሪ ባታሊዮን እና 300 ሰዎች ያሉበት የለቀምት ባንዳ ወደ አርጆ ልኮ የአካባቢው ገጠር የነበረው አበበ ብሩ ከእነዚተሰቡና 25 ባለመብመንኛ ተከታዮቹ በግዳታ እጃቸው ለጣሊያኖች እንዲሰጡ መገደዳቸውን የሚገልጽ ሪፖርት ለግራዚያኒ ይደርሰዋል።

ይህ ሁሉ ምክንያት በማድረግ ግራዚያኒ ለኩሉኔል ማልታ በላከው ቴሌግራም አበበ ብሩ ወደ ለቀምት ተወስዶ ከዚያ ወደ አዲስ አበባ ባስቸኳይ በአሮፕላን እንዲላክ ብሎ ካዘዘው በኋላ፣ ስለ አማራ የሆኑ ሰዎች በሚመለከት[2] "አማራመንገዶችሁ የምታገኙት አማራ ሁሉ መፍጀት እንደሚያስፈልግ እምነቱ መሆኑን ይገልጽለታል። ምክንያቱም ኩሉኔሉ አበበ ብሩ ከተያዘ በኋላ ለቀሩት አማሮች የዚሁ ዓይነት ተግባር እንዳይፈጽሙ እናስረዳቸዋለን፣ እንመክራቸዋለን ብሎ ሪፖርት አቅርቦ ስለነበረ ለአማሮች

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 149 V II
[2] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 239 V II





በወሊጋ ያገኛችሁትን አማራ ሁሉ ግደሉ ብሎ ትእዛዝ [illegible] የጦር ግንባር ወንጀል የፈጸመ በሊሉቸም ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የጦር ግንባር ወንጀል የፈጸመ ወስኝ ማርሻል ግራዚያኒ

ለማስረዳት መሞከር ከንቱ ድካም መሆኑን ይገልጽለታል። ስለ አማሮች ጉዳይ ኩሉኔሉ በጥሞና እንዲያስብበት አንድ የዓረቦች ተረት ይጠቅስለታል። የዓረቦች ተረት "አንድ እባብ በመንገድ ካገኘህ ሳትነካው ልታልፈው ትችላለህ አንድ አማራ ካጋጠመህ ግን ጭንቅላቱን ጨፍልቀው" የሚል መሆኑን ገልጾ፣ ተረቱን ከመከተል ሌላ አማራጭ እንደሌለ መመሪያ ይሰጠዋል።

## የጂማ፣ ሳዮ፣ ዩብዶ መያዝ

ጣሊያኖች ለቀምት ከተቆጣጠሩ በኋላ ሳዩም በጆቴ ልጆች ወንድማማቾች እማካኝነት በእጃቸው እንዲገቡ ስለሚቆጠር ወለጋ በሙሉ እንደተቆጣጠሩ ይገምቱ ነበር። ሳዮ ከጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ኃይሎች ጥቃት ለመከላከል የጆቴ ልጆች ወንድማማቾች የነበራቸው 5000 ተዋጊዎች።

ሀ/ 2500 በፊታውራሪ የሐንስ ስር ሆነው ከራስ እምሩ ከአደራ ዩብዶ የሚመጣ ጠላት ለመከከል ተሰማርቷል።

ለ/ በፊታውራሪ ሆማዕና የሚመሩ 600 ታጣቂዎች ከጎሬ የሚመጣ ጠላት ከቢትወደድ ወልደጻድቅ ጥቃት ለመከላከል ተሰማርቷል።

ሐ/ 1000 ታጣቂዎች በልጅ እስራኤል ሆማዕና የሚመሩ ከቢን ሻንቱል የሚመጣ የጠላት ጥቃት ለመከላከል ተሰማርተው ነበር።

በቤን ሻንጉል የነበረ ሁኔታ የቆየ እርስ በርስ የሥልጣን ሽኩቻ ከልሆነ የኢጣሊያ ግዛት ለመጋፋት አልነበረም። በግዮ እንደሚታየው ጣሊያኖች እንዳወጡት፦

ሀ/ አሶር ፣ ጉድሩ፣ ቶሩጊ፣ ከምባታ፣ ወላሞ፣ ኖኖ የአርበኞች ቡድኖች ቢኖሩም የኢጣሊያ አገዛዝ ደጋፊ ተብለው የገመቷቸው ነበሩ።

ለ/ በጅማ ፀክንቲባ ጠናጋሻው የሚመሩ 2000 አርበኞች ይቆጣጠሩት ስለነበረ ውጅንብር የሰፈነበት አካባቢ ሆኖ ነበር፣ ሆኖም ለጣሊያኖች ባደረ በአባ ጆቢር እማካኝነት ጣሊያኖች ሀገሩን ለመቆጣጠር ብዙ ችግር አላጋጠማቸውም።

ሐ/ የጉማ፣ ሊሙ እናሪያ፣ ከፋ፣ ጊሚራ ሕዝብ አቋም የታወቀ አልነበረም፣ ምክንያቱም የእነዚህ ወረዳዎች ሀገረ ገዢ የነበረው ደጃዝማች ታዬ ጉሉላቴ አዲስ አበባ በጣሊያኖች እጅ ከወደቀችበት ጊዜ ጀምሮ በይፋ እጁን ለጣሊያኖች ስጥቻለሁ ቢልም የጎሬ የጊዜያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ውክልና ተቀብሎ ነበር።

መ/ ኢሉባቦርና ማጂ ለጣሊያኖች በግልጽ የሚቃወሙ ነበሩ። የኢጣሊያኖች ዋና ዓላማ ራስ እምሩ ወደ ጂማ እምርቶ አካባቢውን ተቆጣጥሮ ከራስ ደስታ ጋራ እንዳይገናኝ ለማድረግ ነበረ።

# ወደ ጅማ ጉዞና የጅማ የደጃዝማች ባልቻ መገደል

ከአዲስ አበባ በየብስ ጅማን ለመያዝ ኃላፊነት የተሰጠው ብላባ ጆቢር እየተረዳ ኩሉኒል ፕሪንቺፓለ ነበረ። ዘግች መራዊቱ የተዋቀረው በአስካሮች ብቻ ነበረ።

ሀ/ 45ኛ ባታሊዮን ከ10ኛ ብሪጌድ የተወሰደ

ለ/ 1000 የአባ ጆቢር ባንዳዎች

ሐ/ መድፈኛ ክፍል ከ7ኛ ብሪጌድ የተወሰደ መሳሪዎች

ድምር 200 ሁሉም አገረ መንገዳቸው ሌሎች ወዶዘማቾች የሚተባተሉበት ኖቬምበር 4 ከአዲስ አበባ እንዲነሳ ሆነ። አገረመንገዳቸው የደጃዝማች ባልቻ አርበኞች የሰፈሩበት ይደርሳሉ። ኩሉኒል ፕሪንቺፓለ አርበኞችን ለማጥቃት በቻለቃ ሮሌ (Rolle) የሚመሩ 500 ታጣቂዎች ይመድባል። ከባድ ውጊያ ከተካሄደ በኋላ አርበኞቹ ይሸነፋሉ፤ ደጃዝማች ባልቻ ተማርከው ይረሸናል። ኖቬምበር 10 ጊቤ ይደርሳሉ፤ ኖቬምበር 12 አባልቲ ይደርሳሉ። ኖቬምበር 14 ኩሉኒል ፕሪንቺፓለ ጅማ ለሚገኘው ከንቲባ ጋሻው ጠና እጁን እንዲሰጥ ደብዳቤ ይልክለታል፤ ለማስፈራሪያም በጅማ ሰማይ ላይ የኢጣሊያ ጦር አሪዮፕላኖች እንዲበሩ በጠየቀው መሠረት 26 አሪዮፕላኖች በጅማ ብቻ ሳይሆን በጎሬ፣ ጋምቤላ፣ ደምቢዶሎ፣ ሰዮ፣ ዋርቀ የማስፈራሪያ በረራ ያደርጋሉ። ኖቬምበር 18 ጣሊያኖች ጅማ ገብተው በሱልጣኑ (አባ ጂፋ) ቤተመንግሥት ባንዲራቸው ተከለው ይውለበለባል።

## የሳዩ ወረራ በአየር

ጣሊያኖች በየብስ አድካሚ የአገረኛ ወታደራዊ ዘመቻ በፊት በአየር ኃይል ወታደሮቻቸውን ዘለቀምት አውርደው እንደተቆጣጠሩዋት ሁሉ ሳዮን (ደምቢዶሉ) ለመቆጣጠር በዚሁ ዘዴ ተጠቅሟል። ኖቬምበር 11 ቀን 9 የኢጣሊያ አየር ኃይል አሪዮፕላኖች ሳዮ፣ ዐረፉ፣ የፊታውራሪ ሆማዕና ታጣቂዎች በታላቅ ክብርና ደስታ ተቀበሏቸው። ግራዚያኒ ኖቬምበር 15 ለጆቴ ልጆች ዮሐንስና ሆማዕና በጻፈው ደብዳቤ የጋላ ሕዝብ ከሐበሻ ባርነት ነፃ ይወጣል እንደ ባሪያ ሳይሆን እንደ ነፃ ሰዎች ትሆናላችሁ፤ በታላችሁ እንድትረጉ ብሎም አስጠንቅቋቸዋል[1] ጣሊያኖች ሳዮ እንደገቡ እንደልማዳቸው ባንዳ ማቅጠር ጀመሩ። በኩሉኒል ማልታ የሚመራ 1ኛ ኢንዲጂኒ ብሪጌድ ከለቀምት ወደ ዩብዶና ጊምቢ ሲንቀሳቀሱ በጄኔራል ተሲተሪ የሚመራ 7ኛ ኢንዲጂኒ 7ኛና 16ኛ ባታሊዮኖች ፈረሰኛ ያቀፈ ብሪጌድ ዘለቀምት ብቻቸውን ለመተካት ኖቬምበር 6 ቀን ከአዲስ አበባ ተነሳ ኩሉኒል ማልታ ኖቬምበር 14 ጊምቢ ደረሰ። የአርጆ ብላታ ድሬሣ መኩንን የተባለው ለጣሊያኖች እጁን ሰጥቻለሁ ካለ በኋላ ለጣሊያኖች ደጋፊዎች ለማግኘት ቅስቀሳ እንዲያደርግና ባንዳ እንዲመለምል ተነግሮት፣ እሱ ግን ከራስ እምሩ በምስጢር ሲሰማማ ስለተገኘ ኩሉኒል ማልታ አንድ ባታሊዮን ኢንዲጂኒና ባንዳ ልኮ ተይዞ እንዲታሰር አድርገዋል፣ የአርጆ አካባቢም ትጥቅ አስፈትተዋል። በኩሉኒል ሚላኖ የሚመራ 16ኛ ብሪጌድ ኖቬምበር 15 ከአዲስ አበባ ወደ አምቦ ለቀምት ለመሄድ ተጓዘ። ከብላታ ድሬሣ ጋራ 6 የዘታች ሹሞች 29 ተዋጊዎች ሕዝቡ መሣሪያ እስኪያስረክብ እንደ መያዣ ታስረው ወደ ለቀምት ተወሰዱ።

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N. 333 V II






የሽሬ ጦርነት ጀግና ራስ እምሩ በሱዳን በደቶኛነት ለመኖር በእንግሊዞች የተሰጠው ዕድል ሳይቀበል በጣሊያኖች ላይ ጦርነት በመቀጠል ስለመረጠ 500 ወታደሮች በመምራት በፍልሚያ ላይ እንዳለ ብዙት ባላቸው የኢጣሊያ ጦር የተከበበ መሆኑን በመቀ ሕዝቡን ዘወትር ከማስጨረስ ለጣሊያኖች እጁን ለመስጠት መርጦ ወደ ኢጣሊያ ወህር ተወስዶ ታስር ከቆዬ በኋላ የ2ኛ ዓለም ጦርነት ... ተመልሰዋል።



Ras Imirù



ሲልቪያ ፓንክርስት እንግሊዛዊት የሰብአዊ መብት ተሟጋች ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመችው የወታደራዊ ወረራን በመቃወም (New times and Ethiopia News) የተባለው ጋዜጣ መስራችና ሥራ አስኪያጅ የኢትዮጵያ ሐቀኛ ወዳጅ

10ኛ የኮሎኔል ሚላኖ ብሬጌድ በ54ኛ፣ 55ኛ እና 56ኛ ባታሊዮኖች እንዲሁም በ10 ቡድን የኢንጂነር መድፈኛ የተገነባ ነው። ጣሊያኖች የራስ እምሩ እንቅስቃሴ ቀን በቀን ይከታተሉት ነበር። በመጨረሻ የደረሳቸው መረጃ ተክለአብ የተባለው 1000 ታጣቂዎች ያሉት ከጅማ ተባርሮ ኖቬምበር 24 ወደ ኮሳ ሄዷል፣ ከእሱ ጋራም ከንቲባ ጠናጋሻው፣ ብላታ ተክለሐዋርያት ይገኛሉ።

## የራስ እምሩ ከበባና መያዝ

አሁን ራስ እምሩ ያለበት ከሞላ ጎደል ስለታወቀ ከቦ ለመያዝ ጣሊያኖች ያደረጉት እንቅስቃሴ እንደሚከተለው ይመስላል።

ሀ/ የኮሎኔል ማልታ ጦር ወደ ጎሬ ያመራል ኖቬምበር 19

ለ/ ከአዲስ አበባ በኮሎኔል ግራሲ (Grassi) የሚመራ 18ኛና 12ኛ የኤርትራ ባታሊዮን ወዘተ ያሉበት ኃይለኛ ጦር ለማጠናከሪያ ወደ ጅማ ይላካል።

ሐ/ ከለቀምት 7ኛ ብሬጌድ በጀኔራል ተሲቶሬ የሚመራ ወደ ዲደሳ ተጉዞ ኖቬምበር 19 ከአባ ጆቢር ተዋጊዎች እንዲቀላቀል
ኖቬምበር 26 ጎሬ በኮሎኔል ማልታ ጦር ወደቀች። የጎሬ አቡነ ሚካኤል እመመኝ ብሎ ወደ ኮሎኔል ማልታ አልቀረበም በተደረገው ማጣሪያ ግን እንደሸሸ ተረጋግጧል፣ ኣያመልጥም ብሏል። በሻለቃ ቺሪኖ (Cirino) በተደረገው ክትትል አባ ሚካኤል፣ ቀኛዝማች ይነሱ እና 50 ታጣቂዎች ተማርከዋል።

ኖቬምበር 30 ታዬ ጉሉላቴና ቢተወደድ ወልደጻድቅ ከራስ እምሩ ጋራ ነበሩ። ራስ እምሩ በኤርትራውያን ከዳተኞችና በቀድሞ የወለጋ የጦር መኮንኖች እየተረዳ ጦርነቱን ለመቀጠል ፍላጎት የነበረው ሲሆን ታዬ ጉሉላቴ ግን እጁን ለጣሊያኖች ለመስጠት ያዘነበለ ነበር። በራስ እምሩ ላይ ከበባ ለማጠናከር ሀ/ ኮሎኔል ማልታ ከጎሬ ወደ ቦንጋ መዝለቅ አለበት ለ/ ፕሬንቺቫለ ከጅማ ወደ ቮጋ ሐ/ ተሲቶሬ ከለቀምት ወደ ጉግ ዲደሳ። ራስ እምሩ ዲሴምበር 4-9 አጋሮ እንደነበረ ተረጋግጦ ነበር፤ ኖቬምበር 8 ራስ እምሩ ወደ ጌራ ከፉ ለመሄድ ቦሌ የሚባል ቦታ እንደሚገኝ ለጣሊያኖች መረጃ ይደርሳቸዋል። ዲሴምበር 11 ታዬ ጉሉላቴ ከኮሎኔል ማልታ ቀርቦ እጁን እንዲሰጥ ተጠርቶ ከደጃዝማች አርአያና ከነጋ ድረስ ተሰማ እሸቴ ጋራ ሆኖ ቀርቧል። ዲሴምበር 12 ቢተወደድ ወልደጻድቅ ቀርቦ እጁን ሰጥቷል፣ ወደ ቦንጋ ተወስዷል፣ ሁሉም ያስረከቡት መሣሪያ እየተቆጠረ መሆኑን ኮሎኔል ማልታ ለግራዚያኒ ባስተላለፈው ቴሌግራም ገልጸዋል። ቦንጋ በጣሊያኖች የተያዘችው ዲሴምበር 10 ነበር።

ኮሎኔል ፕሬንቺቫለ ኖቬምበር 12 ከጅማ ተነስቶ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ራስ እምሩ ወዳለበት በሚሄድበት ጊዜ ከራስ እምሩ ጦር አንድ ክፍል በድንገት ጊዮቾ በተባለው ቦታ ላይ ተገናኝቶ ከባድ ውጊያ ይገጥመዋል፣ በውጊያው በራሱ በራስ እምሩ ነበረ፣ የውጊያ ዝርዝር ኮሎኔሉ በሰፊው ድፎ አቅርበዋል። በውጊያው ሚዳ የታይፕ ማሽኖች፣ ስለ ውትድርና ትምህርታዊ መጽሐፎች፣ የግል ደብዳቤዎች ተገኝቷል። ከጣሊያኖች ወገን አንድ የጦር መኮንን ሲሞት 7 ቆስሏል 47 ኢንጂነር ሲሞቱ 108 ቆስሏል። ስለሞቱ አርበኞች አልተጠቀሰም ሆኖም በደፈና የተማረኩ ተገድለዋል ብሏል። የራስ እምሩ ወታደሮች በከዳተኞች ኤርትራውያንና በቀድሞ በወለጋ የጦር መኮንኖች ግስልጠኛ ተማሪዎች የተገነቡ ናቸው ብሏል። ራስ እምሩ ወደ ኩሉ እምልጦ እንዳይገባ መንገድ እየዘጉበት ነበር፣ ለማግሥቱም በተደረገው ውጊያ ብዙ የተማረኩ አርበኞች ተገድለዋል፣ ቤቶችና ሕፃናት በነፃ ተለቀዋል፣



ከጣሊያኖች ባንዳዎች የሞቱ 3 የቆሰሉ 6 ነበሩ፣ ከአርበኞች 20 ተገድለዋል ብለዋል።

ዲሴምበር 15 ጧት ጣሊያኖች ራስ እምሩ ወደ ቸረቻ እያመራ መሆኑን መረጃ ይደርሳቸዋል። በዚሁ ጊዜ ጣሊያኖች በፍጥነት ገስግሰው ወደ ቸረቻ ወንዝ ያመራሉ፣ ከራስ እምሩ ፊት አጥቂዎች ተገናኝተው ውጊያ ይገጥማሉ፣ ዋናው የራስ እምሩ ጦር በ200 ሜትር ርቀት ይገኝ ነበር። የራስ እምሩ ጦር ለውጊያ ተዘጋጅቶ የነበረ፣ ብዛት ያላቸው የኢጣሊያ ተዋጊዎች በማየቱ ዲሴምበር 16 ከጣሊያኖች ጋራ ለመነጋገር ይጠይቃል።

በመጀመሪያ ራስ እምሩ ወደ ሱዳን እንዲሄድ እንዲፈቀድለት ጠይቆ ነበር፣ ሆኖም ጣሊያኖች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እጁን እንዲሰጥ ስለጠየቁት፣ እጁን እንዲሰጥ መቀበል ግድ ሆነበት።

ዲሴምበር 16 ከሰዓት በኋላ የእጅ መስጠትና ትጥቅ ማስፈታት ተካሄደ 5000 ወታደሮች እጃቸው ሰጡ 1800 ጠበመንጃዎች 39 መትረየሶች ሁሉም ዘመናዊ በደኅና ሁኔታ ተማረኩ። ዲሴምበር 18 ራስ እምሩና ከፍተኛ ሹሞች ወደ ቦንጋ ተወሰዱ፣ ከመታሰር ለማምለጥ የሚሞክሩ አርበኞች እየታደኑ ነበር። ጣሊያኖች ራስ እምሩ የነበረው የወታደር ብዛት ይገምቱት የነበረ ከ1500 ያነሰ ነበረ። ግራዚያኒ ለቅኝ ግዛቶች ሚንስትር በላከው ቴሌግራም ራስ እምሩ እየተዋጋ ተይዞ ቢሆን ኖሮ ወዲያውኑ እንዲረሸን ትእዛዝ እሰጥ ነበረ። በተያዘበት ሁኔታ ግን ራስ ደስታም እጁን እንዲሰጥ ማበረታቻ እንዲሆን እንዲያዝ ብቻ ተደረገ። ራስ እምሩ ከተማረከ በኋላም እምልጦ እንዳይሸሽ ይጠረጥሩት ነበር።

## የጋምቤላ መያዝ

90 አስካሪና 2 የኢጣሊያ ጦር መኮንኖች በአዲስ አበባ ጋምቤላን እንዲቆጣጠሩ ስለተመረጡ እስከ ላሎ በአሮፕላን ተወስዶ በእግር እስከ ጋምቤላ ተጉዘው ዲሴምበር 17 ጋምቤላ ደረሱ። በቦታው 50 ባንዳዎች ነበሩ፣ ተጨምረባቸው 200 ሆነዋል። በዚሁ ቀንም የተለያዩ እቃዎች የጫኑ አሮፕላኖች ከአዲስ አበባ ጋምቤላ ደርሰዋል፣ የጉምሩክ ሠራተኞችም አስፍረው ነበር።

## የበንሻንጉል መያዝ

በቤን ሻንጉል የነበረ ችግር ከእንጃዎች እርስ በርስ የሥልጣን ሽኩቻ ብቻ ነበር ጣሊያኖች የሚነካ አልነበረም፣ እንጃዎቹ 1/ የጆቴ ወንድሞች 2/ ሼክ ኢል ሆገሊ 3/ ደጃዝማች መብራቱ ነበሩ።

ለሼክ ኢል ሆገሊ ከንጉሡ የበጌ ግዛት ቀድሞ የጆቴ የነበረው ይሰጠዋል። ደጃዝማች ጆቴ በድንገት ይሞታል፣ 4 ልጆቹ ወደ ሸዋ ለግዞት ይወሰዳሉ፣ ሁለቱ በእስር እንዳሉ ይሞታሉ፣ አንዱ በእንግሊዝ ሲላው በአዲስ አበባ። እዚ ኃይለሥላሴ ሀገሩን ለማረጋጋት ያልሞቱት ሁለት የጆቴ ልጆች በመጀመሪያ የጊዳም ወረዳ ቀጥሎም የእኖ ወረዳ ግዛት ይሰጣቸዋል። በጣሊያን ወረራ ኃይለሥላሴ ከሥልጣን ሲወርድ የጆቴ ልጆች የአባታቸው ግዛት የነበረ መሬት እንዲሰጣቸው ለሼኩ ይጠይቃሉ። እሱ መሬቱን ለማስረከብ ሳይሆን ግብር ከመክፈል ብቻ ፈቃደኛ ነበረ። የጆቴ ልጆች ሀሸኩ ሐሳብ ስላልተስማሙ በደጃዝማች መብራቱ እርዳታ የበጌ ወረዳ ግዛት ወረው ይያዛሉ፣ ሼኩ ሀገሩን ለቆ ሩቅ ቦታ ይሰፍራል፣ (ጎዣ የተባለው ቦታ)። ደጃዝማች መብራቱ ከሼኩ

ያለው ትራኔ እንደሚከተለው ነው፡፡ የሙስታፋ አባት ፊታውራሪ መሐመድ የቤን ሻንጉል አካል ቢሆንም ራሱ የቻለ አንድ አንስተኛ ግዛት በእኩል ደረጃ ከሌሎች የወረዳ ግዛቶች ነበረ፡፡ ፊታውራሪ መሐመድ እስረኛ ሆኖ ወደ አዲስ አበባ ሲወሰድ ግዛቱ ለሸክ ኢል ሆጎሊ ይሰጣል ደጃዝማች ሙስታፋም ለመቀበል ይገደዳል፡፡

ከጣሊያኖች ጋራ ያለው ሁኔታ የጆቴ ልጆችና ደጃዝማች ሙስታፋ ምዕራብ ወለጋ በጣሊያኖች እጅ እንዲገባ ያደረጉት እርዳታ ከፍተኛ ስለሆነ ለጣሊያኖች ባለውለታዎች ናቸው፡፡ ሸክ ኢል ሆጎሊ ወኪሉን አዲስ አበባ በመላክ እጁን እንዲሰጥና የኢጣሊያ መንግሥት ጥያቄውን እንዲቀበለው ከመኩትኮት አላረፈም ነበር፡፡

ቤን ሻንጉልን ለመያዝ የተሰማራ የኢጣሊያ በጀነራል ደላ ቦና Della Bona የሚመራ ነበረ፡፡ የኢትዮጵያ የጠረፍ መሬቶች የእንግሊዝ መንግሥት ተሻቀዳድሞ እንዳይዛቸው ፍራት ነበራቸው፡፡ የጣሊያኖች ወደ ቤን ሻንጉል ዘመቻ የተጀመረው ደሰምበር 24 ቀን ነበር፡፡ አባይን አቋርጠው ጀነዋሪ 4 በልፎዲዮ ይደርሳሉ ጀነዋሪ 5 አፎዱ፣ ጀነዋሪ 22 አሶሳ፣ 31 ቦጊ ወዘተ..

## የጉራፋርዳ በጣሊያኖች መያዝ

የወርቅ፣ የብርና የብረት ማእድን አላት የተባለች የጉራፋርዳ ወረዳ ደጃዝማች ታዬ ጉሉላቴ ለእንግሊዞች ለመስጠት ተስማምቶ እንደነበረ ጣሊያኖች መረጃ ደርሰዋቸው ነበረ፡፡ ከዚህ በመነሳት ጣሊያኖች ተሻቀዳድመው ለመያዝ ወሰኑ፡፡ በጣሊያኖች ስም ግንባር ቀደም ዘማች የነበረው ለጣሊያኖች ያደረ ባንዳ ቀኛዝማች በቀለ ሲሆን ደሰምዘር 22 ከግራዚያኒ በአሬዮፕላን በተወረወረለት ትእዛዝ መሠረት በታላቅ ደስታ ትእዛዙን ስለተቀበለ ደሰምበር 25 ጉራፋርዳን ለመቆጣጠር ችሏል፡፡ የራስ እምሩ ያልተያዙ አርበኞች በየሜካው እያሳደደ እንዲለቅም ትእዛዝ ተሰጥቶት የነበረ ሌላ የጣሊያኖች ባንዳ ፊታውራሪ መጂት የተባለው ለቀኛዝማች በቀለ ጣሊያኖች እርዳታ እንዲሰጣሩ አደረጉት፡፡ ከዚህ በኋላ ነው ጉራፋርዳን እንዲይዙ የተመደቡ መደበኛ የኢጣሊያ ተወጊዮች ሊገቡ የቻሉ፡፡

በዚሁ ዓይነት በምዕራብ ኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖዋል ብለው በማሰብ ጀነራል ጀሉዞ ጅማ ዋና ከተማ በማድረግ የጋላና ሲዳማ ክልላዊ መንግሥት መሪና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የሚል ሹመት የነበረው ፌብሩዋሪ 14, 1937 በጅማ ስራውን ጀመረ፡፡ በዚሁ ጊዜ በአርበኞችና በጣሊያኖች የነበረ አሰላለፍ የሚከተለው ነበረ፡፡

## የአርበኞች አሰላለፍ

1. ሌሙ ቦቶር ተራራዎች በብላታ ታከለ ወልደሐዋርያት የአዲስ አበባ ከንቲባ የነበረ የሚመሩ
2. በኩሉ ኮንታ በደጃዝማች ድገቱ የሚመሩ
3. በጋሞና ጋርዱላ በደጃዝማች ወልደማርያም የሚመሩ የራስ ደስታና የበየነ መርዕድ የተቀላቀሉባቸው
4. ቡርጂና ዶሎ ተራራ በፊታውራሪ ታደመ የሚመሩ

የጣሊያኖች አሰላለፍ ከተቂት የምሕንድስና የከባድ መሣሪያና የጦር መኮንኖች በስተቀር በኢንዲጀኒ አስካሪና በባንዳዎች የተገነባ ስለሆነ



በጣሊያኖችና በኢትዮጵያውያን የሚደረገው ጦርነት ሳይሆን በኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቸው የሚያደርጉት ጦርነት መልክ ነበረው፡፡

1. በቤን ሻንጉል ሀ/ 22ኛና 28ኛ ኢንዲጀኒ ባታሊዮኖች ለ/ ባለ ግመል 3ኛ ባንዳ ሐ/ ምዕራባዊ ቀላ ቡድን ባንዳ መ/ የጣሊያኖች ምሕንድስና፡፡
2. ጎሬና ደምቢዶሉ ጦር ሰፈሮች ሀ/ 7ኛና 16 ኢንዲጀኒ ባታሊዮን ለ/ 7ኛ መድፈኛ ጣሊያኖች ሐ/ ምሕንድስና ጣሊያኖች
3. ለቀምት ሀ/ 54ኛ፣ 56ኛ ኢንዲጀኒ ባታሊዮኖች ለ/ ምሕንድስና ጣሊያኖች ሐ/ መድፈኛ ጣሊያኖች
4. ኖኖ ሀ/ ዘ1ኛ ብሪጌድ አንድ ሻለቃ ኢንዲጀኒ ለ/ መድፈኛ ጣሊያኖች ሐ/ ባንደ በሊ መ/ ባንዳ ራስ ኃይሉ
5. ጅማ ሀ/ 12ኛ ባታሊዮን ኢንዲጀኒ ለ/ 45ኛ ባታሊዮን ሙስሊም ሐ/መድፈኛ ጣሊያኖች መ/ ከባድ መድፈኛ ጣሊያኖች ሰ/ ታንከኛ ጣሊያኖች ረ/ የሮሌ (Rolle) ባንዳ ሠ/ የሙስሊም ፕሩነቲ (Prunetti) ባንዳ
6. ከፋ ጊሚራ ሀ/ 1ኛ፣ 6ኛና 8ኛ ባታሊዮን ኢንዲጀኒ ለ/ የምሕንድስና ጣሊያኖች ሐ/ መድፈኛ ጣሊያኖች መ/ የገብረመድኅን ባንዳ የከበደ ባንዳ ረ/ የበቀለ ባንዳ ሠ/ የመጂት ባንዳ ቀ/ የመሮኔ Merone ወለጋ ቡድን ባንዳ
7. ሶዶ ሆሣዕና ሀ/ 25ኛ፣ 17ኛ ኢንዲጀኒ ባታሊዮኖች ለ/ የምሕንድስና ጣሊያኖች
8. ጉራጌ ዙዋይ 10ኛ፣ 11ኛና፣ 12ኛ የዓረብ ሶማል ባታሊዮኖች፣ ባንዳ ቱቺ
9. ሻሸመኔ 9ኛ ባታሊዮን ዓረብ ሶማል
10. ሀገረ ማርያም 7ኛ ቡድን ባንዳ ዱባት
11. የጠረፍ ማልካ መራና ሱተፋኒያ ጠባቂዮች 1ኛ ቡድን ባንዳ ዱባት

እላይ በተጠቀሱ ቦታዎች ሁሉ ጣሊያኖች ከፌብሩዋሪ 28 ጀምሮ እስከ አፕሪል 26, 1937 አነስተኛ ውጊያዎች በማካሄድ ይዞታቸውን አጠናክረዋል፣ ይሁን እንጂ በባኮና በሮዶልፍ ሐይቅ እንዲሁም በሱተፋኒያ ሐይቅ አሰሳ የተካሄደ በመዶ ወር ነበረ፡፡

# ሰ/ ሲዳማና ሐይቆች

## ሀ/ መጀመሪያ ዙር አክቶበር ዲሰምበር 1936

ሳደ Sade ዲሊ አጠገብ

አክቶበር 19 በሳዳ ውጊያ 2 የኢጣሊያ መኮንኖች ሲሞቱ 10 ቆስሏል፡፡ ተራ ወታደሮች 5 ሲሞቱ 27 ቆስሏል፡፡ ኢንዲጀኒ 37 ሲሞቱ 119 ቆስሏል፡፡ ኖቨምበር 6 ስለ አርበኞች ጣሊያኖች የደረሳቸው መረጃዎች የሚከተሉት ነበረ፡፡

1/ደጃዝማች ገብረማርያም ከ1500 ወታደሮች ጋራ ከተፈሪ ከላ እስከ ዲላ በሚርጎ ወንዝ አካባቢ የጣሊያኖች ወደፊት መግፋት ለማደናቀፍ ሰፍረዋል፡፡

2/ ፊታውራሪ ታደመና ተሰማ 500 ተዋጊዮች ቡሌ ሰፍረዋል፡፡

3/ በይርጋ ዓለም 300 ከዳተኞች ኤርትራውያን ሰፍረዋል፡፡

# ቡሌ

ደሰምበር 12 በጀነራል ኖቫሪኒ የሚመራ ጣሊያኖች ከፊታውራሪ ተሰማ ከሚመሩ አርበኞች ግጭት ይፈጠራል። በጣሊያኖች ግምት 50 አርበኞች ሞቷል፣ ከጣሊያኖች ወገን 2 ሲሞቱ 20 ቆስሏል (ኢንዲጂኒ)

## ራስ ደስታ

ደሰምበር 4 ቀን ራስ ደስታ በሻምበል ቱቺ አማካኝነት ለሕይወቱ ዋስትና ከተሰጠው እጁን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን አስታውቆ ነበር። ራስ ደስታ እጁን እንዳይሰጥ የሚቃወሙ 1ኛ ደጃዝማች ገብረማርያም 2ኛ ከዳተኞች አስካሪ ኤርትራውያን ነበሩ። ግራዚያኒ ጦሩን በሙሉ ይዞ ከገባ ለራሱ ለሕይወት ዋስትና ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ገለጸለት፤ ራስ ደስታ እጁን ለመስጠት ስለዘገዩ ግራዚያኒ በጀነራል ጀሎሶ አማካኝነት ደሰምበር 31 ራስ ደስታ እጁን እንዲሰጥ 7 ቀን ብቻ ጊዜ እንዲሰጠው ከዚሁ ጊዜ በኋላ ግን ምህረት እንደማይደረግለት እንዲነገረው ያዝዛል። ራስ ደስታ ግን ጣሊያኖች የማይቀበሉት ቅድመ ሁኔታ በመልእክተኛ ካስታኛ አማካኝነት በማቅረብ እጁን ሳይሰጥ ቀረ።

ጀነራል ጀሎሶ በቴሌግራም እንደገለጸው በተለያዩ ቦታዎች ከኦክቶበር 15 እስከ ወሩ መጨረሻ በተደረጉ ግጭቶች በጣሊያኖች ወገን የደረሰው ጉዳት 2 ጦር መኮንኖች ሲሞቱ 12 ቆስሏል፣ ባለ ሌላ ማዕረግ የሞተ የለም የቆሰሉ 6 ተራ ወታደሮች ጣሊያኖች የሞቱ 10 የቆሰሉ 55 ነበረ። ኢንዲጂኒ የሞቱ 104 የቆሰሉ 197[1]

በሌላ ሪፖርት ጀነራል ጀሎሶ በሰፕተምበር 10 እስከ 15, 2 የጦር መኮንኖች ቆስሏል፣ 3 ባለ ሌላ ማዕረግ ቆስሏል፣ ተራ የኢጣሊያ ወታደሮች 29 ቆስሏል፤ ኢንዲጂኒ የሞቱ 19 የቆሰሉ 69 መሆናቸውን ገልጸዋል። እንዲሁም ከሰፕተምበር 15 እስከ 30 የሞቱ የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 11 የቆሰሉ 13፣ ኢንዲጂኒ የሞቱ 8 የቆሰሉ 12 መሆናቸውን ገልጧል።

በተለያዩ ውጊያዎች ከኖቬምበር 6 እስከ ደሰምበር 16 በጣሊያኖች ላይ የደረሱ ጉዳቶች

| ቀንና ወር | የጦር መኮንኖች | | ጣሊያኖች | | ኢንዲጂኒ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሞቱ | የቆሰሉ | የሞቱ | የቆሰሉ | የሞቱ | የቆሰሉ |
| ከ1እስከ 15 ኦክቶበር | - | 2 | 7 | 31 | 19 | 69 |
| ከ15እስከ30 ” | 7 | 12 | 16 | 35 | 104 | 197 |
| ከ1እስከ15 ኖቬምበር | - | 4 | 3 | 4 | - | 8 |
| ከ15 እስከ 30 ” | 4 | - | 2 | 20 | 5 | 23 |
| ከ1እስከ15 ዲሰምበር | - | 1 | - | - | - | 29 |
| ድምር | 8 | 16 | 28 | 90 | 128 | 326 |

በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት አልተገለጸም ግን ከባድ ነበረ ብሏል።

(1) Governo Generale A.O.I ibd Allegato 221 V II



## ለ/ 2ኛ ዙር ከጀነዋሪ 1 ፌብሩዋሪ 15

ጀነዋሪ 5, 1937 የአርበኞች አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበር።

1. ዋናው የራስ ደስታ ጦር በአርባጉጉ ከሸና ሰፍር ይገኛል፤ በቀድሞ አስካሪ ከዳተኞች ኤርትራውያንና በደጃዝማች ገብረማርያም የተከበበ ስለነበረ እጁን ለጣሊያኖች ለመስጠት ነፃነት አልነበረውም፤ ምራሉ ወደቅ ነበር።
2. ደጃዝማች በየነ መርዕድ 2000 ወታደር (ባለ ጉባ) የሰፈረ
3. ደጃዝማች መኩንን ወልዴ 2000 ወታደር በሶዶ ወላሞ የሰፈረ
4. በደጃዝማች ጎመዱ ጊሰት የሚመሩ ከአርሲ የመጡ ከምባታ የሰፈሩ
5. በፊታውራሪ ታደመ የሚመሩ በደሎ ተራራ አካባቢ የሰፈሩ

የአካባቢው አግራና ጉራጌ ሕዝብ የራስ ደስታ ደጋፊ ነበረ የአርሲ ኦሮሞ የጣሊያኖች ደጋፊ ነበሩ። በሻምበል ቱቺ የሚመራ ትግሬዩ ደጃዝማች ተከሉ ባንዳ ከአርሲ ኦሮሞች 5000 (አምስት ሺህ) ታጣቂዎች ድጋፍ አቅርበዋል።

ጣሊያኖች የነበሩዋቸው ወታደሮች የሚከተሉት ነበረ።

1. ወደ ኮርሉ የሚያመሩ በሻምበል ቱቺ የሚመሩ የትግራይ ባንዳዎች፣ 5000 ኦሮሞች ወዶዘማቾች ባንዳዎች የተቀላቀሉበት
2. በሆገረማርያም 4 ባታሊዮኖች ዓረብ ሶማልና መድፈኞች ጣሊያኖች እንዲሁም 1ኛና 12ኛ ቡድን ባንዳ ዱባት
3. በዲላ አንድ ባታሊዮን ባለ ከባድ መሣሪያ ጣሊያኖች
4. በሻሎ 1ኛ ልዩ ቡድን
5. በጅቢ ተራራ የሰፈረ የሊቢያ ዲቪዚዮን
6. በሀረርጌ የሰፈሩ በጀነራል ናዚ የሚመሩ ወታደሮች በደቡብ ምዕራብ በራስ ደስታ ላይ ዘመቻ እንዲካፈሉ ተደርገዋል።

የማጥቃት እርምጃ የሚጀመረው ለጀነዋሪ 20 እንዲሆን ተወስኗል። ዘመቻው የሚመራው ወደ ደቡብ የመጣው በራሱ በማርሻል ግራዚያኒ ነው።

ከኦሮሞ አርሲ ሌላ ጣሊያኖች 3000 (ሶስት ሺህ) ሲዳማ ተዋጊዎች አሰማርቷል። በተጨማሪም 1 ባታሊዮን አማራ 1 ባታሊዮን ኤርትራውያን በዘመቻው ተካፋይ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

ሻምበል ቱቺ 600 (ስድስት) ሌላ የሲዳማ ተዋጊዎች ወዶዘማቾች ድጋፍ አግኝቷል።

በራስ ደስታ ላይ የሚደረገው ዘመቻ ይህ ሁሉ የተጠቀሰው የወታደር አገረኛ ኃይልና 50 አሮፕላኖች ያለማቋረጥ የሚጥሉት ቦምብ አልበቃም ብለውቸው ጣሊያኖች ወላሞን ለመቆጣጠር ባቡር ሐዲድ መስመር ከሚቆጣጠሩ ተቀንሰው በጀነራል ማሪዮቲ የሚመሩ የ9ኛ ብሪጌድ ክፍል በጀነራል ጀሎሶ ስር እንዲሆን አድርገዋል።

በአርባጉጉ የሰፈሩ የራስ ደስታ ወታደሮች ብዛት ከ4 እስከ 6 ሺህ የሚገመቱ ብቻ ነበሩ።

ከጀነዋሪ 7 እስከ 27, 1937 በተለያዩ ቦታዎች በተደረጉ ውጊያዎች ከአርበኞች 1000 (አንድ ሺህ) ተገድለዋል። ከጣሊያኖች ወገን 2 የጦር መኮንኖች ተገድለዋል 3 ቆስለዋል የኢጣሊያ ተራ ወታደሮች 3 ቆስሏል ኢንዲጂኒ 93 ተገድለዋል 119 ቆስሏል። 6000 ጠብመንጃዎች 37 መትረየሶች ተማርከዋል።

የሞቱና የቆሰሉ መጥቀስ ብቻ የተደረጉ ውጊያዎች ክባድነት አያሳዩም በተለይ በሕዝቡና በአርበኞች ላይ የደረሰው ጉዳትና ሲታይ አያሳይም። በሕዝቡና በአርበኞች ላይ ጣሊያኖች ያደረሱት የነበረ በደል ለመረዳት ማርሻል ግራዚያኒና የኢጣሊያ ጀነራሎችና ኮኔሎች በየቀኑ ይለዋወጡባቸው የነበሩ ብዙ ቴሌግራሞች እንዳንዶቹ ማገለባበጥ ያስፈልጋል።

ግራዚያኒ ለሚፈጽሙት ወንጀል የደስታ መግለጫ ሲልኩላቸው እነሱም የሚደረግላቸው ማበረታቻ ክብርና ኩራት ይሰማቸው ነበር። ግን ብዙ ሰው እንደገደለ ውድድርና ፉክክር ነበረ የያዙት

ማርሻል ግራዚያኒ ለጀነራል ትራኪያ ደሰምበር 15,1936 የሰጠው መመሪያ የደሴ አዲስ አበባ መንገድ ፀጥታ ለማስከበር ትጥቅ የማስፈታት ተግባር ሙሉ በሙሉ መሆን እንዳለበት ነው፤ ጠንቋዮችንም ወይንም የተጠረጠሩ ወንደቤዎችንም ለማውደም ሙሉ በሙሉ መሆን እንዳለበት ነው[1]

ጀነራል ትራኪያ ደሰምበር 25 እኛቸው ከሰሙ መሐከል ወይዘሮ ብዙነሽ ሃብተሥላሴ የደጃዝማች አስፋወሰን ካሣ ሚስት ነበረች ብሏል። ቀጥሎም ትጥቅ ስለማስፈታቱ ተግባር ከደሰምበር 9 እስከ 26 5የክባድ መትረየስ 36 ቀላል መትረየስ 3340 ጠብመንጃዎች፣ 1 ታንክ፣ 65,000 ጥይቶች ተማርከዋል ብሏል።

ሻምበል ቱቺ ከአርሲ ሰዎች ጋራ ባለው መልካም ግንኙነት ደሰምበር 31 ባደረገላቸው ጥሪ መሠረት 3,000 አርሲ ወደ እሱ ሲቀርቡ 800 ጠብመንጃ የታጠቁ በእሱ ስር እንዲሆኑ ፈቅዷል። የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች በሚልኳቸው ቴሌግራሞች አርበኞችን ሽፍቶች ብለው ሲጠሩዋቸው አርሲ ከጣሊያኖች ጉን ሆኖ ወያዘማቾች አርበኞች ብለው ይጠሩዋቸው ነበር።

በሻምበል ቱቺ ስር የሚገኙ አርሲ ራስ ደስታን ለመከታተል 1000 ከአዳሚቱሉ ጀነዋሪ 2,1937 ተንስቷል በዚሁ ቀን ኮሬሌ ደርሰዋል፣ ከቀኛዝማች ወልደጻድቅ ጋሞት አድርገው ቀኛዝማቾች ወደ ሸራ ሰለሸሽ ሸራ በአየር እንዲደበደብ ጠይቀዋል፣ እነሱም ጀነዋሪ 3 ወደ ሸራ ያመራሉ። ሻምበል ቱቺ ጀነዋሪ 3 ሌሎች 80 አርሲ አርሞ መሣሪያ የታጠቁ አርበኞቹን ለመዋጋት ስለጠየቁ አቀበላቸዋለሁ ብሏል።

ጀነራል ጄሉዞ ለግራዚያኒ ጀነዋሪ 3,1937 ባስተላለፈው ቴሌግራም ራስ ደስታ 10 ኪሎ ሜትር ከአርባ ጉጉ እንደሚገኝ እጁን እንዳይሰጥ ዋናው ተቃውሞ የሚያጋጥመው ከቀድሞ አስካሪ ከዳተኞች ኤርትራውያን መሆኑን ገልጸዋል፣ በተለይ የካሳታኛ ተልእኮ ከሸሸፈ በኋላ እየተከታተሉት ይገኛሉ ብሏል[2]።

ጀነዋሪ 4 ሻምበል ቱቺ 156 የታጠቁ አርሲ ከእሱ ጉን ሆነው አርበኞቹን ለመዋጋት ጠይቋል ብሏል ሆኖም ለጊዜው አልተቀበልኳቸውም ብሏል። ሌሎች የሲዳማ ተዋጊዎች በግራዝማች መንገሥቱ የሚመሩ ከእሱ ጉን ሆነው አርበኞቹን እንዲዋጉ የጠየቁት መሆናቸውን ሻምበል ቱቺ በቴሌግራም ገልጧል። ጄሉዞ ጀነዋሪ 6 ብዛት ያላቸው መረጃ ሰጪዎችና ባንዳዎች በራስ ደስታ ዙሪያ ተሰማርቷል፣ መንገዶቹ ሁሉ በጠባቂዎች ታጥረዋል፤ በአየርም በታው ያለማቋረጥ እየታደበደበ ነው ብሏል። አርበኞች ካካ በሚባል ተራራ ይገኛሉ። ሻምበል ቱቺ ጀነዋሪ 6 ባስተላለፈው ቴሌግራም ባገኛቸው መረጃዎች መሰረት በከዳተኞች ኤርትራውያንና በሐበሾች ጠብ ተነስቶ ከሁለቱ ወገኖች 6 ሞቷል ብሏል።

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 773 V II
[2] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 847 V II



ጀነራል ጄሉዞ ጀነዋሪ 7 ባስተላለፈው በሌላ ቴሌግራም ራስ ደስታ ሞራሉ ወድቆ ይገኛል ወደ ኬንያ ለመሸሽ ሃሳብ አለው ሆኖም የቀድሞ አስካሪ ከዳተኞቹ እና ደጃዝማች ገብረማርያም እንዳይሸሽ እንደ እስረኛ እየጠበቁት ይገኛሉ፣ ባንዳ አርሲ ከራስ ደስታ ወታደሮች ግጭት እየፈጠሩ ይገኛሉ የአየር ኃይልም ድብደባ እያካሄደ ይገኛል[1]።

ጀነዋሪ 8 ጀነራል ጄሉዞ ባስተላለፈው ቴሌግራም ራስ ደስታ ከአርባጉጉ የለቀቀ መሆኑን አስካሪ ከዳተኞች ሸሽቶ እንዳያመልጥ እየተከታተሉት መሆኑን ገልጸዋል[2]።

ጀነዋሪ 9 ጀነራል ጄሉዞ ባስተላለፈው ሌላ ቴሌግራም ፊታውራሪ ተሰማ እና ገረመው ወደ ጣሊያኖች ሄደው እጃቸው ለመስጠት አስበው ነበር. ነገር ግን ከዳተኞች አስካሪ ተኩስ በመክፈት ሃሳባቸውን እንዲቀይሩ አደረጉዋቸው[3]።

ጀነራል ጄሉዞ ጀነዋሪ 10 እና 11 ባስተላለፋቸው ቴሌግራሞች የራስ ደስታ አርበኞች ከኢጣሊያ ባንዳዎች እንደተጋጩና የዳዋ ከዳተኞች ኤርትራውያን ተካፋይ እንደነበሩ ገልጧል[4]።

ጀነዋሪ 12 ግራዚያኒ ለጀራል ባስተላለፈው ቴሌግራም የሲዳማ ሰዎች ለወደፊት ጥሩ አስካሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለጊዜው ጨቤን ይዘው ወደ ራስ ደስታ እንዲዘምቱ ማድረግ እንደሚቻል፣ ስዚሁም ከሸባዲና ባላባት ለሚሰ ዋራሞ ስምምነት እንደፈጠረና ባሉት 3000 ተዋጊዎች በቡሼራ ላይ እንዲሰማሩና ከበስተኋላው የኢጣሊያ መደበኛ ድጋፍ እንዲያደርጉለት ትእዛዝ ሰጥቶ፣ ሌሎች ባለባቶችም የእሱ አርአያ እንዲከተሉ መጣር እንደሚያስፈልግ እና ለማደፋፈሪያ በሕይወትም ሞቶም ራስ ደስታን መያዝ ለቻለ ሁሉ ገንዘብ እንደሚከፈለው እንዲነገራቸው በማለት መመሪያ ሰጥቷል። ጀነራል ጄሉዞም መልስ ሲሰጥ በትእዛዙ መሠረት እፈጽማለሁ ብሏል።

ጀነዋሪ 14 ጀነራል ጄሉዞ ለግራዚያኒ በላከው ቴሌግራም ራስ ደስታ በፊት አጥቂ ወታደሮቹ በከዳተኞች የተጠናከሩ ዛሬ የኢጣሊያ ዓረብ ሶማል ወታደሮችን አጥቅቶ በተደረገው ውጊያ ሁለት አስካሬ ሞቷል አንድ የኢጣሊያ ሶር መኩንን እና 5 አስካሪ ቆስሏል። ከራስ ደስታ ወገን የሞቱ ብዙ ናቸው ከእነሱ ውስጥም የኢጣሊያ ቡሉክባሽ የነበረው[5] ከዳተኛ አስካሪ ከራስ ደስታ ግራዝማች ሹመት ከንጉሡም ቀኛዝማች ተሰጥቶት የነበረ ተገድለዋል ብሏል። ራስ ደስታ የዳዋ ከዳተኞች አስካሪ ኤርትራውያን በፍጥነት መንቀሳቀስ እንዲችሉ ፈረሶች ዘርፎ አድሏቸዋል ብሏል።

ጀነራል ናዚ ጀነዋሪ 16 ባስተላለፈው ቴሌግራም ሊቢያውያን ወታደሮች ሰላ ካራ በተባለው ቦታ (ሐረርጌ) የተማረኩ 9 አማሮች የገደሉ መሆናቸውን ገልጧል።

ጀነራል ጄሉዞ ጀነዋሪ 17 ባስተላለፈው ቴሌግራም አርበኞች በጣሊያኖች ተኩስ እየከፈቱ እንደሚሸሹ ገልጦ ደጃዝማች ገብረማርያም እና የዳዋ ከዳተኞች አስካሪ ከጣሊያኖች ጋራ በግጭት የተካፈሉ እንዳይሸሹ ይጠብቁዋቸዋል ብሏል።

ጀነራል ጄሉዞ ጀነዋሪ 20 ባስተላለፈው ቴሌግራም ወደፊት የሚገሰግሱ ወታደሮቹ ከአርበኞች ጋራ ውጊያ እየገጠማቸው መሆኑን ገልጦ አርበኞቹ

[1] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 866 V II
[2] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 874 V II
[3] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 882 V II
[4] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 887-893 V II
[5] Governo Generale A.O.I. Allegato N.909 V II

የሚመሩ በግራዝማች በዛብዘ እና በሰለባ እንዲሁም በሌላ ኤርትራዊ መሆናቸውን አብራርተዋል።

ጣሊያኖች በአርበኞች ላይ ከፍተኛ ጥቃት የሚፈጽሙበት ወቅት ነው። ጀነዋሪ 20 ጀነራል ጀሉዞ ባስተላለፈው ቴሌግራም አርበኞች ባጣዳፊ ሸሽተው እየመለጡ መሆናቸውን ገልጦ ብዛት ያላቸው በጌዳ የተጣሉ ሴቶችና ሕፃናት ወደ ጣሊያኖች እየተጠለሉ መሆናቸውን አስረድቷል። በሌላ ቴሌግራምም በዚሁ ዕለት አንድ ኖርወይ ተወላጅ ሐኪም ከራስ ደስታ ጋራ እንደሚገኝ ገልጧል። ከራስ ደስታ ጋራ ደጃዝማች ገብረማርያምና ጥቂት የዳዋ ከዳተኞች አስካሪ እንደሚገኙ፣ ቀኛዝማች ፀጋ ጣሊያኖችን እየተቋቋመ መሆኑን ገልጧል።

ሻምበል ቱቺ ጀነዋሪ 20 ባስተላለፈው ቴሌግራም አርሲ አርሞ ወደዘማቾች 5000 ከአዳሚቱሉ የተነሱ መሆናቸውን ከእነሱ ውስጥም 1500 ጠብመንጃ የታጠቁ 2000 ፈረሰኞች እንደነበሩ ሌሎች 500 ባንዳም አብረው እንደዘመቱ ገልጧል።

ጀነዋሪ 21 ጀነራል ኩበዱ (Cubeddu) ባስተላለፈው ቴሌግራም ከአርበኞች ከፍተኛ ውጊያ ተደርጎ 57 አርበኞች እንደሞቱ ከእነሱ ወስጥም ከዳተኞች የቀድሞ አስካሪ ኤርትራውያን እንደነበሩባቸው ገልጧል፣ ከጣሊያኖች ወገን አንድ ኢጣሊያዊና 14 ኢንዲጂኒ ሲገደሉ አንድ ኢጣሊያዊና 16 ኢንዲጂኒ ቆስሏል ሁሉም ከባንዳ። 1000 ጠብመንጃዎችና 12 መትረየሶች ተማርከዋል[1]።

ጀነራል ጀሉዞ ጀነዋሪ 23 ባስተላለፈው ቴሌግራም ራስ ደስታ ቺሬ በተባለው ቦታ ይገኝ እንደነበረ አረጋግጧል፣ የዳዋ ከዳተኞች አስካሪ የሚገኙባቸው 500 አርበኞች እሱ ጋራ እንደነበሩ ገልጧል። ጀነዋሪ 24 ጀነራል ጀሉዞ ባስተላለፈው ቴሌግራም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ከጦር ሜዳ የሚሸሹ ማየት አስደናቂ ስለሆነ በፊልም ቢቀረጽ ጥሩ ነበር ብሏል።

## ጀነዋሪ 28 የነበረ ሁኔታ

ጣሊያኖች በአርበጎና፣ ከሻና፣ ቺሬ፣ ጋዮ ባደረሱባቸው ጥቃቶች አርበኞች ተበታትነው እንደገና ተደራጅተው ባለ የነበሩ የጀዝማች በየነ መርዕድም ጣሊያኖች ባደረሱባቸው ጥቃት ከቦታቸው ለቀው ኮር ከርጲብተባለው ተራራ ሰፍረው ስለነበረ፣ ሁለቱ ቡድኖች በዚሁ ቦታ ተቀላቅለው ይገኙ ነበረ። ከዚህም አርበኞች ወደወላሞና ጉራጌ ለማምራት ሃሳብ ነበራቸው።
ጣሊያኖች፡-

① ከአርባጎጎና ከሸና ጀነራል ጀሉዞ
② ከቦርሲ፣ ጉራምባ ወንዶ ሻምበል ቱቺ
③ ከሻሻመኔ በዶዶላ የሰፈሩም የፓቦሊኒ ጦር ነበረ።

አርበኞች ከሁበ እና የባና መሐል ወደ ወላሞና ከምባታ እንዳይዘልቁ ጣሊያኖች በብ ቆመው ይጠብቁዋቸው ነበር። ጀነዋሪ 31 አርበኞች በራስ ደስታ እየተመሩ ወደ ጀደብ ተራራዎች ተጠግተው የነበሩ በጣሊያኖች ጥቃት ደርሶባቸው ከፍተኛ ውጊያ ተካሂዶ ጉዳት ደረሰባቸው፣ አርበኞች በአየርም ከፍተኛ ድብደባ ይደርስባቸው ስለነበረ ተበታትነው ከጣሊያኖች ከበባ እልቂት ሊያመልጡ ችሏል። ምርኮኞች አርበኞች በውጊያ የተካፈሉ በብዙ ሺህ

[1] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 972 V II



የሚቆጠሩ እንደነበረ የደረሰባቸው ጉዳትም 0600 የሚገመት እንደነበረ መስክረዋል፣ ፊታውራሪ ሽመልስ በውጊያው እንደተገደለ መስክረዋል።

ከፌብሩዋሪ 2 ጀምሮ ጣሊያኖች አርበኞች በጎዳቡት ሲከታተሉዋቸው ነበረ፣ ፌብሩዋሪ 8 ጠዋት ከፍተኛ ውጊያ ተካሄደ በጣሊያኖች ግምት ① 200 አርበኞች ተገደሉ ② 250 ተማረኩ ③ 350 ጠብመንጃዎችና 3 መትረየሶች ሊያዙ ④ 300 የአርበኞች ቤተሰብና አሽከሮች ተማረኩ ⑤ ብዙ መቶ የሚቆጠሩ ከብቶች ተያዙ የቀሩት አርበኞች ተበታተኑ። ጣሊያኖችም መከታተል አቁመው አርበኞች እስኪሰበሰቡ መጠበቅ መረጡ።

## 3ኛ ዙር ውጊያ የፌብሩዋሪ ወር ሁለተኛ አጋማሽ

አርበኞች ወደ ሰሜንና ወደ ጉራጌ ደጋፊያቸው የነበረ ወገን መሸሻቸው ለየካቲት 12 አዲስ አበባ ላይ ግራዚያኒን ለመግደል የተቃጣ ሙከራ የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ብለው ጣሊያኖች ግምት ወስደው ነበር። የመግደል ሙከራ ቢሳካ በሚፈጠረው ውዥንብርም ተጠቅመው አርበኞች ወደ አዲስ አበባ ለመግባት ይችሉ ነበረ። ምናልባት በዚሁ ምክንያት ነው ከመግደል ሙከራ በኋላ በአዲስ አበባ አዲስ ከተማ እንደመብረቅ ራስ ደስታና ደጃዝማች ገብረማርያም አዲስ አበባ መግባታቸው ዜና ተሰምቶ ነበር።

በዚሁ ጊዜ በአርበኞች ላይ የነበራቸው የፍርሐት ስሜት የተነሳ በሰሜንና በምዕራብ ኢትዮጵያ የነበሩ ወታደሮቻቸው በቀር ከሞላው ኢትዮጵያ የነበሩዋቸው ወታደሮች በአስር የሚቆጠሩ ጀነራሎችና ኮሎኔሎች የሚመሩ ወደ ዝዋይና ጉራጌ ሀገር አዘመቷቸው።
በዚሁ መሠረት፡-

1. ጀነራል ናሳሲ ከሐይቆች አካባቢ
2. ዓረብ ለማል ባታሊዮኖች
3. ባንዳ ፔሊዛሪ (Pellizzari)
4. ባንዳ ቱቺ
5. ከሐረርጌ የሊቢያ ዲቪዚዮን በጀነራል ኩበዱ የሚመሩ
6. ምዕራብ ባሕር ሐዲድን ይጠብቁ ከነበሩ ወታደሮች አብዛኛው ዋና አዛዥ ጀነራል ጋሊና ጭምር
7. ከሰሜን ሸዋ በጀነራል ትራኪያ የሚመሩ
8. በባቡር ሐዲድ የነበሩ የጀነራል ናታለ፣ ቶስቲ ወታደሮች
9. ባንዳ ክሪኒቲ (Criniti)

ግራዚያኒ ከሰሜን የሚዘምቱ ጣሊያኖች ጀነራል ትራኪያ ኮሎኔል ቶስቲ በጀነራል ጋሊና ስር ሆነው እንዲዘምቱ፣ ጀነራል (ቶንሰል ጊስኪ) ብቻ እቦታው እንዲቀር አደረገ፣ በፍሪ አቅጣጫ ወደ ከምባታ እንዲንቀሳቀሱ አደረገ። የምዕራብ ኢትዮጵያ ጦርም በተጠንቀቅ እንዲቆም ተደርገዋል።

## ፌብሩዋሪ 11-15

በአዳሚቱሉ እና በመቂ የነበሩ አርበኞች ጣሊያኖች እንቅስቃሴያቸውን እንዲከታተሏቸው ነበር፣ እንደዚሁም ከዙቋላ ወደ ጉራጌ የሚወስደው መንገድም ባንዳ ሞጆና ባንዳ አዳማ የተባሉ የአርበኞች እንቅስቃሴ እንዲከታተሉ ተደረገ።

## ፌብሩዋሪ 16 እና 17

በኰሎኔል ናቻለ የሚመሩ፣ በኰሎኔል ሾግክን የሚመሩ፣ እንደዚሁም በጀነራል ሚስኪ የሚመሩ የዓረብ ሶማል ባታሊዮኖች ያሉባቸው የሻምበል ቱቺ ባንዳና የፐሊዛሬ ባንዳ የሚያጠቃልል ከመቂ በስተሰሜን አርበኞች ይገኙበታል በተባለ ቦታ ሰፈሩ፡፡

## የመቂ ውጊያ

አርበኞችን ከበናል ብለው ጣሊያኖች በሚተማመኑበት ሰዓት አርበኞች ከከበባው ለመውጣት በጣሊያኖች ላይ ጥቃት ፈጸሙ፣ ከባድ ውጊያዎች ተካሄዱ፡፡ የአርበኞች ጥቃቶች ዋና ዓላማ የጣሊያኖች ጥበቃና ትኩረት አሳስተው ለማምለጥ እንዲችሉ ነበረ፡፡ አርበኞች ዕቅዳቸው ተሳክቶላቸው 12ኛ ባታሊዮን ዓረብ ሶማልና ባንዳ ፐሊዛሬ መሐል ክፍተት ነፃ ቦታ አግኝተው ወደ ጉራጌ ሀገር ለማምለጥ ችሏል፡፡ የሻምበል ቱቺ ባንዳዎች አርበኞችን በየሄዱበት እንዲከታተሉቸዋውና ወደ ቡታጅራ እንዲያመሩ ታዘዙ፡፡ አርበኞች የሚገኙበት ጎጀቲ መሆኑን ስለተሰማ ሁሉም ወደ ጎጀቲ በመገስገስ 1200 ከሚሆኑ አርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥመው እንዲበታተኑ አደረጉዋቸው፡፡

## ፌብሩዋሪ 20

የናታለ ጦር ጎጀቲ እንደደረሰ ራስ ደስታ በዚሁ አካባቢ እንደሚገኝ የሚል መረጃ ያገኛል፡፡ በዚሁ ጊዜ አንድ ባታሊዮን ጦር ፊት ለፊት አጥቂ ሌላ ባታሊዮን በቀኝ አጥቂ በማሰማራት ውጊያ በአርበኞች ላይ ይከፍታል፣ አርበኞችም በኃይል እየተከላከሉ ከዋሉ በኋላ ጭለማ ይሰያቸዋል፡፡ በዚሁ ቀን ውጊያው ጀግናው ደጃዝማች ገብረማርያም ተገደለ፣ ደጃዝማች በየነ መርዕድም ተማረከ ፣ እየር ኃይል ከፍተኛ እስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ይህ የጣሊያኖች ድል ለአዲስ አበባው የመግደል ሙከራ ተገቢ የሆነ የበቀል እርምጃ ነው ብለው በመገምገም በጣም ተደስተውበታል፤ራስ ደስታ በሽሽት አምልጧል፡፡

## ፌብሩዋሪ 21

በዚሁ ቀን ጣሊያኖች ከጎጀቲ በስተምዕራብ አርበኞቹን በመፈለግና ሕዝቡን በመጨፍጨፍ አሳልፈዋል፡፡ የቱቺ ጦር ወደ ሸርሸራ ሰፍሮ መስካን የራስ ደስታ እናት ትውልድ ሀገር ድረስ በመሄድ እያሰሰ ነበር፡፡

ኰሎኔል ናታለ እና ጀነራል ጋሊና በሰሜናዊ እና ደቡባዊ ጉራጌ እያሰሱ ይሄዱ ነበር፡፡

## ፌብሩዋሪ 22 እና 23

ጀነራል ጋሊና ፌብሩዋሪ 22 ሞሉሁን ነበረ በ23 ቶሌ ደርሶ ነበረ፡፡ ሻምበል ቱቺ ፌብሩዋሪ 23 ራስ ደስታ ከ40 ተከታዮቹ ጋራ ሆኖ ወደ ኢንዣ እንደሄደ መረጃ ያገኛል፡፡ በዚሁ ጊዜ የእሱ ባንዳዎች አንድ ሌሊቱን በመጓዝ ወደ ሰፍራው ደርሶ ሳይነጋ ራስ ደስታ ያለበት ቦታ እንዲከብና ራስ ደስታን እንዲይዝ ትእዛዝ በመስጠት ያሰማራል፡፡ ጀነራል ጋሊና ወደ ቶሌ አቅጣጫ



ያመራል የኰሎኔል ናታሌ ጦርም ዘሰፈው ክዘባ ለማድረግ ወደ ሆሆ ያሰማራል፡፡ ከዚህም ኩቶሌ ወደ ደመራስ፣ ወልቂጤ፣ እገ፣ ጉመር አርባ መዝለቅ ነበረባቸው፡፡

## ፌብሩዋሪ 24

በዚሁ ቀን ጠዋት ራስ ደስታ የመሸገበት በባንዳ ቱቺ ተከበበ፣ አጭር ውጊያ በኋላ ራስ ደስታ ተማረከ ምህረት እንዲደረግለት ጠየቀ ከሰዓት በኋላ ግን ተረሸነ፡፡ ከፌብሩዋሪ 25 እስከ ማርች 4 ጀነራል ጋሊና እና ኰሎኔል ናታለ የተበታተኑ የራስ ደስታ ጦር ፍለጋ ኩቶሌ ደመራስ፣ ወልቂጤ፣ ኢጃ ጉመር አርባራጌ ተሰማርተው ከቆዩ በኋላ ወደእየምድብ ስራቸው ተመለሱ፡፡ ጣሊያኖች የራስ ደስታ መያዝ በየካቲት 12 ከተደረገው የግራዚያኒ የመግደል ሙከራ እያይዘውታል፣ የግራዚያኒ የመግደል ሙከራ የራስ ደስታ መገደል ተበቅለናል ብሏል፡፡ የጀነራሎችና የኰሎኔሎች ጋጋታ ጥቂት አርበኞችን ለመዋጋት ነው፡፡ ጣሊያኖች የእግዚአብሔር ፍርድ ተፈጽመዋል እያሉ ጉራቸው ያሰሙ ነበረ፣ ይሁን እንጂ ትግሉ ቀጥሎ ጣሊያኖች ተሸንፈው ኢትዮጵያ ከሀገራችን ወጥቷል፡፡

ፌብሩዋሪ 1 ቀን ጀነራል ናዚ ባስተላለፈው ቴሌግራም ኰሎኔል ፓስኮሊኒ ተከታትሎ አርበኞችን እንዲያጠቃ ባዘዘው መሠረት ኦሮታ በተባለው ተራራ ከአርበኞች ጋራ ባደረገው ውጊያ ከተማረኩ ሰዎች ከደጃዝማች በየነ መርዕድ ፊታውራሪ በሐደና ግራዝማች ደምሴ ጋራ ይጓዙ የነበሩ ሴቶች ይገኙባቸው ነበር፡፡ እነሱ በሰጡት ቃል በአርበኞች የደረሰ ጉዳት የሞቱና የቆሰሉ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ እንደነበረ ገልጧል፡፡ እንደዚሁም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አርበኞች ከጣሊያኖች እየሸሹ ወደ ወላሞ ለመሄድ እየሞከሩ መሆናቸውን ገልጧል፡፡

ከአርበኞች ወገን ከሞቱ መሐከል 8 ሹሞችና 50 ኤርትራውያን ከዳተኞች እንደሚገኙባቸው ተናግረዋል፡፡

ፌብሩዋሪ 1 ቀን ጀነራል ናዚ ባስተላለፈው በሌላ ቴሌግራም ኰሎኔል ፓስኮሊኒ (Pascolini) ከአርበኞች ጋራ ከባድ ውጊያ አድርጎ እንደነበረና የአርበኞቹም ብዛት በብዙ ሺህ የሚቆጠር እንደነበረ ከተማረኩ ሰዎች ለመረዳት እንደተቻለ፣ አርበኞችም ይመሩ የነበሩ በራስ ደስታ በደጃዝማች ገብረማርያምና በደጃዝማች በየነ መርዕድ እና በፊታውራሪ ሽመልስ እንደነበረ ገልጧል፡፡

በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት በትክክል ባይታወቅም ከፍተኛ ነው ብሏል፣ በጣሊያኖች ወገን የደረሰው ጉዳት የሞቱና የቆሰሉ አንድ መቶ የሚጠጉ ነበሩ፡፡ ከቆሰሉ መሐል አንድ የኢጣሊያ የጦር መኰንን ብቻ ነበረ፡፡

ላይ ስለተጠቀሰው ውጊያ አስመልክቶ ግራዚያኒ ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ባስተላለፈው ቴሌግራም ጀነራል ናዚ ያልገለጠው የተማረኩ ሴቶች የተገደሉ መሆናቸውን ገልጧል[1]፡፡

ፌብሩዋሪ 3 ግራዚያኒ በየዓና ስለተደረገው ውጊያ አስመልክቶ ባስተላለፈው ቴሌግራም[2] በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት የሞቱና የቆሰሉ 200 የሚጠጋ ነበረ 4 የጦር መኰንኖች ተገድለዋል 4 ቆስሏል፡፡ በአርበኞች የደረሰ ጉዳት እንደ አንድ ቱሪ ነው ብሏል፡፡ ይህ ኰሎኔል ፓስኮሊኒ ያደረገው ውጊያ ነው፡፡ በዚሁ ቀን በዚሁ አካባቢ ናዚ ሻምበል ቱቺ ከአርበኞች ጋራ ስላደረገው

---

[1] Governo Generale A.O.I Allegato N 1046 V II
[2] Governo Generale A.O.I Allegato N 1047 V II

(አርበኞች) ከመኖሪያቸው በላይ መሪዎቻቸው ደጃዝማች በየነ መርዕድ ገብረማርያም የተገደሉ መሆናቸውን፣ ራስ ደስታ ቆስሎ ሸሽቶ ያመለጠ መሆኑን አብራርተዋቸዋል። ለጣሊያኖች ጥሩ ያላየ የጎጀቲ መንደር ተገቢውን ቅጣት የደረሰበት መሆኑን ገልጧል። ፌብሩዋሪ 23 ጄኔራል ጋሊና ቶሊ መንደር ደርሶ በመንደሩ ሕዝብ እንዳሳገኘ ገልጧል፣ ራስ ደስታ 2 ቀን በፊት 3 ሰዓት በእግር መንገድ ርቆ የሚገኘው ኮካ ከሚባለው መንደር ደርሶ መንደሩን እንዳቃጠለው ገልጧል እንደ ባታሊዮን ጦር አጋማይ ወደሚባለው መንደር ልኮ ገብረማርያም የሚኖርበት ስለሆነ ስለ ራስ ደስታ የት እንደሚገኝ መረጃ ለማግኘት በመንደሩ ሕዝብም የመቀጣጫ ጭፍጨፋ ለማካሄድ ነበር፣ የተገኙ መረጃዎች ግን የተለያዩና ተቃራኒ ነበሩ ብሏል። ከዚና አጋማይ የተባሉ መንደሮች የሸፍቶች ቤተሰቦች መኖሪያ ስለሆኑ እንዲወድሙ ተደርገዋል። ራስ ደስታ ባለፈው ምሽት 4 ሰዓት በዚሁ ኮካ መንደር እንዳለፈና ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ እንደሄደ፣ ፊታውራሪ ታደሰ 30 ተዋጊዎች ጋራ አብሮ እንደነበረ፣ ራስ ደስታ በተቅማጥ ይሰቃይ እንደነበረ፣ የገብረማርያም ሚስት 100 ታጣቂዎች አስከትላ ቶኩር ወደ ተባለው 3 ቀን እግር የሚርቅ መንደር እንደመራች፣ ሻምበል ቱቺ መስኪን የራስ ደስታ እናት የቀድሞ መኖሪያ ድረስ በመዝለቅ ያገኘው ነገር እንዳልነበረ፣ ለማግስቱ ጠዋት ሐቦ ወደ ተባለው ቦታ አርበኞች ያመሩበት ነው ስለተባለ እስካሁ እንደሚልክ ገልጧል።

ፌብሩዋሪ 24[1] ከዋናው መሥሪያ ቤት ከአዲስ አበባ በኢታ ማጆር ሰው ሰራሽ የጦር ክፍሎች የተላለፈው ቴሌግራም ፌብሩዋሪ 19 (የካቲት 12) እስተራ የመግደል ሙከራ በኋላ ሽፍትነት የሚገኙ መሪዎች ሁሉ ከሸመልስ በኋላ በየነ መርዕድ በኋላም ገብረማርያም ዛሬም ራስ ደስታ በሻምበል ቱቺ ጦር ተማርኮ ስለተገደለ የእግዚአብሔር ፍትሕ ፍርዱን ሰጥቷል ብሏል።

በዚሁ ቀን ፌብሩዋሪ 24, 1937[2] ከመትር ለየት ያለ ሪጅም የራግርት ቴሌግራም ግራዚያኒ ለዱቼ መብሊኒ በላከው ዱቼ ሆይ በማለት ይጀምራል ከራስ እምሩ መያዝ በኋላ የመጨረሻው የተቃዋሚዎች መሪ ራስ ደስታን ለማውደም በዕጡኝ ትእዛዝ መሠረት፣ እኛን በሰላም እንዲሰጥ የተደረገ ሙከራ ከከሸፈ በኋላ ከቡርንትም እኛን በሰላም እንዲሰጥ 7 ቀናት ጊዜ እንዲሰጠውና ቀኑ ካለፈ በኋላ ግን ምህረት እንደማይደረግለት በሰጡኝ መመሪያ መሠረት የተሰጠው ጊዜ እንዳለፈ እኔ ራሴ በራስ ደስታ ላይ የሚደረገው ዘመቻ ለመምራት ወደ ይርጋገለም ሄጄ ነበር። በእርግጥም ከሸዋ በተደረጉ ወጊያዎች የጉጂ ዶል 1ኛ መቻ..ሊያ በሚከበርበት ጀኑዋሪ 20-21-22 ራስ ደስታ ከፍተኛ ሽንፈት ደርሶበት 500 ጠብመንጃዎች 30 መትረየሶችና 4 መድፎች ተማርከው ነበር። ደጃዝማች በየነ መርዕድ በነበረበት በባሌ ከፍተኛ ጥቃት ከጣሊያኖች ስለደረሰበት ወላም በጣሊያኖች ያልተያዘ ስለመሰለው ወደ ወላም ለማምራት በማሰብ ከጣሊያኖች ጦር ጥበቃ እምልጠ በየብና ለማለፍ ችሎ ስለነበረ ራስ ደስታ ያሉበትው ድጋፍ ለማግኘት ችሎ ነበር። በዚሁ ጊዜ በራስ ደስታ ላይ እንደዚሁም በደጃዝማች ገብረማርያም ላይና ይከተሉት በነበሩት የዓዋ ከፍተኞች ኤርትራውያን፣ ከእነሱ ጋራ በተቀላቀለው የበየነ መርዕድ ኃይለኛ ጦር ላይ ፣ በጀኔራል ናዚና በጀኔራል ጀሎዚ የሚመሩ የኢጣሊያ ወታደሮች በማምራ ጥቃት እንዲፈጽሙባቸው አዘዝኩ። ባስከተለው ከባድ የየዋና ውጊያዎች ከትልቁ የሲቢያ ዲቪዚዮን ብቻው 7 የጦር መኮንኖችና

[1] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 1155 V II
[2] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 1156 V II






ራስ ደስታ ዘሜካ ዘቡታጅራ ከመገደሉ ጥቂት ሰዓት በፊት

(fot. «Illustrazione Italiana»)

Ras Destà, subito dopo la cattura, viene interrogato davanti al Tribunale di guerra



ራስ ደስታ የተገደለበት አጠገብ የሚገኘው ዛፍ

BUTTAGERÀ — L'ALBERO PRESSO CUI FU UCCISO RAS DESTÀ

ሳለ ውጊያ ባስተላለፈው ቴሌግራም በአርበኞች የደረሰው ጉዳት 60 ተገድሏል፣ ከባንዳ ቁጥ የሞቱ 22 የቆሰሉ 23 ነበሩ። በኰሎኔል ፓስኮሊኒ ጦር ላይ የደረሰው ጉዳት በትክክል እንደሚከተለው ነበረ ብሏል። 3 የጦር መኰንኖች ተገድለዋል 5 ቆስሏል የኢጣሊያ ተራ ወታደር የቆሰለ 1 ኢንጂነር የተገደሉ 100 የቆሰሉ 138። በዚሁ ቀን ናዚ ባስተላለፈው ቴሌግራም የሞቱና የቆሰሉ ጣሊያኖች የስም ዝርዝር ከገለጸ በኋላ ከሊቢያ የሞቱ 53 የቆሰሉ 102፤ ከባንዳ የሞቱ 47 የቆሰሉ 36 መሆናቸውን አስረድቷል።

ከዚህ በላይ ስለተጠቀሱ ውጊያዎች አስመልክቶ ግራዚያኒ ፌብሩዋሪ 5 ለቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ባስተላለፈው ቴሌግራም ጀነራል ናዚ ያልገለጸው የተማረኩ ሰዎች (ሴቶች ቤተሰቦች ጭምር) የተገደሉ መሆናቸውን ገልጧል።[1)]

ፌብሩዋሪ 20 ኰሎኔል ናታለ ባስተላለፈው ቴሌግራም የራስ ደስታ ተዋጊዎች ከጎጀቲ በስተደቡብ እንደሚገኙ ከማረካቸው ሰዎች ባገኛቸው መረጃዎች ለማወቅ መቻሉን ገልጾ ራስ ደስታና ደጃዝማች ገብረማርያም ወደ ሰላም እያመሩ መሆናቸውን፣ ደጃዝማች መርዕድ ሚስቱ ቀስሰው ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ሃሳብ እንዳላቸው አብራርቷል።

ፌብሩዋሪ 20 ኰሎኔል ናታለ ባስተላለፈው ሌላ ቴሌግራም ከጎጀቲ መንደር በስተሰሜን ውጊያዎች እየተካሄደ መሆናቸውን፣ ደጃዝማች በየነ መርዕድ ፊታውራሪ ተሰማ ወልደጊዮርጊስ፣ ቀኛዝማች በላይነህ ዲሉማ፣ ቀኛዝማች ብዛብህ አካሉ የተማረኩ መሆናቸውን ገልጧል። በውጊያው ተካፋይ የነበሩ ራስ ደስታና ደጃዝማች ገብረማርያም መቁሰላቸው አለመቁሰላቸው ለማረጋገጥ አልቻልኩም ብሏል። በተገኘው ድል ተጠቅሜ አርበኞቹን ለማሳደድ 2 ባታሊዮን ጦር እንዲላኩልኝ እለምናለሁ። በሁለቱ ወገን የደረሰ ጉዳት ለወደፊት እገልጻለሁ፣ በጎጀቲ በስተሰሜን ራስ ደስታ ሊገኙበት ስለሚችል በአየር እንዲደበደብ እለምናለሁ ብሏል።

ፌብሩዋሪ 21 (2) ኰሎኔል ናታለ ባስተላለፈው ቴሌግራም ትናንት በጎጀቲ የተካሄደው ውጊያ ውጤት እየሰጠ ነው፤ በአሁኑ ሰዓት ትናንት ጦርነቱን ይመራ የነበረው የደጃዝማች ገብረማርያም ሞት እያረጋገጥኩሁ ነው። የደጃዝማች ገብረማርያም የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አስከሬን ፎቶግራፍ አስነሥቼ ደጃዝማች በየነ መርዕድ፣ ፊታውራሪ ተሰማ፣ ደጃዝማች ተክሉ፣ እንዲሁም የአርመን ዜጋ የሆነች ሴት ሁሉም በአንድነት ደጃዝማች ገብረማርያም መሆኑን አረጋግጠው መስክረዋል።

ፌብሩዋሪ 21 ጀነራል ሚስኪ ባስተላለፈው ቴሌግራም የበየነ መርዕድ ልጅ ተሰልቦ በመንገድ አግኝቶ እንደሰበሰበው ገልጧል፣ በጣሊያኑ ፐሊዛሪና በግራዝማች ጋሰሳ የሚመሩ ባንዳዎች አሰሳ አድርገው 200 ሰዎች መያዛቸውን ከእነሱ ውስጥም 60 ባለመማረያ እንደነበሩ ገልጧል። እስካሁን በተደረገው አሰሳ 635 ሰዎች ለውጊያ ብቁ የሆኑ ከ1200 የሚበልጡ ሴቶች ሕፃናት ሽማግሌዎች ተማርከዋል። ከአርበኞች ወገን የደረሰ ጉዳት የሞቱ 300 ሰዎች ናቸው፣ ከጣሊያኖች ወገን የደረሰ ጉዳት ገና አልተረጋገጠም ብሏል።

ፌብሩዋሪ 22 ጀነራል ጋሪቦልዲ ከአዲስ አበባ ለተሰየሙ የጦር ክፍሎች በላከው ቴሌግራም በኰሎኔል ፓስኮሊኒ PASCOLINI የሚመሩ ተዋጊዎች ባካሄዱት ውጊያ ፊታውራሪ ሽመልስ ተገድለዋል። በሐይቆችና በጎጀቲ በናታለ ቁጥ ፐሊዛሪ የሚመሩ ወታደሮች እንደዚሁም በጀነራል ሚስኪ የሚመሩ 12ኛ ዓረብ ሶማል ወታደሮች ባደረጉዋቸው ውጊያዎች በብዙ መቶ ሽፍቶች

[1)] Governo Generale A.O.I Allegato N. 1059 V II
[(2)] Governo Generale A.O.I Allegato N. 1138 V II



300 ወታደሮች ተገድለዋል። ከዚህ በኋላ ከብዙ ቦታዎች ባገኘናቸው መረጃዎች የሽፍቶች (አርበኞች) መሰብሰቢያ ጉራጌና ከምባታ መሆናቸውን ስለታወቀ በእነዚህ ቦታዎች እንድናተኩር ተደረገ። በዚሁ መሠረት ከጀነራል ጋሊናና ጀነራል ሚስኪ እንደዚሁም ኰሎኔል ናታሌ በሞጆ ለስብሰባ ተቀምጠን በሁለት አቅጣጫ ወደ ጉራጌና ከምባታ እንዲዘምቱ አደረግሁ። የዚሁ ታክቲክ ውጤት ሙሉ በሙሉ የተሳካ ስለሆነ ኰሎኔል ናታሌ በጎጀቲ ባካሄደው ጦርነት በየነ መርዕድን በቁጥጥሩ ስር በማዋል እንዲረሸን ከማድረጉም በላይ ገብረማርያም ተገደኛ የኢጣሊያ ጠላት ነው፣ በ1931 የኢትዮጵያ ጦር በመምራት ሶማሊያን ለመቆጣጠርና ለመያዝ እቅድ ነበረው። የጎጀቲ ጦርነት ይመራ የነበረው በራስ ደስታ ነበረ፤ እሱ ግን አምልጦ ለመሸሽ ችሎ ነበር ሆኖም በጉበዙ ሻምበል ቁጥ የሚመሩ የደጃዝማች ተክሉ የትግራይ ባንዳዎች ተማርኮ ወዲያውኑ በጥይት ተደብድቦ እንዲገደል ተደርገዋል። በዚሁ ወቅትም በሕይወቴ ላይ የመግደል ሙከራ የተቃጣበት ነበር፣ ራስ ደስታና ደጃዝማች ገብረማርያም ተበሩ በመቁረጥ ወደ ሰሜን በሚሸሹበት ጊዜ አዲስ አበባን ለመያዝ እየገሰገሱ ነው የሚል ወሬ በአዲስ አበባ ይናፈስ ነበረ። ዱቼ ሆይ ይህ የሕሊና ዕረፍት የሚሰጠን ድል ለክቡርነትዎ እያበረከትኩ፤ ከእንግዲህ በምዕራብና በደቡብ ኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት በመፍጠር፣ በሸዋ በሚፍጨረጨሩ ተቃዋሚ ኃይሎችን ለመደምሰስ ብቻ እናተኩራለን የክቡርነትዎ ፍጹም ታማኝ በማለት ሪፖርቱን ደምድሟል። በዚሁ ቀን ፌብሩዋሪ 24 ሻምበል ቁጥ ለግራዚያኒ በላከው ቴሌግራም ዛሬ 24 ከጠዋቱ 12 ሰዓት የእኔ ተዋጊዎች ራስ ደስታ ዳምጠው ማርከዋል፣ ክቡር የመንግሥት መሪ (ሙሶሊኒ) በሰጡት ትእዛዝ መሠረት በምሽቱ በ11፡30 በጥይት ተደብድቦ ተረሽነዋል ብሏል።

በዚሁ ቀን ሻምበል ቁጥ ዝርዝር ማብራሪያ ሲሰጥ ራስ ደስታ ወደሸሸበት ከእኔ ባንዳዎች በቂ ኃይል ልኬ ሙሉ ሌሊት ተጉዘው ራስ ደስታ ከ5 ሹሞች ሌሎች አርበኞች ይገኙበት ወደነበረ ምሑር ደርሰው ባንዳዎች ሌሊቱ መንደሩን ከበበው ከአጭር ውጊያ በኋላ ውጊያን በማቆም እጁን ለባንዳዎች ይሰጣል። በዚሁ ውጊያ ፊታውራሪ ካሣ ባላምባራስ ተሰማ ልጅ ሬጋ ፀሐፊው ኢልያስና 20 አርበኞች ተገድለዋል፣ ሌሎች የራስ ደስታ ተከታዮች አርበኞች የቆሰሉ ወደ እኔ ድንኳን እየመጡ ይገኛሉ። ከእኔ ባንዳ ጉዳት አልደረሰም፣ 2 መትረየስና 40 ጠብመንጃዎች ተማርከዋል። ከመረሸኑ በፊት ራስ ደስታ በደጃዝማች ተክሉ መሸሻ እንደተያዘ የሚል ጽሑፍ አስፈርሚያለሁ ብሏል[(1)]።

## ረ. ጨርጨር አርሲ

መጀመሪያ ዙር ብለው ጣሊያኖች የጠሩት በጨርጨርና ጋራሙለታ በፊታውራሪ በሐደና ፊታውራሪ ሺመልስ የሚመሩ አርበኞች ላይ ብዙ ወታደሮች ከማሰማራታቸው በላይ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጀግኖች ወደ ጣሊያኖች የገቡ በቀድሞ ጀግና በፊታውራሪ ሚሊዮንና በሌሎች መሪዎች ባንዳዎች ሳይሆን አርበኞች የሚል መጠሪያ በጣሊያኖች የተሰጣቸው እየተረዱ ነበረ። ዋናዎቹ የአርበኞች መሪዎችና ተዋጊዎች በጣሊያኖች ሳይገደሉ ወይንም ሳይማረኩ ወደ ሌላ አካባቢ ለመሄድ ችሏል። የጣሊያኖች ዋና ዓላማ የባቡር ሐዲድ ስትራቴጂ አስተማማኝ ለማድረግ ነበር። በአርሲ የሰፈሩ አርበኞች

[(1)] Governo Generale A.O.I. Allegato N. 1159 V II

ከጨርጨር ጋራሙለታ የሸሹ በፊታውራሪ በሐደና ሺመልስ የሚመሩ እንደዚሁም በሰፍራው የነበሩ በልጅ አበበ ዳጋፋር የሚመሩ ነበሩ) ጉጉ ብሚባሉ ተራራዎች ከገለምሶና ጨለሉል መሐል የሰፈሩ 6000 የሚያጠቃልል ነበረ። ቀጥሉ ግን በጣሊያኖች ተሰብኮ ልጅ አበበ ደጋፋር ወደ ጣሊያኖች ከመግባቱም በላይ ከጉናቸው ተሰልፎ አርበኞችን እንዲዋጋ በጠየቀው መሠረት ተፈቅዶለት ባንዳ ሆኖ ነበር። 2ኛው የአርበኞች ቡድን ቢራቄ በጢቾ ይገኝ የነበረ ነው፣ 5000 ተዋጊዎች ነበሩት ከየረር ውጊያ ሸሽተው ወደዚሁ ቦታ የሰፈሩ ናቸው። የኢትዮጵያ አርበኞች ከጣሊያኖች በደረሰባቸው ጥቃት በማምስጥ በፊታውራሪ ሺመልስ የሚመሩ 1000 በፊታውራሪ በሐደ የሚመሩ 4000 ወደ ሲዳሞ በማምራት ከራስ ደስታና በየነ መርዕድ ጦር ሊቀላቀሉ ችሏል።

በደሰምበር መጨረሻ ጣሊያኖች የአርበኞች መፈራረስ ምልክት በማለት ደስ ያሰኛቸው ተፈጠረ። በፊታውራሪ ሺመልስና በቀለ እየለ አርበኞች ከፊታውራሪ ወሊሺ አርበኞች ያስመግባባት ተፈጥሮ ግጭት ተፈጥሮ ፊታውራሪ ወሊሺ ለጣሊያኖች እጁን በጥቷል።

## ሠ. ባሌ

አርበኞችን ለማጥፋት የተዘጋጁ ጣሊያን ወገን የሚከተሉ ነበሩ።

1. 11ኛ የአማራ ባታሊዮን በደዳቻና ሳያማና መሐል
2. 38ኛ የሶማል ባታሊዮን በሸዳላና አንቾራ መሐከል
3. የምሥራቅ አሩሲ ጦር ሀ/37ኛ የአማራ ባታሊዮን ለ/4ኛ የሶማል ባታሊዮን እና ሐ/ ዱባት ከአንቾራና መአቡል ቃሲም መሐል
4. የጨርጨርና ግራሙለታ ጦር 5ኛ ሀ/ የሶማል ባታሊዮን ለ/ ዱባት ሐ/ የ1ኛ ባታሊዮን በከፊል ከአቡል ቃሲምና መልካ ሚልኪ መሐል
5. በጦር ሰፈሮች (ሚልከይ፣ ግልካ ቲቢ እግጋሉ) የሰፈሩ
6. ባሂቱ ባንዳ ከጊኘር በስተምሥራቅ
7. ዳሎ ባንዳ በማእከላዊ መንግሥት የሚታዘዝ

በአርበኞች ወገን የተሰለፉ የሚከተሉት ነበረ

1. በፊታውራሪ ሻለቃ አሰፋው የሚመሩ አብዛኛው የቀድሞ የኢትዮጵያ መደበኛ ጦር 1700 ወታደር 50 መትረየሶች የነበራቸው በጉሬ አካባቢ ሰፍረው ነበር።
2. በፊታውራሪ በሐደ የሚመሩ 1200 በማኮና አካባቢ
2. በፊታውራሪ ተሰማ የሚመሩ በጥቂት መቶ የሚገመቱ ከጊኘርና ግላን መሐል የሰፈሩ
4. በቀኛዝማች ተዘራ የሚመሩ በጥቂት መቶ የሚገመቱ በዓራብሊግ ተራራ የሰፈሩ
5. በባራምባራስ አለምሴ የሚመሩ 300 በኢጀርሳ የሰፈሩ

### ሀ/ የጉሬዱ ውጊያ ፌብሩዋሪ 22-23

ውጊያው በሻለቃ አሰፋው የሚመሩ አርበኞች ፌብሩዋሪ 22 ሌሊት በጀነራል ኩበዱ የሚመሩ የኢጣሊያ ጦርን በማጥቃት ተጀመረ። ሲነጋ መልሶ ማጥቃት አካሄደው፤ ከቀኑ 6 ሰዓት ከአርበኞች የተሰነዘረባቸው ሌላ ጥቃትን በመመለስ በአሬፕላኖች እየታገዙ 2 ሰዓት የቆየ ውጊያ ተካሄዶ አርበኞችን ሊያባርሩ ችሏል። አርበኞች 150 ወታደሮች ተገድሉባቸዋል።



### ለ/ የታማሞ ውጊያ

ማርች 2 ሌሊት አርበኞች በታማሞ ተራራ ሰፍረው እንደሚገኙ ስለታወቀ የጀነራል ኩበዱ ጦር በዋት ጉዞውን ጀምሮ ከቀኑ 10 ሰዓት የአራብሊግና ታማሞ ተራራ ደረሰ፣ ቦታው በአርበኞች እንደተያዘ ተረጋገጠ። የአርበኞች ተዋጊዎች ብዛት 2200 ነበረ፣ 50 መትረየሶች ነበራቸው። 7ኛና 9ኛ የሊቢያ ባታሊዮን ከከባድ ውጊያ በኋላ ታማሞን ሲቆጣጠሩ አርበኞች በማፈግፈግ አምልጠው ከቦታው ለቀዋል። አርበኞች 500 ተገድሉባቸዋል፣ ከሞትም መሐከል ፊታውራሪ ተፈራ ይገኝበታል።

### ሐ/ የዋራ ቆምቦ ውጊያ

በኮሎኔል በሪዮ (Berio) የሚመራ ሌላ የኢጣሊያ ጦር ወደ ጊኘር እያማራ የነበረ ማርችን ዋራ ቆምቦ ወንዝ ደርሶ ከወንዙ በስተግራ የሰፈሩ አርበኞችን ጥቃት ሰነዘረ፣ ከባድ ውጊያ ተካሄዶ አርበኞች ወደ ጊኘር አፈገፈጉ አርበኞች መልሶ ማጥቃት አካሄደው ነበር ጣሊያኖችም ተከላከሉዋቸዋል። ከአርበኞች የተገደሉ 200 መሆናቸውን ተገመቷል፣ ከሞቱት መሐከል ግራዝማች እምሩ ይገኙበታል። በዚሁ ቦታ ጣሊያኖች ወድቆ የተከሰከሰ የራሳቸው አሬፕላኖች ሰብርባሬ አገኙ። የሰፈሩ ሰዎች እንደመሰከሩ የግራዝማች እምሩ አርበኞች በአሬፕላኑ ውስጥ ከነበሩ ጣሊያኖች ውጊያ ገጥመው 4 ጣሊያኖች ሲገደሉ 5ኛ ተማርኮ ከፊታውራሪ በሐደ ጋራ ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ እንደተወሰደ ተናግረዋል።

### መ/ የጉሬ ውጊያ

በጀነራል ኩበዱ የሚመሩ ጣሊያኖች ታማሞን ተቆጣጥረው ከሰነበቱ በኋላ ማርች 5 ወደ ጉሬ አመርተው አቢናስ ተራራ ሲደርሱ ከአርበኞች ተኩስ ተከፈተባቸው። አርበኞች በሻለቃ አሰፋው የሚመሩ የፊታውራሪ በሐደ የተቀላቀሉባቸው ነበሩ። በጨበጣ ሳይቀር ከባድ ውጊያ ተካሂደ አርበኞች ከጉሬ ለቀው ወጥተዋል። በአርበኞች የደረሰው ጉዳት የተገደሉ 200 ነበሩ።

በዚሁ በባሌ የሚደረገው ውጊያ የተደመደመ መሆኑን ገምቷል።

ከፌብሩዋሪ 22 እስከ ማርች 14 በባሌ በተደረጉ ውጊያዎች የደረሱ ጉዳቶች ከሁለቱ ወገኖች የሚከተሰው ነበረ።

### ሀ/ ከአርበኞች

1. በጦር ሜዳ የተገደሉ 1000 የሚጠጉ
2. ተማርከው የተገደሉ 500
3. የተማረኩ ባሰታየት 3000

የተማረኩ የጦር መሣሪያዎች 8.500 ጠብመንጃዎች 53 መትረየሶች መድፎች 3

### ለ/ ከጣሊይኖች

1. የጦር መኩንኖች የተገደሉ 3 የቆሰሉ 3
2. ተራ የኢጣሊያ ወታደሮች የተገደሉ 2 የቆሰሉ 3

3. ኢንዲጀኒ የተገደሉ 56 የቆሰሉ 138

## ሰ/ የአርሆ ውጊያ

በባሌ ከተጠቀሱት ውጊያዎች በኋላ ጣሊያኖች አርበኞችን በማሳደድ ላይ ይገኙ ነበረ። አፕሪል 11 38ኛ የሶማል ባታሊዮን በአርሆ አጠገብ ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከከባድ ውጊያ በኋላ ከአርበኞች ወገን ከመቶ የሚበልጡ ተገድለዋል፤ ከጣሊያኖች ወገን 2 የጦር መኮንኖች ሲቆስሉ 15 አስካሪ ተገድለዋል 50 ቆስሏል። በፊታውራሪ በሐዱ ተማርኮ ተወስዶ የነበረ ኢጣሊያዊ የአሬዮፕላን አብራሪ በውጊያው ተገድለዋል። ፊታውራሪ በሐዱ ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ ገብቷል።

በዚሁ ዓይነት የባሌ ውጊያ ፍጻሜ ያገኘ መሆኑን ጣሊያኖች ገምቷል።

ስለ ጉራጌ ሊሊት በ22 ፌብሩዋሪ የተደረገው ውጊያ ጀኔራል ናዚ ባደረገው ሪፖርት 2 ባለ ጥቁር ሸሚዝ የኢጣሊያ ወታደሮች ተገድለዋል ። 1 ቆስሏል 2 ሊቢያውያን ተገድለዋል። በተዋቂ ውጊያ አንድ የጦር መኮንን ሲቆስል ሊብያውያን አንድ ተገድሎ 6 ቆስሏል። በሞሽ ሆነው የኢጣሊያ ጥቃት የሞከሩ ሁሉ ተማርከው ተገድለዋል። ጣሊያኖች አርበኞችን በሚያሳድዱበት ጊዜ አንድ መቶ አለቃ በከባድ ቆስሏል አንድ 50 አለቃ በቀላል ቆስሏል። ከ1ኛ እግረኛ ሊቢያውያን 1 ሲሞት 8 ቆስሏል፤ ከ4ኛ እግረኛ ሊቢያውያን 1 ሲገደል 11 ቆስሏል፤ ከአርሞ አርበኞች (ባንዳ) 2 ሲገደሉ 5 ቆስሏል የተማረኩ 30 አርበኞች ተገድለዋል።

በዋራ ቆምቦ በተካሄደው ውጊያ የተማረኩ 15 ምርኮኞች ተገድለዋል። 2 ጣሊያኖች ቆስሏል። 13 ኢንዲጀኒ ሊቢያውያን ሲገደሉ 25 ቆስሏል። እጃቸውን ለመስጠት የቀረቡ ከጊኘር የመጡ ፊታውራሪ ተሰማና ቀኛዝማች ግዛው አብረው ከቀረቡ አርበኞች ጋራ ተገድለዋል።[1] ጀኔራል ኩበዱ አሰሳ በሚያደርጉበት ጊዜ 20 አርበኞችና ሌሎችም ሴቶቹ ሕፃናት ተማርከው ተገድለዋል። በተጨማሪም ግራዝማች ይልማና 40 የተማረኩ ወይንም እጃቸው የሰጡ አርበኞች ተገድለዋል።[2] ማርች 5 በጉሬ በተካሄደው ውጊያ ጀኔራል ናዚ ባደረገው ቴሌግራም መሠረት 2 ጣሊያኖች የጦር መኮንኖች ተገድለዋል፤ አንድ ባለ ሌላ ማዕረግ ቆስሏል። 31 ኢንዲጀኒ አስካሪ ሊቢያውያን ሲገደሉ 80 ቆስሏል። 3 ባንዳ ተገድለዋል።

በምዕራብ ባሌ የዳሉ (Dallo) ባንዳ አዛዥ የተማረኩ 29 የቀድሞ አስካሪ ኤርትራውያን ከዳተኞች ተገድለዋል[3]።

ማርሻል ግራዚያኒ ማርች 13 ለጀኔራል ናዚ በላከው ቴሌግራም የኢጣሊያ አምባገነን መሪ ዱቼ ሙሶሊኒ በግራዚያኒ በኩል ጀኔራል ናዚ በመፈጸም ላይ ያለው ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ መደሰቱን የላከለት መሆኑን ገልጾ እሱም በበኩሉ በቃል እንደነገርኩህ ሁሉ በመፈጸም ላይ ያለኸው ተግባር ትምህርት ሰጪና ወሳኝነት ያለው ብሏል[4]። አርሆ አፕሪል 11 ስለተደረገው ውጊያ ግራዚያኒ እንደገለጸው 2 የኢጣሊያ የጦር መኮንኖች ቆስሏል 15 አስካሪ ተገድሏል 50 ቆስሏል ብሏል። ጀኔራል ናዚ በበኩሉ ስለዚህ ውጊያ በላከው ቴሌግራም ብዛት ያላቸው አርበኞች ቆስለው ወይንም ሳይቆስሉ የተማረኩ

[1] Governo Generale A.O.I. ibd Allegato V1171 V II
[2] Governo Generale A.O.I. ibd Allegato V1172 V II
[3] Governo Generale A.O.I. ibd Allegato V1174 V II
[4] Governo Generale A.O.I. ibd Allegato V1192 V II



ተገድለዋል። በተጨማሪም ጣሊያኖች አሰሳ በሚያደርጉበት ጊዜ የማረኳቸው የሚሸሹ 26 አርበኞች ተገድለዋል።

## ቀ. ሰላሌ

በዲሴምበር መጨረሻ በሸዋ የነበሩ ዋናዎቹ የአርበኞች ቡድኖች የሚከተሉት ናቸው።

1. በራሴ ወንድማሞቹ አበራና አስፋወሰን ካሣ፤ ልጅ መስፍን ስለሺ።
2. በግንደበረትና መገር ዘውዱ አስፋው
3. ውጫሌ (ከዱበር ወንዝ በስተሰሜን፤ የአበራ ካሣ የበታች ሹሞች
4. ደነባ ወደ ወረኢሉ በሚወስደው መንገድ አበበ አረጋይ.

አበበ አረጋይ በጣሊያኖች የተሾሙ አስተዳዳሪዎች እየሻረ የራሱ ይመድብ ነበረ።

በሸዋ አርበኞችን ለማጥፋት የተመደቡ የኢጣሊያ ወታደሮች ሀ/ በደብረብርሃን ለ/ በአዲስ አበባ ሐ/ በአምቦ መ/ በደብረማርቆስ ሰ/ በደብረሲናና ደባ ሰፈረው ነበር። ጣሊያኖች በሚስጢር የተያዘ "F" ብለው የሰየሙት ፕላን አውጥተው ነበር። ለዚሁ ዘመቻ 1. በበሌ 2. ትራኪያ 3. ጋሬሊ 4. ቶስቲ 5. ናታሌ 6. የአልፒን ባታሊዮን 7. የወንዝ ጠባቂ ቡድን ተዘጋጅተው ነበር።

ከአርበኞች መሪዎች ድፍረትና ንቃት የተሞላበት እንቅስቃሴዎች ይወስድ የነበረ አበበ አረጋይ ነበረ። ጀኔራል ትራኪያ የአርበኞች መሪ የአበበ አረጋይ ጦር ለመደምሰስ በመንዲዳ ብቻ በመወሰን የኢጣሊያ ኃይል የማሳየት እርምጃ እንዲወሰድ ጠይቆ ስለተፈቀደለት፤ ጀኔራል ትራኪያ 1ኛ 3ባታሊዮኖች ኤርትራውያን፤ 2ኛ የደብረብርሃንና የሸዋ ባንዳዎች 3ኛ ከባድ መሣሪያዎች በመያዝ ወደ መንዲዳ አመራ። በጀኔራል ቶስቲ የሚመራ ጦርም የኢጣሊያ ኃይል ለማሳየት ወደ ደነባ አመራ። ጀኔራል ትራኪያ ደሰምበር 9 መንዲዳን ሲቆጣጠር በአበበ አረጋይ ቤተሰቦችና ንብረቶች ላይ የበቀል እርምጃ ወሰዷል። በየብስ የሚደረገው ጥቃት በአየር ኃይል የተደገፈ ነበር። አርበኞች ጣሊያኖችን ሳይገጥሙ ወደ ሬቼ አፈገፈጉ። ከዚህ በኋላ አርበኞች በቀላሉ የማይበገሩ መሆናቸውን ስላወቀ ግራዚያኒ የ"F" ምስጢራዊ ፕላን በሥራ ላይ እንዲውል ትእዛዝ በመስጠት 1. ትራኪያ 2. ቶስቲ 3. ጋሬሊ 4. በሌ 5. ናታሌ የሚመሩ ጦሮች አሰማራ።

ዘመቻው የሚመራው ራሱ ግራዚያኒ ነበረ፤

1. በትራኪያ ቶስቲ የሚመሩ ወታደሮችና የደብረብርሃንና የሸዋ ባንዳዎች ያሉባቸው በሁለት መስመሮች ከደነባ ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ መራመድ ነበረባቸው።
2. በጋሬሊ የሚመራ ጦር ከእንጦጦ ወደ ሰሜን እንዲያመራ
3. በበሌ የሚመራ ጦር የራስ ኃይሉ ባንዳ ያለበት ከአምቦ ወደ ሰሜን ምሥራቅ እንዲያመራ
4. በናታሌ የሚመራ ጦር ከየከተል (ጉጃም) አባይን በ[illegible] ተሻግሮ በአባና ኢዳቦ ወደ ሬቼ ማምራት ነበረበት።

በዚሁ መሠረት አርበኞቹ በሁሉም አቅጣጫ ስለተከዘዙ ማምለጫ እልነበራቸውም፤ በሬቼ ተሰባስበው ነበረ።

ደሰምበር 19 በጉር ወንዝ ዘውዱ አባኮራን እና ዘውዱ አባፋርዳ የተባሉ አርበኞች በጣሊያኖች ላይ ተኩስ ይከፍታሉ፤ ሆኖም በጣሊያኖች መደበኛና ባንዳ ወታደሮች ተባርረዋል፡፡

በመቱ ዋሻ በሰፈሩ አርበኞች ላይ ጣሊያኖች ጥቃት ፈጽመው 150 አርበኞችን ገድለው በመንደሩ ላይ የበቀል እርምጃ መቀጫ ወስደዋል፤ ደብረሊባኖስን ተቆጣጥረዋል እንደዚሁም ፍቼን ተቆጣጠሩ፡፡ ግራዚያኒ ለወታደሮቹ የሰጠው መመሪያ በአሁኑ ሰዓት የዘመቻ ዓላማ 1. አበራ ካሣን ለመያዝ 2. ፍቼን ባስተማማኝ መቆጣጠር 3. አካባቢውን በሙሉ ማጽዳት የሚል ነበረ፡፡

# የራስ ካሣ ልጆች መያዝና መገደል የአረበኞች ትግል አላደከመውም

ደጃዝማች አበራና አስፋወሰን በደጋሞና፤ በሰላሌ ተራራዎች ይገኙ እንደነበረ ጀነራል ትራኪያ ሰላወቀ ከበባውን በማጥበብ ሊይዛቸው ችሏል፡፡ የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ከግራዚያኒ ጀምሮ ከልክ በላይ ተደሰቷል፡፡ የግዛታቸው ማእከል በሆነው በፊቼ ከተማ አደባባይ አዲስ አበባን ለማጥቃትና ለመያዝ፤ የአዲስ አበባ ደሴ መንገድ ለማቋረጥ ትእዛዝ ይሰጡበት በነበረው የራስ ካሣ ልጆችን በመገደላቸው የአርበኞች ትግል ያበቃለት መሆኑን መሰሏቸው ከመጠን በላይ ተደስተው ደስታቸውን ይገልጹ ነበር፡፡

ደሰምበር 21 ቀን ጀነራል ትራኪያ ለግራዚያኒ ባደረገው ቴሌግራም ከምሽቱ 12 35 አበራና ወንድወሰን ካሣ በፊቼ አደባባይ የተረሸኑ መሆናቸውን ገልጧል፡፡ አርበኞች በጦር ሜዳ የሞቱ 60፤ ተማርከው የተገደሉ 53 ነበሩ፤ ኢጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት 4 የተገደሉ 31 የቆሰሉ ናቸው ብሏል፡፡ ግራዚያኒ ለጀነራል ትራኪያ ባስተላለፈው ትእዛዝ ትጥቅ የማስፈታት ሂደት እንዲከናወን፤ ሽፍቶችን ወይንም ሽፍቶች (አርበኞች) መሆናቸውን የተጠረጠሩ ሁሉ ለማጥፋትም ሙሉ በሙሉ እንዲካሄድ አደራ ብሉ ማንኛውንም እርምጃ ተወስዶ የደሴ አዲስ አበባ መንገድ ፀጥታ አስተማማኝ ማድረግ አስፈላጊ ነው፤ ይህ ሁሉ ተግባር ለማከናወን ኃላፊነት የተሰጠው ሰው እምነት የሚጣልበት ነው፡፡ ጀነራል ትራኪያ ሕዝቡ በኢጣሊያ ኃይለኛነት እንዲያምን ለማድረግና ለማስፈራራት በዘመቻው የተካፈሉ 14,000 የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ወታደሮች በፊቼ ሰልፍ እንዲያደርጉ አዝዞ፤ ወታደራዊ ሰልፍንም ጉብኝቷል፡፡ በሰልፍ ሕዝቡና ቤተክህነቱ ደንግጧል፤ ብዙ የቀድሞ ሹሞች እጃቸውን ሰጥቷል ብሏል፡፡

ጣሊያኖች ጥላን "F" ሙሉ በሙሉ ግቡን መትቷል ብሏል፡፡ ሆኖም የራስ ካሣ ልጆችንመገደል ምንም እንኳን ከፍተኛ የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣኖች የነበሩ ቢሆኑም፤ የአርበኞች የትጥቅ ትግል አላዳከመውም፡፡ ጣሊያኖች ራሳቸው የአርበኞች መሪዎች ብለው የጠቀሷቸው ያለመያዛቸውና ያለመገደላቸው የጣሊያኖች ግምት ስሕተት መሆኑን እንረዳለን፡፡

ደሰምበር 24 ጀነራል ትራኪያ ለግራዚያኒ ባስተላለፈው ቴሌግራም በባራምባራስ ዘውዱ አባፋርዳ የሚመሩ አርበኞች ከፊቼ ዘመቻ ወደ ሸዋ የተመለሱ ከጣሊያኖች ባንዳዎች ጋራ ውጊያ እንደተካሄደ ገልጧል፡፡

በ1937 ጀነዋሪ መጀመሪያ ጣሊያኖች ራሳቸው አርበኞች እንዳልተደመሰሱ አምነዋል፡፡ ከፊቼ እስከ አባይ ድረስ ሰፍረው ይገኙ የነበሩ



አርበኞች 1. በኃይለማርያም ማሞ 2. በዘውዱ አባኮራን 3. ዘውዱ አባፋርዳ 4. ዘውዱ አስፋው 5. መሰፍን ስለሺ የሚመሩ ነበሩ፡፡

በሸዋ ቆርማሽ፤ ተጉለት፤ መንዝ ሰፍረው ይገኙ የነበሩ የምሥራቃዊ ክፍል የተባሉ እንደ ቀድሞ በአንድ መሪ (አበራ ካሣ) አይመሩም፤ ሞራላቸው ወድቀዋል በማለት አሁንም ጣሊያኖች የተሳሳተ ግምት በአርበኞች ላይ ነበራቸው፤ ምክንያቱም ድሮም በአንድ መሪ የተጠቃለሉ አልነበሩም፡፡

በጀነራል ቶሴቲ የሚመሩ የኢጣሊያ ቅኝ ገዢ ወታደሮች ከፊቼ ዘመቻ በኋላ ጀነዋሪ 4 ከፊቼ ተነስተው ጀነዋሪ 6 ኢያርሶ ሲደርሱ በጎርጂ ሸለቆ በፊታውራሪ ዘውዱ አባኮራን የሚመሩ አርበኞች ላይ ጥቃት ፈጽመው98 አርበኞች ተገድለዋል፤ ከጣሊያን ወገን የደረሰ ጉዳት አልተገለጸም፡፡ እንደዚሁም በዚሁ ቀን ጀነዋሪ 6 የቀኛዝማች ይርጉ፤ ቀኛዝማች ገብረመስቀልና ፊታውራሪ ተሰማ የኢጣሊያ ባንዳዎችና ጀነራል ትራኪያ በቴሌግራም ለግራዚያኒ እንደገለጠው ከአርበኞች ጥቃት ተፈጽሞባቸው 20 አርበኞች ተገድለዋል ብለዋል፡፡

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ከራስ ካሣ ልጆች ግድያ በኋላ የአርበኞች ትግል የመቀነስ ምልክት እንዳልነበረ ነው፡፡

ጣሊያኖች መሣሪያ እንዲያስረክቡ ትእዛዝ የሰጧቸው መንደሮች ትእዛዙን አላከበሩም ብሏቸው በመንደሮች ላይ ጭፍጨፋ ቢፈጽሙም ውጤት አላገኙም፡፡

ጀነራል ትራኪያ ከአባይና ጃማ ጃርሶ መካከል 2ቱ ቀኛዝማች ዘውዱ ይገኛሉ ስለተባለ ለጀነራል ቶሴቲ አካባቢውን አሰሳ አድርጎ እንዲይዛቸው ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር፡፡

ሌላ የኢጣሊያ ኮሎኔል ለአሰሳ የተሰማራ ማርቲኔሊ (Martinelli) በዚሁ አካባቢ (ኢዳቦ) በኃይለማርያም ማሞ ከሚመሩ አርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከአርበኞች ወገን 40 ተገድለዋል ብሏል፡፡ ከጣሊያኖች 5 አስካሪ ኢንዲጂኒ ኤርትራውያን ተገድለዋል፤ 7 ቆስሏል አንድ የኢጣሊያ መቶ አለቃ ቆስሏል፡፡ ጀነራል ትራኪያ ደሰምበር 19 ከኃይለማርያም ማሞ ጋራ ስለተደረገው ውጊያ ተጨማሪ ሲሰጥ ኃይለማርያም ከነበሩት 200 ተዋጊዎች 50 ብቻ አስካሪ ቁዳተኞች ያሉባቸው ተከትለውት ሲሸሹ ሌሎች ግን ገበሬዎች በግዴታ ከእሱ ጉን ሆነው እንዲዋጉ የተደረጉ ስለነበረ አልተከተሉትም፡፡

በሸዋ ሰሜን ምሥራቅ የነበሩ አርበኞች ከራስ ካሣ ልጆች መገደል በኋላ እንደ ቀድሞ ሰፍረው ይገኛሉ እነሱም፡፡

1/ በተጉለት በወልዴ ተሰማ የሚመሩ
2/ በመንዝ በደጃዝማች አውራሪስ የሚመሩ
3/ በአንኮበር አካባቢ በባራምባራስ ይልማ የሚመሩ
4/ በእለልቱ በጅማ ሰምበቴ የሚመሩ

በእነዚህ አርበኞች ላይ የደብረሊና አንኮበር ደብሬብርሃን ባንዳዎች አሰማርተባቸው ነበር፤ ከባራምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ ጀነዋሪ 11 ቀን መታሰርና መገደል ጣሊያኖች ውጤት አላገኙም፡፡

በሸዋ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን የተደረጉ ውጊያዎች ሰላሌና ምሥራቅ ሸዋ የሚሸፍን ከኖቬምበር ወር መጨረሻ እስከ ጀነዋሪ ወር እንደሚከተለው ሊጠቃለል ይችላል፡፡

ከጣሊያኖች የሞቱ 140 የቆሰሉ 159 ከአርበኞች የሞቱ 574 የቆሰሉ በትክክል አይታወቅም ተማርከው የተገደሉ 271 እነሱም የሰጡ፡-

1/ 6 ደጃዝማቾች
2/ 33 ፊታውራሪ
3/ 89 አነስተኛ ሹሞች

4/ 13 ወይዛዝርት የታሰሩት ሹሞች በመዶች

## በ. በሸዋ ሰላምና ማረጋጋትን ለመፍጠር ጣሊያኖች የፈጸሙት ተግባር፡፡

የተደረገው ሙከራ ጣሊያኖች ለ2 ወር ፌብሩዋሪ፣ ማርች፣ አፕሪል ይዘልቃታል፡፡ ይሁን እንጂ ጥረታቸው ከደሴ አዲስ አበባ ያለው የመኪና መንገድ ጥበቃ ማድረግ ብቻ የተወሰነ ነበረ፤ መንዝ፣ መርሐቤቴ፣ ሞረድ የመሳሰሉ አካባቢዎች ለመግባት እንኳን እንዳልሞከሩ ራሳቸው ጣሊያኖች አምነዋል፡፡

ሸዋ በጣሊያኖች ላይ የማይታረቅ ትራኔ እንዳለው ለመገንዘብ ችለናል ብሏል፡፡

## 1. ፌብሩዋሪ

አርበኞቹ እየተጠናከሩ ከመሔድ በቀር ጣሊያኖች እንደተመኙት አልጠፉም

1. ከፊቼ በስተምዕራብ በሙገር ሸለቆ ልጅ ኃይለማርያም ማሞ እና ባራምባራስ ዘውዱ አባቆርጳ ሰፍረዋል፡፡
2. ከደብረብርሃን በስሜን እና በስተምዕራብ በአንሳሮ ለጣሊያኖች ተገዥነቱ አስተማማኝ ያልሆነ አንድ ምስሌኔ ስውር ቀስቃሽነት በድብቅ ፀረ ጣሊያኖች ዐመጽ ነበረ፡፡
3. በሞረድ፣ ሞጆ ጅሩ በአበበ አረጋይ የሚመራ የማያበርድ ፀረ ጣሊያኖች ዐመጽ ነበረ፡፡
4. በተጉለት ዐመፀኞቹ አነስተኛ ቢሆኑም የቀድሞ መንግሥት አደገኛ ሹሞች ነበሩባቸው፡፡
5. በሸኖ ኮርማሽ አካባቢ በአለልቱ በአደገኛ ሽፍታ በጅማ ሰምቡቴ የሚመሩ አርበኞች ሰፍረዋል፡፡
6. ከሞፈር በስተሰሜን በመንዝ ደጃዝማች አውራሪስ በግልጽ ሽፍታ ባይሆንም ምግብና የጦር መሣሪያ ለአርበኞች እያቀበሉ ከሽፍቶች ጋራ ግንኙነት ነበረው፡፡

የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ወታደሮች በደብረብርሃን፣ ደብረሲና አንኮበርና ሸኖ ኮርማች፣ መንዲዳ፣ ሺዋንጉርት ፊቼ ጦር ሰፈሮቻቸው ተወስነው ይቀመጡ ነበር፡፡

የደጃዝማች አውራሪስ ልጆች ለጣሊያኖች ያደሩ ለጣሊያኖች እጃቸው የሰጡ ስለነበረ በመንዝ የነበረ ፀረ ጣሊያኖች ዐመጽ በእነሱ አማካኝነት በፖለቲካ መፍትሔ ይገኝበታል የሚል እምነት ነበራቸው፡፡

ጣሊያኖች በቅድሚያ በሙገር፣ በአለልቱ በጅሩ ሞረድ ሞጆ ያስቸግሩ የነበሩ አርበኞችን ለመደምሰስ እቅድ አውጥተው በ2ኛ ጊዜ ደግሞ በተጉለት የነበሩ አርበኞችን ለማጥፋት ሃሳብ ነበራቸው፡፡

## የኢምበርተራ (ሞጆ) ውጊያ፣ የአበበ አረጋይ ጦር መከበብ

በአበበ አረጋይ የሚመሩ አርበኞች በጃማና ሞፈር የሰፈሩ መሆናቸውን የሚል መረጃ ስለደረሰባቸው ጣሊያኖች ከበባ አድርገው ሊደመስሱቸው በማሰብ



1. በፊቼ መንዲዳ 6ኛ ብሪጌድ 2. በሞጋ እና ፀጋ ወደብ 11ኛ ብሪጌድ ከመንዲዳ ሞጆ የሰፈሩ ተመድበው ከደጃዝማች አውራሪስም እንዲያገናኙ ጥበቃ ያደርጉ ነበር፡፡ የአበበ አረጋይ አርበኞች ወደ ደነባ በሚጓዙበት ጊዜ ጊንደ ኮሬ በተባለ ቦታ በጣሊያኖች የጀነራል ቶስቲ ጦር ተኩስ በመክፈታቸው ለጣሊያኖች የአካባቢው ሕዝብ ለመፍጀት ምክንያት ሆኖላቸው ነበር፡፡ ጀነራል ትራኪያ ሪፖርት እንዳደረገው በተጉለት ጀነዋሪ 30 5አርበኞች በሕዝቡ ላይ ዘረፋ ለመፈጸም የሞከሩ ተረሽነዋል ብሏል፡፡ በአንኮበር አካባቢ ጀነዋሪ 3 ጣሊያኖች ያገኙዋቸው የአርበኞች ቡድኖች አባርረው 30 ቤቶችን አቃጥለዋል፡፡ በጊንደ ኮሬ ተኩስ ከከፈቱ አርበኞች አንድ በጦር ሜዳ ሲገደል 2 ተማርከው ተገድለዋል፤ የጊንደ ኮሬ መንደር በጣሊያኖች ላይ ተኩስ በመክፈቱ ተደምስሰዋል፡፡ ኰሎኔል ቶስቲ አበበ አረጋይ ወደ እምበርተራ ይገኛል ስለተባለ ጀነራል ትራኪያ ከመንዲዳና ከፊቼ ወታደሮች በማስመጣት ከምዕራብና ምሥራቅ መውጫ ዘግቶ ሲጠባበቅ ኰሎኔል ቶስቲ እምበርተራ በመዝለቅ ውጊያ ገጥሞ አርበኞች ግን ለማምለጥ ችሏል፤ በጣሊያኖች ግምት ከአርበኞች .100 ተገድለዋል፡፡

## የእምቡር ውጊያ (አለልቱ)

በጅማ ሰምቡቴ የሚመሩ አርበኞች በምሽጋቸው በእምቡር ሰፍረው እንደሚገኙ ጣሊያኖች ስለደረሱበት በመልክተኞቻቸውና በምስሌኔዎቻቸው አማካኝነት ዝብሮች እንዲዘምቱባቸው አደረጉዋቸው፡፡

በእምቡር (አለልቱ) የሰፈሩ አርበኞችን ለመደምሰስ ጣሊያኖች በ3 አቅጣጫ ወታደሮቻቸው ለውጊያ አሰማርቷል፡፡

1ኛ 5ኛ ባታሊዮን ኢንዲጀኒ እና የሸኖ ባንዳዎች በሰሬው ከበባ እንዲያካሂዱ፣ ከሸኖ አለልቱ፣ ጨፌ ማርያም የሚያመሩ

2ኛ ፊት ለፊት የሚገጥሙ በሁለት መስመር የተሰማሩ ባለጥቁር ሸሚዝ ፋሽስት ወታደሮች ከሸኖ ኮርማሽ ጨፌ ማርያም የሚያመሩ በኮቺና ባርበሪኒ የሚመሩ (Coci Barberini). ሁሉም በጀነራል ጋቲ ቆንስል የሚመሩ (Console Generale Gatti) ጠዋት ፌብሩዋሪ 11 ቀን በአርበኞች ምሽግ ላይ ጥቃት ፈጸሙ፣ ከሁለት ሰዓት የፈጀ ውጊያ በኋላ አርበኞች በሌሊት ጨለማ ተገን በማድረግ ሊያመልጡ ችሏል፡፡

በአርበኞች የደረሰ ጉዳት 225 ተገድለዋል፣ ጅማ ሰንበቴ ራሱም ቆስሏል፡፡ ፌብሩዋሪ 18 ጣሊያኖች በአካባቢው ሰላም መረጋጋት አስፍረናል ብለው ወደ ጦር ሰፈራቸው ወደ ሸኖ ተመለሱ፡፡ ከጣሊያኖች ወገን 2 ባለጥቁር ሸሚዝ ቆስሏል፣ 6 አስካሪ ሲገደሉ 15 ቆስሏል፡፡

በሙገር አካባቢ በፌብሩዋሪ 10 ውጊያ የተገደሉ አስካሪ ሊቢያውያን ሬሳቸው የተቆራረጠ ያልተቀበሩ ፌብሩዋሪ 16 ቀን ተገኝቷል፡፡

ፌብሩዋሪ 18 በኢጣሊያ ጦር ላይ ጥቃት የፈጸመ ተማርኳል፤ በዚሁ ቀን በፊታውራሪ አለሙ የሚመራ ባንዳና በአርበኞች ግጭት ተደርጓል አንድ ባንዳና አንድ አርበኛ ተገድለዋል፡፡ 2 በአለሙ የተማረኩ 5 በእር አካባቢ ሕዝብ ከኃይለማርያም ማሞ ጉን ተሰልፈው ተዋግቷል የተባለው የተማረኩ በምሽት በፊቼ ተገድለዋል፡፡

# የሙገር ውጊያዎች

በኃይለማርያም ማሞ የሚመሩ አርበኞች አልተደመሰሱም ስለነበረ ፌብሩዋሪ 10 ጣሊያኖች በ11ኛ ብሪጌድ ጥቃት ፈጸሙባቸው፤ ይሁን እንጂ ከተከላከሉ በኋላ ለማፈግፈግ ችሉ ነበር። ጣሊያኖች አርበኞች ምንም አልተነኩም በማለት የአገር መንደርተኞችም ለጣሊያኖች ረድታችኋል በመባል ከአርበኞች ጥቃት ይደርስባቸው ስለነበረ፣ ጣሊያኖች በኮሎኔል ጋሬሊ የሚመሩ የፈታውራሪ ኀለሙ ኢገርሳ ባንዳዎች አሰማሩባቸው። አርበኛ አፈግፍገው ወደ ሙሉ መንደር ሊሄዱ ችሏል። ጣሊያኖች እንዳመኑት 11ኛ በቦታው ሊያሰፍን የቻለው ሰላም ጊዜያዊ ብቻ ነበረ፣ በግራዚያኒ ትእዛዝ መሠረት ጣሊያኖች ሙሉ በሙሉ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን አልቻሉም።

ፌብሩዋሪ 10 ስለተደረገ ውጊያ ጀኔራል ትራኪያ ባስተላለፈው ቴሌግራም 300 ቤቶች እንዲደመሰሱ ተደርጓል ብሏል። በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት 4 ሲሞቱ 12 ቆስሏል፣ ከአርበኞች 55 ተገድለዋል፣ ጣሊያኖች አርበኞችን በሚያሳድዱበት ጊዜ ሌሎች 200 ቤቶች በእሳት እንዲጋዩ ተደርጓል። ከኢጣሊያ ወገን 4 ሞቷል 12 ቆስሏል.

ጀኔራል ትራኪያ ፌብሩዋሪ 20 ባደረገው ቴሌ[illegible] ኢጣሊያ የባንዳ መሪ ኀለሙ በሙገር ሸለቆ በኃይለማርያም ማሞና በዘውዴ አባፋርዳ ጥቃት አካሄደ ከጣሊያኖች ወገን 5 ቆስሏል ከአርበኞች በጦር ሜዳ የተገደሉ ብዙ ነበሩ የተማረኩ 6 ከምሽቱ በ12 ሰዓት በሬቹ አደባባይ ተገድለዋል።

ጣሊያኖች በፌብሩዋሪ ወር ያካሄዱት ውጊያ ሲገመገም በጅማ ሰምቡቴ የሚመሩ አርበኞችን እንዲበታተኑ አድርገናል፣ በኃይለማርያም ማሞ የሚመሩ ከሙገር ወደ ሙሉ እንዲሸሹ አድርገናል፣ በአበበ አረጋይ የሚመሩ ከጅሩ አዳባ እንዲሸገሩ አድርገናል፣ በሰላሌ ቋሚ ባይሆንም ጊዜያዊ ሰላም እንዲሰፍን አድርገናል፣ በዋዩ ደነባ ከአርበኞች ግጭት ነፃ እንዲሆን አድርገናል። በዚሁ መሠረት የደሴ አዲስ አበባ መንገድ በስተምሥራቅ ሰላምና መረጋጋት ሰፍኗል በማለት በዚሁ ለማድረግ ያቀዱት ግቡን መትቷል ብሏል። አከሉም ጣሊያኖች እንዳመኑት በእምበርተራና በእምቡር ያሸነፍናቸው አርበኞች ወደሞፈር አካባቢ ሸሽተው ሄደው፣ ጣሊያኖችን ለማጥቃት በተለያዩ መሪዎች ስር ሆነው በተለይም በአበበ አረጋይ በሰላ ድንጋይ አካባቢ ይገኙ ነበር።

የግራዚያኒ የመግደል ሙከራ ምክንያት ጣሊያኖች ያደረጉት የሕዝብ ጭፍጨፋ በመፍራት የሸሹ ሁሉ በደብረሊባኖስ ገዳም ከመጠለላቸው በላይ በሙሉ በእንሳርና በተጉለት ከነበሩ አርበኞች በመቀላቀላቸው የአርበኞች ትግል ነፍስ እንዲዘራና ብርታት እንዲያገኝ ረድቷል። በሌላ በኩልም ለጣሊያኖች በደረሱዋቸው መረጃዎች መሠረት በራስ ደስታ ትእዛዝ መሠረት እነዚህ እየተጠናከሩ የመጡ የአርበኞች ቡድኖች ወደፊት አዲስ አበባን ለመያዝ ለሚደረገው ዘመቻ የሰሜን ጦር ግንባር ሠራዊት ሊሆኑ ይችላሉ።

## 2 የማርች ወር ውጊያዎች

### ሀ/ በተጉለት ውጊያ

በተጉለት ከተሰበሰቡ 3000 አርበኞች 200 የወታደር ደምብ ልብስ የለበሱ የቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ወታደሮች ነበሩ 20 ከዳተኞች አስካሪ ኤርትራውያን ነበሩ። የአርበኞች ዓላማ በጠርማ በር የመኪና መንገድን



ማስናከል ነበር፣ ጥቃታቸውም በሥራ ላይ በማዋል ለመጀመር አስበው የነበረ ለፌብሩዋሪ 25 ነበር።

የአርበኞችን ዓላማ ለማክሸፍ የጣሊያኖች ሰሜን ምዕራብ ሸዋ አዝ ያወጣው እቅድ፡-

1. አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ የመኪና መንገድ ትራፊክ እንዳይቋረጥ ማድረግ
2. የአርበኞች በጣሊያኖች ላይ የሚፈጽሙት ግፊት ለመከላከል እስከ ሞፈር ማባረር
3. የአርበኞችን ኃይል መበታተንና ማውደም
4. በጣሊያኖች ላይ ጥላቻ በሚያሳዩ የተጉለት መንደሮች ከባድ ቅጣት መፈጸም የሚያጠቃልል ነበረ።

ለዚሁ ተግባር ጣሊያኖች ያሰማሩዋቸው ወታደሮች የሚከተሉት ነበረ።

1ኛ በኮሎኔል ጋይቢ (Gaibi) የሚመራ ጠንካራ የፊት አጥቂ ጦር 4ኛ እና 5ኛ ባታሊዮኖች እንዲሁም 6ኛ መድፈኛ ያቀፈ ነበረ።

2ኛ ዋናው ጦር ሀ/ 5ኛ የቅኝ ግዛት ባታሊዮን ለ/ 3ኛ መድፈኛ ሐ/ 358ኛ እና 220ኛ የጥቁር ሸሚዞች ፋሺስት ወታደሮችና አብሮዋቸው የሚጓዝ መድፈኛ "ቺሬኔ" (Cirene)

3ኛ እላይ ከተጠቀሱ የጦር ክፍሎች ተቀላቅለው የሚዘምቱ ሀ/ የደብረሲና ለ/ የደብረብርሃን ሐ/ የአንኮብር መ/ የሸዋ ሰ/ በግለሰብ ሹሞች የሚመሩ ባንዳዎች ይገኙበት ነበር።

ፌብሩዋሪ 22 የኢጣሊያ ዘማች ሠራዊት ጉዞውን በመጀመር የዚንጀሮ ጊቤ ወንዝ አሰሳ አካሄደ 23 በጣርማበር አካባቢ አንድ ኃይለኛ የአርበኛ ቡድንን አባረረ። በ24 አምባ በተርጌን ተቀማጭር ከባድ ቅጣት ከመፈጸሙ በላይ በጅብ ዋሻ አካባቢ ያገኛቸውን 200 አርበኞች እንዲበታተኑ አድርገዋቸዋል።

ፌብሩዋሪ 25 በ3 አቅጣጫ የመጣ የአረበኞች ቡድን ጠርማበርን ለመያዝ የሞከሩ ብዙ ሰው ተገድሉባቸው ጣሊያኖች ተከላከለው መልሰዋቸዋል። በ26 እና 27 በአካባቢው ሰፊ አሰሳ አካሂዷል በ28 አርበኞች ጉዳት ስለደረሰባቸው ወደ ዘንደጉርና ሰላ ድንጋይ አፈገፈጉ።

ጣሊያኖች ለዘመቻ ሲነሱ የሚገጥሟቸው የአርበኞች ስም ዝርዝር ጀኔራል ትራኪያ እንደሚከተለው ይገልጸዋል።

1. በአንኮበር አካባቢ የነበረ ሀ/ ልጅ አየለ ኃይሌ ለ/ ልጅ ደስታ ሃብተሥላሴ ሐ/ ፈረደ እንዳርጌ
2. በዋዩና ደነባ በራምባራስ አበበ አረጋይ በቦታው ከነበሩ ባራምባራስ በቸሀ፣ ቢሻ ወልደና ተሰማ፣ ልጅ ይማም ወዘተ ጋራ ተቀላቅሏል።
3 በመንዝ የደጃዝማች አውራሪስና ልጆቹ።

ጀኔራል ትራኪያ እንደገለጸው[1] በጅብ ዋሻ በተደረገው ግጭት ከጣሊያኖች ወገን አንድ ባንዳ ቆስሏል። ከአርበኞች አንድ በጦር ሜዳ ሲገደል ሌላው ተማርኮ ተገድለዋል። የተገደለው ምርኮኛ ከመገደሉ በፊት በ24 በአምባ በተርጊ በተደረገው ውጊያ አርበኞች 35 እንደሞቱባቸውና ብዙ እንደቆሰሉባቸው ተናግረዋል። በደብረብርሃን 4 ዘራፊዎች(አርበኞች) ተረሸነዋል።

በሬቹ የኢጣሊያ ጦር አዛዥ እንደገለጸው የኃይለማርያም ማሞ አርበኞች ባለፉት ቀናት በጋሬሊ (Garelli) በሚመራ የኢጣሊያ ጦርና በኀለሙ

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N 1162 V II

በሚመሩ ባንዳዎች ጉዳት ደርሶበት የነበረ ከአዲስ አበባ የፈለሱ ስለተቀላቀሉበት 400 ተዋጊዎች በማግኘት ተንካሬ አግኝቷል ብሏል፡፡

ግርች 1 ቀን ጣሊያኖች ጉር ሥላሴን ተቆጣጠሩ ይኸም የመኪና መንገድ ለመቆጣጠር አስተማማኝ ያደርገዋል ብሏል፡፡ ግርች 6 ቀን በአምበር ሸለቆ ከነበሩ 400 አርበኞች ውጊያ ተደርጎ አርበኞች 10 ተዋጊዎች ሞቶባቸዋል፡፡

ጣሊያኖች አርበኞችን አውድመናል እንዲበታተኑ አድርገናል ካሉ በኋላ አክሎም ብዛት ያላቸው በሰላ ድንጋይ ተሰባሰበው ስለሚገኙ በእነዚህ አርበኞች ላይ የከፍሉ የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ጠሩን አዝምቶ ግርች 9 ሰላ ድንጋይን ለመያዝ ወሰነ፤ በሁለት አቅጣጫ በቀኝ ዋና ጦር ግንባር በኮሎኔል ጋይቢ የሚመራ ሰላ ድንጋይን ለመያዝ በግራ[1]ኮሎኔል ፑቺ (Pucci) የሚመራ እምቢሴን ለመያዝ ግርች 10 ሰላ ድንጋይ ተያዘ፤ በአርበኞች ላይ ከባድ ጉዳት ደርሶዋል፤ ከ11-14 በአካባቢው አሰሳ ተካሄዷል፤ 100 አርበኞች ተገድለዋል፤ በአካባቢው ለላምና መረጋጋት በመስፈኑ የሰላ ድንጋይ ሳሀሊት ደብረ ምጥማቅ ግርያም ቤተክርስቲያኖች እቸቸውን ሰጥቷል፡፡

ጀነራል ትራኪያ ግርች 10 ባስተላለፈው ሪፖርት ሁለቱ ኮሎኔሎች በሚዘምቱበት ጊዜ የበላይ አዛዥ ስለነበረ፤ ከኮሎኔል ጋይቢ ጉን ሆኖ የዘመተ ታማኝ የኢጣሊያ የደብረሲና ባንዳ አዛዥ የነበረ በጣሊያኖች ፊታውራሪ ሆኖ የነበረ በጦርነቱ ተገድለዋል ብሏል፡፡ ከቀኑ በ8:30 ተጠባባቂ የኢጣሊያ ወታደሮች ከአርበኞች ጥቃት ደርሶባቸው 3 ወታደሮች ቆስሏል፤ በ11 ሰዓት ሰላ ድንጋይ ተያዘች፤ አካባቢው ሁሉ እቃውን ይዞ ስለሸሸ ሰው አልባ ሆኖ ነበረ፡፡ ሁሉም ቤቶች እንዲቃጠሉ ተደርገዋል፤ ከ25 ኪሎ ሜትር የበለጠ መሬት አንድ ቤት እንኳን ቆሞ ያልተቃጠለ አይታይም ነበር፡፡ ከአርበኞች 30 በጦር ሜዳ ተገድለዋል 7 ተማርከው ተረሽነዋል፡፡ ከጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት የተገደሉ 5 የቆሰሉ 10 ነበሩ፡፡

ግርች 23 ጀነራል ትራኪያ ለግራዚያኒ በላከው ሌላ ሪፖርት ከ25 ኪሎ ሜትር በላይ በሙሉ ወድሟል፤ 40 መንደሮች ወድመዋል፤ ከ4,000 የሚበልጡ ቤቶች እንዲቃጠሉ ተደርገዋል፡፡ በጣሊያኖች ወገን የደረሰ ጉዳት የተገደሉ 31 የቆሰሉ 30 ነበሩ፡፡ ከአርበኞች በጦር ሜዳ የተገደሉ 212 ተማርከው የተገደሉ 396 ነበሩ፤ ተጉለት የሚገባት ቅጣት አግኝታለች ብሏል፡፡[1]

## 3. የእንሳሮ ውጊያ

በእንሳሮ ሰፍሮ የነበረ ስውር ዐመጽ ከግራዚያኒ የመግደል ሙከራ በኋላ ገሀድ የወጣው ከአዲስ አበባ ከእልቂት ለማምለጥ ሲሉ መጥተው ሲቀላቀሉበት ነው፡፡[2]፡፡ በእንሳሮ የነበሩ አርበኞች ለማውደም የተሰጠው ለኮሎኔል ጋሪሊ ነበረ፤ ትጥቅ ለማስፈታትም የሚያጠቃልል ነበረ፡፡ ብዙ ሰዎች የኢጣሊያ ወታደሮች በሚመጡበት ጊዜ ወደ ሽፍትነት ተሰማርቷል፡፡ በዚሁ የተነሳ ጣሊያኖች አሰሳ ማድረግና ሰው መግደል ጀመሩ፡፡ ፀጋ ወደብ በተባለው ወንዝ ከአርበኞች ጋራ የተደረገው ግጭት የሚጠቀስ ነው፡፡ ግርች 21 በተደረገው ግጭት አርበኞች ተበታትነዋል፡፡ ሕዝቡ ወደ እየቤቱ ሲመለስ ታይቷል፤ የኢጣሊያ ወታደሮችም ወደ ፍቼ ተመለሱ፡፡

---

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N. 1209 V II
[2] Governo Generale A.O.I ibd Testo N. 371 V II



ጀነራል ትራኪያ ግርች 21 ስለ እንሳሮ የላከው ሪፖርት ኮሎኔል ጋራሊ ሕዝቡ ወደ እየቤቱ እንዲመለስ የተሰጠው የጊዜ ገደብ እንዳለቀ የእንሳሮ አካባቢ መንደሮች ወደ ቤታቸው ያልተመለሱ ቤቶችና መንደሮች እንዲወድሙ አርገዋል፤ በአርበኞች አሰሳ በሚደረግበት ጊዜ 15 አርበኞች በጦር ሜዳ 12 ተማርከው ተገድለዋል፡፡ በጣሊያኖች ላይ የደረሰ ጉዳት የሞተ 1 የቆሰለ 2 ነበሩ፡፡

አርበኞቹ ጣሊያኖች በሚመጡበት ጊዜ ፀጋ ወደብ ወደ ተባለው ቦታ ሸሽተው ሄደው ስለነበረ ሊፈልጓቸው በመጡ ጣሊያኖች ላይ ተኩስ ከፈቱባቸው፡፡ ከአጭር ውጊያ በኋላ ሸሽተው አመለጡ፤ 22 አርበኞች ተገድለዋል፡፡ ከአርበኞች መሪ አንዱ የነበረው ሸቴ ዬሬ ተማርኮ ተገድለዋል፤ 750 ከብቶች በጣሊያኖች ተዘርፈዋል፡፡ ፊታውራሪ እምባው የተባለ ከጣሊያኖች ጉን ነኝ ሲል የነበረው ከግራዚያኒ መግደል ሙከራ በኋላ፤ የጦር መሣሪያ ለያዙ ሰዎች ሁሉ በፀረ ኢጣሊያ ትግል እንዲዘጋጁ ምክር ይሰጥ እንደነበረ ተረጋግጧል፡፡ የእሱ እህትም ፊታውራሪ መርከያ ከደብረሊባኖስ ሸሽተው የመጡ መጠለያ የሰጠ እንዲሸሽ ድጋፍ በመስጠቷ ተይዛ ታስራለች፡፡[1]

## 4. የሙገር ውጊያ

ከግራዚያኒ የመግደል ሙከራ በኋላ 300 ከአዲስ አበባ የሸሹ ወደዚሁ አካባቢ መጥተው ነበር፡፡ ግርች 12 ኃይለማርያም ማሞ የእህል ስንቅ ለመግዛት ወደ ሙገር መምጣቱ ጣሊያኖች መረጃ ስለደረሳቸው፤ ግርች 14 11ኛ ብሪጌድ ወደ ስፍራው ላኩ፤ ግርች 15 እና 16 ጣሊያኖች አርበኞችን ወደ ሙሉ በማሳደድ ላይ ነበሩ በሕዝቡ ላይም ኃይለማርያም በመደገፋቸው ከባድ ቅጣት ፈጽመዋል፡፡

ግርች 15 ጀነራል ትራኪያ ስለ ሙገር ውጊያ የላከው ሪፖርት ኃይለማርያም ማሞ በእንቅልፍ እንዳለ በድንገት ተገኝቶ ሆኖም የገል ንብረቱ እንኳን ሳይሰበስብ ለማምለጥ ችለዋል፤ አርበኞች 21 ሰዎች ተገድሉባቸዋል፡፡ ከጣሊያኖች ወገን 3 ቆስሏል፡፡ በታማኙ በጣሊያን ባንዳ በፊታውራሪ ግሰሙ እየተረዳ የአካባቢ ሕዝብ አርበኞቹን ለማሳደድ ተባብረዋል፡፡ ጉሐዕዮን ተወላጅ የጣሊያን አስካሪ የነበረና የከፋ ቸፈራ ባሕቱ የተባለ፤ በሬቺ ኋሪ የሆነው የራስ ካሣ ሚኒስትር የነበረ ደጃዝማች ወርቅነህ ለጣሊያኖች እጁ በሰጠው ተይዘዋል፤ በሬቺ ለኢጣሊያዊ ሀገረ ገዥ ስላስረከበው ከቡሩ አባት ጋራ በአደባባይ ተገድለዋል[2]፡፡


አበበ አረጋይ ከተጉለት ወደ ሞጃ ሄዷል፤ ከእሱ ጋራ በተደረገው ግጭት የኢጣሊያ የባንዳ መሪ ተገድሏል፡፡

ግርች 16 ጀነራል ትራኪያ በሰጠው ሪፖርት በሰላ ድንጋይ በአበበ አረጋይ አርበኞችና በጣሊያኖች ባንዳዎች መሐል ተኩስ ልውውጥ ተደርጎ ከሁለቱ ወገኖች አንዳንድ ሰው ተገድለዋል፡፡ በሙገር የአርበኞች እንቅስቃሴ ቀጥለዋል፡፡ ምንም እንኳን በግርግ ማህለጊዮርጊስ ከሚመሩ አርበኞች ከዳተኞች ኤርትራውያን ካሉባቸው ጋራ ከባድ የጠብመንጃና የመትረየስ ተኩስ ቢያጋጥምም ጣለያኖች እንተኔ የተባለ መንደር ለመያዝ ችለዋል፡፡ ፊታውራሪ ማህለጊዮርጊስ የግርግ አባት የኃይለማርያም ማሞ አጎት ነው፡፡ አርበኞች ከሞቱባቸው 9 ሰዎች አንዱ የአስካሪ ልብስ የለበሰ ከዳተኛ ኤርትራዊ ነበረ፡፡

---

[1] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N.1204 V II
[2] Governo Generale A.O.I ibd Allegato N.1193 V II

# የኢትዮጵያ አስተዳደር አከፋፈል በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን




ጣሊያኖች የኢትዮጵያ መሬትን ቆርሰው ኤርትራ ብለው እንደሰየሙት ሁሉ መላዋን ኢትዮጵያ በተቆጣጠሩበት ጊዜ የኢትዮጵያ ስምን አጥፍተው ሰርዘው ኢጣሊያኖች ምሥራቅ አፍሪካ AOI የሚል መጠሪያ ነበረ የሰጧት።



የአካባቢ መንደሮች ተደምስሰዋል። አርበኞቹ ሲሸሹ ኃይለኛ ተኩስ በጣሊያኖች ላይ ይተኩሱ ነበር።

# 3. የአፕሪል ወር ውጊያ

ጣሊያኖች በሸዋ ሰላምና ማረጋጋት ለማስፈን ያደረጉት ጥረት ግቡ እንዳልመታ ማመን ጀምረዋል። ጣሊያኖች እንደተመኙ እየተዳከሙ የመጡ አርበኞች አልነበሩም በተገላቢጦች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከሙ የመጡ ጣሊያኖች ነበሩ፣ ባንፃሩም እየተጠናከሩ የመጡ አርበኞች ነበሩ። ጣሊያኖች እንዳመኑ በአንድ አካባቢ አርበኞችን ደምስሰናል አጥፍተናል ብለን ወደ ሌላ አካባቢ ለተመሳሳይ ተግባር ስንሰማራ፣ ቀደም ብለን ከአርበኞች ያፀዳነው አካባቢ በተጠናከረ መልኩ አርበኞች የሰፈሩበት የአርበኞች መናኸሪያ ሆኖ እናገኘዋለን በማለት አርበኞችን በማጥፋት ሰቅዳቸው እንዳልተሳካላቸው ይገልጹ ነበረ[1]። ጣሊያኖች አርበኞችን ለማጥፋት ያደረጉት ኃይለኛ ሙከራ እንዳልተሳካላቸው የሚያሳይ ምልክት በሰሜን ምሥራቅ ሸዋ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ የነበረ ጀነራል ትራኪዮ ተሸሮ በጀነራል ማሌቲ (Maletti) መተካቱ ነው።

የአርበኞች ድፍረት ለመግታት አዲሱ የጦር አዛዥ የወሰደው እስቸኳይ ጊዜያዊ እርምጃ ሁኔታዎቹ እስኪማሙ ድረስ ደብረሲናንና የአዲስ አበባ ደሴ የመኪና መንገድን ደኅንነት ለመጠበቅ ኮሎኔል ጋይቢ ከፍተኛ ጦርን በመምራት ወደ ስላ ድንጋይ በመላክ ነበር። ማርች 29 ጣሊያኖች ከሞፈር ወንዝ ባሻገር ሰፍረው ለ3 ተከፍለው አርበኞች ጥቃት ለመፈጸም እንደተዘጋጁ መረጃ ደደርሳቸዋል። 1ኛ የተኘ መንዲዳን ለማጥቃት 2ኛ ማዕከለኛ በአበበ አረጋይ የሚመራ ከሁሉ ኃይለኛ ከሁሉ የሚያስጋ ከሁሉ የበለጠ አመራር ያለው ብለው የገመቱት ስላ ድንጋይን ለማጥቃት ዓላማ ያለው 3ኛ የግራ በምሥራብ መንዝ የሰፈረ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለአበበ አረጋይ ድጋፍ የሚሰጥ።

ጀነራል ማሌቲ በአበበ አረጋይ ብቻ ያነጣጠረ በ3 አቅጣጫ ጦር ለማሰማራት ወሰነ፣ የአበበ አረጋይ አደጋ ከሰጠገደ በኋላ በሁለተኛ ዙር ወደ ዋዩ መንዲዳ ራቱን ማዞር፣ የ3ኛ ቡድን ስለተባለው በመንዝ ስለሰፈረው ግን ወደ ጣሊያኖች ደቡብ ዘልቆ እንዳይመጣ ክትትል ማድረግ ብቻ የተወሰነ ዓላማ ነበረው። የጣሊያኖች ዓላማ በአሁኑ ወቅት አርበኞቹን ወዳሉበት ሄዶው ለማጥቃትና ለመደምሰስ ሳይሆን በመከላከል አዘንብለው የደሴ አዲስ አበባ የመኪና መንገድ አርበኞች እንዳያቋርጡባቸው ዘብ መቆም ብቻ ነበረ። ትግሉ ለ5 ዓመት የቀጠለው በዚሁ መልኩ ነበረ።

ጀነራል ማሌቲ በ3 አቅጣጫ በአበበ አረጋይ አዘመትኳቸው የሚላቸው የጦሩ ክፍሎች 1ኛ በቀኝ በኩል በኮሎኔል ጋይቢ የሚመራ ቡድን ሌላ 2ኛ በግራ ቢጋሬሊ (Garelli) የሚመራ በመሐል በአንጀሊ (Angeli) የሚመራ አሰማራ። የማያ ንድፍ ተመልከት።

አፕሪል 3 እና 4 ደጋማመው ያጠቁ የነበሩ አርበኞች ነበሩ፣ በጫጫ እና በሬማ ወንዞች በኩል ወደ ወራና ዘልቀው ለመኪና መንገድ አደጋ እንዳያደርሱና ከዘባ እንዳይፈጽሙባቸው ጣሊያኖች ስጋት ላይ ወድቀው ነበሩ። ጣሊያኖች አርበኞቹን ከመኪና ማራቅ ካልሆነ ለመደምሰስ ፍላጎትም ችሎታም

[1] Governo Generale A.O.I ibd Testo P. 373 V II

ራስ አበበ አረጋይ



ታጋይ ይሞታል ትግሉ ግን አይሞትም የሚለው አባባል በኢትዮጵያ በተግባር ሲውል ታይቷል።

ጣሊያኖች እነ ራስ ደስታን ደጃዝማች አበራ ካሣን ወዘተ በመግደል የኢትዮጵያውያንን የአርበኝነት ትግል የደመሰሱ መስሏቸው ነበር፣ ሆኖም ኢትዮጵያ በታሪኳ፣ ጀግኖች በገር ወዳዶች፣ የሚፈልቁባት አገር፣ የጀግኖች መሆን ተብላ ስለምትታወቅ በጣሊያኖች በግፍ የተገደሉትን የአርበኞች መሪዎች ፈለግ ተከትለው ሌሎች አርበኞች ታጋዮች እነ ራስ አበበ አረጋይ ትግሉን በመቀጠል በያቤቱ አፋፋሙት እንጂ ኢትዮጵያ ለጣሊያኖች ቅኝ ገዢዎች እጅዋን አልሰጠችም።



አልነበራቸውም። ስለዚህ ከውጊያው በኋላ እንደእየፍላጎታቸው ወደ ነፃ መሬታቸው ወደ መርሐቤቴና መንዝ ለማፈግፈግ ይችሉ ነበር።

ጣሊያኖች የሕልም ምኞት ፊውዳል የሚሏቸው እንደ ደጃዝማች አበራና አስፋወሰን ካሣ ካጠፉ በኋላ የአርበኞች የትጥቅ ትግል ያበቃል የሚል ስእምነታቸው ስሁተት መሆኑን አምነው የተቀበሉ ይመስላል፣ አምነው ባይቀበሉም ጊዜው እየተደገቻቸው በመሄድ የ2ኛ የዓለም ጦርነት እየተቃረበ ይሄድ ነበረ፣ የቅኝ ግዛቶች ግብቲያም እየተቃረበ ይሄድ ነበረ፣የጣሊያኖች አስተሳሰብ ግን 100-200 ዓመት ወደ ኋላ የቀረ ነበረ።

ማርች 28 ቀን ጀነራል ትራኪያ በላከው ቴሌግራም አንድ ግለሰብ ከአርበኞች ጋራ በምስጢር በግሲፋና የተደረት ንግድ በማካሄዱ በፍቼ ተረሽኖዋል ብሏል።

አፕሪል 4 ጀነራል ግስቲ ስለተካሄዱ ጦርነቶች ባቀረበው ሪፖርት 2 የኢጣሊያ የጦር መኰንኖች ተገድለዋል 2 ቆስሏል፣ አስካሪና ባንዳዎች 11 ተገድለዋል 23 ቆስሏል። ከአርበኞች ወገን 360 በጦር ሜዳ የተገደሉ 62 ተማርከው የተረሸኑ። ከተገደሉ ውስጥ ብዙ ታዋቂነት የነበራቸው ነበሩ፣ እንደዚሁም 2 አስካሪ ከዳተኞች ኤርትራውያን ነበሩ።

በተደጋጋሚ የሚጠቅሷቸው ከዳተኞች አስካሪ ኤርትራውያን ጣሊያኖች በአምሳላቸው የፈጠሩዋቸው ለጣሊያኖች ታማኝ ኤርትራውያን እንክርዳዶች እንዴት ሊገኙ ቻሉ በግለት በንዴትና በቅድሚያ ይገድሉዋቸው የነበረ በዚሁ የተነሳ ነው። በአሁኑ ወቅት የሚታየው ሁኔታ ስናስገናዝበው ጣሊያኖች ለኤርትራውያን 100 ዓመት ብቻ ጣሊያኖች ኤርትራ የሚል ስም ከሰጧቸው ጊዜ ጀምሮ ታሪክ እንዳላቸው አምነው እንዲቀበሉ የተሳካላቸው ይመስላል። Popoli Imbelli e guerrieri ጅሎችና ጦረኞች ለኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች አገልጋዮች ብቻ ለመሆን የተፈጠሩ፣በጣሊያኖች ትእዛዝ ኢትዮጵያን እንዲጠሉና እንዲወጉ የተፈጠሩ፣ ለጣሊያኖች ዘረኞች ቅኝ ገዢዎች፣ የዓለም ታሪክ ቀድሞ ሮሙ ባይቀድማቸው፣ ዓለማቸው ተሳክቶላቸው እንደነበረ እንረዳለን።

አፕሪል 5 ጀነራል ግስቲ ባስተላለፈው ሪፖርት በጦርነቱ ስለተገደሉ ሰዎች በተጨማሪ ሲገልጽ ሌሎች 52 ተገድለዋል ካለ በኋላ ሕዝቡና 14 ቤተክርስቲያኖች ለጣሊያኖች ታማኝነታቸውን ገልጸዋል ብሏል። አበበ አረጋይ ወደ ምዕራብ መንዝ እንዳመራ ተረጋግጧል፣ ሆኖም ወደ አዳባይ እንደሚመለስ ይታመናል። በአዳባይ እንደ ሊቢያ ቼሬናይካ ብዙ ዋሻዎች ጉድጓዶች፣ ከቼሬናይካ በ1000 ጊዜ ተባዝተው የሚበልጡ ይገኛሉ ብሏል።

አፕሪል 6 ጀነራል ግስቲ ባደረገው ሪፖርት ስለተደረጉ ጦርነቶች አስመልክቶ ሲጽፍ ባለፈው ያስተላለፈውን በማረም በጦር ሜዳ የተገደሉ አርበኞች 412 እንደነበሩ ተማርከው የተገደሉ 63 እንደነበሩ አብራርቷል፣ ብዙ የአርበኞች የእህል ጎተራም እንዲቃጠል ተደርገዋል ብሏል።

አፕሪል 7 ጀነራል ግስቲ ባቀረበው ሪፖርት አበበ አረጋይ ቀድሞ በጣሊያኖች ላይ ጦርነት ከመክፈቱ በፊት ጣሊያኖች እንዲቀድሙት ወሎ ከሚገኘው የኢጣሊያ ጦር በመስማማት ጣሊያኖች ቀድመው ጥቃት እንዲፈጽሙ ለማድረግ እሞክራለሁ ብሏል።

በድምሩ ግን በጣሊያኖች የተገደሉ አርበኞች 556 ነበሩ። ጣሊያኖች በመንዝ፣ በመራቤቴ፣ በሞረድ ብዛት ያላቸው አርበኞች የሰፈሩበት አርበኞችን ለመደምሰስ ዕቅድ ያወጣሉ። ይህ ከመደረጉ በፊት ግን በዋዩ ጅሩ፣ ወበራ በስውር የሚንቀሳቀሱ አርበኞችን ቅድሚያ በመስጠት ማጥፋት ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ።

# የእንሳሮ ውጊያ (ሳህ ዳብር)

የእንሳሮ ሕዝብ የጦር መሣሪያ አላስረከብም ብሎ ነበረ፡፡ ጣሊያኖች አበበ አረጋይና ደጃዝማች አውራሪስ ወደ ሱዳን ወይንም ወደ ጅቡቲ ሀገር ለቀው ለመሄድ ሃሳብ እንዳላቸው መረጃ ስለደረሳቸው ከመርሐቤቴና ከእንሳሮ ወደ አባይ የሚወስድ መንገድ ሁሉ ይቆጣጠሩ ነበር፡፡ የእንሳሮ ሕዝብን ትጥቅ ለማስፈታት ኮሎኔል ጆርዳኖ ስለተመደበ ኮሎኔሉ ሰራውን ለማከናወን ወደ ሰሚ መድኃኔ ዓለም የእንሳሮ ዋና ከተማ በማምራት አፕሪል 14 እቦታው ሊደርስ ፈረ ሕዝብ ንብረቱን ይዞ ሀገሩን ለቆ ነበረ፡፡ ቦርሳና በተባለው ወንዝ አርበኞች መስፈራቸውን ስላወቀ ኮሎኔል ጆርዳና አፕሪል 16 አሰሳ ለማድረግ ይሰማራል፣ ጸዲመሰስ የተሰጠው ትእዛዝ ችላ በማድረግ ያለው ኃይል በቂ ነው ብሎ በማሰብ አሰሳ ሲጀምር፣ አንድ ክፍል ወታደሮቹ አፕሪል 17 ሳህ ዳብር በተባለው ቦታ በአርበኞች ተከበበ፡፡ ከመንዲዳ እና ከፍቼ ረዳት ወታደሮች ስለተላኩለት ከእልቂት ሊድን ችሏል፡፡ አፕሪል 22 ከከበባው ካስለቀቁ በኋላ ከባድ አሰሳና ቅጣት በሕዝቡ ላይ አካሄዷል፡፡ በዚሁ ውጊያ በጣሊያን ወገን የደረሰ ጉዳት 3 የጦር መኰንኖች የቆሰሉ 41 ወታደሮች ሲሞቱ 50 ቆስሏል፡፡ በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት የተገደሉ 432 ከአንድ ሺህ (1000) በላይ ቤቶች በእሳት እንዲጋዩ ተደርገዋል፡፡ ጣሊያኖች በ1 ዓመት ውስጥ ከአርበኞች ጋራ የተካሄደው ትግል ሲገመገም፡ ጥሩ ውጤት እንዳልተገኘ አምኗል፡፡

ለዚሁም ብዙ ምክንያቶች ሰጥቷል፣ የመሬቱ ገደላ ገደል መሆኑ፣ የአርበኞቹ በፍጥነት እንደ እሞራ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሸዋ ሕዝብ ያለው የቆየ ስር የሰደደ በጣሊያኖች ላይ ጠላትነት፤ስለዚህ በሀገሩ ዘላቂ ሰላም ሊሰፍን የሚችለው በጊዜ ብዛት ነው በማለት አጠቃላይ ግምገማ ደርሰዋል፡፡

አፕሪል 17 ኮሎኔል ጋሬሊ ባስተላለፈው ሪፖርት ሻለቃ ጆርዳኖ ብዙ የአርበኞች ከብቶች እንደዘረፈ፣ በውጊያም 7 አርበኞችን እንደገደለ ገልጧል፡፡ አፕሪል 19 ጀነራል ማለቲ ባስተላለፈው ሪፖርት ሻለቃ ጆርዳኖ በአርበኞች ተከቦ በአደገኛ ሁኔታ ይገኝ እንደነበረ ገልጾ ከአደጋ ሊያመልጥ የቻለው በ5ኛ ባታሊዮንና በኮሎኔል ጋረሊ ባደረጉለት እርዳታ መሆኑን አብራርቷል፡፡ በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት የተገደሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡ በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት አንድ የመቶ አለቃ ያሉባቸው 17 ተገድለዋል 46 ቆስሏል፣ 22 የደረሱበት ያልታወቀ ከእነሱ መሐልም አንድ ኢጣሊያዊ መቶ አለቃ፣ በሚቀጠሉት ቀናት የምናደርስባቸው በጣም ከባድ እንደሚሆን ገልጧል፡፡

አፕሪል 21 ጀነራል ማለቲ ባስተላለፈው ሪፖርት ኮሎኔል በላከለት ሪፖርት መሠረት በማድረግ ለ10 ኪሎ ሜትር የበቀልና የመቀጫ እርምጃዎች ተወስዷል፣ በ18 እና 19 ውጊያ የተካሄዱባቸው ቦታዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ቤቶች ተቃጥለዋል ወድመዋል፣ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ገበሬዎች ከአርበኞች ጋራ በመተባበራቸው ተይዘው ተረሽነዋል፡፡ በጣሊያኖች የደረሰ ጉዳት የቆሰለ አንድ ብቻ ነው፣ የደረሱበት አልታወቀም ከተባሉ 2 አስካሪ ተገኝቷል ብሏል፡፡

አፕሪል 24 ጀነራል ማለቲ በላከው ሪፖርት የዓመቱ አንዳንድ ሹሞች እጃቸውን ለመስጠት ስለቀረቡ በዳውሊ መንደሮች ነጋድሬስና ሁለት ሌሎች ባንዳዎች በመግደላቸው ባደረገው የሰብኩት ቅጣት ቀንሻለሁ ብሏል፤ ሆኖም 680 ቤቶች እንዲቃጠሉ ተደርገዋል 206 ሰዎች ተይዘው ተረሽነዋል፣ የአጎርቲ ሕዝብና ቤተክርስቲያኖች ቀርበው እጅ ነስተው ሰጦታ አቅርበዋል፣ በሕዝቡ ላይ የተፈጸመው ቅጣት ትክክልና ፍትሐዊ መሆኑን ሕዝቡ አምኖበታል ብሏል፡፡



በሌሎች ክፍለሀገሮችም የአርበኞች ትግል እንደቀጠለ ነበረ፡፡ ጀነራል ናዚ ፌብሩዋሪ 27 ባስተላለፈው ሪፖርት በተደረገው ክትትል ለአንድ ባራምባራስ ከፊታውራሪ በሐደ ጋራ ትብብር በማድረጉ ባሻ ካሊደ የጦር መሣሪያ ደብቆ በመገኘቱ ተረሽነዋል ብሏል፡፡

ማርች 10 ጀነራል ጀሉዞ በሰጠው ሪፖርት የዳረማ ባንዳ በዲላ አጠገብ ከአርበኞች ጋራ ባደረገው ውጊያ አርበኞች 850 ከብቶች ጥለው ሲሸሹ 30 ተገድሉባቸዋል፣ ከኢጣሊያ ባንዳ የሞቱ 18 የቆሰሉ 6 ነበሩ፡፡፡ የአደላ ባንዳ አዛዥ ከቁኒ ተራራ አጠገብ 2 የቀድሞ የኢጣሊያ አስካሪ ከዳተኞች ኤርትራውያንን ማርከ በጥይት ደብድቦ ገድሏቸዋል፣ እንደዚሁም የዳሉ ባንዳ 29 የኤርትራ የቀድሞ አስካሪ ከዳተኞችን ማርኮ ገድሏቸዋል፡፡

ማርች 16 ጀነራል ጀሉዞ ባደረገው ሪፖርት ከባንዳ ሮሌ (Rolle) አንድ ክፍል በሳንቶሮና በደ ሉረንዞ (Santoro e De Lorenzo) የሚመሩ 300 ከጊቤ እናሪያ በስተምዕራብ በብላታ ታከለ ወልደሐዋሪያት ከሚመሩ አርበኞች ውጊያ ተካሄዶ አርበኞች እንዲሸሹ አድርገዋቸዋል፡፡ ከጣሊያን ወገን የመቶ አለቃ ሳንቶሮ በጠና ቆስሏል፣ ከባድ 8 ሲቆሰሉ 8 ተገድለዋል፡፡ ከአርበኞች 50 በጦር ሜዳ ሲገደሉ 3 ተማርከው ተገድለዋል፡፡

አፕሪል 23 ጀነራል ጀሉዞ ባደረገው ሪፖርት 2 ባታሊዮኖችና ባንዳዎች ያቀፈ በኮሎኔል ማሮኔ (Marone) የሚመራ የኢጣሊያ ጦር 1500 ከሚገመቱ አርበኞች በኮንታ ውጊያ ተደርጎ ከጣሊያኖች ወገን አንድ ምክትል መቶ አለቃና 9 ባንዳዎች ሲሞቱ 16 ቆስሏል፣ ከአርበኞች 100 ተገድለዋል፡፡

ማርች 30 ኮሎኔል ሰራሊያ (Serraglia) በላከው ሪፖርት በቦካ ዋሲ አጠገብ ኮሎኔል ከራዶ ባንዳ ከአርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከአርበኞች ወገን ብዙ ሞቷል፡፡ መንደሩ ሸፍታ በመሆኑ ወድመዋል፣ ከጣሊያን ወገን 3 ኢንዲጀኒ አስካሪ ተገድለዋል፡፡

ማርች 31 ኮሎኔል ሰራሊያ በላከው ሪፖርት የኮሎኔል ኮራዶ (Corrado) ባንዳ በባኮ 400 ከሚገመቱ አርበኞች ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከአርበኞች ወገን 215 ተገድለዋል መንደሩ በሙሉ ሸፍታ በመሆኑ ተደምስሰዋል፡፡

አፕሪል 1 ቀን ኮሎኔል ሰራሊያ ባደረገው ሪፖርት የኮራዶ ባንዳ 300 ከሚገመቱ አርበኞች ውጊያ ገጥሞ ከጣሊያን ወገን 3 ሲሞቱ ከአርበኞች 32 ተገድለዋል፡፡ 13 አግራ ተማርከው ተገድለዋል፡፡

አፕሪል 13 ጀነራል ጀሉዞ በላከው ሪፖርት የኮሎኔል ማሮኔ ባንዳ አፕሪል 11 በወሶ ከአርበኞች ጋራ በገጠመው ውጊያ ከአርበኞች ወገን 10 ተገድለዋል፡፡ 4 አግራ ከነመሣሪያ የተገኙ ተይዘው ተገድለዋል፡፡

አፕሪል 20 ጀነራል ጀሉዞ በላከው ቴሌግራም በሰዶ አካባቢ ኤሶ የተባለው መንደር እንዲቃጠል ተደርገዋል፣ 21 አርበኞች ተይዘው ተገድለዋል፡፡ ዋካ በተባለው መንደር ደጃዝማች ድንቁና የሚከተሉት ሌሎች ተገድለዋል፡፡ 1. ፊታውራሪ ተሰማ ደመነ 2. ኃይሉ መኩንን 3. ሂርደ ታከለ 4. ታቻኒ 5. መስፍን ብሩ 6. ወሰኔ 7. አሰፋው ፋሪስ 8. ተሰማ 9. 11ቀኛዝማች 10. 9 ግራዝማች

አፕሪል 23 ሰራሊያ ባደረገው ሪፖርት በቶሌ በሞሊኖር የሚመሩ ባንዳዎች ከአርበኞች ጋራ ባደረጉት ውጊያ ከአርበኞች ወገን ብዙ መቶ ተገድለዋል፣ ቆስሏል፣ ብዙ ሹሞች ከሞቱና ከቆሰሉ ይገኙባቸዋል፡፡ በአርበኞች መሐል የቀድሞ አስካሪ ኤርትራውያን ከዳተኞች ተስተውለዋል፡፡ ከጣሊያን ወገን 13 ኤርትራውያን ተገድለዋል፡፡ የቆሰሉ አንድ ኢጣሊያዊ ሻምበል ሌላ ኢጣሊያዊ ዜጋ 34 ኤርትራውያን 3 ዓረብ ሶማል፡፡ የሞሊኖር ባንዳ 27 አግራ ማርከው ገድለዋል፡፡ ጀነራል ፋሪነቲ (Farinetti) ጠባያቸው አጠራጣሪ ይመስል የነበረ 13 አግራዎች እንዲረሸኑ አድርገዋል፡፡ ከዚሁም

በላይ 32 አግራዎችና 100 ተከታዮቻቸው ተይዘው ታስረዋል፡፡ ጀነራል ደላ ቦና (ቤንቨንጉት) ሕዝቡ መግሪያ እንዳያስረክብ ሲሰብኩ ስለተገኙ ሁለት ሰዎች ተረሽነዋል፡፡

ጅማ አጠገብ ቀኛዝማች ለገሰ ፋንታ ተይዞ ተገድለዋል፣ እንደዚሁም ጀኮርሳ በተባለው መንደር 25 ኪሎ ሜትር ከጅማ ቀኛዝማች ቦጋለ ፋንታና 4 ተከታዮቹ ተይዘው ተገድለዋል፡፡

አፕሪል 25 ኮሎኔል ሰራሊያ ባደረገው ሪፖርት አንድ ቀኛዝማች ያለባቸው አርበኞች በድንገት ተይዘው ተገድለዋል፡፡ የሞሊናር ባንዳ አንድ ቀኛዝማችና 52 አግራ አርበኞችን ማርኮ ገድለዋል፡፡ እንደዚሁም በቦንጊ አካባቢ በአሰላ የተያዙ 152 አግራ ሽፍቶች (አርበኞች) ተገድለዋል፡፡ በለቀምት ጀነራል ፋሬኑቲ 32 የአርጆ አግራ ሽፍቶች ረሽነዋል፡፡ ቢበሺ የተባለው ብቸኛ የቀድሞ ሹም በአርጆ አደገኛ ግለሰብ ተገድለዋል፡፡ ከመገደሉ በፊት ጥያቄ በሚደረግለት ጊዜ 6 ጥይቶች ካልታወቁ ሰዎች ስለተተኮሱ የአርጆ መንደር በሙሉ በእሳት እንዲቃጠል ተደርገዋል፤ ለወደፊት ቁጥራቸው የሚገለጽ ብዙ ሰዎች ተገድለዋል፡፡

አፕሪል 26 ኮሎኔል ሰራሊያ ባደረገው የማብራሪያ ሪፖርት በአርጆ የሕዝብ ጭፍጨፋ ስንት ሰው እንደተገደለ ገና አላውቅም ብሏል፡፡ በተቃጠሉ ቤቶች ብዙ የጦር መሣሪያዎች ተገኝቷል ወርቅ ግን አልተገኘም ብለዋል፡፡ የአርጆ ጉዳይ ለወደፊት ችግር እንደማይፈጥርብን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያከተመ ይመስላል፡፡

የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ በኢትዮጵያ 1ኛ ዓመት ከሞላ ጎደል ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ይመስላል፡፡ በቀሩት 4 ዓመታት የተፈጸሙት ወንጀሎች ከዚህ የባሱ እንጂ ያነሱ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ጣሊያኖች በፈጸሙት የሕዝብ ጭፍጨፋ በጦር ወንጀለኝነት ወይንም በዘር በማጥፋት ወንጀል

አልተጠየቁም፡፡ ብዙ ኢትዮጵያውያን ግን በገዛ ወንድሞቻቸው በፈጸሙት ወንጀል በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሷል፡፡ እንደ ደንቡ ከሆነ ኢትዮጵያውያን በገዛ ወንድሞቻቸው የፈጸሙት ወንጀል የዘር ማጥፋት ወንጀል ሊባል አይገባም ምክንያቱም የፖለቲካ አክራሪነት ወንጀል ነው፡፡ በሌላ የዓለም ክፍሎችም የተከሰተ ነው፡፡ የዘር ማጥፋት የሚባለው ናዚስት ጀርመኖች በይሁዶች ላይ የፈጸሙት የሕዝብ ጭፍጨፋ ነው፡፡ ጀርመኖች የመፍጀት ዓላማ የነበራቸው 6 ሚሊዮን ይሁዶች ብቻ አልነበረም፣ ዓላማቸው በዓለም ያሉትን ይሁዶች ሁሉ ለመፍጀት ነበር፡፡ ጣሊያኖችም ዘረኝነታቸው በጥቁሮች ላይ ስለነበረ እንደ ጀርመኖች ለማድረግ አይመለሱም ነበር፡፡ አጠቃላይ የጥቁር ሰው ፍጅት ያላደረጉበት ምክንያት በርሕሩሕነታቸው ሳይሆን ሁኔታዎች ስላልተመቻቹላቸው ብቻ ነው፡፡ ሌላ ምክንያትም ነበረ፤ ከፊል ጣሊያኖች ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ፈጅተን ጨርሰን በመሬቱ ጣሊያኖች እናሰፍርበት የሚሉ ነበሩ፣ ሌሎች ጣሊያኖች ደግሞ ጥቁሮች ይጠቅሙናል አገልጋዮች እናደርጋቸዋለን መፍጀት የለብንም የሚሉ ነበሩ፡፡ በከርከር ላይ እንዳሉ ከሀገራችን ተዋርደው ወጥቷል፡፡ ጣሊያኖች ወራዳ መሆናቸው ስለማይሰማቸው አሁንም በነ አድራጊዮች ነን እያሉ እየለፈለፉ ይገኛሉ፡፡



# ክፍል 2

## የኢጣሊያ ዘረኝነት
## ምዕራፍ አንድ ቅድመ ፋሺዝም ዘረኝነት

### 1. ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝና ዘረኝነት መሥራች 1891

ኢጣሊያ በዐድዋ ሽንፈት ከገጠማት በኋላ የኤርትራ ሀገረ ገዢ ብላ ሾማ ለአሥር ዓመት ከ1897 ዓ.ም. ጀምሮ የገዛ ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የተባለው ሰው የቱስካና ተወላጅ በኤርትራ ውስጥ እስከዛሬ ጨቋኝ የቅኝ ግዛት አስተዳደር በመመሥረቱ ለኤርትራ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የኢጣሊያን ቅኝ ግዛቶች እንዲሰራበት ተደርጐ ኢጣሊያ ተወዳዳሪ የሌላት ጨቋኝ ቅኝ ገዥ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ይህ ሰው የኤርትራ ሀገረ ገዥ ተብሎ ከመሾሙ ከ6 ዓመት በፊት በ1891 ዓ.ም. በደረሰው መጽሐፍ የኢጣሊያ ዓላማ ዜጎቿን በኤርትራ ማስፈር ስለሆነ ለሀገሩ ተወላጆች የምታደርግላቸው እርዳታ ከምድረ ገጽ ቶሎ ብነው እንዲጠፉ ማድረግ ብቻ ነው ብሎ ነበር፡፡ ከፋሺዝም በፊት ሆነ በኋላ መጽሐፉ ለአሥር ጊዜ ታትሞ የወጣ በመሆኑ በኢጣሊያን ሕዝብ ዘንድ መጽሐፉ ምን ያህል ተወዳጅነት እንደነበረው ያሳያል፣ የጣሊያኖች ማንነትም አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ 1/ ፈርዲናንዶ ማርቲኒ የእንግሊዝ ወይም ፈረንሳይ ዜጋ ቢሆን ኖሮ እንኳን ሹመት ሊሰጠው የሕዝብ ተቃውሞ ተነስቶበት በሕይወቱ ለመኖር በሚያሰጋው ደረጃ ይደርስበት ይችል ነበር፡፡ በኢጣሊያ ግን አዋቂ ሰው የሚያሰኘው ነበር፡፡ በሕዝቡ ለፓርላማ ለ45 ዓመታት ተመርጦ ሰርተዋል፡፡ ከኢጣሊያ ንጉሥ ልዩ አክብሮት አግኝቷል፡፡ በኢጣሊያ መንግሥታት ቅድመ ፋሺስትና በፋሽስት ዘመን ከፍተኛ ሥራና ሹመት ማዕረግ አግኝቷል፡፡

Diario Eritreo የተባለው በሕይወት እንዳለ የደረሰው መጽሐፍ የታተመው በድህረ ፋሺዝም በዲሞክራሲ የሚባለው የኢጣሊያ መንግሥት ጊዜ ነው፡፡ የእጅ ጽሑፍ ከልጁ የተረከበው መጽሐፍ በሚታተምበት ጊዜ ማርቲኒ ሞቶ ስለነበረ ልጁም ሞቶ ስለነበረ የእጅ ጽሑፉ ተረክበው እንዲታተም ያደረጉ ሰዎች መጽሐፉን ለማስታወቅ 60 ገጽ መቅድም በመጽሐፍ በአስተዳደር አዋቂነት በከፍተኛ ደረጃ አዋቂ በማድረግ እያወደሱ ጽፈውለታል፡፡ የኢጣሊያ መንግሥት እንደዚህ ያለ አስተሳሰብ እንዳለው እያወቀ ሀገረ ገዥ ሹሞ መላኩ በዓላማው ተስማምቶበት ዓላማውን በሥራ እንዲያውለው ነው የላከው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በሥራ ላይ ለማዋል ያልሞከረበት ምክንያት ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ጅቡቲ፣ የኤርትራ ጎረቤቶች ስላሉ ሕዝቡ ወደእነዚህ ሀገሮች ለመሸሽ ስለሚችል ከንቱ ሙከራ ስለሆነበት ነው፡፡ አልሞከረም ለማለትም አይቻልም፣ በአነስተኛ ደረጃ ወደ አሰብ እና ወደ ደሴቶች ወደ ናቅሩ እየተላኩ የሚያጠፉቸው ሰዎች ነበሩ፡፡

ብዙዎች ኢትዮጵያውያን በመደነቅም ሆነ በመውቀስ ስለ ሻእቢያ ስለ ኢሕአዴግ እንደዚሁም ስለ ኦነግ መድህን ወዘተ… መከራከር ይወዳሉ፣ ስለ ጣሊያኖች ሊነሳ ግን ከታሪክ ምሁራን ሳይቀር እንዲነሳ አይፈልጉም፣ እነሱ ተዋቸው ያሉኝ ምሑራን አስታውሳለሁ፡፡ ትክክል አስተሳሰብ አይመስለኝም ዋና ጠላታችን ትተን እርስ በእርሳችን መነታረክ ውጤት ያለው አይመስለኝም፡፡